# ንቃ!

## ከአስመሳይ ሃይማኖተኞች ተጠንቀቅ!

### 2ኛ ጴጥሮስ፥ 2ኛ እና 3ኛ ዮሐንስና ይሁዳ መልእክቶች

ጽሑፍ፡- በዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

ትርጉም፡- በመስፍን ታዬ

እርማት፡- በተስፋዬ መስፍንና በዓቢይ ደምሴ

Copyright © 1996 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia. Originally published in English under the title of BE ALERT, Copyright © 1984 by SP pubilcations, Inc. Wheaton, Illinois 60187, U.S.A. All rights reserved.

# ማውጫ


መቅድም

ገጽ

1. ማወቅና ማደግ (2ኛ ጴጥሮስ 1፡ 1-11) . . . . . . . . 1
2. ንቃና አስታውስ! (2ኛ ጴጥሮስ 1፡ 12-21) . . . . . 15
3. ከአስመሳዮች ተጠንቀቅ (2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 1-9) . . . . . 30
4. ለፍርድ የተለዩ ሰዎች (2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 10-16) . . . . 44
5. ሐሰተኛ ነፃነት (2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 17-22) . . . . . . 60
6. በሚያፌዙት ላይ ማፌዝ (2ኛ ጴጥሮስ 3፡ 1-10) . . . . 73
7. ትጉ ሁን! (2ኛ ጴጥሮስ 3፡ 11-18) . . . . . . . . 87
8. ታማኝ ቤተሰብ (2ኛ ዮሐንስ) . . . . . . . . . . 101
9. እውነቱ ይህ ነው (3ኛ ዮሐንስ) . . . . . . . . 116
10. የክተት ጥሪ! (ይሁዳ 1-7) . . . . . . . . . 131
11. መናፍቃንን እወቃቸው! (ይሁዳ 8-16) . . . . . . 146
12. መሰናከል የለብህም (ይሁዳ 17-25) . . . . . . . 160

# መቅድም

«ክርስቲያን ነኝ» በምትለዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉም ነገር ጤናማ ነው ማለት አይቻልም።

በአሁኑ ጊዜ ሐሰተኛ አስተማሪዎችና ሐሰተኛ ትምህርቶች በስፋት ተሰራጭተው ስለሚገኙ፥ ይህንን አደገኛ አዝማሚያ የእግዚአብሔር ወገኖች የሆኑ ሁሉ በንቃት ሊቋቋሙት ይገባል።

ከተሳሳተ ግንዛቤ የተነሣ ቤተ ክርስቲያን አንድም ሊጎዳት በሚችል ክፍፍል እየታመሰች፥ አለበለዚያም ሐሰተኛ የሆነ ኅብረት በመፍጠር እየተጠቃች ነው። አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ከሚቃወሙ አስተሳሰቦቻችንና ድርጊቶቻችን የተነሣ ጠላትን እየረዳን፥ ወንድማማችነትን ደግሞ እየጎዳን ነው ያለነው።

ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ይሁዳ መናፍቃንን መለየት እንድንለማመድና በድብቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡትን አስመሳዮች ለይተን እንድናውቅ ሊረዱን ይችላሉ። እንደዚሁም እነዚህን የመሳሰሉት ሐሰተኛ ሐዋርያት የሚያስተምሯቸውንና ዛሬ እንደ ክርስቲያናዊ እውነቶች የሚቆጠሩትን መናፍቃዊ ትምህርቶች በቀላሉ ለመገንዘብና ለይተን ለማውጣት ያስችሉናል።

እኔም ይህንን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ የነበረኝ ሁኔታ ሁሉ ይሁዳ በደብዳቤው መክፈቻ ላይ ከገለጠው ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ በበኩሌ ስለ እምነታችን ቀና የሆኑ ነገሮች ማለትም ስለ ክርስትና ሕይወት በረከቶች መጽሐፍ ብጽፍ የበለጠ በመረጥኩም ነበር፤ ነገር ግን ጠላት ተጠናክሮና ሊያጠቃን ባሰፈሰፈበት ጊዜ የሚያስፈልገን የሽርሽር ግብዣ ሳይሆን የሠራዊት ክተት ጥሪ እንደሆነ ሁላችንም የምንገነዘበው ነው።

«እንግዳ ሰዎችን በማስተናገድ፥ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ሳያውቁ መላእክትን ያስተናግዳሉ፤ ነገር ግን እንግዳ ትምህርቶችን በማስተናገድ ብዙዎች ሳያውቁ አጋንንትን አስተናግደዋል» በማለት ጆን ፍላቬል ያሳስበናል።

ስለዚህ ጊዜው አሁን ነውና አንተም ከተመሳሳይ ስሕተት ላይ እንዳትወድቅ ነቅተህ ጠብቅ! ዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

# የ2ኛ ጴጥሮስ መልእክት ንድፈ-አሳብ።

1. ገለጻ ፡- የክርስቶስ እውቀት - 1፡1-21
   ሀ. የእውቀት ስጦታ- 1፡1-4
   ለ. በእውቀት ማደግ- 1፡5-11
   ሐ. የእውቀት መሠረት- 1፡12-21
2. ግምገማ፡- ሐሰተኛ አስተማሪዎች - 2፡1-22
   ሀ. ትምህርታቸው ሲወገዝ - 2፡1-9
   ለ. ባሕርያቸው - 2፡10-17
   ሐ. እነርሱ ነን የሚሉት - 2፡18-22
3. መምከር፡- እውነተኛው ክርስቲያን - 3፡1-18
   ሀ. አስተውሉ - 3፡1-7
   ለ. አትርሱ - 3፡8-10
   ሐ. ትጉ - 3፡11-14
   መ. ተጠንቀቁ - 3፡15-18

# ማወቅና ማደግ

## 2ኛ ጴጥሮስ 1፡ 1-11

ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል የንቃትን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ሐዋርያው ጴጥሮስ ከልቡ ተገንዝቦ ነበር። እርሱ በወጣትነት ዘመኑ ማንኛውንም አደጋ በድፍረት የሚጋፈጥ፥ በራሱም ከመጠን በላይ በመተማመኑ የጌታን ማስጠንቀቂያዎች እንኳ ያለማስተዋል አዝማሚያ ነበረው። በትዕግሥት መጠበቅ ሲገባው ተቻኩሎ ከፊት ይቀድም ነበር፤ መጸለይ ሲገባው ይተኛ ነበር፤ መስማት ሲገባው ያወራ ነበር። በመሆኑም ጴጥሮስ ደፋር፥ ሆኖም ግን ግድየለሽ ክርስቲያን ነበር።

ይሁን እንጂ የጥንቃቄን አስፈላጊነት ትምህርት ቀስ በቀስ ለማወቅ በመቻሉ፥ እኛንም በተመሳሳይ ሁኔታ ሊያስተምረንና ሊረዳን ይፈልጋል። ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልእክቱ በእግዚአብሔር ላይ ሲያተኩር (1ኛ ጴጥሮስ 5፡ 12)፥ በዚህ በሁለተኛው መልእክቱ ውስጥ ግን አትኩሮቱ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ሊኖረን በሚገባው እውቀት ላይ ነው። በዚህ አጭር መልእክት ውስጥ ማወቅ ወይም እውቀት የሚለው ቃል ቢያንስ አሥራ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል። ምንም እንኳ እውቀት የሚለው ቃል ስለ አንድ የተወሰነ እውነታ የሚኖረንን ምሁራዊ መረዳት የሚያካትት ቢሆንም፥ ይህ ግን ቃሉን ሙሉ በሙሉ አይገልጸውም። ቃሉ ጌታችን በዮሐንስ 17፡3 ላይ በተጠቀመበት ዓይነት ስሜት በእውነት ውስጥ ያለንን ሕያው ተሳትፎ የሚገልጽ ነው። «እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።»

ጴጥሮስ ደብዳቤውን የሚጀምረው የክርስትና ሕይወት ምን መሆን እንደሚገባው በመግለጽ ነው። ስለ አስመሳዮች ምንነት ከመግለጹ በፊት ስለ እውነተኛ አማኞች ሁኔታ አብራርቷል። ሐሰትን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችለው ቀላሉ አማራጭ የእውነትን ባሕርያት በቅድሚያ መረዳት ነው። ጴጥሮስ ለእውነተኛ የክርስትና ሕይወት ማረጋገጫ የሚሆኑ ሦስት ጠቃሚ ነጥቦችን አስፍሮልናል።

## የክርስትና ሕይወት በእምነት ይጀምራል
### (2ኛ ጴጥሮስ 1፡ 1-4)

ጴጥሮስ ይህንን «የክብር እምነት» ብሎ ይጠራዋል። ይኸውም ዛሬ ከጌታ ጋር መቆማችን ከዘመናት በፊት ከነበሩት ከሐዋርያት እምነት ጋር አንድ ዓይነት ነው ለማለት ነው። ሐዋርያቱ ከክርስቶስ ጋር አብሮ የመኖር፥ በዓይናቸው እርሱን የማየት፥ እንዲሁም በተአምራቱ የመካፈል ዕድል የነበራቸው በመሆናቸው ብቻ ከእኛ የተለየ በረከት አልሰጣቸውም። ጌታን ለመውደድ፥ ለማመንና ከብሩን ለመካፈል እርሱን በሥጋዊ ዓይኖቻችን ማየት አያስፈልገንም (1ኛ ጴጥሮስ 1፡8)።

ይህ እምነት አካላዊ ባሕርይ ባለው ላይ ነው (1፡ 1-2)። ያ አካል ኢየሱስ ክርስቶስ፥ የእግዚአብሔር ልጅ አዳኛችን ነው። በደብዳቤው መጀመሪያ ጴጥሮስ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት አስረግጧል። «አምላካችን» እና «መድኃኒታችን» የሚሉት ሁለት ቃላት ሁለት የተለያዩ ባሕርያት የሚገልጹ አይደሉም፤ አንድን አካል እንጂ! እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጳውሎስ በቲቶ 2፡ 10 እና 3፡ 4 ላይ በተመሳሳይ አገላለጽ ተጠቅሟል።

ጴጥሮስ ይህንን የተከበረ መጠሪያ በ1፡ 11 ፤ 2፡20፤ 3፡2 እና 3፡ 18 ላይ በመደጋገም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን ለአንባቢዎቹ አሳስቧል። አዳኝ «ደኅንነትን የሚያስገኝ» ማለት ነው፤ ደኅንነት የሚለው ቃል ደግሞ በዚያን ዘመን በነበሩት ሰዎች ዘንድ የተለመደ ነበር። በመዝገበ ቃላታቸው ውስጥ የቃሉ ትርጉም «ከችግር መላቀቅ» በተለይም ደግሞ «ከጠላት መዳን» ማለት ነበር። «ጤናና ዋስትና» የሚለውንም አሳብ ይዟል። ሰውነትን ከስቃይና በበሽታ ከመጠቃት ለማላቀቅ ስለሚረዳ አንድ ሐኪም እንደ አዳኝ ይታይ ነበረ። እንደዚሁም ሕዝቡን ከሽንፈት ስለሚያድን ድል ነሺ የጦር መሪ እንደ አዳኝ ይታይ ነበር። የአንድ አገር ጥበበኛ መሪም ሕዝቡን በሥርዓት በመጠበቁና ከውርደት በማዳኑ እንደ አዳኝ ይቆጠር ነበር።

«አዳኝ» የሚለው ስያሜ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደሚስማማ ለማየት በጥቂቱም ቢሆን መረዳትን ይጠይቃል። በእርግጥ እርሱ ከኃጢአት በሽታ ልብን የሚፈውስ ታላቁ ሐኪም ነው። እርሱ ጠላቶቻችንን- (ኃጢአትን፥ ሞትን፥ ሰይጣንንና ሲኦልን) ያሸነፈና ወደ ድል እየመራን ያለ ባለድል ጦረኛ ነው (2 ቆሮ. 2፡ 14 ጀምሮ)። እርሱ

«አምላክና አዳኛችን» (2ኛ ጴጥሮስ 1፡1)፤ «ጌታችንና መድኃኒታችን» (1፡11) እና «ጌታና መድኃኒታችን» (2፡20) ነው። መድኃኒታችን ለመሆን በመስቀል ላይ ሕይወቱን መስጠትና ለዓለም ኃጢአት መሞት ነበረበት።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሌላ ከማንም ሰው ሊገኙ የማይችሉ ሦስት «መንፈሳዊ ባሕርያት» አሉት፤ እነርሱም፡- ጽድቅ፤ ጸጋ እንዲሁም ሰላም ናቸው። እንደ አዳኝህ አድርገህ ስታምነው የርሱ ጽድቅ የአንተ ይሆናልና በእግዚአብሔር ፊት የመቆም መብት ይኖርሃል (2ኛ ቆሮ. 5፡21)። ይህንን ጽድቅ በራስህ ልታገኘው ፈጽሞ አትችልም፤ ይህ ለሚያምኑ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። «እንደ ምሕረቱ መጠን .... አዳነን፥ እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም» (ቲቶ 3፡5)።

ጸጋ ማለት ፍጹም ነፃ የሆነ የእግዚአብሔር ችሮታ ነው። እግዚአብሔር በምሕረቱ የሚገባንን አልሰጠንም፤ በጸጋው ግን የማይገባንን ሰጠን። አምላካችን «የጸጋ ሁሉ አምላክ» ነው (1ኛ ጴጥ. 5፡10)። ያንን ጸጋ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እኛ ያፈስሰዋል (ዮሐ. 1፡16)።

የዚህ ልምድ ውጤት ሰላም ይሆናል። ይህም ማለት ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር (ሮሜ 5፡1) እንዲሁም የእግዚአብሔር ሰላም (ፊልጵ. 4፡6-7) ማለት ነው። በእርግጥ እኛ ከእርሱ ጋር ስንራመድና የተስፋ ቃሎቹን ስናምን የእግዚአብሔር ጸጋና ሰላም ይበዛልናል።

ይህ እምነት የእግዚአብሔርን ኃይል ያካትታል (1፡3)። የክርስትና ሕይወት በሚያድን እምነት ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት በማመን ይጀምራል። ኢየሱስ ክርስቶስን በግላችሁ ስታውቁት፥ ወዲያውኑ የእግዚአብሔርንም ኃይል ትለማመዳላችሁ፤ ይህ ኃይል ደግሞ ሕይወትንና እግዚአብሔርን መምሰልን ያፈራል። ያልዳነው ኃጢአተኛ የሞተ ነው (ኤፌ. 2፡1-3)። ከሞት ሊያስነሣው የሚችለው ደግሞ ክርስቶስ ብቻ ነው (ዮሐ. 5፡24)። ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ሲያስነሣ «ፍቱትና ይሂድ ተውት» አለ (ዮሐ. 11፡44)። የመግነዝ ልብሱን አስወግዱ! ማለቱ ነበር።

በክርስቶስ ባላችሁ እምነት ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ስትወለዱ ሙሉ ሆናችሁ ነው የተወለዳችሁት። ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልጋችሁን ማንኛውንም ነገር እግዚአብሔር ይሰጣችኋል። ስለዚህ

ምንም ሌላ ነገር መጨመር የለበትም! «በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል» (ቆላ. 2፡10)። ሐሰተኞዎቹ አስተማሪዎች በጴጥሮስ መልእክት አንባቢያን ሕይወት ላይ ሊጨመር የሚገባው አንድ «ልዩ ትምህርት» እንዳላቸው ተናግረዋል። ጴጥሮስ ግን ምንም ነገር ሊጨመር እንደማይችል ያውቅ ነበር። ልክ አንድ ጤነኛ ሕፃን ለሕይወት ከሚያስፈልጉት ሕዋሳት ጋር እንደሚወለድና ማደግ ብቻ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፥ እንዲሁም ክርስቲያን የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ያለውና ማደግ ብቻ የሚያስፈልገው ነው። እግዚአብሔር አንድ ጊዜ የፈጠረውን ሰው ጉድለት አግኝቶበት ወይም በመሳሳቱ ሌላ ተጨማሪ ነገር ለማከል ሲል እንዲመለስ አይጠራውም።

አንድ ሕፃን እንዴት እንደሚያድግ የሚወስን የተወሰነ ውስጣዊ የአካል መዋቅር እንዳለው ሁሉ፥ እንዲሁም አማኙ «ክብርንና በጎነትን ለመለማመድ በውስጣዊ አካሉ የተዋቀረ ነው። አንድ ቀን እንደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሆናል» (ሮሜ 8፡29፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡2)። «ወደ ዘላለም ክብሩ የተጠራን» ነንና (1ኛ ጴጥ. 5፡10) እኛ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስና ሕዝቦቹን ወደ ሰማይ ሲወስድ ያንን ክብር እንካፈላለን።

ሆኖም ግን «እኛም . . . ለበጎነት ተጠርተናል»። «ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራንን የእርሱን በጎነት እንድንናገር» የዳንን ነን (1ኛ ጴጥ. 2፡9)። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆን ወደ ሰማይ እስከምንደርስ ድረስ መጠበቅ የለብንም! ዛሬ በባሕርያችንና በጠባያችን የእርሱን ውበትና ጸጋ መግለጥ አለብን።

ይህ እምነት የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ያካትታል (1፡4)። እግዚአብሔር የሰጠን ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልገንን ብቻ ሳይሆን፥ በምድራዊ ሕይወታችንም እግዚአብሔርን በመምሰል እንድናድግ የሚያግዘንን ቃሉንም ጭምር ነው። እነዚህ የተስፋ ቃሎች ታላቅ ናቸው፤ ምክንያቱም ከታላቅ አምላክ የመጡና ወደ ታላቅ ሕይወት የሚመሩ በመሆናቸው ነው። ዋጋቸው በአእምሮ ስሌት የማይደረስበት ነውና እጅግ የከበሩ ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል ከሌለን እሱን የሚተካልን ሌላ ምንም ዓይነት አማራጭ የለንም። ጴጥሮስ ክቡር የሚለውን ቃል ሳይወደው አይቀርም፤ ምክንያቱም ስለ «ክብር እምነት» (2ኛ ጴጥ. 1፡1ን፤ ከ1ኛ ጴጥ. 1፡7 ጋር አነጻጽር)፤ ስለ «ተከበረ ተስፋ» (2ኛ ጴጥ. 1፡4)፤ ስለ «ክቡር ደም» (1ኛ ጴጥ. 1፡19)፤ ስለ «ከበረ

ድንጋይ» (1ኛ ጴጥ. 2፡4፥6) እንዲሁም «ስለ ከበረው አዳኝ» (1ኛ ጴጥ. 2፡7) ጽፏልና።

ኃጢአተኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን፥ የእግዚአብሔርን ሕይወትና ባሕርይ በእርሱ ውስጥ ለማኖር ሲል የእግዚአብሔር መንፈስ በእግዚአብሔር ቃል ይጠቀማል። አንድ ሕፃን የወላጆቹን ባሕርይ ይካፈላል፤ እንዲሁም ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰው የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ ይካፈላል። የጠፋው ኃጢአተኛ የሞተ ነው፤ ክርስቲያን ግን መለኮታዊውን ባሕርይ ስለሚካፈል ሕያው ነው። የጠፋው ኃጢአተኛ ከረከሰው ባሕርይው የተነሣ እየበሰበሰ ነው፤ ክርስቲያን ግን በውስጡ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ ስላለው ሕያው የሆነውን እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት ሊለማመድ ይችላል። የሰው ዘር በጥፋት ባርነት ሥር ነው ያለው (ሮሜ 8፡21)፤ አማኝ ግን የመለኮታዊ ባሕርይ አንድ ገጽታ የሆነውን ነፃነትና ዕድገት ይካፈላል።

ተፈጥሮ ፍላጎትን ይወስናል። እሪያ ጭቃን ይፈልጋል፤ ውሻ ደግሞ የራሱን ትፋት እንኳ ይበላል (2ኛ ጴጥ. 2፡22)፤ በግ ግን የለመለመ መስክን ይመኛል። ተፈጥሮ ባሕርይንም በዚያው መጠን ይወስናል። ንስር የንስር ባሕርይ ስላለው ይበርራል፤ ዓሣ ደግሞ ያለው የዓሣ ባሕርይ ስለሆነ ይዋኛል። እንደዚሁ ሁሉ ተፈጥሮ አካባቢንም ይወስናል፡- ሽኮኮዎች ዛፍ ላይ ነው የሚኖሩት፤ ፍልፈሎች ከመሬት ሥር ቆፍረው ሲገቡ ሙጭልጭላዎች ደግሞ በውኃ ውስጥ ይዋኛሉ። ተፈጥሮ ኅብረትንም ይወስናል። አንበሶች በአንድነት ይጓዛሉ፤ በጎች በመንጋ፥ ዓሦችም በዘራቸው ይሄዳሉ።

ተፈጥሮ ፍላጎትን ከወሰነና እኛ ደግሞ በውስጣችን የእግዚአብሔር ባሕርይ ካለን፥ ንጹሕና ቅዱስ ለሆነው ብቻ ፍላጎት ይኖረናል ማለት ነው። ጠባያችን እንደ እግዚአብሔር አብ መሆን አለበት፤ ደግሞም ከባሕርያችን ጋር በሚስማማ «መንፈሳዊ አካባቢ» ውስጥ ልንኖር ይገባናል። ለባሕርያችን ከሚስማማው ጋር ኅብረት መፍጠር አለብን (2ኛ ቆሮ. 6፡14-20ን ተመልከት)፤ ለእግዚአብሔር ልጅ ትክክለኛና ፍሬ የሚያፈራ ብቸኛው ሕይወት እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት ነው።

ይህንን መለኮታዊ ባሕርይ ስለያዝን በዚህ በአሁኑ ክፉ ዓለም ካለው ርኩሰትና ውርደት «ሙሉ በሙሉ አምልጠናል።» አዲሱን ባሕርያችንን

በቃሉ ምግብ ከመገብነው ለዓለም ምናምንቴ ነገር የሚኖረን ፍላጎት የመነመነ ይሆናል፤ ነገር ግን ሮሜ 13፡14 «ምኞቱን እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ» ሲል ኃጢአተኛ ባሕርያችን ግን«የቀድሞውን ኃጢአት» ይመኛል (2ኛ ጴጥ. 1፡9)፤ ለእግዚአብሔርም ሳንታዘዝ እንቀራለን። እግዚአብሔርን በመምሰል መኖር ማለት በውስጥ ያለውን አዲሱን ባሕርይ የመንከባከብ ውጤት ነው።

## የእምነት ውጤት መንፈሳዊ ዕድገት ነው
(2ኛ ጴጥ. 1፡5-7)

ሕይወት ባለበት ዕድገት መኖር አለበት። አዲሱ ልደት የዕድገት መጀመሪያው እንጂ መጨረሻው አይደለም፤ እግዚአብሔር ለልጆቹ እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ይሰጣቸዋል። ልጆቹ ግን እርሱ በሰጣቸው «የጸጋ መሣሪያዎች» ለመጠቀም ራሳቸውን ማዘጋጀትና መትጋት ይኖርባቸዋል። መንፈሳዊ ዕድገት እንዲሁ የሚመጣ አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር መተባበርን፥ መንፈሳዊ ትጋትንና ለሥነ -ሥርዓት ሕግጋት ተገዢ መሆንን ይጠይቃል። «የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ . . . በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» (ፊልጵ. 2፡12-13)።

ጴጥሮስ እግዚአብሔርን የመምሰልን ሕይወት በማስመልከት ሰባት ባህርያት ዘርዝሯል፤ ይሁን እንጂ እኛ እነዚህን ባሕርያት እንደተለያዩ የመቁጠሪያ ዕቃዎች ወይም ሰባት የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች አድርገን መቁጠር የለብንም። «መጨመር» የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም «በልግስና መስጠት» ማለት ነው። በሌላ አነጋገር አንዱን ዓይነት የጸጋ ሕይወት ስንለማመድ ሌላውንም ዓይነት እናሳድጋለን ማለት ነው። እነዚህ ጸጋዎች ቅርንጫፍ ከግንዱ እንዲሁም እንቡጦች ከቅርንጫፉ ጋር እንዳላቸው ግንኙነት ዓይነት እርስ በርሳቸው የተያያዙ ናቸው። እንደ «መንፈስ ፍሬ» (ገላ. 5፡22-23) እነዚህ ባሕርያት በሕይወታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ከሚኖረን ወሳኝ ግንኙነት ተነሥተው በዚያው መጠን ያድጋሉ፤ ስለዚህ መንፈሳዊ ዕድገት የእግዚአብሔር ሥራ ብቻ እንደሆነ በማሰብ ሁሉንም ለእግዚአብሔር ብቻ መተው የለበትም። ጴጥሮስ «ማንኛውንም ጥረት . . . አድርጉ» ነው የሚለው። እግዚአብሔር አብና ልጁ አብረው መሥራት አለባቸው።

ጴጥሮስ ከዘረዘራቸው ወሳኝ ባሕርያት መካከል የመጀመሪያው በጎነት ነበር። ይህንን ቃል በቁጥር 3 ላይ አይተነዋል፤ እናም ቃሉ በመሠረቱ «የበለጠውን ወይም ከሁሉም የከበረውን» ማለት ነው። ለግሪክ ፈላስፎች ይህ የአንድ ነገርን መሟላት የሚያመለክት ነበር። በተፈጥሮ ያለ ማንኛውም ነገር ዓላማውን ሲፈጽም ያ በጎነት ማለት ወይም ግብረገባዊ ሙላት ክቡርነት ማለት ነው። ቃሉ ታላላቅ ሥራዎችን ለማድረግ፥ አማልክት ያላቸውን ኃይል ለመግለጽም አገልግሏል። እህልን የሚያመርት መሬት የተሟላና የተከበረ ነው፤ ምክንያቱም የሚፈለግበትን እያሟላ ስለሆነ ነው። በትክክል የሚሠራ መሣሪያ «የተሟላ» ነው፤ ምክንያቱም አንድ መሣሪያ እንዲያደርግ የሚጠበቅበትን እያደረገ ስለሆነ ነው።

አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ማስከበር ይጠበቅበታል፤ ምክንያቱም በውስጡ የእግዚአብሔር ባሕርይ ስላለው ነው፤ ስለዚህ ይህንን ሲያደርግ በሕይወት ውስጥ ያለውን ዓላማውን እየፈጸመ ስለሆነ የተሟላና የተከበረ ነገር እየሠራ ነው ማለት ነው። በክርስትና ሕይወት ውስጥ እውነተኛ በጎነት የቁንጅ ያህል መልካም ቢሆን፥ የሰውየውን ሰብአዊ ጠባዮች ለማሳመር ሲባል የሚደረግ ሳይሆን ሰውየውን በበለጠ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲመስል የሚያስችሉትን መለኮታዊ ባሕርያት ማዳበር ማለት ነው።

እምነት በጎነትን እንድናሳድግ ይረዳናል፤ በጎነት ደግሞ እውቀትን እንድናሳድግ ይረዳናል (2ኛ ጴጥ. 1፡5)። በቁጥር 2ና3 ላይ እውቀት ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ሙሉ እውቀት» ወይም «የሚያድግ እውቀት» ማለት ነው። እዚህ የተጠቀሰው ቃል ተግባራዊ እውቀት ወይም መለየት የሚለውን አሳብ ያመለክተናል። ይህም ሕይወትን በተሳካ ሁኔታ የመያዝን ችሎታ የሚያሳይ እንጂ ሰማያዊውን ነገር ብቻ ልናውጠነጥን በኑሮአችን ግን መክሰርን የሚያመለክት አይደለም። የዚህ ዓይነት እውቀት እንዲሁ አይመጣም። የሚመጣው ለእግዚአብሔር ፈቃድ ከመታዘዝ ነው (ዮሐ. 7፡17)። በክርስትና ሕይወታችሁ ውስጥ ልብንና አእምሮን፥ ባሕርይንና እውቀትን መለያየት የለባችሁም።

በጴጥሮስ የመንፈሳዊ በጎነቶች ዝርዝር ውስጥ የሚቀጥለው ዓይነተኛ ባሕርይ ራስን መግዛት ነው። «ትዕግሥተኛ ሰው ከኃያል ሰው ይሻላል፥በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስድ ይበልጣል፥» (ምሳሌ

16፡32)። «ቅጥር እንደሌላት እንደ ፈረሰች ከተማ፥ መንፈሱን የማይከለክል ሰው እንዲሁ ነው» (ምሳሌ 25፡28)።

ብዙውን ጊዜ ጳውሎስ በደብዳቤዎቹ ውስጥ አንድ ክርስቲያን ሽልማቱን ማግኘት ከፈለገ እንደ አንድ ሯጭ ያላሰለሰ ልምምድ ማድረግ እንደሚኖርበትና ራሱን ለሥነ-ሥርዓት ማስገዛት እንደሚገባው ገልጿል (1ኛ ቆሮ. 9፡24-27፤ ፊልጵ. 3፡12-16፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡7-8)።

ትዕግሥት ማለት ሁኔታዎች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ የሚኖረን የመጽናት ችሎታ ማለት ነው። ራስን መግዛት የሕይወትን ምኞቶች ከመቆጣጠር ጋር የተያያዘ ሲሆን፥ መጽናት ግን በመጀመሪያ ደረጃ የተያያዘው ከሕይወት ግፊቶችና ችግሮች ጋር ነው። (ችግረኞች ሰዎችን ያለማቋረጥ መርዳት የመሥዋዕትነትን ብቃት ያሳያል)። ብዙውን ጊዜ ለምቾት ራሱን የሚያደላድል ሰው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙት ለመቋቋም አይችልም፤ ስለዚህም በቀላሉ ተስፋ ይቆርጣል።

ትዕግሥት እንዲሁ የሚያድግ ነገር ሳይሆን እኛ ለፍተን የምናገኘው ነገር ነው። ያዕቆብ 1፡2-8 ሊኖረን ስለሚገባው ትክክለኛ ዝንባሌ ያመለክታል። ፈተናዎች እንደሚደርሱብን መጠበቅ አለብን፤ ምክንያቱም ካለፈተናዎች ጽናትን ፈጽሞ ልንማር አንችልም። በእምነት በመጽናት ፈተናዎች በእኛ ላይ ሳይሆን ለእኛ እንዲሠሩልን ልናደርግ ይገባናል፤ ምክንያቱም በችግሮቻችን ውስጥ እግዚአብሔር በሥራ ላይ እንደሆነ ስለምናውቅ ነው። ውሳኔዎችን ለማድረግ የሚያስፈልገንን ጥበብ ከጠየቅነው እግዚአብሔር ያንን ጥበብ ይሰጠናል። ማንም ሰው ፈተናዎች ስለደረሱበት አይደሰትም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ለእኛ ጥቅምና ለራሱ ክብር እንዲሆን በማድረግ ስለሚሠራ፥ በፈተናዎች ሳቢያ ልናዳብረው በምንችለው መተማመን እንደሰታለን።

እግዚአብሔርን መምሰል ማለት በቀላሉ የእግዚአብሔርን ባሕርይ መምሰል ማለት ነው። በመጀመሪያው የግሪክ ቋንቋ ይህ ቃል «በሚገባ ማምለክ» ማለት ነበር። ይህም ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ያለውን ሰው የሚገልጽ ነበር። ምናልባት አክብሮት እና «ፈሪሃ እግዚአብሔር» የሚሉት ቃላት ይህንን ስያሜ ለመተርጎም የበለጠ ይቀርቡ ይሆናል። አንድን ሰው የተለየ የሚያደርገው እንደዚህ ዓይነቱ ባሕሪይው

ነው። ይህን ዓይነቱም ሰው የሌሎችን ሕይወት ከሚቆጣጠሩት የሕይወት ጥቃቅን ነገሮች፥ ከምኞቶችና ከማንኛውም ተጽዕኖ በላይ ይኖራል፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ይመኛል፤ ይህንንም ሲያደርግ የሌሎችን መልካም ኑሮ ይመኛል።

እግዚአብሔርን መምሰል ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ነገር እንደሆነ አድርገን ፈጽሞ ማሰብ የለብንም፤ ምክንያቱም በሚገባ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነገር ስለሆነ ነው። እግዚአብሔርን የሚመስል ሰው ትክክለኛና ጨዋነት የተሞላባቸውን የከበሩ ውሳኔዎች ያደርጋል። ሥቃይን ወይም ፈተናን ለማምለጥ ሲል ብቻ ቀላል መንገድን አይመርጥም። ትክክለኛ ስለሆነና የእግዚአብሔርም ፈቃድ ስለሆነ ትክክለኛ የሆነውን ያደርጋል።

ወንድማዊ ፍቅር (መዋደድ) የሚለውን ሌላ የበጎነት ባሕርይ (በግሪክ ፊላደልፊያ) ጴጥሮስ የተማረው ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም ደቀ መዛሙርቱ እርስ በእርሳቸው ይከራከሩና ይጨቃጨቁ እንደነበር ስለምንረዳ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ከወደድን ወንድሞችንም መውደድ አለብን። «ግብዝነት የሌለበትን የወንድማማች መዋደድ» (1ኛ ጴጥ. 1፡22) መለማመድ አለብን እንጂ የምንወዳቸው መስለን ለመታየት ብቻ መሞከር የለብንም። «የወንድማማች መዋደድ ይኑር» (ዕብ. 13፡1)። «በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» (ሮሜ 12፡10)። በክርስቶስ ያሉትን ወንድሞችና እኅቶች መውደዳችን ከእግዚአብሔር እንደተወለድን የሚያሳይ አንድ ማስረጃ ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡1-2)።

የክርስትና ዕድገት ከወንድማማች መዋደድ በላይ የሚጨምረው ነገር አለ፤ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለመሞት ሲሄድ እንዳሳየው ሁሉ እኛም ለመሥዋዕትነት የሚያደርሰን ፍቅር ሊኖረን ይገባል። በቁጥር 7 ላይ የተነገረው የፍቅር ዓይነት እግዚአብሔር ለጠፉ ኃጢአተኞች የሚያሳየው ዓይነት ፍቅር ማለትም «አጋፔ» የሚባለው የፍቅር ዓይነት ነው። ይህ እኛ በመንፈስ ስንመላለስ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ የሚያፈራው የፍቅር ዓይነት (ሮሜ 5፡5፤ ገላ. 5፡22) በ1ኛ ቆሮ. 13 ላይ የተገለጸው ፍቅር ነው። ወንድማዊ ፍቅር አለን ስንል የምንወደው ከሌሎች ጋር ባለን ተመሳሳይነት ሲሆን በአጋፔ ፍቅር ግን የባሕርይ ልዩነት ሳናደርግ መውደድ ማለት ነው።

የወደቀው የሰው ልጅ ተፈጥሮ እነዚህን ሰባት የክርስትና ባሕርያት ራሱ በራሱ ሊያመነጫቸው አይችልም። የእግዚአብሔር መንፈስ ነው በውስጣችን የሚፈጥራቸው። አስደናቂ ራስን የመግዛት ችሎታና ጽናት ያላቸው ያልዳኑ ሰዎች አሉ፤ ነገር ግን እነዚህ በነ ሁኔታዎች የሚያመለክቱት ወደ ጌታ ሳይሆን ወደ ራሳቸው ነው። ክብሩን እነርሱው ይወስዱታል። እግዚአብሔር የልጁን ውብ ባሕርይ በክርስቲያን ውስጥ ሲያፈራ ግን ምስጋናውንና ክብሩን የሚቀበለው እግዚአብሔር ብቻ ይሆናል።

መለኮታዊ ባሕርይ ስላለን በመንፈስ ልናድግና ይህን ዓይነት ክርስቲያናዊ ጠባይ ልናዳብር እንችላለን። ይህ ዕድገት የሚገኘው በእግዚአብሔር ኃይልና ክቡር በሆኑት የተስፋ ቃሎች አማካይነት ነው። መለኮታዊው ባሕርይ ውስጣችን ነው ያለው። እግዚአብሔር «የልጁን መልክ እንድንመስል»ይፈልጋል (ሮሜ 8፡29)። እኛ ግን በትጋት ከእግዚአብሔር ጋር ከተባበርንና እርሱ አትረፍርፎ በሰጠን ጸጋ ከተጠቀምን በውስጣችን ያለው ሕይወት ያንን መልክ ያንጸባርቃል።

አስደናቂው ነገር ደግሞ የክርስቶስን መልክ በእኛ ውስጥ የመፍጠሩ ሂደት የእኛን የራሳችንን ሰብእና የሚያስወግድ አለመሆኑ ነው። የክርስቶስን መልክ ብንይዝም እንኳ እኛነታችን ግን ምንጊዜም አብሮን ይኖራል።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉት አደገኛ ነገሮች አንዱ መስሎ ለመታየት የምናደርገው ሙከራ ነው። ሰዎች መጋቢያቸውን፤ ወይም አንድን የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም አንድ «ታዋቂ ክርስቲያን» መስሎ የመታየት አዝማሚያ አላቸው። በዚህም ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስን ካለመምሰላቸው ሌላ ትክክለኛ እነርሱነታቸውንም እስከማጣት ይደርሳሉ። በሁለቱም መንገዶች ይከስራሉ! በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ልጅ ወላጆቹን ቢመስልም እንኳ በአንዳንድ ሁኔታዎች የተለየ እንደሆነ ሁሉ፥ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ልጅ የበለጠ ኢየሱስ ክርስቶስን ቢመስልም አንዱ ከሌላው የተለየ ነው። ወላጆች አምሳያቸውን ይወልዳሉ እንጂ በመልክና በጠባይ ቁርጥ የእነርሱ ግልባጭ የሆኑ ልጆች አይደለም የሚወልዱት። አስተዋይ ወላጆች ልጆቻቸው ማንነታቸውን ይዘው እንዲኖሩ ያበረታቱአቸዋል።

## መንፈሳዊ ዕድገት ተግባራዊ ውጤቶችን ያስገኛል
(2ኛ ጴጥ. 1፡8-11)

አማኝ በመንፈስ እያደገ ለመሆኑ እንዴት እርግጠኛ መሆን ይችላል? ጴጥሮስ ለእውነተኛ መንፈሳዊ ዕድገት ሦስት ማስረጃዎችን ያቀርባል።

ፍሬያማነት (1፡8)፡- ክርስቲያናዊ ባሕርይ ወይም ጠባይ እራሱን የቻለ አንድ ግብ ሲሆን በሌላም በኩል ከመጨረሻው ግብ ለመድረስ የሚረዳ መንገድም ነው። የበለጠ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በሆንን መጠን፥ መንፈስ ቅዱስ በምስክርነትና በአገልግሎት የበለጠ ሊጠቀምብን ይችላል። የማያድግ አማኝ ሥራ ፈት፥ መካን ወይም ፍሬ ቢስ ነው። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለው እውቀት በሕይወቱ ምንም ዓይነት ተግባራዊ ውጤት አያፈራም። ሥራ ፈቶች ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ውጤት አልባ» እንደ ማለትም ነው። የማያድጉ ሰዎች በሌላውም የሕይወት ገጽታቸው አብዛኛውን ጊዜ ተሸናፊ ናቸው!

ከማውቃቸው በጣም ውጤታማ ክርስቲያኖች መካከል አንዳንዶቹ የተለየ ችሎታ ወይም የሚስብ ሰብእና እንኳ የሌላቸው ናቸው፤ ሆኖም እግዚአብሔር በሚገርም ሁኔታ ተጠቅሞባቸዋል። ለምን? ምክንያቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን እየመሰሉ በመሄዳቸው ስለሆነ ነው። ከእግዚአብሔር በረከት ሊገኝ የሚችለው ዓይነት ጠባይና ባሕርይ አላቸው። የታመኑ ስለሆኑ ፍሬያማዎች ናቸው፤ በክርስትና ልምዳቸው እያደጉ ስለሆኑ ስኬታማ ናቸው።

መለኮታዊ ባሕርይ ስላለን እነዚህ ውብ ባሕርያት «በእኛ ውስጥ» ይኖራሉ። በሕይወታችን ውስጥና በሕይወታችን በኩል እንዲበዙና ፍሬ እንዲያፈሩ ልንከባከባቸው ይገባናል።

ማየት (ራእይ) (1፡9)፡- የምግብ ጥናት ባለሙያዎች የምንመገበው የምግብ ዓይነት የማየት ኃይላችንን ሊለወጥ እንደሚችል ይነግሩናል፤ በመንፈሳዊው ሁኔታም እንዲሁ ነው። ያልዳነው ሰው ሰይጣን አእምሮውን ስላሳወረበት በጨለማ ውስጥ ነው ያለው (2ኛ ቆሮ. 4፡3-4)። አንድ ሰው ዓይኖቹ ከመከፈታቸውና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት ከመቻሉ በፊት የግድ ዳግመኛ መወለድ አለበት (ዮሐ. 3፡3)። ይሁን እንጂ፥ ዓይኖቻችን ከተከፈቱ በኋላም ቢሆን የማየት ኃይላችንን መጨመርና

እግዚአብሔርን እንድናይ የሚፈለግብንን ሁሉ እንድናይ ያስፈልጋል። «አርቆ ማየት ይሳነዋል» የሚለው ሐረግ በቅርብ ያሉትን ብቻ መመልከት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ይህ በርቀት ማየት ባለቻሉ ዓይኖቹ እየጨፈነ ወይም እያጨናቆረ ያለ ሰው ምሳሌ ነው።

የአንዳንድ ክርስቲያኖች የማየት ችሎታ ካሉበት ቤተ ክርስቲያን ወይም ድርጅት ውጪ ሰፋ አድርጎ አይመለከትም፤ በዓለም ዙሪያ ያሉትን የእግዚአብሔር ቤተሰብ ብዛት አያስተውልም። አንዳንድ ክርስቲያኖች ደግሞ በዙሪያቸው ያለውን ችግር ብቻ የሚያዩ እንጂ አሻግረው ለጠፋው ዓለም ግን ምንም የማየት ችሎታ የሌላቸው ናቸው። አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲኖር ምን ማድረግ ትችላለህ? በማለት ፊሊፕ ብሩክስን ጠየቀው። እርሱም፡- «ክርስቲያኖች ወንጌልን እንዲያስፋፉ እሰብክና መባም እሰበስብ ነበር» ብሎ መለሰለት። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን «ዓይናችሁን አንሡ አዝመራውም አሁን እንደነጣ እርሻውን ተመልከቱ» አላቸው (ዮሐ. 4፡35)።

አንዳንድ ማኅበረ ምእመናን በሎዶቅያ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ይመስላሉ። «ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም» ስለሚሉ ኩሩዎች ናቸው፤ «ጎስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆቱም» መሆናቸውንም አያስተውሉም (ራእይ 3፡17)። በመንፈሳዊ ነገር በቅርብ ያለውን ብቻ ማየት አሳዛኝ ሲሆን፥ ዕውር መሆን ደግሞ የበለጠ አሳዛኝ ነው።

እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውን የምንዘነጋ ከሆነ ስለ ክርስቶስ ለሌሎች ለመናገር ንቁዎች አንሆንም። በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነጽተናል! ደግሞም ይቅር ተብለናል! እግዚአብሔር ዓይኖቻችንን አብርቷል! ያደረገውን አንርሳ! ይልቅስ ለተደረገልን ነገር አመስጋኞች እንሁንና መንፈሳዊ ዓይናችንን እናጥራ። የእግዚአብሔር ሰዎች ዓይኖቻቸውን ጨፍነው መመላለስ የለባቸውም፤ ሕይወት በጣም አጭር ነው፤ የዓለም ጉስቁልና ደግሞ በጣም ብዙ ነው!

ዋስትና (1፡10-11)፡- ዓይኖችህን ጨፍነህ ብትመላለስ ትደናቀፋለህ! በማደግ ላይ ያለ ክርስቲያን ግን በክርስቶስ ውስጥ ዋስትና እንዳለው ስለሚያውቅ በመተማመን ይመላለሳል። ለመዳናችን ዋስትና የሚያሰጠው

ወይም የሚያስገኝለት ስለ እምነታችን ማውራታችን አይደለም፤ ያንን እርግጠኝነት የሚሰጠን በእምነት ማደጋችን ነው። የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚናገር፥ ነገር ግን በጠባይና በባሕርዩ ምንም ዓይነት የመንፈሳዊ ዕድገት ምልክት የማያሳይ ሰው ራሱን እያታለለና ወደ ፍርድ እያቀረበ ነው።

ጴጥሮስ «መጠራት» እና «መመረጥ» አብረው እንደሚሄዱ ጠቁሟል። ሕዝቡን የሚመርጠው ያው አምላክ የሚጠራበትንም መንገድ ደግሞ ያዘጋጃል። ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች እንደጻፈው እነኚህ ሁለቱ አብረው የሚሄዱ በመሆናቸው «እግዚአብሔር ... ለመዳን እንደ በኩራት መርጧችኋልና ... በወንጌላችን ጠራችሁ» ብሏል (2ኛ ተሰ. 2፡13-14)። ላልዳኑት ሰዎች መመረጥን አንሰብክም፤ ወንጌልን ነው የምንሰብከው። እግዚአብሔር ግን ያንን ወንጌል ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ ለመጥራት ይጠቀምበታል፤ ከዚያ ደግሞ እነዚያ ኃጢአተኞች በእግዚአብሔር እንደተመረጡ ያውቃሉ!

ጴጥሮስ በመንፈስ ላለማደግ ወይም በክርስትና ሕይወት ላለመትጋት መመረጥ እንደ ምክንያት መወሰድ እንደሌለበት ጠቁሟል። አንዳንድ አማኞች «ሊሆን ያለው ይሆናል። ልናደርግ የምንችለው ምንም ነገር የለም» ይላሉ፤ ነገር ግን ጴጥሮስ «ትጉ» ብሎ ይመክራል። ይህም «ማንኛውንም ጥረት አድርጉ» ማለት ነው (ይህንኑ ግስ በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡5 ላይ ተጠቅሞበታል)። ፈቃዱን ለማድረግ ከመቻላችን በፊት እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ መሥራት እንዳለበት እውነት ነው (ፊልጵ. 2፡12-13)። እግዚአብሔር እንዲሠራ የእኛ ፈቃደኝነት ማስፈለጉም እውነት ነው፤ እኛም ከእርሱ ጋር መተባበር አለብን። መለኮታዊ መጠራት ለሰው ልጅ ስንፍና በጭራሽ ምክንያት መሆን አይችልም።

ስለ መመረጡና መጠራቱ እርግጠኛ የሆነ ክርስቲያን ፈጽሞ «አይሰናከልም።» በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ግን ያለማወላወልና በትጋት በሕይወቱ ያስመሰክራል። ሁልጊዜ በተራራ ራስ ላይ ባይኖርም ዘውትር ወደላይ ይወጣል። «እነዚህን ነገሮች» ካደረግን (በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡5-7 የተዘረዘሩትን ነገሮች ከቁ. 8 ጋር አነጻጽር)፤ በየዕለት ኑሯችን ክርስቲያናዊ ዕድገትንና ጠባይን ካሳየን እንደተለወጥንና አንድ ቀን በመንግሥት ለማያት እንደምንሆን እርግጠኞች መሆን እንችላለን።

በእርግጥ በማደግ ላይ ያለ ክርስቲያን ወደ ዘላለማዊው መንግሥት «በሙላት መግባትን» ሊናፍቅ ይችላል! ግሪኮች ይህንን ሐረግ የኦሎምፒክ አሸናፊዎች ወደ አገራቸው ሲመለሱ የሚሰጣቸውን አቀባበል ለመግለጥ ይጠቀሙበት ነበር። ሁሉም አማኝ ወደ ዘላለማዊ መንግሥት ይደርሳል፤ አንዳንዶች ግን ከሌሎች የተለየ አቀባበል ይደረግላቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ «በእሳት እንደሚድን» ዓይነት ሆነው ነው የሚድኑት (1ኛ ቆሮ. 3፡15)።

በ2ኛ ጴጥ. 1፡11 ላይ ያለው «አገለገለ» የሚለው ቃል በቁጥር 5 ላይ ከተጠቀሰው «ጨመረ» ከሚለው ጋር አንድ ዓይነት ነው፤ ይህም በግሪክ «የድራማውን ቡድን ወጪ መክፈል» የሚል ትርጉም ያለው ቃል ነው። የግሪክ የቴአትር ቡድኖች ድራማቸውን ሲያቀርቡ በጣም ብዙ የሆነውን ወጪ አንድ ሰው ይሸፍናል። ቃሉም ውሎ ሲያድር «በልግስና መስጠት» የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር። በመንፈስ ለማደግ በገፍ ከሰጠን (ቁ. 5) እኛም በበኩላችን መንግሥተ ሰማያት ስንገባ እግዚአብሔር በገፍ ይሰጠናል።

እስቲ በማደግ ላይ ያለ ክርስቲያን የሚደሰትባቸውን በረከቶች አስቧቸው:- ፍሬያማነት፥ የማየት ችሎታ፥ ዋስትና፥ መንግሥተ ሰማያት ያለውን መልካም ነገር ሁሉና መንግሥተ ሰማያትም ጭምር ነው!

የክርስትና ሕይወት በእምነት ይጀምራል፤ ያም እምነት ሙት እምነት ካልሆነ በቀር ወደ መንፈሳዊ እድገት መምራት አለበት። ሙት እምነት የሚያድን እምነት አይደለም (ያዕቆብ 2፡14-26)። እምነት ወደ ዕድገት ይመራል፤ ዕድገት ደግሞ በሕይወትና በአገልግሎት ውስጥ ወዳሉ ተግባራዊ ውጤቶች ይመራል። የዚህ ዓይነት ክርስቲያናዊ ልምድ ያላቸው ሰዎች በሐሰት መምህራን ወጥመድ አይወድቁም።

# ንቃና አስታውስ!

## 2ኛ ጴጥሮስ 1፡ 12-21

ሐሰተኛ ትምህርትን ለመቋቋም ተወዳዳሪ የማይገኝለት መከላከያ ንጹሕና እውነተኛ ሕይወት መኖር ነው። በእምነታቸው ጽኑ በሆኑ ታዳጊ ክርስቲያን የተሞላች ቤተ ክርስቲያን የማስመሰል ክርስትና ባላቸው ሐሰተኛ ሐዋርያት ትምህርት አትታለልም፤ ሆኖም ግን ይህ ክርስቲያናዊ ሕይወት ሥልጣን ባለው በእግዚአብሔር ቃል ላይ መመሥረት አለበት። ሐሰተኛ አስተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስን በደምብ የማያውቁትንና ዳሩ ግን ከጌታ ጋር «ልምዶችን» ለማድረግ የሚመኙትን ሰዎች ለማታለል ቀላል ሆኖ ያገኙታል። በግላዊ ልምድ ብቻ መታመንና መለኮታዊ መገለጽን ችላ ማለት አደገኛ ነገር ነው።

ጴጥሮስ በ2ኛ መልእክቱ በ1ኛው ምዕራፍ አጋማሽ ላይ ስለ ክርስቲያናዊ ልምድ አብራርቷል። በመጨረሻው ግማሽ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ስለተሰጠን መገለጽ አብራርቷል። ዓላማውም የእግዚአብሔርን ቃል ስለማወቅ ጥቅምና ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ ስለመደገፍ አስፈላጊነት ማሳየት ነው። ምን እንደሚያምንና ለምን እንደሚያምን የሚያውቅ ክርስቲያን በሐሰተኛ አስተማሪዎችና በጠማማ ትምህርቶቻቸው ብዙ ጊዜ አይታለልም።

ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን ቃል አስተማማኝነትና ዘላቂነት፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሰዎች፥ ከልምዶችና ከዓለም ሁኔታዎች ጋር በማመሳከር በጥንቃቄ አብራርቶታል።

### ሰዎች ይሞታሉ፤ ቃሉ ግን ሕያው ሆኖ ይኖራል (2ኛ ጴጥ. 1፡12-15)

ሐዋርያትና የአዲስ ኪዳን ነቢያት በስብከታቸውና በትምህርታቸው የቤተ ክርስቲያንን መሠረት ጥለዋል (ኤፌ. 2፡20)። እኛ ደግሞ የኋለኞቹ ትውልዶች በዚያ መሠረት ላይ እየገነባን ነው። ሆኖም ሰዎቹ መሠረቱ አልነበሩም፤ መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (1ኛ ቆሮ. 3፡11)። እርሱ ሕንጻውን በአንድነት የሚያገናኝ ዋናው የማዕዘን ድንጋይም ነው (ኤፌ. 2፡20)። ቤተ ክርስቲያን እንድትጸና ካስፈለገ በተራ ሰዎች ላይ መገንባት የለባትም። በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ብቻ መገንባት አለባት።

ጴጥሮስ መቼ እንደሚሞትና እንዴት እንደሚሞት ጌታችን ነግሮት ነበር። «በሽመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ፤ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል» (ዮሐ. 21፡18)። ይህም ጳንጠቆስጤ ከሆነ ከአጭር ጊዜ በኋላ ጴጥሮስ ከእስር ቤት ተጥሎ በማግሥቱ ሊገደል እንደታቀደ ቢያውቅም፥ ሌሊቱን እንዴት በሰላም አንቀላፍቶ ለማሳለፍ የቻለበትን ምክንያት ያስረዳል። ጴጥሮስ ሕይወቱ በሄሮዶስ እጅ እንደማታልፍ በእርግጥ ያውቅ ነበር (የሐዋ. 12፡1 ጀምሮ)። ከአፈ-ታሪክ እንደምንረዳው ጴጥሮስ በሮም ተሰቀለ፥ እንደታመኑት የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁሉ ግን ጴጥሮስ ሥራው እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት መኖር ነበረበት።

ይህንን ደብዳቤ ለመጻፍ ጴጥሮስን ያነሣሡት ከአገልግሎቱ ልምድ የቀሰማቸው ቢያንስ ሦስት መነሻ አሳቦች ነበሩ። የመጀመሪያው ለክርስቶስ ትእዛዝ መታዘዝ ነበር፥ «ቸል አላለም» (2ኛ ጴጥ. 1፡12)። ኢየሱስ ለጴጥሮስ «አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችን አጽና» ብሎት ነበር (ሉቃስ 22፡32)። ስለዚህም ሊፈጽመው የሚገባው ልዩ አገልግሎት እንደነበረው አውቋል።

ሁለተኛው መነሻ አሳቡ ይህ ማሳሰቢያ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚገባው መገንዘቡ ነበር። «ተስማሚ ይመስለኛል» ብሎ የጻፈው «ትክክለኛና ተገቢም ነው» ማለት ነው። ሁልጊዜ ቅዱሳንን ማነቃቃትና የእግዚአብሔርን ቃል ማሳሰብ ትክክል ነው!

ሦስተኛው መነሻ አሳብ በ2ኛ ጴጥ. 1፡15 ላይ «እተጋለሁ» በሚለው ቃል ተጠቅሷል። በቁጥር 5 እና 10 ላይ ትጋት ተብሎ ከተተረጎመው ቃል ጋር አንድ ነው። ይህም «አንድ ነገር ለመሥራት በቅንዓት መነሣሣትን ወይም መበርታትን» ነው የሚያሳየው። ጴጥሮስ በቅርቡ እንደሚሞት አውቆ ነበር፤ ስለዚህም ጊዜው ከመድረሱ በፊት መንፈሳዊ ኃላፊነቶቹን ሊወጣ ይፈልጋል። እኔና እናንተ ግን መቼ እንደምንሞት አናውቅምና ዛሬውኑ ትጉዎች መሆን ብንጀምር ይሻለናል!

ጴጥሮስ ሊያከናውን የፈለገው ምን ነበር? መልሱ በቁጥር 12፥13 እና 15 ላይ በተደጋገመው ቃል ውስጥ ይገኛል፤ ይህም «ማሰብ»ነው። ጴጥሮስ ይህን ነጥብ ፈጽሞ እንዳይረሱት ስለፈለገ የአንባቢዎቹን አእምሮ

በእግዚአብሔር ቃል ማነቃቃት ይፈልጋል። «... በማሳሰቤ ላነቃችሁ የሚገባኝ ይመስለኛል» (1፡13)። ላነቃችሁ የሚለው ግሥ ከእንቅልፍ ልቀስቅሳችሁ እንደ ማለት ነው። ይህንኑ ቃል በገሊላ ባሕር ተነሥቶ የነበረውን ማዕበል ለመግለጽ ተጠቅሞበታል (ዮሐ. 6፡18)። ጴጥሮስ አእምሮአችን እውነትን የመረዳትና ከዚያም ቀስ በቀስ ቸል የማለት አዝማሚያ እንዳለው አውቋል። ማስታወስ የሚገባንን እንረሳለን፤ መርሳት የሚገባንን እናስታውሳለን!

ይህ መልእክት የተላከላቸው አንባቢያን እውነትን ቀደም ሲል ያወቁ ከመሆናቸውም ሌላ ለጊዜው ጸንተውበትም ነበር (2ኛ ጴጥ. 1፡12)። ይህም ማለት ያንን እውነት ለዘለቄታው ያስታውሱታል ወይም ተግባራዊ ያደርጉታል ማለት ሊሆን አይችልም። መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠበት አንዱ ምክንያት ምእመናን የተማሩትን ትምህርት እንዲያስታውሱ ለመርዳት ነበር (ዮሐ. 14፡26)። ለምሳሌ እኔ ራሴ ባለኝ የራድዮ አገልግሎት አንድን ነገር ደጋግሜ በመናገሬ ቅር ከሚላቸው አድማጮች ብዙ ደብዳቤዎች ደርሰውኝ ነበር። ለእነኚህ ሰዎች መልስ ስሰጣቸው ብዙውን ጊዜ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ 3፡1 ላይ የጻፈውን እጠቅስላቸዋለሁ - «ስለ አንድ ነገር መልሼ ልጽፍላችሁ እኔን አይታክተኝም ለእናንተ ግን ደህና ነው።» ሁላችንም እንደምናስታውሰው ጌታችን ብዙውን ጊዜ ሕዝቡን ሲያስተምር ደጋግሞ ይናገር ነበር፤ እርሱ ደግሞ ታላቅ አስተማሪ ነበር።

ጴጥሮስ የሚሞትበት ጊዜ እንደተቃረበ አውቆ ነበር፤ ስለዚህ ፈጽሞ የማይሞት አንድ ነገር ትቶ ለማለፍ ይፈልጋል፤ ይኸውም የእግዚአብሔርን ቃል በጽሑፍ ማስፈርን ነው። እንደተመኘውም ሁለቱ መልእክቶቹ በመንፈስ ተመርተው ከተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል በመሆን ለዘመናት ቅዱሳንን እያገለገሉ ናቸው። ሰዎች ይሞታሉ፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን ሕያው ሆኖ ይኖራል።

ከዚህ በተጨማሪም ጴጥሮስ በተዘዋዋሪ መንገድ የማርቆስን ወንጌል መጥቀሱ ይሆናል። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ለዮሐንስ ማርቆስ ለመጽሐፉ የሚሆነውን መረጃ ይሰጠው ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በጴጥሮስ እንደተጠቀመ ያምናሉ (1ኛ ጴጥ. 5፡13ን ተመልከት)። ከቤተ ክርስቲያን

አባቶች አንዱ ፓፒያስ፡- ማርቆስ «የጴጥሮስ ደቀ መዝሙርና አስተርጓሚ» ነበር ብሏል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ የወንጌልን መልእክት ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው ካላስተላለፈች ሕልውናዋ ያከትማል። አስተማማኝ የተጻፈ መገለጥ ባይኖር ኖሮ በቃላት በሚተላለፍ አፈ ታሪክ ላይ ብቻ መደገፍ ይኖርብን ነበር፤ «ሹክሹክታ» የተባለውን የቡድን ጨዋታ ተጫውታችሁ ታውቁ እንደሆነ፥ አንድ ዐረፍተ ነገር ከአንድ ሰው ወደ ሌላው በቃል ሲተላለፍ ምን ያህል እንደሚለወጥ ታውቃላችሁ! እኛም የምንደገፈው በሞቱ ሰዎች አፈ ታሪክ ላይ ሳይሆን የምንተማመነው በሕያው ቃል እውነት ላይ ነው። ሰዎች ይሞታሉ፤ ቃሉ ግን ለዘለአለም ይኖራል።

አስተማማኝ የጽሑፍ መገለጥ ባይኖረን ኖሮ የቤተ ክርስቲያን ዕድል የማስታወስ ችሎታ ባላቸው ሰዎች ላይ ብቻ በሆነም ነበር። በማስታወስ ችሎታቸው የሚመኩ ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት ሄደው የምስክርነት ቃላቸውን ለመስጠት አያፍሩም። ሆኖም ሦስት ታማኝ ምስክሮች ስለ መኪና ግጭት ሦስት የተለያየ አሳብ ስለሚመሰክሩ ያስገርመን ይሆናል። የማስታወስ ችሎታችን ፍጹም ያልሆነና የመምረጥ ባሕርይ ያለው ነው። አብዛኛውን ጊዜ ማስታወስ የምንፈልገውን ነገር ብቻ እናስታውሳለን፥ ያም ሆኖ ደግሞ ብዙ ጊዜ በተጣመመ መልኩ እናቀርበዋለን።

ለእኛ ግን ደግነቱ በጽሑፍ በሰፈረው የእግዚአብሔር ቃል ላይ መደገፍ መቻላችን ነው። «የተጻፈ» ስለሆነ ለዘለአለም ደግሞ እንደተጻፈ ይጸናል። በዚህ በሕያው ቃል ልንድን (1ኛ ጴጥ. 1፡23-25)፤ ተመግበነው ልናድግበት (1ኛ ጴጥ. 2፡2) እንዲሁም ስናምነውና ስንታዘዘው ልንመራበትና ልንጠበቅበት እንችላለን።

## ገጠመኞች ይረሳሉ፤ ቃሉ ግን ይጸናል
## (2ኛ ጴጥ. 1፡16-18)

የዚህ አንቀጽ አትኩሮት በኢየሱስ ክርስቶስ መለወጥ ላይ ነው። የጌታችን የመለወጡ ገጠመኝ በማቴዎስ (17፡1 ጀምሮ)፤ በማርቆስ (9፡2-8) እና በሉቃስ (9፡28-36) ተዘግቧል፤ ሆኖም ከእነዚህ ጸሐፊዎች ውስጥ ማንም በዚህ ውስጥ አልተሳተፈበትም! ጴጥሮስ ግን ገጠመኙ ሲፈጸም በስፍራው ነበር! በእርግጥም ደግሞ ጴጥሮስ በዚህ ክፍል የተጠቀማቸው ቃላት ራሳቸው

(2ኛ ጴጥ. 1፡12-18) በመለወጥ ተራራ ላይ የነበረውን ገጠመኝ ያስታውሱናል። ማደሪያ በሚለው ቃል ሁለት ጊዜ ተጠቅሟል (ቁ. 13-14)። ይህም «በዚህ ሦስት ዳስ እንሥራ» በማለት ጴጥሮስ (ማቴ. 17፡4) በጊዜው ተናግሮት የነበረውን ያመለክታል። በ 2ኛ ጴጥ. 1፡15 «ማውጣት» የሚለውን የግሪክ ቃል ተጠቅሞአል፤ ቃሉ የእስራኤልንም ከግብፅ መውጣት ሲጠቁም፥ ይኸው ቃል በሉቃስ 9፡31 ተጠቅሶአል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን እንደ ሽንፈት አልቆጠረውም፤ ለእርሱ «መውጣት» ማለት ነበር፤ ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ባወጣበት መንገድ እራሱ ሕዝቡን ከእስራት ያወጣቸዋል! ጴጥሮስ የራሱን ሞት እንደ «መውጣት»፤ ከእስራት እንደ መፈታት ገልጾታል።

በ2ኛ ጴጥ. 1፡16-19 ያለውን «እኛ» የሚለውን የተውላጠ ስም ድግግሞሽ አስተውሉ። ይህ ያመለከተው ጴጥሮስን፤ ያዕቆብንና ዮሐንስን ነው። ኢየሱስ በተለወጠበት ተራራ ላይ ከጌታ ጋር የነበሩ ብቸኛ ሐዋርያት እነዚህ ሦስቱ ብቻ ነበሩ። (ዮሐንስ በወንጌሉ 1፡14 ላይ ይህንን ገጠመኝ ሲጠቅስ «ክብሩን አየን» ብሎአል)። እነዚህ ሦስት ሰዎች ጌታ ከሞት እስከሚነሣ ድረስ ስለ ኢየሱስ መለወጥ መናገር አልነበረባቸውም (ማቴ. 17፡9)። ከዚያ በኋላ ግን በተራራው ላይ ምን እንደሆነ ለሌሎቹ ምእመናን ተናገሩ።

የመለወጡ ዓይነተኛ መልእክት ምን ነበረ? በአንድ በኩል ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠውን ምስክርነት አረጋግጧል (ማቴ. 16፡13-16)። ጴጥሮስ ወልድን በክብሩ አየው፤ አብ ደግሞ ከሰማይ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» በማለት ሲናገር ሰማ (2ኛ ጴጥ. 1፡17)። በመጀመሪያ በክርስቶስ እናምናለን፤ ከዚያም ጌትነቱን እንመሰክራለን፤ እርሱ ደግሞ አስደናቂ ማረጋገጫ ይሰጠናል።

ይህ የመለወጡ ምሥጢር ወደ ቀራንዮ እየተቃረበ ለነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ ልዩ ማስረጃነት ነበረው። ይኸውም ለዓለም ኃጢአት መሥዋዕት ለመሆን ለሚጠብቀው ሞት እግዚአብሔር አብ ልጁን የሚያበረታታበት መንገድ ነበር። በዚሁ ወቅት ሕግና ነቢያት (ሙሴና ኤልያስ) አገልግሎቱን አመልክተዋል፤ አሁን ደግሞ እርሱ እነዚያን ቃሎች ይፈጽማል። አብ ከሰማይ ተናግሮ እርሱን እንደሚወደውና ደስ እንደሚሰኝበት አረጋገጠለት።

በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እስከሆንን ድረስ መለወጥ ወደ ክብር የሚያደርሰን ለመሆኑ ዓይነተኛ ማረጋገጫ ነው።

ሦስተኛው መልእክት ደግሞ ከተስፋይቱ መንግሥት ጋር የተያያዘ ነው። የመለወጡ ታሪክ በተዘገበባቸው በሦስቱም ወንጌላት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሚናገሩ ዐረፍተ ነገሮች እናገኛለን (ማቴ. 16፡28፤ ማር. 9፡1፤ ሉቃስ 9፡27)። ኢየሱስ አንዳንዶቹ ደቀ መዛሙርት ከመሞታቸው በፊት የእግዚአብሔርን መንግሥት ኃይል እንደሚያዩ ቃል ገብቷል! ይህም ጌታችን በመለወጥ ተራራ ላይ ክብሩን ሲገልጥ ተፈጽሞአል። የጌታችንን የመስቀሉን ትምህርት ሊረዱ ላልቻሉ ደቀ መዛሙርት ሲባል የተነገረ የማረጋገጫ ቃል ነበር። እንግዲህ እርሱ በቅርቡ የሚሞት ከሆነ በእነዚያ ወራት ሁሉ ሲሰብከው የነበረው የተስፋው መንግሥት ምን ሊሆን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚያስገኝ ነበር።

ስለዚህ ጴጥሮስ በደብዳቤው ስለዚሁ ጉዳይ ለምን እንደተናገረ አሁን ልንረዳ እንችላለን። ይኸውም የእግዚአብሔር መንግሥት ፈጽሞ እንደማትመጣ የሚያስተምረውን የሐሰተኛ ሐዋርያትን ትምህርት እየተቃወመ መሆኑን ልናይ እንችላለን (2ኛ ጴጥ. 3፡3 ጀምሮ)። እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች የክርስቶስን መምጣት ተስፋ ከደዋል! በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ፋንታ እነዚህ አስመሳዮች «በብልሃት የተፈጠረውን ተረት» በማውራት ከአማኞች የተባረከውን ተስፋቸውን የሚሰርቀውን የሐሰት ወሬ ነዙ (1፡16)።

ተረት የሚለው ቃል በእውነት ላይ ያልተመሠረተ የፈጠራ ታሪክ ማለት ነው። የግሪኩና የሮማው ዓለም በአማልክት ተረቶች የተሞሉ ነበሩ። እነዚህም ዓለምንና አመጣጡን ለማብራራት የሚሞክሩ ተራ የሰው አስተሳሰቦች ናቸው። እነዚህ ልብ ወለድ አፈ ታሪኮች የቱን ያህል ማራኪ ቢሆኑም ክርስቲያን ሊያደምጣቸው አይገባውም (1ኛ ጢሞ. 1፡4)፤ ይልቁኑ አጥብቆ ሊርቃቸው ይገባል (1ኛ ጢሞ. 4፡7)። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ወደፊት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛን ትምህርት ለመስማት የማይፈልጉ አስመሳይ ክርስቲያኖች ስለመምጣታቸው ሲገልጽ፥ «እውነትን ከመስማት ጆሮዎቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ» በማለት (2ኛ ጢሞ. 4፡4) አስጠንቅቆታል። እንደዚሁም ጳውሎስ ቲቶንም ጭምር ስለ «አይሁድ ተረት» አስጠንቅቆታል (ቲቶ 1፡14)። ስለዚህ ከአይሁድ

አንዳንዶቹ እንኳን የተቀደሱትን ቅዱሳት መጻሕፍት ትተው የሰው ፈጠራ የሆኑ ትምህርቶችን በምትኩ ተቀብለዋል።

ኢየሱስ በተለወጠበት ተራራ ላይ ጴጥሮስ ያየውንና የሰማውን በአጭሩ ጽፏል። ኢየሱስ ክርስቶስን ግርማና ክብር ተጎናጽፎ አይቶታል፤ ስለዚህ የኢየሱስ ክርስቶስን «ኃይልና መምጣት» መግለጥ መሰከረ። ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ሲወለድ ክብሩን በግልጥ አላሳየም። እርግጥ ክብሩን በተአምራቶቹ ገልጧል (ዮሐ. 2፡11)፤ ሆኖም ይህንንም ቢሆን በቅድሚያ ለደቀ መዛሙርቱ ሲል ያደረገው ነበር። ፊቱ አያንጸባርቅም ነበር ወይም ደግሞ በራሱ ላይ ቅዱስነቱን የሚያመለክት የብርሃን ፀዳል አልነበረውም። «መልክና ውበት የለውም፤ ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም» (ኢሳ. 53፡2)።

ጴጥሮስ የክርስቶስን ክብር ብቻ አልነበረም ያየው፤ ነገር ግን የአብን ድምፅ «ከገናናው ክብር» ሰምቷል። ምስክሮች ማለት ያዩትንና የሰሙትን በትክክል የሚናገሩ ሰዎች ናቸው (የሐዋ. ሥራ. 4፡20)። ጴጥሮስ ደግሞ የታመነ ምስክር ነበረ። የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነውን? አዎን ነው! እንዴት እናውቃለን? አብ ልጄ ነው ብሎ ስለተናገረ ነዋ!

እኔና እናንተ ለኢየሱስ መለወጥ የዓይን ምስክሮች አልነበርንም፤ ጴጥሮስ ግን በዚያ ነበርና በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ገጠመኙን በታማኝነት ዘግቦልናል። ገጠመኞች ይጠፋሉ፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን ይጸናል! ገጠመኞች የማይጨበጡ ናቸው፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን ተጨባጭ ነው። ገጠመኞች በተለያዩ ተሳታፊዎች በተለያዩ መንገዶች ሊተረጎሙ ይችላሉ፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን አንድ ግልጥ መልእክት ብቻ ነው ያለው። ስለ ገጠመኞቻችን የምናስታውሰው ሳናውቀው ሊፋለስ ይችላል፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን ሳይፋለስ ለዘላለም ይጸናል።

2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 2ን ስናጠና የሐሰት አስተማሪዎች ሰዎችን ከእግዚአብሔር ቃል ለማስናከልና ቃሉን ወደሚፃረሩ «ጥልቅ ገጠመኞች» ለማስገባት እንደሚሞክሩ እንመለከታለን። እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች በመንፈስ ከሆነው የእግዚአብሔር ቃል ፈንታ «የፈጠራ ነገር» በማውራት ለማወናበድ ይሞክራሉ (2፡3)። እንዲሁም «የጥፋት ኑፋቄን» ያስተምራሉ (2፡1)። እንግዲህ ይህ የሞትና የሕይወት ጉዳይ መሆኑን በጥብቅ ልናጤነው

ይገባል! አንድ ሰው እውነትን ካመነ በሕይወት ይኖራል፤ ውሸትን ካመነ ይሞታል፤ በደኅንነትና በኩነኔ መካከል ያለውም ልዩነት ይኸው ነው።

ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ በተራራ ላይ መለወጥ ለማስገንዘብ በሚያደርገው ሙከራ ለአንባቢዎቹ ስለ ክርስትና እምነት ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶችን አስረግጧል። ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነትም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አስረግጧል። የማንኛውም ሃይማኖት መመዘኛ ፈተና «ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ትላለህ?» የሚለው ጥያቄ ነው። አንድ የሃይማኖት አስተማሪ ስለ ክርስቶስ አምላክነት ከካደ ሐሰተኛ ነው ማለት ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡ 18-29፤ 4፡ 1-6)።

ይህ የመጀመሪያው መመዘኛ ጥያቄ ብቻ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም «የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ምንድን ነው? ለምን መጣ? ለምንስ አደረገ?» የሚለውንም መጠየቅ አለብን። መለወጡ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይሰጠናል። ይኸውም ሙሴና ኤልያስ «በክብርም ታይተው በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስላለው ስለ መውጣቱ ይናገሩ ነበርና» (ሉቃስ 9፡ 31)። ስለዚህ አንዳንድ ዘመናዊ የሥነ-መለኮት ሰዎች እንድናምን እንደሚፈልጉት የሞቱን ምሳሌነት ብቻ አልነበረም፤ መውጣትና የተላከበትን ዓላማ ማሳካት ነበረበት። በመስቀል ላይ አንድ ነገር አከናውኗል፤ ይኸውም የጠፉ ኃጢአተኞችን መዋጀት ነው!

ከዚህም በላይ መለወጡ ለቅዱሳት መጻሕፍት እውነተኛነት ማረጋገጫም ነበር። ሙሴ ሕግን ወክሏል፤ ኤልያስ ነቢያትን ወክሏል፤ ሁለቱም ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አመልክተዋል (ዕብ. 1፡ 1-3)። ኢየሱስ ሕግንና ነቢያትን ፈጽሞአል (ሉቃስ 24፡ 27)። እርሱ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ተቀብሎአል፤ በዚህ ምክንያት እኛም በመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት እናምናለን። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነትና ሥልጣን ከጥያቄ ውስጥ እያስገቡ የሚከራከሩት ከሙሴ፥ ከኤልያስ ወይም ከጴጥሮስ ጋር ሳይሆን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።

ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔርን መንግሥት እውነተኛነትንም አረጋግጧል። እኛ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያለን ዕድለኞቹ ሰዎች ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ መስቀሉና ስለ መንግሥቱ ያስተማራቸውን ተከታታይ ትምህርቶች ወደ ኋላ መለስ ብለን ለማጥናትና ለመረዳት እንችላለን። በዚያን ጊዜ ግን የነበሩት

እነዚያ አሥራ ሁለት ሰዎች በጣም ግራ ተጋብተው ነበር። በመከራውና በክብሩ፥ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥቱ መካከል ስላለው ግንኙነት አልተረዱም ነበር፤ (የጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክት ይህንን ርእስ ያብራራል)። በተለወጠበት ወቅት ኢየሱስ ለተከታዮቹ መከራው ወደ ክብር እንደሚመራ እንዲሁም የመስቀሉ የመጨረሻ ውጤት አክሊል እንደሆነ ግልጽ አድርጓል።

እያንዳንዳቸው ወደፊት መከራ መቀበላቸው የማይቀር ነውና ስለዚህ ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ ከመለወጡ ሊማሩት የሚገባቸው አንድ በጣም ተግባራዊ ትምህርት ነበር። ያዕቆብ ከሐዋርያት መካከል ለመሞት የመጀመሪያው ነበር (የሐዋ. 12፡1-2)። ዮሐንስ ረዥም ሕይወት ኖረ፤ ነገር ግን ይህ ወደ ግዞትና ወደ መከራ መራው (ራእይ 1፡9)። ጴጥሮስ በሚያገለግልበት ወቅት የተለያየ መከራ ተቀበለ፤ ከዚያ በኋላ ልክ ጌታ እንደተነበየው ሕይወቱን በመሥዋዕትነት አሳልፎ ሰጠ። ኢየሱስ በተለወጠበት ተራራ ላይ ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ መከራና ክብር አብረው እንደሚሄዱ ተማሩ፤ ለጌታ ሲሉ መከራን ለሚቀበሉ ሁሉ የእግዚአብሔር አብ ልዩ ፍቅርና አበረታችነቱ እንደሚያድርባቸው ተረዱ። ለእኛም ዛሬ የሚያስፈልገን ይህን ዓይነት ትምህርት ነው።

ምንም እንኳ ጴጥሮስ በመካከላችን በአካል ተገኝቶ ገጠመኙን ሊያካፍለን ባይችልም፥ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት በቋሚነት አብሮን እንዲኖር የዚያን ገጠመኝ ዘገባ በጽሑፉ አካፍሎናል። እነዚህን ገጠመኞች ለማባዛት መሞከር አያስፈልገንም፤ እንዲያውም ሰይጣን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ሊመሩን የሚችሉ የማስመሰል ገጠመኞች በቀላሉ ሊፈጥርና ሊያወናብደን ስለሚችል እንደነዚህ ካሉ አደገኛ ገጠመኞች መራቅ ይገባናል።

በዚህ ደብዳቤ መጀመሪያ ላይ «የከብር እምነት» የሚለውን ግሩም ዜና አስታውሱ። ይህ እምነታችን ከሐዋርያት ጋር «የእኩልነት ደረጃ» ይሰጠናል ማለት ነው! እነርሱ በአንደኛ ማዕረግ ተጉዘው እኛን በሁለተኛ ማዕረግ እንድንጓዝ አልተውንም! «ካገኙነው ጋር የተካከለ የክብር እምነት» የሚሉትን ቃላት ነው ጴጥሮስ የጻፈው። እኛ በመለወጥ ተራራ ላይ ከእርሱ ጋር አልነበርንም፤ ሆኖም ግን በጥሞና ስናስበውና የእግዚአብሔር መንፈስ የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር እንዲገልጥልን ስንፈቅድለት፥ አሁንም ቢሆን የዚያ ገጠመኝ ተካፋይ ልንሆን እንችላለን።

ከእነዚህ ንጽጽሮች ሁለት ጠቃሚ እውነቶችን ተምረናል፤ ይኸውም፡- ሰዎች ይሞታሉ ቃሉ ግን ሕያው ነው የሚለውንና እንዲሁም ገጠመኞች ይጠፋሉ ቃሉ ግን ይጸናል የሚለውን ነው። ቀጥለን እንደምንመለከተው ጴጥሮስ ሦስተኛ ንጽጽራዊ ገለጻ አቅርቦአል።

## ዓለም ይጨልማል፤ ቃሉ ግን ያበራል
(2ኛ ጴጥ. 1፡19-21)

በአንዳንድ አቅጣጫዎች ስንመለከት የዓለም ሁኔታ እየተሻሻለ ነው ለማለት እንችላለን። በሕክምና፥ በትራንስፖርትና በመገናኛ በኩል ስለታዩት ዕድገቶች እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ሐዋርያት በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ከሰበኩላቸው ለሚበልጡ ሰዎች እኔ በአንድ የሬድዮ ፕሮግራም ልሰብክ እችላለሁ። ወደ ብዙ ውጪ አገሮች ሊሰራጩና ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ሊተረጎሙ የሚችሉ መጻሕፍት ልጽፍ እችላለሁ። በሳይንስ ግኝቶች በኩል ዓለም ትልቅ ዕድገት አሳይቷል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ ልብ አሁንም ዓመፀኛ ነው። በሁኔታዎች መሻሻላችን ሕይወታችንን አላሻሻለውም። የሕክምና ሳይንስ ሰዎች ረዘም ላለ ጊዜ እንዲኖሩ ቢያስችልም፥ ዳሩ ግን የተሻለ ሕይወት ለመምራታቸው ዋስትና አይሰጥም። ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎችም ከእውነት ይልቅ ሐሰትን በከፍተኛ ፍጥነት ለማሰራጨት ሲያስችሉ፥ ጄት አውሮፕላኖች ደግሞ በፍጥነት ወደ ፈለግነው ቦታ እንድንደርስ አስችለውናል፤ ችግሩ ግን የምንሄድባቸው የተሻሉ ቦታዎች አለመኖራቸው ነው!

ዓለማችን በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ በመዋጧ ልንደነቅ አይገባም። በተራራው ስብከት ውስጥ ጌታችን በሐሰተኛ ትምህርቶቻቸው ቤተ ክርስቲያንን የሚወርሩ መናፍቃን እንደሚነሡ አስጠንቅቋል (ማቴ. 7፡13-29)። እንደዚሁም ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል (የሐዋ. 20፡28-35)። በሌሎችም መልእክቶቹ ተጨማሪ ማስጠንቀቂያዎችን መስጠቱን እንመለከታለን (ሮሜ 16፡17-20፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡1-15፤ ገላ. 1፡1-9፤ ፊልጵ. 3፡17-21፤ ቆላ. 2፡4፥8፤ 1ኛ ጢሞ. 4፤ 2 ጢሞ. 3-4)። ታላቁ «የፍቅር ሐዋርያ» ዮሐንስ እንኳን ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ስለሚሹ ፀረ-ክርስቲያን አስተማሪዎች አስጠንቅቋል (1ኛ ዮሐ. 2፡18-29፤ 4፡1-6)።

በሌላ አነጋገር ሐዋርያት ዓለም በግብረ- ገባዊም ሆነ በመንፈሳዊ ነገሮች እየተሻሻለች ትሄዳለች የሚል ግምት አልነበራቸውም። ሁሉም ሐሰተኛ አስተማሪዎች በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሰርገው እንደሚገቡ፥ ሐሰተኛ ትምህርቶችን እንደሚያስተዋውቁና ብዙ ሰዎችን ወደ ተሳሳተ መንገድ እንደሚመሩ ቤተ ክርስቲያንን አስጠንቅቀዋል። ዓለም ከጊዜ ጊዜ በተባባሰ ሁኔታ እየጨለመች ትሄዳለች፤ ይህም ቢሆን ግን የእግዚአብሔር ቃል እንደ ምንጊዜውም በበለጠ ብርሃን ያበራል።

## ጴጥሮስ ስለዚህ ቃል ሦስት ማረጋገጫዎች ሰጥቷል።

እርግጠኛው ቃል ነው (1፡19)። ጴጥሮስ ኢየሱስ በተለወጥበት ተራራ ላይ ከሆነው ነገር ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ እርግጠኛ ነው የሚል አሳብ አልነበረውም። ያ የሕይወት ገጠመኝ እውንና እውነት የሆነውን ያህል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውም ዘገባ አስተማማኝ ነው። ቀደም ሲል እንዳየነው የጌታ መለወጡ በትንቢት ቃል ለተሰጠው የተስፋ ቃል ማረጋገጫ ነበር፤ አሁን ደግሞ ጴጥሮስ ካጋጠመው ነገር የተነሣ የዚህ የተስፋ ቃል እርግጥኝነትን በበለጠ ጨምሯል። ኢየሱስ በተለወጠ ጊዜ የመለወጥ ክንውኑ የትንቢት ተስፋ ቃሎችን ተጨባጭነት እውን አድርጎታል። ሐሰተኛዎቹ ሐዋርያት የመምጣቱን የተስፋ ቃል ዋጋ ሊያሳጡት ቢሞክሩም (3፡3 ጀምሮ) መጽሐፍ ቅዱስ እርግጠኛ ሆኖ ይነግረናል። ከሁሉ በላይ የመንግሥቱ የተስፋ ቃል በሙሴ፥ በኤልያስ፥ በእግዚአብሔር ልጅና በአብ በተደጋጋሚ ተረጋግጧል! መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን እንድታነበው ዘገባውን ጽፏል!

«የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው» (መዝ. [19]፡7)። «ምስክርህ እጅግ የታመነ ነው» (መዝ. [93]፡5)። «ትእዛዙም ሁሉ የታመነ ነው» (መዝ. [111]፡7)። «ስለዚህ ወደ ትእዛዝህ ሁሉ አቀናሁ፥ የዓመፅንም መንገድ ሁሉ ጠላሁ» (መዝ. [119]፡128)።

2ኛ ጴጥሮስ 1፡16 ንና 19ን እያይዘን ስናነበው የቱን ያህል አስገራሚ ነው። «በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ላንከተል . . . ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን።» ብዙ ጊዜ በምንጓዝበት ወቅት በአይሮፕላን ጣቢያዎች መጻሕፍታቸውን እንድገዛቸው የሚፈልጉ የሐሰት ትምህርት አስፋፊዎች ያጋጥሙኛል። እኔ ግን እውነተኛ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል

ስላለኝና የሰዎች ሃይማኖታዊ ተረቶች ስለማያስፈልጉኝ ሁልጊዜ አልገዛቸሁም እላለሁ። «ገለባ ከስንዴ ጋር ምን አለው? ይላል እግዚአብሔር» (ኤር. 23፡28)።

አንድ ቀን ግን ከእነዚያ መጻሕፍት አንዱን በወንዶች ሽንት ቤት ውስጥ ስላገኘሁት ላነበው ወሰንኩ። ካነበብኩት በኋላም በውስጡ የሰፈሩትን እንደነዚያ ያሉ የሞኝ ተረቶችን ማን ሊያምናቸው እንደሚችል ልገምተው ከምችለው በላይ ሆነብኝ። ለይስሙላ ያህል መጽሐፉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ይናገራል። ጸሐፊው ግን ቅዱሳት መጻሕፍትን በጣም ከማጣመሙ የተነሣ የተጠቀሱት ጥቅሶች እሱ ራሱ ለማለት ከሚፈልገው ጋር እንዲስማሙ አድርጓቸዋል። በብልሃት የተፈጠሩ ተረቶች ነበሩ! እነዚያን ውሸቶች የሚያምን ማንም ሰው ቢኖር፥ በእነዚያ ሽፋኖች መካከል መንፈሳዊ ሞት መኖሩን መገንዘብ አለበት።

የሚያበራ ቃል ነው (1፡19)። ጴጥሮስ ዓለምን «ጨለማ ስፍራ» ብሎ ሲገልጽ ለዚህም የተጠቀመበት ቃል ትርጉም «ጭፍንፍን ያለ» የሚል ነው። ይህም የሚሰጠን ሥዕል በጨለማ የተዋጠን የምድር ቤት ወይም መውጫ የሌለው ረግረግ ስፍራን ነው። የሰው ልጅ ታሪክ በተዋበው የገነት አትክልት ስፍራ ጀመረ፤ ዛሬ ግን ያ የአትክልት ስፍራ ጨፍጋጋና ረግረግ ሆኗል። የዚህን ዓለም ሥርዓት ስትመለከቱ የሚታያችሁ የልባችሁን መንፈሳዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሥዕል ነው። ምንም እንኳ በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ አሁንም ውበትን ብናይም፥ ሆኖም ግን የሰው ዘር በእግዚአብሔር ፍጥረት ላይ በሚያደርሰው ጥፋት የተነሣ፥ በሚሠራው በማናቸውም ነገሮች ውስጥ ውበት አናይም። ጴጥሮስ ይህንን ዓለም እንደ ዔደን ገነት አልተመለከተውም፤ እኛም ከዚህ በተለየ ሁኔታ ማየት የለብንም።

እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ቃሉም ብርሃን ነው። «ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው» (መዝ. [119]፡105)። ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በመጀመሩ «በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ» (ማቴ. 4፡16)። የእርሱ ወደዚህ ዓለም መምጣት የአዲስ ቀን ንጋት ነበረ (ሉቃስ 1፡78)። እኛ ክርስቲያኖች የዓለም ብርሃን ነን፤ (ማቴ. 5፡14-16)፤ ሰዎች ደግሞ መንገዱን እንዲያዩና እንዲድኑ (ፊልጵ. 2፡14-16) የሕይወትን ቃል የማቅረብ ዕድልና ኃላፊነት የተሰጠን ለእኛ ነው።

እንደ አማኞች ይህንን ቃል መጠበቅና እሱ በሚለው ነገር ሕይወታችንን ማስገዛት አለብን። ለማያምኑ ወደ ዘላለም ጨለማ እስከሚደርሱ ድረስ ነገሮች እየደበዘዙና እየጨለሙ ይሄዳሉ፤ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ግን የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስና የከበረውን አዲስ ቀን መንጋት ይናፍቃሉ። ሐሰተኛ አስተማሪዎች በክርስቶስ መመለስና በአዲስ ቀን መንጋት አሳብ ይዘብታሉ፤ ጴጥሮስ ግን የእግዚአብሔርን ቃል ሐቀኝነት አስረግጧል። «የጌታ ቀን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል» (2ኛ ጴጥ. 3፡10)።

ከመንጋቱ በፊት ለጨለማው መወገድ አብሣሪ የሆነው «የንጋት ኮከብ» ደምቆ ያበራል። ለቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ «የሚያበራ የንጋት ኮከብ» ነው (ራእይ 22፡16)። ቀኑ ምንም ያህል ቢጨልም የመምጣቱ ተስፋ ደምቆ ያበራል (ዘኁልቁ 24፡17ን ተመልከት)። ለሚያምኑ ፈውስን ለማያምኑት ግን ፍርድን የሚያመጣ «የጽድቅ ፀሐይ» ነው (ሚልክያስ 4፡1-2)። ስለዚህ እኛስ የቁን ያህል የእግዚአብሔርን እርግጠኛና የሚያበራ ቃል አመስጋኞች ልንሆንና በዚህ በጨለማ ጊዜያት በተስፋ ልንጠብቀው ይገባን ይሆን?

በመንፈስ የተሰጠ ቃል ነው (1፡20-21)። ይህ የእግዚአብሔርን ቃል መለኮታዊነት ከሚያስረግጡት ሁለቱ የቅዱሳት መጻሕፍት አንደኛው ነው። ሌላው 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡14-17 ላይ የሚገኘው ነው። ጴጥሮስ ቅዱሳት መጻሕፍት «በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው» የእግዚአብሔር ሰዎች የጻፉት እንጂ ሰዎች በራሳቸው አሳብና ቃላት ተጠቅመው የጻፉት እንዳልሆነ አስረግጧል። ተነድተው ተብሎ የተተረጎመው ቃል «አብሮ መወሰድ - መርከብ በንፋስ እንደሚወሰድ» ማለት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት «በእግዚአብሔር እፍ የተባለባቸው» ናቸው፤ የሰው ፈጠራዎች አይደሉም።

አሁንም ቢሆን ጴጥሮስ ሐሰተኛ ሐዋርያትን እንደገና እየተቃወመ ነበር። እነርሱም «የተፈጠረ ነገር» አስተምረዋል (2ኛ ጴጥ. 2፡3)፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሌላ ትርጉም እንዲሰጡ አጣምመዋቸዋል (3፡16)። የክርስቶስን መምጣት የተስፋ ቃል አላመኑበትምና (3፡3-4) ስለዚህ የትንቢት ቃሎችንም ጭምር ክደዋል።

ቃሉን የሰጠው መንፈስ እስከሆነ፥ ቃሉን ማስተማርና በትክክል መተርጎም የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው (1ኛ ቆሮ. 2፡14-15ን

ተመለከቱ)። በእርግጥ እያንዳንዱ ሐሰተኛ አስተማሪ «በመንፈስ እንደተመራ» ይናገራል፤ ነገር ግን ያ በአግባቡ የማይጠቀምበት የእግዚአብሔር ቃል ራሱ ቶሎ ያጋልጠዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በሰው ፈቃድ እስካልመጣ ድረስ ሰው በራሱ ፈቃድ ሊረዳው አይቻልም። ከአይሁድ መምህራን አንዱና መሪ የነበረው ኒቆዲሞስ እንኳ በጣም አስፈላጊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርት አላወቀም ነበር (ዮሐ. 3፡ 10-12)።

በ2ኛ ጴጥ. 1፡20 ላይ ጴጥሮስ መጽሐፍ ቅዱስን በግል ማጥናትን እየከለከለ አልነበረም። አንዳንድ የሃይማኖት ቡድኖች መጻሕፍትን መተርጎም የሚችሉት «መንፈሳዊ መሪዎች» ብቻ እንደሆኑ ከማስተማራቸውም ሌላ ይህንን ጥቅስ እንደ መከላከያቸው ተጠቅመውበታል፤ ነገር ግን ጴጥሮስ በመሠረቱ የጻፈው ስለ መጻሕፍት ምንጭ እንጂ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጎም አልነበረም። ቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጡት በእግዚአብሔር መንፈስ በተነዱ ቅዱሳን ሰዎች ነው። ስለዚህ በመንፈስ እስከ ተሰጠ ድረስ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ሊያስተምረው የሚገባው።

ለገዛ ራሱ ተብሎ የተተረጎመው ቃል «የግሉ» ወይም «የራሱ» ማለት ነው። ይህም የሚያስተላልፈው አሳብ ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ የተጻፉ እስከሆነ ድረስ «በወጥነት» ሊጠኑ እንጂ አንዱ መጽሐፍ ከሌሎች ተለይቶ መታየት የለበትም የሚል ነው። ጥቅሶችን ከትክክለኛው ዐውደ ምንባባቸው እስከለየናቸው ለማንኛውም ነገር በማስረገጫነት በመጥቀስ ለመጠቀም ይቻላል። ይህን ደግሞ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ያለሐፍረት የሚጠቀሙበት መንገድ ነው። ጴጥሮስ የሐዋርያት ምስክርነት የትንቢቱን ቃል ምስክርነት ማረጋገጡን እንደገለጸው ሁሉ፥ ምንም ቅራኔ የሌለበት አንድ ብቸኛ መልእክት መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ስለዚህ እነዚህ አስተማሪዎች የኑፋቄ ትምህርቶቻቸውን «ለማስረገጥ» የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል አሳስቶ በመጠቀም ይሆናል። የተለያዩ ክፍሎችን ከዐውደ ምንባባችው ውጪ ለይቶ በመጥቀስ እንደ ትክክለኛ እንዳልሆኑ ማስረጃዎች ሲጠቀሙባችው ይታያል።

የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው ለተራ ሰዎች እንጂ ለሥነ-መለኮት ሊቃውንት አይደለም። ጸሐፊዎቹ በዚያ መልኩ እንዲጻፍ ባደረገው መንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተራ ሰዎች ሊገባቸው፥ ሊረዱትና እንዲሁም ተግባራዊ

ሊያደርጉት ይችላሉ ብለው በገመቱት መንገድ አዘጋጅተውታል። ቅን የሆነ አማኝ ግለሰብ ሲያነበውና የእግዚአብሔርን ቃል በጥሞና ሲያስበው ስለ እግዚአብሔር ሊማር ይችላል፤ እውነትን እንዲያሳዩት «የተመራመሩ ሰዎች» አያስፈልጉትም። እንዲህም ስለተባለ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማብራራትና የማዛመድ ስጦታ ያላቸውን ልዩ ሰዎች ማለትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አስተማሪዎችን አገልግሎት መቃወም አይደለም (ኤፌ. 4፡11)። እንደዚሁ ሁሉ እነዚህን ትምህርቶች በበለጠ ግልጽ ለማድረግና ለማስረዳት ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዓመታት ባደረገችው ጥረት የተገኘውን «የተከማቸ ጥበብ» ለመቃወም አይደለም። አስተማሪዎችና የእምነት መግለጫዎች የራሳቸው የሆነ ክልል አላቸው፤ በመሆኑም ከአማኝ ግለሰብ ኅሊና ውስጥ የቃሉን ሥልጣን ያለአግባብ መንጠቅ የለባቸውም።

ሌሊቱ እስከሚነጋ ድረስ የጌታችን የመምጣቱ ፍቅር በልባችን ውስጥ እንደሚያበራ ኮከብ አድርገን ልንጠነቀቅለት ይገባል (2ኛ ጴጥ. 1፡19)። መገለጡን የማንወድ ከሆን የቀኑን መድረስ በጉጉት አንጠባበቀውም። ያንን መጠባበቅ ብሩህ አድርጎ የሚያቆየው ደግሞ ቃሉ ነው።

ሰዎች ይሞታሉ፤ ቃሉ ግን ሕያው ነው። ገጠመኞች ይጠፋሉ፤ ቃሉ ግን ይጸናል። ዓለም እየጨለመ ይሄዳል፤ የትንቢቱ መብራት ግን እየደመቀ ይበራል። ሕይወቱን በእግዚአብሔር ቃል ያ የሚገነባና የአዳኙን መመለስ የሚጠብቅ አማኝ በሐሰተኛ አስተማሪዎች ተገፋፍቶ መንገዱን ለቆ የመመራት ዕድል አይገጥመውም። በመንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት የተማረና በእርግጠኛው የእግዚአብሔር ቃል ላይ ጸንቶ የተመሠረተ ይሆናል።

የጴጥሮስ መልእክት «ንቃ - እና አስታውስ!» ነው። የምትተኛ ቤተ ክርስቲያን የሰይጣን መፈንጫ ናት። ሰዎች ተኝተው ሳሉ ነው ጠላት መጥቶ እንክርዳዱን የዘራው (ማቴ. 13፡24 ጀምሮ)። እንደዚሁም ጴጥሮስ ኢየሱስ በተለወጠበት ተራራ ላይ አንቀላፍቶ በነበረበት ጊዜ ብዙ ነገር ሊያመልጠው ይችል ነበር።

«ንቃ!» ነው የሐዋርያው መልእክት። ስለዚህ «ንቃና አስታውስ!»

# ከአስመሳዮች ተጠንቀቅ

## 2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 1-9

ዛሬ በዓለም ላይ እጅግ በጣም ስኬታማ ከሆኑት ገንዘብ የማግኚያ መንገዶች አንዱ «የውሸት ኪነ-ጥበብ» ነው። አንድ ወጥ ሥራዎችን በማስመሰል የተሠሩ «የማስመሰል ሥዕሎችን» መሸጥ ነው። አንዳንድ ምርጥ የሥዕል ማሳያ አዳራሾችና የግል ስብስቦች እንኳን ታላላቅ የፈጠራ ሥራዎች በሆኑ ሥዕሎች ግልባጭ ቅጂዎች ተወርረዋል። እንዲሁም አሳታሚዎች በፍጹም «እውነተኛ» ያልሆኑትን ጽሑፎችን በመግዛትና በማሳተም በማጭበርበር ተግባር ላይ ይካፈላሉ።

የማስመሰል አሠራሮች አዲስ ግኝቶች አይደሉም። «ታላቁ አስመሳይ» ሰይጣን (2ኛ ቆሮ. 11፡13-15) ሔዋንን በገነት ካሳሳታት ጊዜ ጀምሮ አሁንም በርትቶ በመሥራት ላይ ይገኛል (ዘፍ. 3፡1-7፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡1-4)። እርሱም የራሱ የሆኑ ሐሰተኛ ክርስቲያኖች (ማቴ. 13፡38፤ ዮሐ. 8፡44)፥ ሐሰተኛ ወንጌል (ገላ. 1፡6-9) እና እንዲሁም ሐሰተኛ ጽድቅ አለው (ሮሜ 9፡30-10፡4)። ብሎም አንድ ቀን ሐሰተኛውን ክርስቶስ ለዓለም ያቀርባል (2ኛ ተሰ. 2)።

የእስራኤል ሕዝብ በሐሰተኞች ነቢያት ሁልጊዜ ወደ ተሳሳተ መንገድ ይመራ ነበር። ኤልያስ ከበአል ነቢያት ጋር ቢታገልም እነርሱ ግን የጣዖት አምልኮ ያራምዱ ነበረ፤ ይሁን እንጂ የባሰ ጥፋት ያደረሱት ለያሕዌ አምላክ የቆሙ በማስመሰል ያውጁ የነበሩት የአይሁድ ሐሰተኛ ነቢያት ነበሩ። ኤርምያስና ሕዝቅኤል ይህንን የሚመሳሰለውን የአስመሳዮች አገልግሎት ቢያጋልጡም ሕዝቡ ግን የውሸት ነቢያትን በዚያው መጠን ተከተላቸው። ለምን? ምክንያቱ የሐሰተኛ ነቢያት ሃይማኖት ለተከታዮቹ ቀላል፥ አመቺና ዝነኛ ስለነበረ ነው። ሐሰተኛ ነቢያት የውሸት ሰላም የመስበካቸው ጉዳይ የተረጋገጠ ቢሆንም ሕዝቡን ግን አላስጨነቃቸውም ነበር (ኤር. 6፡14) ምክንያቱም ለመስማት የሚፈልጉት መልእክት ይህን የመሰለውን በመሆኑ ነው!

ሐዋርያትና ነቢያት የቤተ ክርስቲያንን መሠረት ከጣሉ በኋላ ከመድረኩ ተገልለዋል (ኤፌ. 2፡20)። ለዚህም ነው ጴጥሮስ ከሐሰተኛ ነቢያት ይልቅ

ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የጻፈው፤ ምክንያቱም አሁንም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ስላሉ ነው። የቤተ ክርስቲያን አባላት «ነቢይ»ን ላይሰሙ ይችላሉ፤ ቀልዱን አስተማሪ ግን ይሰማሉ። ሰይጣን ሁልጊዜ ውጤት የሚያስገኝለትን አቀራረብ ስለሚያውቅ በሚያዋጣው ዘዴ ይጠቀማል።

ስለዚህ ጴጥሮስ እንድንነቃ ሊያስጠነቅቀን በመፈለጉ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚገኙ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ሦስት መለያ ገጽታዎች አቅርቧል።

## ሐሰተኛ አስተማሪዎች የተገለጹበት ሁኔታ
(2ኛ ጴጥ. 2፡1-3)

ይህ የሚያዝናና ገለጻ አልነበረም! ጴጥሮስ እነኝህን ሰዎች የገለጸበት ቋንቋ ከበድ ያለ ነበር። የይሁዳን መልእክት ስታነቡም በተመሳሳይ ቋንቋ መጠቀሙንና በይበልጥም እውነቱን የሚያፍረጠርጥ መሆኑን ትረዳላችሁ። ጴጥሮስ እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃልና የኑፋቄ ሐሰተኛ ትምህርቶች በመቻቻል በአንድነት ሊኖሩ እንደማይችሉ ተገንዝቦአል። ለቀዶ ጥገና ሐኪሙ በበሽተኛው ውስጥ ያለውን የካንሰር እባጭ ቆርጦ ከመጣል በስተቀር ምንም ዓይነት አማራጭ እንደማይኖረው ሁሉ፥ ጴጥሮስም ሐሰተኛ ትምህርቶችን አስመልክቶ ምንም ዓይነት ድርድር ማካሄድ እንደማይቻል ገልጿል።

አታላይነት (2፡1)፡- ይህ ርእስ በምዕራፉ ሁሉ ውስጥ ደግሞ ደጋግሞ ይታያል። የእነዚህ አስተማሪዎች መልእክት ውሸት ነው፤ ጴጥሮስ የሚያስተምሩትን ነገር «የሚያጠፉ ኑፋቄ» ብሎ ጠርቶታል። በመሠረቱ ኑፋቄ የሚለው ቃል «ማማረጥ» ማለት ነበር፤ ነገር ግን ከጊዜ በኋላ «የተለየ ክፍል ወይም ቡድን» ተባለ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የቡድን መንፈስ ማራመድ አንዱ የሥጋ ሥራ ነው (ገላ. 5፡20)። ምንጊዜም አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ለሌላ አባል «ከኔ ወገን ነህ ወይስ ከመጋቢው ወገን?» ቢለው የቡድን መንፈስ እያራመደና ክፍፍልን እየፈጠረ ነው ማለት ነው። ሐሰተኛ አስተማሪ በራሱ ትምህርቶችና በእውነተኛ የክርስትና እምነት ትምህርቶች መካከል እንድትመርጡ ያስገድዳችኋል።

መልእክታቸው ብቻ ሳይሆን የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎቻቸውም ጭምር ሐሰተኛ ናቸው። የሚያምኑትን በግልጥ ከመናገር ይልቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን

ውስጥ የሐሰት ካባ በመደረብ እውነተኛና ታማኝ ክርስቲያን መስለው ለመታየት ይሞክራሉ። የዚህም ቀጥተኛው አባባል ኑፋቄን «በድብቅ አብረው ያስገባሉ» የሚለው ነው። እውነትን ለመካድ በፊት ለፊት አይደፍሩም። ሐሰተኛ ትምህርቶቻቸውን ከእውነት ጋር ጎን ለጎን ያስቀምጡና የእምነትን ዋና ዋና እውነቶች የሚያምኑ ያስመስላሉ። ሆኖም ብዙ ሳይቆይ እውነተኛውን ትምህርት ያስወግዱና ሐሰተኛ ትምህርታቸውን በቦታው ይተካሉ።

በ2ኛ ጴጥ. 2፡3 ጴጥሮስ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የራሳቸውን ፈጠራ እንደሚጠቀሙ አመልክቶአል። የግሪኩ ቃል «ፕላስቶስ» ነው የሚለው። ከዚህ የእንግሊዝኛውን «ፕላስቲክ» የሚለውን ቃል እናገኛለን። ፕላስቲክ ቃላት እንዲሉ! የፕላስቲክን ቅርጽ እንዳሻ ለመቀያየር እንደሚቻል እነርሱም በፕላስቲክ ቃላት ይጠቀማሉ! ሐሰተኛ አስተማሪዎች እኛ በምንጠቀምባቸው ቃላት ይጠቀሙ እንጂ ለትርጉማቸው ግን ከእኛ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መዝገበ ቃላት አይጠቀሙም። ስለ «ደኅንነት»፥ ስለ «እስትንፋሰ እግዚአብሔር» እና ስለ ክርስትና እምነት ታላላቅ ቃላት ይናገራሉ፤ ነገር ግን ለቃላቱ የሚሰጧቸው ትርጉም እኛ ከምንሰጣቸው በፍጹም የተለዩ ናቸው። ያልበሰሉና ያልተማሩ አማኞች ግን እነዚህን ሰባኪዎች ይሰሙና ወይም መጻሕፍታቸውን ያነቡና እነዚህ ሰዎች በእምነት ትክክለኛ እንደሆኑ ያስባሉ፤ ነገር ግን አይደሉም።

ሰይጣን አታላይ ነው፤ አገልጋዮቹም አታላዮች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስን ለእውነተኛ ትምህርት ሳይሆን ለማታለል ይጠቀሙበታል። ሰይጣን ሔዋንን ሲያታልል በተጠቀመበት ዘዴ ይጠቀማሉ (ዘፍ. 3፡1-6)። ሰይጣን በመጀመሪያ «በውኑ እግዚአብሔር አዝዟልን?» በማለት የእግዚአብሔርን ቃል አስታከኮ ጥያቄ አቀረበ። ከዚያም ቀጥሎ «ሞትን አትሞቱም» በማለት የእግዚአብሔርን ቃል ካደ። በመጨረሻም «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ» በማለት የእግዚአብሔርን ቃል በራሱ ሐሰተኛ ቃል ተክቶ ተናገረ።

የእነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ትምህርት እንደ አጵሎስ ሁሉ ካለማወቅ ወይም ከየዋህነት የመነጨ አልነበረም (የሐዋ. 18፡24-28)። እውነትን ያውቃሉ ግን ሆን ብለው ትተውታል። በአንድ የአገልጋዮች ስብሰባ ላይ አንድ ከእውነተኛው ትምህርት የተለየ አስተሳሰብ የነበረው አንድ አስመሳይ

መጋቢ በ«ጳውሎስ የመጽደቅ አመለካከቶች» ላይ ጽሑፍ እንዲያዘጋጅ እንደተጠየቀ አንብቤ ነበር። እርሱም ያሰማው ትምህርት የወንጌልን እውነትና በእምነት ስለሚገኘው ጽድቅ የሚናገርና ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነበር።

ከዚያ ከመጋቢ አንደበት ይህን በመስማቱ ግራ የተጋባው አንድ ወዳጄ «በዚህ እንደምታምን አላውቅም ነበር» ሲል ከስብሰባው በኋላ ጥያቄ አቀረበለት።

መጋቢውም «አላምንበትም» ሲል መለሰ፥ በመቀጠልም «ስለ መጽደቅ ያሉኝን የግል አመለካከቶች እንድነግራቸው እኔን አልጠየቁኝም። እነርሱ የጠየቁኝ በተለይ የጳውሎስን አመለካከት እንዳሰማቸው ነው» ብሎ መለሰ።

ከሕደት (2፡1)፡- ሐሰተኛ አስተማሪዎች ከሚያምኑበት ይልቅ በሚክዱት ነገር የተነሣ ይበለጥ የታወቁ ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስን በመንፈስ ተመርቶ መጻፍ፥ የሰውን ኃጢአተኛነት፥ የኢየሱስ ክርስቶስን መሥዋዕትነትንና የመስቀል ላይ ሞትን፤ በእምነት ብቻ መዳንን፥ እንዲሁም የዘላለም ፍርድን እውነታ እንኳ ይክዳሉ። በተለይም የኢየሱስን አምላክነት ካስወገዱ የክርስትናን እምነትና እውነት ሙሉ በሙሉ ሊያጠፉ እንደሚችሉ ያውቃሉ። ስለዚህም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ይክዳሉ። ክርስትና ክርስቶስ ነው፤ እሱ ደግሞ ነኝ የሚለውን ካልሆነ፥ የክርስትና እምነት ሊኖር አይችልም።

እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ያልዳኑ ስለ መሆናቸው ግልጽ መሆን አለበት። እነርሱም የተነጻጸሩት ከውሾችና ከአሳማዎች ጋር እንጂ ከበጎች ጋር አይደለም (2፡22)። ይሁዳ እነዚህኑ ሰዎች በሚገባ ከመግለጹም በቁጥር 19 ላይ ደግሞ «መንፈስም የሌላቸው» ብሎ በመሰየም ይጠራቸዋል። አንድ ሰው በውስጡ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሌለው የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም (ሮሜ 8፡9)። የዳነ መስሎ ሊታይ፥ እንዲሁም የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባል ወይም ሹም እንኳን ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ጌታን ቀስ በቀስ መካዱ የማይቀር ነው።

እነዚህ ሰዎች በጌታ «የተዋጁት» በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር? ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን መሞቱ እውነት ሆኖ ሳለ (ኤፌ. 5፡25)፥ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት መሞቱም እውነት ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡2)። በውስጡ ያለውን ዕንቁ እንዲያገኝ እርሻውን በሙሉ (ዓለምን) የገዛው ነጋዴ እርሱ ነው (ማቴ.

13:44)። ይህንን እውነት ተግባራዊ ወደማድረጉ ስንመጣ ግን ደኅንነት ለሚያምኑ ብቻ ነው የተወሰነው፤ ነገር ግን ወደ ብቃት ደረጃ ስንመጣ ሞቱ ለዓለም ሁሉ የሚበቃ ነው። የሚቃወሙትና የሚክዱትን እንኳ ዋጅቶአቸዋል! ይህም ፍዳቸውን የበለጠ ያበዛዋል።

መልካምና እግዚአብሔርን የሚመስሉ ክርስቲያኖች እንኳ በአንዳንድ አነስተኛ የሃይማኖት ትምህርት ነጥቦች ላይ ላይስማሙ ይችላሉ፤ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ ላይ ግን ሁሉም አንድ ያልተለያየ አቋም አላቸው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅና እግዚአብሔር ወልድ ነው። እሱ ብቸኛ አዳኝ ነው። ይህንን መካድ የገዛ ነፍሳችሁን ለፍርድ ማዘጋጀት ነው።

መዳራት (2:2)፡ በተንኮል ወይም በብልግና መጠመድ ማለት ልቅ ሥነ-ምግባር ማለት ነው። ይሁዳ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን «የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ» ብሎ ይከሳቸዋል (ቁ. 4)። እኛም እነኚህ ሰዎች የክርስትናን እምነት እውነቶች ለምን እንደሚክዱ የምንረዳው በዚህ አጋጣሚ ነው። ይኸውም የገዛ ራሳቸውን ምኞት ለማርካት ስለሚፈልጉና ይህንን ደግሞ በሃይማኖት ስም ለማድረግ ስለሚሹ ነው። በኤርምያስ ዘመን የነበሩት ሐሰተኛ ነቢያት በተመሳሳይ ኃጢአት የተያዙ ነበሩ (ኤር. 23:14፥ 32)።

የድርጊታቸውን ክፉ ምሳሌነት ብዙዎች መከተላቸው ሰዎች ከእውነት ይልቅ ውሸትን፥ ከመንፈሳዊው ይልቅ ሥጋዊውን መከተል እንደሚሻላቸው የሚያስረዳ ማረጋገጫ ነው። እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች በአገልግሎታቸው በጣም የተሳካላቸው ናቸው! ስለ ተልእኳቸው መሳካት በየጊዜው የሚያቀርቡት መግለጫ የተጋነነ ነው፤ እነሱን ለመስማት ደግሞ ብዙ ሕዝብ ይሰበሰባል! የሰውን ብዛት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ግን የእውነተኝነት ማረጋገጫ አይደለም። ወደ ጥፋት የሚወስደው ሰፊው መንገድ በሰዎች የተጨናነቀ ነው (ማቴ. 7:13-14)። ብዙዎች የክርቶስ እውነተኛ ባሪያዎች እንደሆኑ ቢናገሩም፥ በመጨረሻው ቀን ግን አላውቃችሁም ይባላሉ (ማቴ. 7:21-23)።

በተከታዮቻቸውስ ምን ይደርሳል? በአንድ በኩል በክርስቶስ ስም ላይ ነቀፋን ያመጣሉ። በእነርሱ እርኩስ አኗኗር የተነሣ የክርስትና እምነት ክፉ ስም ይሰጠዋል። «እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ በግልጥ ይናገራሉ፥ ዳሩ ግን የሚያስጸይፉና የማይታዘዙ ለበጎ ሥራ ሁሉ የማይበቁ ስለ ሆኑ፥

በሥራቸው ይክዱታል» (ቲቶ 1፡16)። «በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና» (ሮሜ 2፡24)። እዚያ የቤተ ክርስቲያን አባላት ቢሆኑም እንኳን በክርስትና ሕይወት አረማመዳቸው መልካም ስም ስለሌላቸው ለክርስቶስ ወንጌል ዕንቅፋቶች ናቸው።

ስግብግብነት (2፡3)፡- የሐሰት አስተማሪዎች ፍላጎት በአንድ ነገር ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። ገንዘብን ማግኘት! የማያውቁትን ሰዎች ይበዘብዛሉ፥ «እንደ ንግድ ዕቃ ያተርፉባቸዋል» ይላል። እንዲሁም የውስጥ ስግብግብነታቸውን ለመሸፈኛ ሃይማኖትን እንደ ካባ ይደርባሉ (1ኛ ተሰ. 2፡5)። ጌታችን ግን ድሀ ሰው ነበር፤ ሐዋርያትም እንዲሁ፤ ሆኖም ሌሎችን ለማገልገል ራሳቸውን ሰጥተው ነበር። እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች በብልሃት ሌሎች እንዲያገለግሏቸው የሚያደርጉ ባለጠጋ ሰዎች ናቸው! ሚክያስ በዘመኑ የነበሩትን የሐሰት ነቢያት በጥሩ ሁኔታ ገልጿቸዋል። «አለቆችዋ በጉቦ ይፈርዳሉ፥ ካህናቶችዋም በዋጋ ያስተምራሉ፥ ነቢያቶችዋም በገንዘብ ያምዋርታሉ» (ሚክ. 3፡11)። በእርግጥ ለሠራተኛ ደመወዝ ይገባዋል (ሉቃስ 10፡7)፤ ነገር ግን ለማገልገል የሚያስነሣው ምክንያት ከገንዘብ ፍላጎት የበለጠ መሆን አለበት። ብዙውን ጊዜ ክፉ ሥራ፥ ገንዘብን መውደድና ትዕቢት የብዙ ሰዎች ጥፋት እንደሆነ ይነገራል። እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች በሦስቱም በደለኞች ነበሩ!

ተከታዮቻቸውን ለማስገረምና በእነርሱም ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር በአስመሳይና እንደ ፕላስቲክ በሚጠማዘዙ ታላላቅ ቃላት ይጠቀማሉ (2ኛ ጴጥ. 2፡18)። ኃጢአተኞችን ለማታለል ለመስማት በሚፈልጓቸውና እኔነታቸውን በሚገነቡ ቃላቶች ይነግሯቸዋል (በ1ኛ ተሰ. 2፡5 ያለውን ንጽጽር ተመልከት)። የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የሚጥሉትንና ወደ ተረቶች ፊቅ የሚሉትን ሰዎች ጆሮ በሚማርክ ወሬ ጆሮአቸውን ያኩላቸዋል (2ኛ ጢሞ. 4፡1-4)። ሃይማኖት በራሱ ደካማ ሰዎችን ለመበዝበዝ በጣም ውጤታማ መሣሪያ ሊሆን ይችላል፤ በመሆኑም እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ሃይማኖትን ማግኘት ለሚፈልጉት ነገር እንደመጠቀሚያ ይገለገሉበታል። ስለዚህ ይህን የመሳሰሉት ሰዎች አገልጋዮች አይደሉም፤ ነጋዴዎች ናቸው እንጂ።

እውነተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ምንም የሚሰውረው ነገር የለውም። ሕይወቱም ሆነ አገልግሎቱ እንደተገለጠ መጽሐፍ ነው። እውነትን

በፍቅር ይሰብካል፤ እንዲሁም የገዛ ራሱን የራስ ወዳድነት አሳቦች ለማራመድ መጻሕፍትን አያጣምምም። ባለጠጋውን አያባብልም፤ ወይም ገንዘብ ለማፍራት ብቻ አያገለግልም። ጳውሎስ እውነተኛውን አገልጋይ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፡2 ላይ ገልጾታል፡- «ነገር ግን የሚያሳፍረውን ስውር ነገር ጥለናልና በተንኰል አንመላለስም የእግዚአብሔርንም ቃል በውሸት አንቀላቅልም፤ እውነትን ለመግለጥ ግን በእግዚአብሔር ፊት ለሰው ሕሊና ሁሉ ራሳችንን እናመሰግናለን።» ይህንን አገላለጽ ጴጥሮስ ከጻፈውና ይሁዳ ከጻፈው ጋር አመሳክሩና ልዩነቱን ታያላችሁ። ስለዚህ ሰዎችን የሚበዘብዙና ጌታን የሚክዱ ሰዎችን አገልግሎት ላለመደገፍ ምንኛ ንቁዎች መሆን አለብን።

## በሐሰተኛ አስተማሪዎች ላይ የሚደርሰው ጥፋት
## (2ኛ ጴጥ. 2፡3-6፥9)

ጴጥሮስ ለእነዚህ «መናፍቃን» ምንም ተስፋ አልታየውም፤ ጥፋታቸው የማይቀርና የተወሰነ ነው። የእርሱም አመለካከት «ከእኛ ጋር ላይስማማ ይችላል፤ ነገር ግን ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ሌሎች ብዙ መንገዶች አሉ» ከሚሉት ከዛሬዎቹ «ለዘብተኛ» የሃይማኖት ሰዎች አስተሳሰብ የተለየ ነበረ። ጴጥሮስ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች «ቅንን መንገድ የተዉ» መሆናቸውን በግልጽ አስቀምጦታል (2ኛ ጴጥ. 2፡15)። ይህ ደግሞ በተሳሳተ መንገድ እየሄዱ ናቸው ማለት ነው! ይዋል ይደር እንጂ፥ ፍርዳቸው የተረጋገጠ ነው። ምርመራው አልቋል፤ የፍርድ ውሳኔው ግን ገና ተግባራዊ አልሆነም። ይህንንም ፍርድ በተመለከተ ጴጥሮስ አይዘገይም ወይም አያንቀላፋም ብሎ ያስረግጣል፤ በጊዜው ይመጣል።

በዚህ ክፍል አማካይነት ጴጥሮስ የሚያሳየን ኃጢአተኛው ምንም ያህል ዋስትናው የተጠበቀለት መስሎ ቢሰማውም በመጨረሻ ፍርድ የማይቀርለት መሆኑን ነው። ይህንንም እውነት ለማብራራት በሦስት ምሳሌዎች ተጠቅሟል። (ይሁዳ 6-8ንም ተመልከት)።

የወደቁት መላእክት (2፡4)፡- ምንም እንኳ ስለ መላእክት አፈጣጠርና ስለ ሉሲፈርና ሠራዊቱ አወዳደቅ ከአሁኑ የበለጠ ለማወቅ ብንመኝም፥ እነኚህ ጉዳዮች በአብዛኛው በምሥጢር ሆነው የቀሩ ናቸው። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ኢሳይያስ 14፡ 12-15 የመላእክት ሁሉ የበላይ የሆነውን የሉሲፈርን ውድቀት ይገልጻል ብለው ያምናሉ። አንዳንድ ተማሪዎች ደግሞ

ሕዝቅኤል 28፡ 11-19 ከተመሳሳይ ጉዳይ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ያስባሉ። ሉሲፈር የመላእክት ሠራዊት አለቃ ሆኖ የእግዚአብሔር ምክትል የነበረ ይመስላል፤ ነገር ግን ትዕቢቱ የእግዚአብሔርን ዙፋን ለመያዝ እንዲመኝ አደረገው። (ጆን ሚልተን የተባለው ደራሲ ይህን ታሪክ «ፓራዳይዝ ሎስት» በተባለው ዝነኛ ግጥሙ ውስጥ ፈጠራ በሆነ መንገድ ሥሎታል።) እንደዚሁም ራእይ 12፡4 የእግዚአብሔር ተቀናቃኝና በኋላም ሰይጣን ከተባለው ከሉሲፈር ጋር ከመላእክት ሢሶው ያህል እንደወደቁ አሳብ ይሰጣል።

እነዚህ የወደቁ መላእክት አሁን የት ናቸው? ሰይጣን ነፃ እንደሆነና በዓለም ውስጥ በሥራ ላይ እንዳለ (1ኛ ጴጥ. 5፡8)፥ እንዲሁም የሚረዱት የአጋንንት ሠራዊት እንዳለው እናውቃለን (ኤፌ. 6፡10-12)፤ እነዚህ ምናልባት ከወደቁት መላእክት አንዳንዶቹ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን ጴጥሮስ አንዳንዶቹ መላእክት ወደ ገሃነም («ታርታሩስ») እንደተጣሉ ተናግሯል። ታርታሩስ የሚለው ቃል ግሪክኛ ሲሆን የሚገልጸውም ዓዘቅት የሆነውን የግዞት ስፍራ ነው። ስለዚህ ይህ ክልል እነዚህ መላእክት የመጨረሻውን ፍርድ በመጠባበቅ በጨለማ ጉድጓድ ውስጥ በሰንሰለት የታሰሩበት የገሃነም የተለየ ክፍል ሊሆን ይችላል። በመሆኑም የዚህን መልእክት ለመረዳት በተጠቀሰው ቁጥር የተደበቁ ምሥጢሮች ላይ መከራከር አስፈላጊ አይደለም። እግዚአብሔር ዓመፅን ይቀጣል፤ እንዲሁም ፈቃዱን የሚጋፉትን አይተዋቸውም። እግዚአብሔር በብዙ አቅጣጫዎች ከሰዎች የሚበልጡትን መላእክት ከፈረደባቸው ዓመፀኛ ሰዎችንም በእርግጥ ይፈርድባቸዋል ማለት ነው።

የቀድሞው ዓለም (2፡5)፡- ዘፍጥረት 6፡3 እግዚአብሔር የጥፋት ውኃን ከመላኩ በፊት 120 ዓመታት እንደጠበቀ ያሳያል። በዚያን ጊዜ ሁሉ ኖኅ የእግዚአብሔርን ጽድቅ «በማወጅ» አገልግሏል። ከጥፋት ውኃው በፊት ስለነበረው ዓለም ገለጻ ማንበብ ከፈለጋችሁ ከሮሜ 1፡18 ጀምሮ አንብቡ። የአሕዛብ ሥልጣኔ በጣም የተበላሸ ስለነበር እግዚአብሔር ምድርን ማጽዳት አስፈልጎት ነበረ። በእግዚአብሔር እምነት የነበራቸው ስምንት ሰዎችን ማለትም ኖኅንና ቤተሰቡን ብቻ አዳነ (ዕብ. 11፡7)።

ሆኖም የኖኅን መልእክት ማንም ሰው አላመነም! ኢየሱስ ኖኅና ቤተሰቡ ወደ መርከብ እስከሚገቡበት ቀን ድረስ ሕዝቡ ዕለት ተዕለት በዓለምና በፈንጠዝያ ይኖሩ እንደነበረ ግልጽ አድርጎታል! (ሉቃስ 17፡26-27)።

በዚያን ጊዜም በኖኅ ላይ የሚስቁና ለሕዝቡም ጎርፍ እንደማይመጣ የሚያስተምሩም ብዙ «ምሁራን» እንደነበሩ ጥርጥር የለውም። እነርሱም ለመከራከሪያ የተጠቀሙበት ዘዴ ይህን ዓይነቱን መዓት ከዚህ በፊት አንድ እንኳ ያየ ሰው አለ? የሚለውን ጥያቄ በማቅረብ ሳይሆን አይቀርም። በጴጥሮስ ዘመን የነበሩ የሐሰተኛ ሐዋርያት የጌታ ቀን እንደማይመጣ «ለማስረገጥ» በተመሳሳይ መከራከሪያ ተጠቅመው ነበር (2ኛ ጴጥ. 3፡3 ጀምሮ)።

ዓለማችንን ከኖኅ ዓለም ጋር ስናወዳድረው አንዳንድ አስፈሪ ንጽጽሮችን ታያላችሁ። ሕዝቡ እየበዛ ነበር (ዘፍ. 6፡1) ዓለም ደግሞ በክፋትና (ዘፍ. 6፡5) በግፍ (ዘፍ. 6፡11፥ 13) ተሞልታ ነበር። ሕግ አልባነት ነግሦ ነበር፤ እውነተኛ አማኞች ጥቂቶች ከመሆናቸውም ማንም ከቁም ነገር የሚቆጥራቸው አልነበረም! ነገር ግን የጥፋት ውኃ መጣና የዓለም ሕዝብ በሙሉ ጠፋ። እግዚአብሔር እውነትን የሚጋፉትን በእርግጥ ይፈርድባቸዋል።

ሰዶምና ገሞራ (2፡6)፡ የዚህ ዘገባ በፍጥረት 18-19 ላይ ሰፍሯል። እግዚአብሔር ደግሞ ስለነዚህ ከተሞች ያለው አመለካከት በዘፍጥረት 13፡13 ላይ ይገኛል፡- «የሰዶም ሰዎች ግን ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች ነበሩ።» ጴጥሮስ «ክፉ» ነበሩ ሲል፥ ይሁዳ ደግሞ «ለዝሙትና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ነበሩ» ይላል (ቁ. 7)። የሰዶም ሰዎች ሴሰኛ ኑሮንና ዓመፀኛ ሥራን ይከተሉ ነበረ (2ኛ ጴጥ. 2፡7-8)። የሙሴ ሕግ ገና አልተሰጠም ነበርና ዓመፀኛ ማለትም ሕግ የለሽ የሚለው ቃል የአይሁድን ሕግ አያመለክትም። ስለዚህ በምን ዓይነት ሁኔታ ነው ሴሰኛ ኑሯቸው «ዓመፀኛ» የተባለው? በኑሮአቸው ከተፈጥሮ የሚቃረኑ ነበሩ (ሮሜ 1፡24-27ን ተመልከት)። የሰዶምና የሌሎች ከተሞች ዓይን ያወጣ ኃጢአት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ የተወገዘው ነው። ይኸውም ከተፈጥሮ ሕግ ውጪ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም፥ ማለትም ሰዶማዊ ወይም ከተመሳሳይ ጾታ ጋር የሚደረግ ግብረ ሥጋ ነበር (ሮሜ 1፡24-27፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡9፤ ዘሌ. 18፡22)።

አብርሃም የመማለድ ጸሎት ቢያደርስና (ዘፍ. 18፡22 ጀምሮ) እንዲሁም የሎጥ የመጨረሻ ደቂቃ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም የሰዶም ሰዎች በእሳትና በዲን ጠፉ። ሎጥ ከተማዋን ጥሎ እስከወጣበት ደቂቃ ድረስ ሕዝቡ ሁሉም ነገር ደኅና እንደሆነ እርግጠኞች ነበሩ፤ ሆኖም እሳቱ ወረደ

(ሉቃስ 17፡28-29)። እግዚአብሔር እነሱን እንዳልማራቸው ሁሉ ዛሬም በፈቃዳቸው ቃሉን የማያምኑበትንና ልጁን የሚክዱትን አይተዋቸውም። እግዚአብሔር በሙት ባሕር ሥር ሰዶምንና ገሞራን ቀበረ። እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች ዛሬ ሊመጣ ካለው መዓት ኃጢአተኞች እንዲጠነቀቁ የሚያስተምሩ ናቸው።

ጴጥሮስ ስለ እርግጠኛው ፍርድ የሚገልጹትን እነዚህን ሦስት ምሳሌዎች ካሳየ በኋላ ትምህርቱን ዋነኛው ርእሱ ከሆነው ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ጋር አዛምዶታል (2፡9)። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን በዚያ በፍርድ ቀን ላለው ልዩ ቅጣት ጠብቋቸዋል። የሐሰት አስተማሪዎች የተሳካላቸው ሊመስሉ ይችላሉ («ብዙዎች» ስለሚከተሏቸው)፤ ነገር ግን በመጨረሻው ይፈረድባቸዋል። ፍርዳችውም አሁን እንኳ እየተዘጋጀ ነው («አይዘገይም» ቁ. 3)፤ እየተዘጋጀ ያለው ደግሞ በመጨረሻው ቀን ተግባራዊ ይሆናል።

እንግዲህ በሐሰተኛ አስተማሪዎችና በእውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች መካከል የቱን ያህል ልዩነት አለ! ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ ቤት እያዘጋጀልን ስለሆነ (ዮሐ. 14፡ 1-6) ለእኛ የተጠበቀልን ውርስ አለን (1ኛ ጴጥ. 1፡4)። ፍርድን ሳይሆን የምንጠባበቀው ሕዝቡን ለክብር ወደ ቤቱ ለመውሰድ የጌታን መምጣት ነው! «እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ» (1ኛ ተሰ. 5፡9)።

ጴጥሮስ ቀጥሎ አሳቡን ወደ ራሳቸው ወደ አማኞች መልሷል። በዚያ በክፉ ዓለም ውስጥ አማኞች ለጌታ እውነተኞች ሆነው መቆየት እንዴት ይችላሉ?

## እውነተኛ አማኞች አርነት ወጥተዋል
(2ኛ ጴጥ. 2፡5-9)

የጴጥሮስ ዓላማ ሐሰተኛ ሐዋርያትን ማውገዝ ብቻ አልነበረም፤ እውነተኛ አማኞችንም ማበረታታት ፈልጎ ነበረ። አሁንም እንደገና ወደ ብሉይ ኪዳን ተመልሶ ስለ አርነት የሚናገሩትን ሁለት ምሳሌዎች ጠቅሷል።

ኖኅ (2፡5)፡- ይህ የእምነት ሰው ባለሁለት መልክ አርነትን ቀምሷል። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር በአካባቢው ካለው ዓለም ብክለት ታድጎታል። ኖኅ ለ120 ዓመታት ሁሉ ለማያምኑት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት ተናግሯል። እሱና ቤተሰቡ በምግባረ ብልሹነትና በመንፈሳዊ

ጨለማ ተከብበው ነበር፤ ሆኖም መብራታቸውን እያበሩ ጠብቀዋል። እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን ከዓለም በመለየት ከለላ አላደረገላቸውም፤ ነገር ግን በጥፋት መካከል ንጹሕ ሆነው እንዲቆዩ በማስቻል ነው የጠበቃቸው። በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እኛም «ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጠናል» (1፡4)።

ጌታችን ሰማያዊውን አባት «ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም» (ዮሐ. 17፡15) ብሎ ማለደ። እስቲ አንድም የሚያምን ወዳጅ በአጠገባቸው በሌለበት በዚያ በክፉ ዓለም ውስጥ ለኖኅና ለሚስቱ ቤተሰብ ማሳደግ ማለት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ገምቱት! ሆኖም እግዚአብሔር ለሦስቱ ወንድ ልጆቻቸው የሚያምኑ ሚስቶች አገኘላቸው፤ እንዲሁም እግዚአብሔር ይህንን ቤት ከዓለም ብክለት ከለለው።

በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን ከዓለም ፍርድ ታድጓል። ዓለምን ለማጥፋት የመጣው የጥፋት ውኃ ኖኅና ቤተሰቡን ግን ከፍርድ በላይ ከፍ አደረጋቸው። በደኅንነት መርከብ ውስጥ የተጠበቁ ነበሩ። በመጀመሪያው መልእክቱ ጴጥሮስ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን መዳናችንን በመርከቧ ምሳሌነት ተመልክቶታል (1ኛ ጴጥ. 3፡20-22)። ሰው ሲጠመቅ ውኃ ውስጥ እንደሚጠልቅ ሁሉ ዓለም በጐርፍ ጥምቀት ውስጥ መጥለቁ፥ ባንጻሩ ግን ኖኅ ውኃው ላይ መንሳፈፉ የትንሣኤና የደኅንነት ሥዕላዊ ምሳሌነት ነበረው።

ጴጥሮስ ለአንባቢዎቹ ታላቁ የፍርድ ቀን ሲመጣ እነሱ በደኅና እንደሚጠበቁ ያስረግጥ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ «የደኅንነት መርከባችን» ነው። ከሚመጣው ቁጣ ያድነናል (1ኛ ተሰ. 1፡10)። እግዚአብሔር ምድር ዳግመኛ በውኃ እንደማትጠፋ ቃል ገብቷል፤ ነገር ግን የእሳት ፍርድ በመቀጠል እየመጣ ነበር (2ኛ ጴጥሮስ 3፡10 ጀምሮ)። ክርስቶስን ያመኑ ፍርድን በፍጹም አያዩም (ዮሐ. 5፡24)፤ ምክንያቱም ፍርዳቸውን በመስቀል ላይ እሱ ስለተሸከመ ነው።

ሎጥ (2፡6-8)፡- አብርሃም ዑርን ለቅቆ ወደ ከነዓን ምድር ሲሄድ የወንድሙን ልጅ ሎጥን አስከትሎት ነበር፤ ነገር ግን ሎጥ በበረከት ምትክ መርገም ሆኖበት ነበር። ከእምነቱ መድከም የተነሣ አብርሃም ወደ ግብጽ በወረደ ጊዜ ሎጥ ከእርሱ ጋር በመሄድ «የዓለምን» ጣዕም ቀመሰ (ዘፍ.

12፡ 10-13፡ 1)። ሎጥ ባለጠጋ እየሆነ ሲመጣ ከአብርሃም መለየት በመፈለጉ፥ ከአጎቱ እግዚአብሔርን የመምሰል መንፈሳዊ ተጽዕኖ ወጣ። ሎጥ ከእግዚአብሔር ጋር ይጓዝ ከነበረው ከአብርሃም ጋር መሄዱ እንዴት ያለ ዕድል ነበረ! ሆኖም ሎጥ ዕድሉን በገዛ እጁ አበላሸው።

ሎጥ ለመኖሪያው አዲስ ቦታ መምረጥ ነበረበት፤ ይህንንም ያደረገው በግብፅ ባየው ነገር ምሳሌነት ተገፋፍቶ ነበር (ዘፍ. 13፡ 10)። አብርሃም ሎጥን ከግብፅ ቢያወጣውም የግብፅን ተጽዕኖ ከሎጥ ልብ ውስጥ ማውጣት አልተቻለውም። ሎጥ «እስከ ሰዶምም ድረስ ድንኳኑን አዘዋወረ» (ዘፍ. 13፡ 12)፤ ከዚያም በመጨረሻ ወደ ሰዶም ገባ (ዘፍ. 14፡ 12)። እግዚአብሔር ሎጥን ከሰዶም ለማውጣት ሲል በአካባቢው ውጊያ በማስነሣት ተጠቅሞ ነበር፤ ሆኖም ግን ሎጥ በቀጥታ ወደዚያው ተመለሰ። ቀድሞውኑም ልቡ ያረፈው በሰዶም ላይ ነበር።

የሎጥን አሳብ ለመረዳት ለእኛ አስቸጋሪ ነገር ነው። ጴጥሮስ ሎጥ የዳነ እንደነበረ ግልጥ አድርጎታል («ጻድቅ ሎጥ ... ያን ጻድቅ») ይለዋል። ሆኖም እኛ ደግሞ እንደዚያ ክፉ ቦታ በሆነው ሰዶም ምን ያደርግ እንደነበረ ስናስበው ይገርመናል። ይሁን እንጂ ዘፍጥረት 19ን በትክክል ከተረዳን፥ ሎጥ ከነበሩት አራት ሴት ልጆች መካከል ሁለቱ የሰዶምን ወንዶች ያገቡ ነበሩ። ሎጥ በሰዶም በኖረበት ጊዜ ሁሉ በሕዝቡ ክፉ ጠባይ ነፍሱ «ትጨነቅ» ነበር። ምናልባት በዚያም መቆየቱ ሊለውጣቸው እንደሚችል አስቦ ይሆናል። ምኞቱ ይህ ከሆነ ደግሞ አልተሳካለትም።

ሆኖም ርኩሰት በሰፈነበት አካባቢ መካከል ሎጥና ቤተሰቡ ቢኖሩም እግዚአብሔር ግን ሳይበከሉ እንዲቆዩ አስችሏቸዋል። እግዚአብሔር ሎጥንና ሁለቱን ሴቶች ልጆቹን ፍርድ በሰዶምና በሌሎች በአካባቢው በነበሩት ከተሞች ላይ ከመውረዱ በፊት አውጥቷቸዋል (ዘፍ. 19)። ሎጥ የዳነው በእርሱ በኩል ከነበረ አንዳች መልካም ነገር የተነሣ አልነበረም። የዳነው አማኝ ስለነበረና አጎቱም አብርሃም ለእርሱ ጸልዮለት ስለነበረ ነው። ከሰዶም ውጪ ያለው አብርሃም በከተማው ውስጥ ከነበረው ሎጥ ይልቅ በእግዚአብሔር ዘንድ የበለጠ ተሰሚነት ነበረው። ሎጥን የተመለከትን እንደሆነ ግን አግብተው የነበሩት ሴት ልጆቹና ባሎቻቸው በማስጠንቀቂያው ከማላገጣቸውም፥ ሚስቱም እግዚአብሔርን ባለመታዘዟ ስለሞተች ሎጥ ለገዛ ቤተሰቡ እንኳ የሚሆን ምስክርነት አልነበረውም።

ሎጥ በሰዶም ለመኖር የመረጠውን ያህል በዚያው መጠን ከቦታው ከፉ ተጽዕኖ መራቅ በቻለም ነበር። የዛሬውን ጊዜ ስንመለከት ግን ብዙ ሰዎች ምንም ምርጫ ስለሌላቸው በዓለም ብክለቶች ተከብበው መኖር አለባቸው። እስቲ በዚህ አጋጣሚ እግዚአብሔርን የማያውቁ አሠሪዎች ያሏቸውን ክርስቲያን ሠራተኞችን ወይም ያልዳኑ ባሎችን ያገቡ ክርስቲያን ሚስቶችን ወይም ያልዳኑ ወላጆች ያሏቸውን አማኝ ልጆችን አስቧቸው። በቢሮዎችና በፋብሪካዎች የሚሠሩ ክርስቲያን ሠራተኞች በቀላሉ አሳብንና ልብን ሊበክሉ የሚችሉ ነገሮችን ለማየትና ለመስማት ይገደዳሉ። ሆኖም ጴጥሮስ ለአንባቢዎቹና ለእኛም ጭምር እግዚአብሔር «የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን» ያውቃል ሲል ማረጋገጫ ሰጥቶናል (2ኛ ጴጥ. 2፡9)። ይህንም የሚያደርገው እኛ በድል እንድንኖር ነው።

እንዲሁም እርሱ እኛን ከፍርድ ለማዳን ይችላል። በኖኅ ጊዜ ፍርዱ የውኃ ፍርድ ነበር፤ በሎጥ ጊዜ ግን የእሳት ፍርድ ነበር። አካባቢው ሰፊ የእሳትና ዲን ምድጃ ሲሆን በዙሪያው የነበሩት ከተሞች በምሕረት የለሽ ጥፋት ወደሙ። ይህም በእርግጥ ጴጥሮስ ስለሚመጣው የእሳት ፍርድ ካስጠነቀቀው ጋር ተነጻጻሪ ነው (3፡10 ጀምሮ)።

ጴጥሮስ ሎጥን ከአካባቢው ርኩሰት የተለየ ሕይወትን የሚኖር ሰው ምሳሌ አድርጎ አልነበረም የሚያቀርበው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከብክለትና ከኩነኔ እንዳዳነው ሰው ምሳሌ ነው የሚጠቀምበት። ሎጥን መላእክቱ እጁን ይዘው ከከተማዋ ጎትተው ማውጣት ስለነበረባቸው የዳነው ከፈቃዱ ውጪ ነበር ለማለት ይቻላል (ዘፍ. 19፡16)። ሎጥ ወደ ሰዶም ገባ፤ ሰዶም ደግሞ ወደ ሎጥ ገባ፤ ያንን ለቅቆ መውጣት ደግሞ አስቸጋሪ ነገር ሆኖ አገኘው!

ጌታችን ስለ ዳግም ምጽአቱ እንድንዘጋጅ ሊያስጠነቅቀን ኖኅንና ሎጥን በምሳሌነት ተጠቅሞባቸዋል (ሉቃስ 17፡26-37)። የሰዶም ሰዎች ፍርድ እየመጣ መሆኑ ግድ ሳይሰጣቸው የዕለት ተዕለት ምኞቶቻቸውን ያሳድዱ ነበር፤ ፍርዱ ተፈጻሚ በሆነበት ጊዜ አልተዘጋጁም ነበር። «ስለዚህ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን እየጠበቃችሁ ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ ሆናችሁ በሰላም በእርሱ እንድትገኙ ትጉ» በማለት ጴጥሮስ ያሳስባል። (2ኛ ጴጥ. 3፡14)።

እግዚአብሔር የሚያመልከውን የሚታደገው ሲሆን የማያመልከውን ደግሞ ለፍርድ ያቆየዋል። እግዚአብሔር የዛሬዎቹን ከተሞች ከፍርድ

ያተረፉቸው ከሆነ ለሰዶምና ለገሞራ መጸጸት ይኖርበታል የሚለው አባባል ብዙ ጊዜ ሲነገር ይሰማል። የእግዚአብሔር ፍርድ ለምን ይዘገያል? ምክንያቱም እግዚአብሔር «ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ . . . ይታገሣል» (2ኛ ጴጥ. 3፡9)። በኖኅ ዘመን የነበረው ኅብረተሰብ ንስሐ የሚገባበትና የሚመለስበት 120 ዓመታት ተሰጥቶት ነበር። ሆኖም እውነትን አልተቀበሉም። የሎጥ ምሳሌነትና ምስክርነት ደካማ ቢሆንም፥ ቢያንስ እውነትን ነገሮአቸው ነበረ፤ ክፉዎች ጎረቤቶቹ ግን ስለ እግዚአብሔር ምንም ነገር መስማት አልፈለጉም ነበር።

ያለንበት ዘመን «እንደ ኖኅ ዘመን» ብቻ ሳይሆን «እንደ ሎጥ ዘመንም» ነው። ብዙ አማኞች የተለያየው ኑሮአቸውን ትተው ከዓለም ጋር እየተመሳሰሉ ናቸው። ደካማዋ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ደካማ ምስክርነት ስላላት ኃጢአተኞች ፍርድ እየመጣ መሆኑን አያምኑም። ኅብረተሰቡ በክፋት የተሞላ ነው፤ በተለይም ሰዶም ትታወቅበት በነበረው ዓይነት ኃጢአት ዓለማችን ተጥለቅልቃለች። ይህ ሁሉ ሲሆን፥ መላው ዓለምም በዓመፅ ሲበከል፥ እግዚአብሔር ግን ያንቀላፋና እንደማይመለከተው ሁሉ ችላ ያለ ይመስላል። ሆኖም አንድ ቀን እሳት ይወርዳል፤ የንስሐ ጊዜም ያልፋል።

የእግዚአብሔር ሕዝቦች ደካማ ቢሆኑም በእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት ከፍርድ ያመልጣሉ። ሎጥና ቤተሰቡ ከከተማ እስከሚወጡ ድረስ እግዚአብሔር ሰዶምን አልፈረደባትም ነበር። የእኔም ጽኑ እምነት እግዚአብሔር ለተመሳሳይ ሁኔታ የራሱን ሕዝብ አውጥቶ ወደ ሰማይ ቤት እስከሚወስዳቸው ድረስ በዚህ ዓለም ላይ ቁጣን እንደማይልክ ነው። «እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ። የምንነቃም ብንሆን፥ የምናንቀላፋም ብንሆን፥ ከእርሱ ጋር አብረን በሕይወት እንኖር ዘንድ ስለ እኛ ሞተ» (1ኛ ተሰ. 5፡9-10)።

በአንድ በቅርብ ቀን እሳቱ ይወርዳል። ተዘጋጅታችኋል?

# ለፍርድ የተለዩ ሰዎች

## 2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 10-16

ጴጥሮስ ስለ ሐሰተኞች ሐዋርያት የሚሰጠውን ገለጻ ገና አልጨረሰም! ዛሬ እንዳሉት አንዳንድ ግዴለሽ አማኞች ሳይሆን፥ የሐሰት አስተማሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመስፋፋታቸው ጴጥሮስ በጣም ተረብሾ ነበረ። አቀራረባቸው ማራኪ ቢሆንም ትምህርቶቻቸው ግን አደገኛ እንደነበሩ በሚገባ ተገንዝቦአል። ስለዚህ አብያተ ክርስቲያናትን ሊያስጠነቅቃቸው ፈልጎ ነበር።

ሆኖም ጴጥሮስ ይህንን ደብዳቤ የከፈተው ስለ ደኅንነት፥ ስለ ክርስቲያናዊ ዕድገት እና ስለ እግዚአብሔር ቃል አስተማማኝነት በሚገልጽ አዎንታዊ ትምህርት መሆኑን አስታውሱ። እርሱ ሚዛናዊ የሆነ አገልግሎት እንዳበረከተ ሁሉ፥ እኛም ያንን ሚዛናዊነት መጠበቅ አለብን። ቻርለስ ስፐርጀን መጽሔቱን ሲጀምር፥ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሲጠግኑ በአንድ እጃቸው ሰይፎቻቸውን፥ በሌላው እጃቸው መለሰኞቻቸውን ይዘው ይሠሩ የነበሩት የመጽሐፈ ነህምያ ሰዎች ስለታወሱት የመጽሔቱን ስም «ሰይፍና መለሰኛ» ብሎ ሰየመው።

አንዳንድ ሰዎች ፈጽመው አፍራሽ የሆነ አግልግሎት ስላላቸው አንዳችም ነገር ጨርሶ አይገነቡም። ጠላትን በመዋጋት የውጊያ ሥራ የበዛባቸው ይመስላሉ! ሌሎችም «ገንቢ» እንደሆኑ ይናገራሉ፤ ነገር ግን የገነቡትን እንኳን ሊጠብቁት አልቻሉም። ጴጥሮስ መናፍቃንን ማጥቃት ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ከመረዳቱም በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ላሉት ምእመናን ጠቃሚ ትምህርት መስጠት ማስፈለጉን ያውቅ ነበር።

በዚህኛው የደብዳቤው ክፍል ጴጥሮስ መናፍቃንን በሦስት ግልጥ ኃጢአቶች ኮንኖአቸዋል።

### ነቃፊነታቸው (2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 10-12)

እዚህ ላይ ጴጥሮስ የሰጠው ሥዕላዊ ገለጻ የሚያመለክተው ራሳቸውን ለማኩራራት ሲሞክሩ ሌላውን ሁሉ የሚያፈርሱትን ደፋሮችና ትዕቢተኛ

ሰዎችን ነው። ለሥልጣን ምንም አክብሮት የላቸውም፤ ከፍተኛ ቦታዎች ያሉትን ሰዎች ሲያጠቁና ስም ሲያጠፉ የማይፈሩ ናቸው።

እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ላይ ሥልጣንን መሥርቷል፤ እኛ ደግሞ ሥልጣንን ስንቃወም እግዚአብሔርን ተገዳደርን ማለት ነው (ሮሜ 13፡1 ጀምሮ)። ወላጆች በልጆቻቸው ላይ (ኤፌ. 6፡1-4)፥ እንዲሁም ቀጣሪዎች በተቀጣሪዎቻቸው ላይ ሥልጣን ሊኖራቸው ይገባል (ኤፌ. 6፡5-8)። እንደ ዜጎች እኛ ክርስቲያኖች በሥልጣን ላይ ላሉት ልንጸልይ (1ኛ ጢሞ. 2፡1-4)፥ አክብሮትን ልናሳያቸው (1ኛ ጴጥ. 2፡11-17)፥ እንዲሁም በመልካም ባሕርያችን እግዚአብሔርን ማስከበር አለብን። የአንድ አጥቢያ ማኅበረ-ምእመናን አባላት የሆንነውም ሁሉ በእኛ ላይ መንፈሳዊ አገዛዝ ያላቸውን ልናከብርና በአገልጎታችው ልናበረታታቸው መጣር አለብን (ዕብ. 13፡7፥ 17፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡1-6)።

የሰው መንግሥት በዓለም ላይ ሥነ ሥርዓትን በማስፈን በእግዚአብሔር የተሰጠ እንደመሆኑ፥ ይህም በአንድ በኩል ቤተ ክርስቲያን ቃሉን እንድታገለግልና የጠፉትን ለክርስቶስ ለመማረክ እንድትችል የሚረዳ ነው (1ኛ ጢሞ. 2፡1-8)። ስለዚህ ያንን ሥልጣናቸውን በእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲጠቀሙበት፥ በሥልጣን ላይ ላሉት በየዕለቱ ልንጸልይላቸው ይገባናል። ለአንድ ክርስቲያን ሕግን መቃወም ቀላል ነገር አይደለም፤ ይህን ሲያደርግ ደግሞ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አለበት። ቅን ሰዎች (ያልዳኑትን የመንግሥት ተቀጣሪዎች ጨምሮ) እንዳይሠቃዩ ተቃውሞ ሲያሰማ፥ ክርስቶስን ሊያስከብር በሚችል ሁኔታ ሊያደርገው ይገባዋል።

የነቀፌታቸው ምክንያት (2፡10)፡- የነቀፌታቸውን ምክንያት በአንድ ቃል መግለጽ ይቻላል፤ ይኸውም፡- የገዛ ሥጋቸው ነው። የሰው መጥፎ ተፈጥሮ ለማንኛውም ዓይነት ሥልጣን እንዲገዛ አይፈልግም። የሥጋ መልእክት ምንጊዜም «የራስህን ምርጫ አድርግ!» የሚል እንደመሆኑ ይህን ደግሞ ብዙ ሰዎች ይከተሉታል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በመጻሕፍት ገቢያ እጅግ ደርቶ የሚገኘው «ስለተሳካ ሕይወት» የሚያስተምሩ የተለያዩ አልባሌ መጻሕፍት ወረርሽኝ ነው። የግል ኑሮን ለማደርጀት ሌሎችን መጉዳትና እስከማስፈራራት ድረስ የሚያበረታቱ ናቸው። እንደነዚህ መጻሕፍት ከሆነ

ዋናው የዕድገት አማራጭ መንገድ ለራስህ ጥንቃቄ በመውሰድ ሌሎች ሰዎችን እንደ መሣሪያ መጠቀም ነው የሚል ሆኖ እናገኘዋለን።

የሰው የውድቀት ባሕርይ ትዕቢትን ያበረታታል። እኔነታቸው ከተነካ እነዚህ የሐሰት ሐዋርያት ራሳቸውን ለመከላከል ምንም ነገር ከማድረግ ወደኋላ አይሉም። የነርሱ አመለካከት ሌሎችን ለማገልገል በፈቃደኝነት ራሱን ባዶ ካደረገውና ከዚያም ለኃጢአታችን እንደ መሥዋዕት ሆኖ ከሞተው ከጌታችን አመለካከት ሙሉ በሙሉ የተቃረነ ነው (ፊልጵ. 2ን ተመልከት)። ጴጥሮስ የገለጻቸው እነዚህ ሰዎች አስመሳዮች ነበሩ፤ ይህ ማለት በክብር ቦታዎች ስላሉት ሲናገሩ «በጣም ደፋሮች» የሆኑ ነበሩ ማለት ነው። ትክክለኛ የሆነ ጀግንነት የመኖሩን ያህል፥ በዚያው ተፃራሪ ሰይጣናዊ የሆነ ደፋርነትም አለ።

እነዚህ ሰዎች ራሰ- ወዳዶች ማለትም «ራሳቸውን ለማስደሰት ብቻ የሚኖሩ» ነበሩ። አሳበ ግትር ነበሩና የሚፈልጉትን ለማግኘት ሲሉ እግዚአብሔርን እንኳ ይቋቋማሉ! የእነርሱን ባሕርይ መጽሐፈ ምሳሌ 21፡24 በደንብ ይገልጸዋል። በውጪ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የሚያገለግሉ ሲመስሉ፥ በውስጣቸው ግን የራሳቸውን እኔነት የሚያጎለብቱና የራሳቸውን መጠለያ የሚያደራጁ ናቸው።

በግትርነታቸው «ሥልጣን ያላቸውን ሲሳደቡ ፍርሃት አይሰማቸውም»። የሚዘልፉት በቀጥታ በሥልጣን ቦታ ያሉትንና «የተከበሩትን» ሰዎች ብቻ ከመሆንም አልፎ፥ በሚቀጥለው ቁጥር ጴጥሮስ ስለ መላእክት እንደማንሣቱ እነርሱንም ጭምር የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አዎን እነዚህ የሐሰት ሐዋርያት መላእክትን እንኳን ይነቅፉሉ! ይህንን በማድረጋቸውም አይሰጉም! በትዕቢታቸው በጣም ደፋሮች ከመሆናቸው የተነሣ ለእግዚአብሔር ፍርድ እንኳ ደንታ የላቸውም።

የነቀፌታቸው ከባድነት (2፡11)፡- መላእክት በመናፍቃን ተነቅፈዋል፤ ነገር ግን መናፍቃን በመላእክት አልተነቀፉም! መላእክት በኃይልና በብርታት ከፍ ያሉ ቢሆኑም እንኳ የራሳቸው ወዳልሆነ ክልል ጥሰው አይገቡም። መላእክት የሉሲፈርን ዓመፅ ያስታውሳሉ። ደግሞም በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ ማመፅ ምን ያህል ከባድ ነገር እንደሆነ

ያውቃሉ። እግዚአብሔር ዓመፀኞቹን መላእክት ከፈረደባቸው ዓመፀኞች ሰዎችን እንዴት የበለጠ ይፈርድባቸዋል!

እዚህ ላይ የተነሣው አሳብ የሚጠቁመው የእግዚአብሔር መላእክት እንኳ በወደቁት መላእክት ላይ በመቃወም እንደማይናገሩ ነው። ፍርድን ሁሉ ለእግዚአብሔር ትተዋል። ይህንን የመላእክትን ጉዳይ ይሁዳ በቁጥር 8-9 ላይ የጠቀሰው ስለሆነ ወደፊት ስለርሱ መልእክት በምናጠናበት ጊዜ ስለጉዳዩ የበለጠ እንረዳለን።

ስለሌሎች ክፉ መናገር ታላቅ ኃጢአት ነው፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች ይህን ማድረግ የለባቸውም። በሥልጣን ላይ ያሉትን ሰዎች ልናከብራቸው ባንችልም ሥልጣን ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስለሆነ ሥልጣኑን ማክበር አለብን። በክርስቶስ ስም የመንግሥት ባለሥልጣናትን የሚነቅፉ ሰዎች ቢኖሩ ቲቶ 3፡ 1-2ን ሊያነቡና በጥልቅ ሊገነዘቡት ይገባል፡- «ለገዦችና ለባለሥልጣኖች የሚገዙና የሚታዘዙ፥ ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ፥ ማንንም የማይሰድቡ፥ የማይከራከሩ፥ ገሮች፥ ለሰው ሁሉ የዋህነትን ሁሉ የሚያሳዩ እንዲሆኑ አሳስባቸው።»

ዳንኤል የንጉሡን ምግብ ላለመብላት ቢወስንም እንኳ ጠባቂውን ችግር ሊያስከትልበት በማይችል በመልካም መንገድ ነው ያደረገው (ዳን. 1)። እንደዚሁም ሐዋርያት በኢየሱስ ስም መስበክ እንዲያቆሙ በሸንጎው የተሠጠውን ትእዛዝ ቢቃወሙም ተቃውሞአቸውን በጨዋነት ነበር ያሳዩት። ይህን ትእዛዝ ባይቀበሉትም እንኳ ሥልጣኑን ግን አክብረው ነበር። ሥጋ ሥራውን ሲጀምር ነው ትዕቢት የሚገባው፤ ከዚያም በኋላ ምላሳችንን እንደ አገልግሎት መሣሪያ ሳይሆን እንደ ጦር ዕቃ እንጠቀምበታለን። «የአፉ ቃል ግፍና ሽንገላ ነው፤ ማስተዋልን በጎ ማድረግንም ተወ» [መዝ. (36)፡3]።

የነቀፌታቸው ፍርድ (2፡ 12)፡- ጴጥሮስ እነዚህን የሐሰት አስተማሪዎች መጨረሻቸው መታረድ ብቻ ከሆነው «አእምሮ የሌላቸው እንስሶች» ጋር አመሳስሎአቸዋል። በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ እንደ አሳማና እንደ ውሻ ተመስለዋል! እንስሳት ሕይወት አላቸው፤ ነገር ግን የሚኖሩት ፈጽሞ በደመ-ነፍስ ነው። እንደ ሰዎች አመዛዛኝ የሆነ አእምሮ የላቸውም። ኢየሱስ የከበሩ ነገሮችን ለማያመሰግኑና አእምሮ ለሌላቸው እንስሶች እንዳናባክን አስጠንቅቆናል (ማቴ. 7፡6)።

በዚህ አጋጣሚ አንድ የደረሰብኝን ነገር ላጫውታችሁ። የመጋቢነት ጉብኝት ለማድረግ ወደ አንድ ኀዘን ቤት ሄጄ በነበረበት ጊዜ ገና ደረጃዎቹን በመውጣት ላይ እያለሁ አንድ ትልቅ ውሻ በጣም ይጮህብኝ ጀመር። ልክ ቤተሰቡን ለመዝረፍ የመጣሁ ነበር የመሰለው። ይሁን እንጂ፥ የሚመራው በደመ-ነፍስ በመሆኑ ማስፈራራቱን ከግምት አላገባሁትም። ምንም በማያውቀው ነገር ጩኸቱን እያምባረቀ ነበረ! ስለዚህ ወደ ቤት ገብቼ ያዘነውን ቤተሰብ እንዳገለግል ባለቤቱ ውሻውን ወስዶ በምድር ቤት ውስጥ ሊቆልፍበት ተገድዶ ነበር።

ይህ ሁኔታ ከእነዚህ ሐሰተኛ ሐዋርያት ጋር ተመሳሳይ ነው:- ምንም ስለማያውቋቸው ነገሮች በጣም ብዙ ውካታ ይፈጥራሉ! በፊሊጵስ የተተረጎመው 2ኛው ጴጥ. 2፡ 12 «ከራሳቸው ልምድ ውጪ ባሉት ነገሮች ላይ ያፌዛሉ» ሲል፥ ኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን ደግሞ «ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በማያስተውሏቸው ነገሮች ይሳደባሉ» ይላል። ታዲያ ይህ የሚያስታውሰኝ አንዲት አስተማሪዬ ተማሪዎችዋ በክፍል ውስጥ እየተንጫጩ ስለሚያስቸግሯት «ጩኸት የሚያበዙት ባዶ በርሜሎች ናቸው» በማለት ትዘልፋቸው የነበረችውን ነው። እነዚህም ሰዎች ከነዚህ የተለዩ አይደሉም!

በአሁኑ ጊዜ የሚያሳዝነው ነገር በተለይ የብዙኃን መገናኛዎች «በለዘብታ ድምፅ» ለሚያስተምሩት ለእውነተኞቹ ለጌታ አገልጋዮች በቂ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ «አፈ-ልቅ» ለሆኑት ሐሰተኛ አስተማሪዎች ሰፊ ዕድል መስጠታቸው ነው። ከዚህ የበለጠ የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ የዋህ የሆኑ አድማጮች፥ «ከንቱ የሆነ ታላቅ ቃል በመናገር» (2፡ 18) በሚያወናብዱት ሐሰተኛ ሰባኪዎች ትምህርት በመደለል እውነቱን ከሐሰት መለየት አለመቻላቸው ነው። የእግዚአብሔር ቃል እውነት ወደ ደኅንነት ሲመራ፥ የመናፍቃን የድፍረት ቃላት ግን ወደ ኩነኔ ያመራሉ።

የእነዚህም «ተናጣቂ አውሬዎች» መጨረሻቸው ጥፋት ይሆናል። ይህን እውነት ጴጥሮስ በ2ኛ መጽሐፉ ምዕራፍ 2 ላይ ብዙ ጊዜ ጠቅሶታል (ቁ. 3-4፥ 9፥ 12፥ 17፥ 20)። እምነትን ለማጥፋት ሲጥሩ እነሱ ራሳቸው ይጠፋሉ። ከብልሹነታቸው የተነሣ እነርሱ ራሳቸው ይበላሻሉ። እሪያ ወደ ጭቃ ውሻም ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ እነዚህንም ሰዎች ተፈጥሮአቸው

ራሱ ወደ ጥፋት ይጎትታቸዋል (2፡22)። የሚያሳዝነው ግን እነዚህ ሰዎች ለጥፋት ከመዳረጋቸው በፊት፥ በሕዝብ ላይ ብዙ ግብረ-ገባዊና መንፈሳዊ ጉዳት ማድረሳቸው ነው።

## ነውረኝነታቸው (2ኛ ጴጥ. 2፡13-14)

«ሥጋዊ ምኞት» ስንል በመሠረቱ «ቧልት» እና «መዳራትን» ያቀፈ ሲሆን፥ በተጨማሪም ቅንጦትን፥ መንደላቀቅንና ብኩንነትን ያካተተ ነው። ሐሰተኞች ሐዋርያት በሚደገፏቸው ሰዎች ኪሳራ (ቁ. 3) የፈንጠዝያና የድሎት ኑሮን ይኖራሉ። በእኛ በራሳችን ኅብረተሰብ ውስጥ «ለአገልግሎታቸው» የገንዘብ እርዳታን የሚለምኑ ግን ውብ በሆኑ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ፥ የድሎት መኪናዎች የሚነዱና ብዙ ብር የሚያወጡ ልብሶችን የሚለብሱ ሰዎች አሉ። ኢየሱስ እኛን ለማበልጸግ ድሀ እንደሆነ ስናስታውስ የእነዚህ ሰዎች አኗኗር ከአዲስ ኪዳን ክርስትና ጋር የሚጋጭ ይመስላል።

ሌሎችን ማታለል ብቻ ሳይሆን ራሳቸውንም እያታለሉ ነው! አኗኗራቸው ትክክለኛ እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ «ሊያስረግጡ» ይችላሉ። በድሮ ጊዜ ሰዎች ክፉ ሥራዎች የሚያደርጉት በሌሊት ነበር፤ እነዚህ ሰዎች ግን በራሳቸው እጅግ ከመተማመናቸው የተነሣ በቀን እንኳ ክፉ ከማድረግ አይመለሱም። አንድ ሰው ክፉ ልማዶቹን አዘውትሮ ከፈጸመ እንደ ጥሩ ምግባር ያያቸዋል።

ይህን ድርጊታቸውን ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ቢያደርጉት ኖሮ ይህንን ያህል ባልገደደንም ነበር፤ ነገር ግን የክርስቲያኖች ኅብረት አካል ናቸው! እነርሱም በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ከጌታ እራት አከባበር ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሚደረገው «የፍቅር ግብዣ» እንኳ ይሳተፉ ነበር። (1ኛ ቆሮ. 11፡20-34)። በዚህ ዓይነቱ ግብዣ ላይ የተሻለ ገቢ ካላቸው ክርስቲያኖች ቸርነት የተነሣ ድሆቹ አማኞች ጥሩ ምግብ የመመገብ ዕድል የሚያገኙበት ነበር፤ ነገር ግን ሐሰተኞዎቹ ሐዋርያት ይህን «የፍቅር ግብዣ» ሀብታቸውን ማሳያና ክፉውን ከመልካሙ መለየት የማይችሉትንና የማያውቁትን ሰዎች መማረኪያ አድርገው ይጠቀሙበት ነበረ።

እነዚህም ሐሰተኛ አስተማሪዎች ለኅብረቱ በረከትን ከማምጣት ይልቅ ጉባኤውን የሚያረክሱ «እርም» እና «ነውር» ሆኑ። በተለያየ መንገድ

በግብዣዎች ላይ ያላቸው ባሕርይ ሌሎችን የሚያረክስና በጌታ ስም ላይ ስድብን የሚያመጣ ነበር፤ እርምና ነውርን ለማስወገድ የሚረዳ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ኤፌ. 5፡27)፤ ሆኖም እነዚህ አስተማሪዎች የቃሉን እውነት አያገለግሉም። እነርሱ እንዲል የሚፈልጉትን እንዲል መጽሐፍ ቅዱስን ያጣምማሉ (2ኛ ጴጥ. 3፡16)።

ይህ ከንጹሕ ሕሊና ውጪ የሚደረግ ርኩሰት በጣም አደገኛ ነገር ነው። ፈሪሳውያንም በዚህ ነገር ወንጀለኞች ነበሩ(ማቴ. 23፡25-28)። የሐሰት ትምህርት፥ ወደ ሐሰት አኗኗር ይመራል፥ ከዚያም የሐሰት አኗኗር የሐሰት ትምህርትን ያበረታታል። ሐሰተኛው ሐዋርያ አንድም የእግዚአብሔርን ቃል «ማስተካከል» አለበት ወይም የኑሮውን አቅጣጫ መለወጥ አለበት፤ እርሱ ደግሞ አኗኗሩን የሚለውጥ ዓይነት ሰው አይደለም! ስለዚህ በሄደበት ሁሉ በምሥጢር ሰዎችን ያረክሳል፤ ኃጢአትን እንዲሠሩ ቀላልና ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል። ወደ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ቢሄዱም መርከስ ይችላል!

አብያተ ክርስቲያኖቻችን ሥልጣንን መለማመድና በሥነ -ሥርዓት መኖርን መማር አለባቸው። ክርስቲያናዊ ፍቅር ማለት እያንዳንዱን የሐሰት ትምህርትና እያንዳንዱን «አኗኗር» መታገሥ ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ነገሮች ትክክል አንዳንድ ነገሮች ደግሞ ስሕተት እንደሆኑ በግልጥ ያስተምራል። እምነቱና ባሕርይው ከእግዚአብሔር ጋር የሚፃረር ማንም ክርስቲያን የጌታን እራት እንዲካፈል ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲኖረው ሊፈቀድለት አይገባም። የማርከሱ ተጽዕኖ ወዲያውኑ ላይታይ ይችላል፤ ነገር ግን በስተመጨረሻ ከባድ ችግሮችን ያስከትላል።

ሁለተኛው የጴጥሮስ መልእክት 2፡14 ሐሰተኛ ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎችን በሁለት ምክንያቶች እንደሚካፈሉ ግልጽ ያደርገዋል፡- በመጀመሪያ የገዛ ራሳቸውን ምኞት ለማርካት ሲሆን፥ ሁለተኛው የተከታዮቻቸውን ቁጥር ለማብዛት የሚያስችላቸውን ወጥመድ ለመዘርጋት ነው።

በኃጢአት እንዲያጠምዷቸው «ልቅ ሴቶችን» ለማግኘት ዓይኖቻቸው ንቁዎች ናቸው። ጳውሎስ «ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ፥ ኃጢአታቸው የተከመረባቸውን በልዩ ልዩ ምኞትም የሚወሰዱትን . . . ሞኞችን ሴቶች

ስለሚማርኩ» ተመሳሳይ የሐሰት ሐዋርያት አስጠንቅቋል (2ኛ ጢሞ. 3፡6)። አንዳንድ «አገልጋዮች» ሃይማኖትን እውነተኛ ማንነታቸውን መሸፈኛ ካባ በማድረግ ተጠቅመውበታል። በተለይ አንዳንድ ሴቶች «ምክር ፍለጋ» ሲሉ ለእነዚህ ሰዎች ይጋለጣሉ። እነዚህም አገልጋዮች ይህን አጋጣሚ የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት ይጠቀሙበታል።

በመጋቢነት ካገለገልኩባቸው ቤተ ክርስቲያናት በአንዱ በመዝሙር አገልግሎት ውስጥ የነበረ አንድ ወጣት፥ ለሌሎች መዘምራን በተለይም ለወጣት ሴቶች ታላቅ «መንፈሳዊ ሰው» መስሎ ለመታየት በተቻለው መጠን ሁሉ ይሞክር እንደነበረ አስታውሳለሁ። ይህ ወጣት በተመስጦ ይጸልይና እንዲሁም ከጌታ ጋር ስላለው ጉዞ ብዙ ጊዜ ይናገር ነበር። በመሆኑም አንዳንድ ሰዎች ተማርከውበት ነበረ፤ እኔ ግን ስሕተት የሆነ ነገር እንዳለና አደጋ እንደሚከተል ይሰማኝ ነበረ። በእርግጥም አዲስ አማኝ ከሆነች አንዲት ወጣት ጋር በተደጋጋሚ ይታይ ጀመር። ብዙ ባስጠነቅቃትም ልትሰማኝ አልፈለገችም። መሳሳቷን ያወቀችው ቆይታ ነበር። አሁን ግን ሕይወትዋ ተስተካክሎ እንደገና እግዚአብሔርን በማገልገል ላይ ስለሆነች ጌታን አመሰግናለሁ። ከመጀመሪያውኑ ብትጠነቀቅ ኖሮ ያ ችግር ባልደረሰባትም ነበር።

የሐሰት አስተማሪዎች ዋና ፍላጎት ምኞታቸውን ማርካት ነው፡- ከኃጢአት ሊቆጠቡ አይችሉም። ግሡ «ለማቆም አለመቻል» የሚለውን አሳብ ይሰጣል። ለምን? ምክንያቱም በባርነት ውስጥ ስለሆኑ ነው (2ኛ ጴጥ. 2፡18-19)። የሐሰት ሐዋርያቱ ራሳቸውን «ነፃ» እንደሆኑ ይቆጥራሉ፤ ሆኖም በጣም በሚያሳዝን ባርነት ውስጥ ናቸው። የነኩት ሁሉ ይረክሳሉ፤ ያሸነፉትን ሁሉ ባሪያ ያደርጋሉ።

«የማይጸኑትን ነፍሳት ያጠምዳሉ» የሚለው አባባል ዓሣ አጥማጅ ዓሣዎችን ለማጥመድ መንጠቆው ላይ በሚያስቀምጠው ምግብ ሊመስል ይችላል። ፈተናን «እንደ ማታለያ ወጥመድ» አድርጎ ባቀረበበት በያዕቆብ 1፡14 ላይ በተመሳሳይ ምሳሌ ተጠቅሟል። በመጀመሪያ ደረጃ ሰይጣን አንድ ጥሩ ማታለያ ከሌለው በስተቀር ፈጽሞ ሊያጠምደን እንደማይችል ያውቃል። ሰይጣን ሔዋንን ሊያታልላት የቻለው አዳምና እርሷ ከተከለከለው ዛፍ ቢበሉ «እንደ እግዚአብሔር» እንደሚሆኑ ቃል ስለገባላት ነው (ዘፍ. 3፡4-5)፤ እነሱም «ማታለያውን ተቀበሉ» እና ተጠመዱ።

ለመሆኑ እነኝህ ሐሰተኛ መምህራን ሰዎችን ለማጥመድ በምን ዓይነት «ማታለያ» ነው የሚጠቀሙት? በአንድ በኩል «ነፃነትን» ያቀርቡላቸዋል (2ኛ ጴጥ. 2፡19)። ይህም ምናልባት የእግዚአብሔርን ጸጋ በማይገባ መንገድ መጠቀም ማለት ሊሆን ይችላል፤ «የአምላካችንን ጸጋ ወደ ሴሰኝነት ይለውጣሉ» (ይሁዳ 4)። «በጸጋ እስከዳንክ ድረስ ኃጢአትን ለማድረግ ነፃነት አለህ» በማለት ያደፋፍሩታል። እንዳውም «የበለጠ ኃጢአትን ስታደርግ የበለጠ የእግዚአብሔር ጸጋ ይበዛልሃል»! ይሉታል። ጳውሎስ ለሐሰት ክርክራቸው በሮሜ 6 ላይ መልስ ሰጥቷል። ይህም እያንዳንዱ አማኝ ሊያውቀው የሚገባ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው።

ከ«ነፃነት» ጎን ለጎን የሚያዘጋጁት ሌላው ወጥመድ «የምኞትን መሟላት» የሚያበሥር ነው። ይህም በዘመናችን ከተለመዱት ቃላት አንዱ ሲሆን «የፈለግኸውን ነገር ማድረግ» እና «የፈለግኸውን ማግኘት» ከሚለው ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። «ቤተ ክርስቲያን የምታቀርበው የክርስትና ሕይወት ለጥንቱ ዘመን የሚስማማና ጊዜ ያለፈበት ነው። እኛ ግን የተሟላህ ሰው የሚያደርግህና እውነተኛውን ማንነትህን እንድታገኝ የሚረዳህ አዲስ ትምህርት ልናካፍልህ እንችላለን» ይላሉ። ልክ እንደ አባካኙ ልጅ ሁሉ እነዚህም የመንፈስ እርካታ ያጡ ነፍሳት ራሳቸውን ለማግኘት ይሞክራሉ፤ ግን በመጨረሻ ራሳቸውን ያጣሉ (ሉቃስ 15፡ 11-24)። የግል ምኞታቸውን ለማሟላት በማሳደድ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ይሆኑና ሌሎችን በማገልገል የሚገኘውን ዕድገት የመካፈል ዕድልን ያጣሉ።

ለኢየሱስ ክርስቶስ ከመገዛት ሌላ ምንም ዓይነት ነፃነትና ሙላት ሊኖር አይችልም። ፒ.ቲ.ፎርሲይዝ የተባለ ሰው «የሕይወት ዓላማ ነፃነትህን ማግኘት ሳይሆን ጌታህን ማግኘት ነው» ብሏል። የአንድ የሙዚቀኛ ተማሪ በአስተማሪ ሥር እንደሚማር ሁሉ፥ ወይም ደግሞ በአንድ አሠልጣኝ ሥር ሆኖ እንደሚሠለጥን ሯጭ ሁሉ፥ ራሱን በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ሥር ያደረገ አማኝም የተሟላ እርካታን ያገኛል።

በሐሰት አስተማሪዎች ወጥመድ የሚወድቁት እነማን ናቸው? እነኝህን ሰዎች ወላዋይነት የሚያጠቃቸው በመሆኑ ጴጥሮስ «የማይድኑ ነፍሳት» ብሏቸዋል። የተሳካ የክርስትና ሕይወት እንዲኖረን ከተፈለገ መጽናት አስፈላጊ ነገር ነው። ልክ አንድ ሕፃን ለመራመድ ወይም ለመሮጥ ከመቻሉ

በፊት መቆምን መማር እንዳለበት ሁሉ፥ እንዲሁ ክርስቲያንም «በጌታ ጸንቶ መቆምን» መማር አለበት። ጳውሎስና ሌሎቹ ሐዋርያት የተለወጡትን ሰዎች በእምነት ለማጽናት ይጥሩ ነበር (ሮሜ 1፡ 11፤ 16፡25፤ 1ኛ ተሰ. 3፡2፥ 13)። ጴጥሮስም በበኩሉ አንባቢዎቹ «በእነርሱ ዘንድ ባለ እውነት እንደጸኑ» እርግጠኛ ቢሆንም (2ኛ ጴጥ. 1፡ 12)፥ ነገር ግን አሁንም በጽናት እንዲቆዩ ያስጠነቅቃቸዋል።

## ዓመፀኛነታቸው (2ኛ ጴጥ. 2፡ 14-16)

ይህን ዓመፃቸውን የፊሊጵስ ትርጉም «ትክክለኛውን መንገድ ትተዋል» በማለት ይገልጸዋል። የሐሰት አስተማሪዎች እግዚአብሔር ያጸናውን ቀጥተኛና ትክክለኛ ጎዳና ያውቃሉ፤ ነገር ግን ሆን ብለው የእግዚአብሔርን መንገድ ትተው በራሳቸው መንገድ ይተኩታል፤ ስለዚህ ጴጥሮስ «በፍጥረታቸው እንደተወለዱ አእምሮ እንደሌላቸው እንስሶች» በማለት (2፡ 12) ከእንስሳት ጋር ማወዳደሩ (2፡2) ሊያስደንቀን አይገባም! «እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ» ብሎ ዘማሪውም ያስጠነቅቃል (መዝ. [32]፡9)። ፈረስ ወደፊት ብቻ መገሥገሥ ሲወድ፥ በቅሎ ደግሞ ወደ ኋላ መቅረት ይወዳል፤ ሁለቱም ከትክክለኛው መንገድ ሊያወጧችሁ ይችላሉ። ምእመናን በጎች ናቸው፤ በጎች ደግሞ ከእረኛው አጠገብ መሆን አለባቸው፤ ካልሆነ ይባዝናሉ።

እስከ አሁን የሐሰት አስተማሪዎች ከሃይማኖት ውጪ የሚሆኑበትን አንዱን ምክንያት ተምረናል፤ ይኸውም፡- የሥጋቸውን ፍላጎት ማርካት መፈለጋቸው ሲሆን፥ ነገር ግን ሁለተኛ ምክንያትም ደግሞ አለ፡- የሚጐመጁ ናቸው። ለግል ጥቅም ሲሉ ሰዎችን መበዝበዝ ይፈልጋሉ። ጴጥሮስ ይህንን በ2ኛ መጽሐፉ 2፡3 ላይ ጠቅሶታል፤ አሁን ደግሞ አሳቡን ያዳብረዋል። የሐሰት አስተማሪው አመለካከት ብቻ አይደለም በግል ፍላጎቱ የተገዛው (ቁ. 14)፤ ነገር ግን ልቡም ጭምር ላየው ሁሉ በመጐምጀት ስሜት የተገዛ ነው። በምቾትና ገንዘብ በማግበስበስ ምኞት እስራት ውስጥ ነው ያለው!

እንዲያውም የሚፈልገውን ለማግኘት የሚችልበትን ጥበብ አዳብሮአል። የኤን.አይ.ቪ. ትርጉም «በስስታቸው የተካኑ ናቸው» ሲላቸው ፊሊጵስ የተባለው ትርጉም ደግሞ የበለጠ ሥዕላዊ አገላለጽ አለው፡- «የሚፈልጉትን ነገር ማግኛ ዘዴአቸው በረዥም ጊዜ ልምድ በጣም የበለጸገ ነው» ይላል።

ሰዎችን በማግባባት የሚፈልጉትን ሁሉ እንዲሰጧቸው የማሳመኛውን ዘዴ አንድ በአንድ ያውቃሉ። እውነተኛው የእግዚአብሔር ባሪያ የሚያስፈልገውን ሁሉ አብ እንደሚያሟላለት ተማምኖ፥ ሰዎች በመስጠት ውስጥ እንዲያድጉ ለመርዳት ሲጥር ሐሰተኛው ሐዋርያ ግን «በገንዘብ ማግኛ ዘዴዎች» ተማምኖ ሰዎችን ሲያገኛቸው በማታለል ከባሰ ችግር ውስጥ ይጥላቸዋል። ያልጸኑትንና የዋሆችን እንዴት መበዝበዝ እንደሚቻል ያውቃል።

አንድ አገልጋይ ያሉትን መልካም አጋጣሚዎችና የሚገጥሙትን የተለያዩ ችግሮች በጸሎት ከሚተባበሩት ወዳጆቹ ጋር መካፈሉ ምንም ክፋት የለውም። ለምሳሌ፥ ለእኔና ለባለቤቴ ብዙ ዓይነት ደብዳቤዎችና ሕትመቶች ይደርሱናል፤ እውነቱን ለመናገር ደግሞ ከደብዳቤዎቹ አንዳንዶቹን ሳናነባቸው እንጥላቸዋለን፤ እንወረውራቸዋለን። ምክንያቱም እነዚህ አገልጋዮች ታማኝ አለመሆናቸውን በማወቃችን ነው። ምንም እንኳ አቀራረባቸው ማራኪ ቢመስልም፥ ነገር ግን በእውነታ ላይ የተመሠረተ ካለመሆኑም በእርዳታ የተለገሠውን ገንዘብ ሁልጊዜ በተገቢው መንገድ አገልግሎት ላይ አያውሉትም። ሌሎቹን ደብዳቤዎችና እትሞች ግን በጥንቃቄ እንብበን፤ ጸልየንባቸውና ተወያይተንባቸው በሥራቸው ውስጥ እንድንሳተፍ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እንጠብቃለን። እግዚአብሔር ያነሣሣውን እያንዳንዱን መልካም ሥራ መረዳት እንደማንችል እናውቃለን፤ ስለዚህ እንደ ክብደታቸውና እውነተኝነታቸውን ከመመርመራችንም እግዚአብሔር ለእኛ በመረጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ ብቻ ለመሳተፍ እንሞክራለን።

ጴጥሮስ ስለ እነዚህ ሰዎች ተንኮለኝነት ሲጽፍ «የተረገሙ ልጆች ናቸው» በማለት ነበር ያወገዛቸው። እነርሱም «የተባረኩ» የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ምትክ፥ የተረገሙ የዲያብሎስ ልጆች ነበሩ (ዮሐንስ 8፡44)። ለምሳሌ በባንክ የተቀመጠ ገንዘባቸው በመጠራቀሙ የተሳካላቸው መስሎ ሊታያቸው ይችላል፤ በመጨረሻ ግን በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ደሀ መሆናቸው ይታወጅላቸዋል፡- «እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ» (ማቴ. 25፡41)። «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?» (ማቴ. 16፡26)።

መጐምጀት ለበለጠ ገንዘብ፥ ለበለጠ ኃይልና ለበለጠ ክብር ያልተገራ (ገደብ የለሽ) ፍላጎት ማሳደር፥ መንገብገብ ማለት ነው። የሚጐመጅ ልብ ፈጽሞ አይረካም። ይህም ገንዘብን መውደድ ለምን የክፋት ሁሉ ምንጭ እንደሆነ ያብራራል (1ኛ ጢሞ. 6፡10)፤ ምክንያቱም አንድ ሰው የበለጠ ለገንዘብ ሲጓጓ ያንን ጉጉት ለማርካት ማንኛውንም ኃጢአት ይፈጽማልና ነው። ገንዘብ አምላኩና ጣዖቱ ስለሆነበት ከዓሥርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን ተላልፏል። ከዚያ የተቀሩትን ለመተላለፍ ቀላልና ተቀባባይ እርምጃ ነው የሚሆንለት፡- መስረቅን፥ መዋሸትን፥ ማመንዘርን፥ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራትንና . . . ወዘተ ያለአንዳች ማመንታት ይፈጽማቸዋል። ይህን ስንመለከት ኢየሱስ «ተጠንቀቁ፤ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ» ብሎ ማስጠንቀቁ የሚያስገርመን አይሆንም (ሉቃስ 12፡15)።

በሰሜን አፍሪካ ያሉ ሕዝቦች ዝንጀሮችን ለመያዝ ጥሩ ዘዴ እንዳላቸው አንብቤአለሁ። በቅል ውስጥ ለዝንጀሮው መዳፍ ብቻ የሚያስገባ ቀዳዳ ይሠራሉ፤ ከዚያም ቅሉን በለውዝ ይሞሉትና ከዛፍ ጋር ያስሩታል። በምሽት ዝንጀሮው ለለውዙ ሲል ቅሉ ውስጥ እጁን ይከታል፤ መዳፉን ግን ከቅሉ ለማውጣት አይችልም። በእርግጥ የጨበጠውን ለውዝ በመልቀቅ መዳፉን ከቅሉ ውስጥ በቀላሉ ሊያወጣው ይችል ነበር፤ ሆኖም ለውዙን መተው አይፈልግም! ከመጐምጀቱ የተነሣ መጨረሻው መጠመድ ይሆናል። የዚህ ዓይነቱ ጅልነት ከእንስሳው ቢጠበቅ አያስገርምም፤ ግን በእግዚአብሔር አምሳል ከተፈጠረው ሰው ይህን መሳይ ስሕተት ይፈጸማል ብለን መጠበቅ አልነበረብንም። ሆኖም ግን ድርጊቱን በየዕለቱ የምናየውና የምንመሰክረው ነው።

ጴጥሮስ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። ቃሎቹን ለማብራራት ኖኅንና ሎጥን በምሳሌነት ተጠቅሞባቸዋል። በ2ኛ ጴጥሮስ 2፡15-16 ደግሞ ትንቢት ተናጋሪውን በለዓምን ያቀርባል። የበለዓም ታሪክ በዘኍልቁ 22-26 ላይ ይገኛል፤ አሁኑኑ አንብቡት።

በለዓም አይሁዶችን ለመርገም የሞከረ የአሕዛብ ነቢይና ምሥጢራዊ ገጸባሕርይ ነው። የሞዓብ ንጉሥ የነበረው ባላቅ እስራኤልን ስለፈራ ለእርዳታ በለዓምን ጠራው። በለዓም ከባላቅ ጋር መተባበር ትክክል እንዳልሆነ ያውቅ

ነበር፤ ነገር ግን ልቡ ጐምጅቶ ነበርና ባላቅ ቃል የገባለትን ገንዘብና ክብር ፈለገ። በለዓም የእግዚአብሔርን እውነትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይወቅ እንጂ ትክክለኛውን መንገድ ትቶ በተሳሳተ ጐዳና ሄደ። በዚህ ድርጊቱ ለሐሰት መምህራን መጐምጀትን ለማሳየት ዓይነተኛ ምሳሌ ሆኖ ቀርቦአል።

ከጅምሩ በለዓም ባላቅን እንዳይረዳ እግዚአብሔር ነግሮታል። በመጀመሪያም በለዓም ቃሉን በማክበር መልእክተኞቹን ወደ ቤታቸው ሰድዷቸው ነበር፤ ነገር ግን ባላቅ ቀድሞ ከላካቸው የበለጡ የከበሩ አለቆችን ሲልክና ብዙ ገንዘብና ክብር ሊሰጠው ቃል ሲገባለት በጉዳዩ ላይ «ሊጸልይበትና» እንደገና ሊያስብበት ወሰነ። በሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔር በለዓምን ሊፈትነው ከአለቆቹ ጋር እንዲሄድ ፈቀደለት። በዚህን ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆንም እንኳ የበለዓምን ምኞት እንዳይሳካለት ፈቀደ።

በለዓም ዕድሉን በጉጉት ተቀበለ፤ ነገር ግን መንገዱን ስቶ መሄድ ሲጀምር እግዚአብሔር በአህያይቱ አንደበት ዓመፀኛውን ነቢይ ገሠጸው። ጌቶቻቸው እንኳ ለመታዘዝ ፈቃደኛ ባይሆኑም ይህ የእንስሳት ለእግዚአብሔር መታዘዝ እንዴት ያስደንቃል! (ኢሳ. 1፡3ን አንብቡ)። እግዚአብሔር ለበለዓም መሠዊያውን እንዲሠራና መሥዋዕቱን እንዲያቀርብ ቢፈቅድለትም፥ ነገር ግን እስራኤልን እንዲረግም አልፈቀደለትም ነበር። ይልቁኑ እግዚአብሔር የበለዓምን እርግማን ወደ በረከት ለወጠ (ዘዳግም 23፡4-5፤ ነህምያ 13፡2)።

በለዓም እስራኤልን ለመርገም አይችልም ነበር፤ ነገር ግን እስራኤልን የሚያሸንፍበትን ዘዴ ለባላቅ መምከር ይችል ነበር። ሞዓባውያን ማድረግ ያለባቸው፥ አይሁዶችን «መልካም ጎረቤቶች» እንዲሆኑ መጋበዝና በግብዣቸውም ላይ እንዲሳተፉ ማግባባት ነበር (ዘኁ. 25)። በዚህ ዘዴ የተታለለው እስራኤል በእግዚአብሔር የተሰጠውን ልዩ ስፍራውን ከመጠበቅ ይልቅ በቀላሉ በመደለል ከሞዓባውያን የዝሙትና የጣዖት አምልኮ ጋር ተቀላቀለ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ሥነ-ሥርዓት ማስያዝ ስለነበረበት ከዚህ ስሕተታቸው የተነሣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ እስራኤላዊያን ሞቱ።

የበለዓምን ሕይወት አስመልክቶ ጴጥሮስ በዚህ ምዕራፍ ትኩረት የሰጠባቸውን ሁለት የስሕተት መንገዶች ማየት ይቻላል፤ እነርሱም፡-

ዓለማዊ ምኞትና መጕምጀት ናቸው። ገንዘብ በመውደዱ እስራኤልን ወደ ምኞት ኃጢአት መራቸው። በለዓም ከእግዚአብሔር መልእክቶችን ማግኘት የሚችል ሰው ቢሆንም፥ እርሱ ግን ሰዎችን ከእግዚአብሔር ሲያርቅ ተገኘ! የርሱን ትንቢታዊ ቅኔ ስታነቡ በርሱ አንደበተ ርቱዕነት መመሰጣችሁ አይቀርም፤ ሆኖም በእግዚአብሔር ላይ ዓመፀ! በለዓም «በድያለሁ» ብሏል (ዘኊ. 22፡34)፤ ነገር ግን ኑዛዜው እውነተኛ አልነበረም። «የጻድቃንን ሞት እኔ ልሙት» ብሎ እንኳ ጸልዮ ነበር (ዘኊ. 23፡10)፤ ግን የጻድቅን ሕይወት ለመኖር አልፈለገም።

በለዓም እስራኤልን እንዲያታልል ባላቅን ስለመከረው እግዚአብሔር በበለዓም ላይ ፈረደ። እስራኤላውያን ምድያማውያንን ሲያሸንፉ በሰይፍ ተገደለ (ዘኊ. 31፡8)። ቀና ባልሆኑ መንገዶቹ «ያገኘውን» ሀብት ሁሉ ማን እንደወረሰው ስንመለከት በጣም ያስገርመናል። ጴጥሮስ የርሱን ገንዘብ «የዓመፃ ደመወዝ» ብሎታል። ይህ ሐረግ የ«ዓመፅ ዋጋ» የተቀበለውን ሌላውን አስመሳይ ሰው ማለትም ይሁዳን ያስታውሰናል (የሐዋ. 1፡18)። እርሱም ደግሞ በሚያሳፍር መልኩ ጠፍቶአል።

ይሁዳ ቁ. 11ን ስናጠና ስለ በለዓም የምንለው ብዙ ይኖረናል፤ ዋናውን ትምህርት ግን ሳንጠቅሰው አናልፍም። በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ያመፀ ሰው ነበር። ጴጥሮስ እንደገለጻቸው የሐሰት አስተማሪዎች ሁሉ በለዓም ትክክለኛውን መንገድ ያውቅ ነበር፤ ነገር ግን ሆን ብሎ የተሳሳተ መንገድን መርጦአል። ምክንያቱም ገንዘብ ማግኘት ፈልጎ ስለነበረ ነው። «የተለየ አመለካከት» በመያዙ «በእግዚአብሔር ፈቃድ መቀለዱን» ቀጠለ (ዘኊ. 22፡41፤ 23፡13፥ 27)። ከእግዚአብሔር እውነተኛ ስጦታ እንደነበረው አያጠራጥርም፤ ይኸውም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አንዳንድ ውብ ትንቢቶችን በመናገሩ ነው፤ ዳሩ ግን ክብርንና ብልጽግናን ለማግኘት ብቻ ያንን ስጦታ ያለአግባብ ተጠቀመበት።

አንድ የባንክ ባለሥልጣን ወደ ገንዘብ ተቀባዩ ቀረበና በምሥጢር «50ሺህ ብር ብሰጥህ፥ የገንዘብ መዝገቡን ለመለወጥ ትረዳኛለህ?» ብሎ ጠየቀው።

«አዎን ልረዳህ የምችል ይመስለኛል» ብሎ መለሰለት። «የምሰጥህ 100 ብር ቢሆንስ ልትረዳኝ ትችላለህ?» «አላደርገውም!» አለ ተቀባዩ በንዴት።

«ማን መሰልኩህ፥ ተራ ሌባ መሰልኩህ?» «ይህ እንኳን የተረጋገጠ ጉዳይ ነው» አለ ባለሥልጣኑ። «ይልቁኑ አሁን የምንነጋገረው ስለ ዋጋው ነው።»

የሚጐመጅ ሰው በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ለማመፅ እንኳ ቢሆን ማንኛውንም ነገር ከማድረግ ወደኋላ አይልም። ጴጥሮስ ይህንን «ዕብደት» ብሎ ጠርቶታል። ቃሉ «ከአእምሮ ውጪ» መሆን ማለት ነው። በለዓም ግን ብልህ የሆነ መስሎታል። ያም ሆነ ይህ፥ ምናልባት ዳግምኛ ሊገኝ የማይችለውን አጋጣሚ እየተጠቀመ ነበር። ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ማንኛውም ዓመፅ ዕብደት ነው፤ ያ ደግሞ ወደ አሳዛኝ ፍጻሜ ነው የሚያደርሰው። አባካኙ ልጅ ምን ያህል ሞኝ እንደነበረ ያስተዋለው «ወደ ልቡ በተመለሰ» ጊዜ ነበር (ሉቃስ 15፡ 17)።

ጴጥሮስ ሦስት የሐሰት አስተማሪዎችን ኃጢአት ኮንኗል፡- ነቀፌታቸውን፥ ነወረኝነታቸው እንዲሁም ደግሞ ዓመፃቸውን። እነዚህ ሁሉ ኃጢአቶች የሚመነጩት ከትዕቢትና ከራስ ወዳድነት ነው። እውነተኛ የእግዚአብሔር ባሪያ ትሑትና ሌሎችን ለማገልገል የሚፈልግ ነው (ፊልጵስዩስ 2፡20-21 ያለውን ልዩነት ተመልከቱ)። እውነተኛው የእግዚአብሔር ባሪያ ስለሚያገኘው ምስጋና ወይም ክፍያ አያስብም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን የሚያገለግለው ከልብ ካለው ፍቅርና ታማኝነት በመሆኑ ነው። እግዚአብሔርንና እግዚአብሔር በዚህ ዓለም የመሠረተውን ሥልጣን ያከብራል። ባጭሩ እውነተኛው የእግዚአብሔር ባሪያ ራሱን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቀርጻል።

በእነዚህ በመጨረሻ ቀናት እርዳታ የሚጠይቁ ብዙ የሐሰት አስተማሪዎች ይኖራሉ። ሰዎችን ለማታለልና ገንዘባቸውን ለማግኘት የማሳመን ስጦታው ያላቸውና የሠለጠኑ ናቸው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት በእውነት ላይ እንዲጸኑ፥ ቅዱሳን መጻሕፍት ተጣምመው ሲተረጐሙ ማወቅና ሕዝቡንም ከብዝበዛ ለማዳን ነቅተው መጠበቅ አስፈላጊ ነው። እኔም «በሃይማኖት ስም የሚያጭበረብሩትን» በማጋለጥ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርጉትን ድርጅቶች በዚህ አጋጣሚ አመሰግናለሁ፤ ነገር ግን አሁንም ቢሆን መናፍስትን የመለየትና በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለንን እውቀት ማደግ አስፈላጊ መሆኑን አጥብቄ አሳስባለሁ።

ምንም እንኳ እነዚህ «ሃይማኖታዊ አጭበርባሪዎች» ሙሉ በሙሉ ተጋልጠው ከሥራቸው የሚባረሩ ባይሆኑም፥ አንድ ቀን እግዚአብሔር በሁሉም ላይ ይፈርዳል! እንደ እንስሳት «ለመጠመድና ለመጥፋት» ይወሰዳሉ (2ኛ ጴጥ. 2፡12)፤ «የዓመፃቸውን ደመወዝ» ይቀበላሉ (2፡13)። ይህም ከሌሎች በዝብዘው የወሰዱትን ዋጋ ለማካካስ ነው። «የተረገሙ ልጆች» ናቸውና (2፡14) ከእግዚአብሔር ፊት ለዘለዓለም ይጠፋሉ።

ለፍርድ የተለዩ ወንዶችና ሴቶች ናቸው፤ አያመልጡም።

- 5 -

# ሐሰተኛ ነፃነት

## 2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 17-22

በአሁኑ ጊዜ የሐሰት ትምህርት ከሚያራምዱት መካከል ብዙዎቹ በአንድ ወቅት ቢያንስ የክርስትናን ወንጌል እናምናለን የሚሉ አብያተ ክርስቲያናት አባሎች እንደነበሩ ስንረዳ መደንገጣችን የማይቀር ነው። እነዚህ ሰዎች በቅዱስ ቁርባንና በሌላውም ሃይማኖታዊ ሥነ- ሥርዓት ተሳትፎ ያደርጉ ነበር። የሐዋርያትን እምነት መግለጫና የጌታን ጸሎት ሲያነበንቡ ነበር። ሆኖም ዛሬ ከክርስትና እምነት አፈንግጠው በመውጣታቸው «ነፃነት እንደሚሰማቸው» አስመስለው ይነግሯችኋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ማንኛውንም ሃይማኖታዊ እምነት በመቃወማቸው በአዲስ ነፃነት እየተደሰቱ እንደሚኖሩ የሚመሰክሩ ሰዎች ያጋጥሟችኋል። «ከዚህ በፊት በእንደዚህ ያለው ነገር አምንበት ነበር፤ አሁን ግን አላምንበትም። የተሻለ ነገር አግኝቻለሁ። በሕይወቴ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃነት ተሰምቶኛል» ብለው በድፍረት ይመሰክራሉ።

በዛሬው ዓለም ነፃነት በጣም አስፈላጊ የሆነ ፅንስ አሳብ ነው፤ ሆኖም ግን ቃሉ በትክክል ምን ማለት እንደሆነ ሁሉም ሰው የተረዳው አይመስልም። እንዲያውም፥ ከአንድ አምባገነን መሪ ጀምሮ እስከ አንድ መሸተኛ ሰው ለነፃነት የሚሰጡትን ትርጉም የተገነዘብን እንደሆነ የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን። ነፃነት ማለት ማንም ሰው የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር የማድረግ ዓቅምና ዕድል አለው ማለት እስከሆነ፥ ማንም ሰው ሙሉ በሙሉ ነፃ መሆን አይችልም። በሌላም በኩል የሚያስደስትህን ማንኛውንም ነገር ማድረግ ከነፃነት ይልቅ ለስሜት ተገዢነትን ወይም ባርነትን የሚያመለክት ነው።

የሐሰት መምህራን ለተከታዮቻቸው ነፃነትን ያቀርቡላቸዋል፤ ይህ «ማታለያ» ደግሞ እውነተኛውን እምነት ጥለው ሐሰተኛዎቹን አስተማሪዎች ለመከተል ወጥመድ ይሆንባቸዋል። አስተማሪዎቹ የነፃነት ተስፋን ይሰጧቸዋል፤ ይህ ተስፋ ግን ፈጽሞ እውን ስለማይሆን፤ ያልጸኑት አማኞች በሚያሳዝን ባርነት ውስጥ ይገባሉ፤ የሚቀርብላቸው ነፃነት ሐሰተኛ ነፃነት

ነውና። ጴጥሮስ ደግሞ ስለ ሐሰተኛነቱ የሚያብራሩ ሦስት ምክንያቶችን ሰጥቷል።

## በሐሰት የተስፋ ቃሎች ላይ የተመሠረተ ነው (2ኛ ጴጥ. 2፡17-18)

እምነት ጥሩ የሚሆነው በሚታመነው ነገር ጥሩነት መጠን ነው። ጣዖት አምላኪው በጣዖቱ ላይ ትልቅ እምነት ሊኖረው ይችል ይሆናል፤ ጣዖቱ ግን ምንም ነገር ሊያደርግለት አይችልም። አንድ ጓደኛዬ በአንድ ኩባንያ አትራፊነት በመተማመን ያለውን ሀብት ለድርጅቱ ማስፋፍያ አውሎት ነበር። ሆኖም ግን፥ ያ ኩባንያ እንደርሱ እምነት ጠንካራ ሆኖ ባለመገኘቱ ከኪሳራ ላይ ወደቀ። እናንተ ግን እምነታችሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ካደረጋችሁ ያ እምነት አንድን ነገር ይፈጽማል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁልጊዜ የተስፋ ቃሎቹን ስለሚጠብቅ ነው። «ከሰጠው ከመልካም ተስፋ ሁሉ አንድ ቃል አልወደቀም» (1ኛ ነገ. 8፡56)።

የእነዚህን የሐሰት ሐዋርያት የተስፋ ቃሎች ባዶነት ለማጉላት ጴጥሮስ በሦስት ጠንካራ ገለጻዎች ተጠቅሟል።

«ውኃ የሌለባቸው ምንጮች» (2፡17)፡- የግሪኩ ቃል ትርጉም የውኃ ጉድጓድ ከማለት ይልቅ «ወራጅ ውኃ» ማለት ነው። ጌታችን ሳምራዊቱን ሴት ሲያገለግል የተጠቀመበት በዚሁ ቃል ነው (ዮሐ. 4፡14)። እንዲሁም ዮሐንስ ቅዱሳን ለዘለዓለም የሚኖሩበትን የእርካታ ሕይወት ለመግለጽ የተጠቀመበት ቃል ነው (ራእይ 7፡17፤ 21፡6)። ውኃ የሌለው ምንጭ ጭራሽ ምንጭ አይደለም! ጉድጓድ ውኃ ባይኖረውም እንኳ ጉድጓድ ተብሎ ይጠራል፤ ውኃ የማይፈልቅበት ምንጭ ግን ምንጭ ተብሎ አይጠራም።

የሰው ልጅ እውነትንና እግዚአብሔርን ለማወቅ አብሮት የተወለደ ጥማት አለ። «እኛን ለራስህ ፈጥረኸናል፤ ስለዚህ በአንተ እስኪያርፍ ድረስ ልባችን ዕረፍት የለውም» በማለት አውግስቲን ጽፏል። ሰዎች ይህንን ጥማት ለማርካት በብዙ መንገዶች ይሞክራሉ፤ ይህ ካልተሳካላቸው በምትኩ ሌላ የእርካታ ምንጭ ይሻሉ፤ የውስጥ ሰላምና እርካታን ሊሰጥ የሚችለው ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

ኢየሱስ አለ፡- «ከዚህ ውኃ (በጉድጓድ ውስጥ ካለው) የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል፤ እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ (ለአንዴና

ለመጨረሻ ጊዜ አንድ ጊዜ የጠጣ) ግን ለዘላለም አይጠማም (ዮሐንስ 4፡13-14)። ይህ እንዴት ያለ ንጽጽር ነው! የዓለምን ውኃ ደጋግማችሁ ጠጥታችሁ ርካታን በፍጹም ላታገኙ ትችላላችሁ፤ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከሕይወት ውኃ አንዴ ጠጥታችሁ የዘላለም ርካታን ታገኛላችሁ። የሐሰት አስተማሪዎቹ የዚህ ዓይነት ስጦታ ማቅረብ አይችሉም፤ ምክንያቱም የሚያቀርቡት ምንም ነገር ስለሌላቸው ነው። የተስፋ ቃል ሊሰጡ ይችላሉ፤ ነገር ግን ተግባራዊ ማድረግ አይችሉም።

«በኃይለኛ ነፋስ የተነዱ ደመናዎች» (2፡17)፡- ቃሉ የሚያመለክተው በሐይቅ ወይም በባሕር ላይ በአውሎ ንፋስ የሚነዱ የጉም ወይም የጭጋግ ደመናዎችን ነው። ደመናዎች የዝናምን መምጣት ማብሠር አለባቸው፤ እነዚህ ደመናዎች ግን የሚያስታውቁት ዓውሎ ንፋስ እየመጣ መሆኑን ብቻ ነው። ይሁዳ የገለጻቸው ግን «በነፋስ የተወሰዱ ውኃ የሌለባቸው ደመናዎች» በማለት ነው (ቁ. 12)። የተደጋገመ ድምፅ ይሰማል፤ እንዲሁም እንቅስቃሴና አንድ የሚታይ ነገር አለ፤ ነገር ግን ምንም ትርፍ ያለው ነገር አያስገኝም። ገበሬው ደመናን አይቶ በደረቀው እርሻው ላይ ዝናብ እንዲፈስ ይጸልያል። የሐሰት አስተማሪዎች የሚሰጡት ምንም ነገር የላቸውም፤ ባዶ ናቸው።

«ድቅድቅ ጨለማ» (12፡17)፡- ድቅድቅ የሚለው ቃል ትርጉም «ድንግዝግዝ፥ ምንም ተስፋ የሌለው» ማለት ነው፤ ስለዚህ ትክክለኛው ትርጉሙ «የጨለማው ጥቁረት» የሚል ይሆናል (ቁ. 4ን ተመልከቱ)። እነዚህ የሐሰት ሐዋርያት ሰዎችን ወደ ብርሃን እንደሚመሩ ተስፋ ይሰጣሉ፤ ነገር ግን የእነርሱ የራሳቸው መጨረሻ ከጨለማም በጣም የጨለመው ስፍራ ይሆናል! (ይሁዳ 6 እና 13ን ተመልከቱ)። የገሃነም አካባቢዎች አንድ ዓይነት አይደሉም፤ አንዳንድ ቦታዎች ከሌሎች ይልቅ ጨለማ ይሆናሉ። የዋህ ሰዎች በእነዚህ የሐሰት ሐዋርያት ከመንገድ ውጪ ተመርተው መጨረሻቸውም ከእነርሱ ጋር ገሃነም መሆኑ እንዴት የሚያሳዝን ነው።

ታዲያ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች የሚሰጡት ምንም ነገር ከሌላቸው ተከታዮች መሳብ የሚችሉት እንዴት ነው? ለዚህ ምክንያቶቹ በ2ኛ ጴጥሮስ 2፡18 ላይ ይገኛሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ አስተማሪዎቹ ትምህርታቸውን ለማስፋፋት አፈ ጮሌዎች ናቸው። «በአየር የተሞሉ፥ ትርጉም በማይሰጡ ቃላት» አድማጮቻቸውን እንዴት መማረክ እንደሚችሉ ያውቃሉ። አብዛኛው ሰው ግን የሚሰማውን እንዴት በጥንቃቄ ማድመጥ እንዳለበትና የእነዚህን የሐሰተኛ መምህራን ንግግራቸውንና ጽሑፎቻቸውን እንዴት መገምገም እንደሚገባው አያውቅም። በአስመሳይ ክርስቲያንና በእውነተኛ የወንጌል አገልጋይ መካከል ያለውን ልዩነት ብዙዎች ጠንቅቀው አያውቁም።

የንግግር ችሎታ ባላቸው ሃይማኖተኞች መማረክ የለብንም። ለምሳሌ አጵሎስ አንደበተ-ርቱዕና ከፍተኛ ስሜት ያለው የሃይማኖት ሰው ቢሆንም፥ ነገር ግን መስበክ የሚገባውን ትክክለኛ መልእክት አያውቅም ነበር (የሐዋ. 18፡24-28)። ጳውሎስ የአማኞቹ እምነት በግል ትምህርቱ ላይ ወይም በጥበቡ ላይ እንዳይገነባ ይጠነቀቅ ነበር (1ኛ ቆሮ. 2፡1-5)። ጳውሎስ ብልህ ምሁር ቢሆንም አገልግሎቱ ግን ቀላልና ተግባራዊ ነበር። የሚሰብከው አድማጮቹን ለመማረክ ሳይሆን እውነትን ለመግለጥ ነበር። መልእክቱን ለሰዎች በማስተላለፍና ሰዎቹን በቁጥጥሩ ሥር በማድረግ መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃል።

ሁለተኛው፥ የሐሰት አስተማሪዎች ሊሳካላቸው የቻለው ትምህርታቸውን ለአሮጌው ሰብአዊ ባሕርይ እንዲስማማ አድርገው ስለሚያቀርቡት ነው! ይህ የማታለያቸው አንድ ክፍል ነው (2ኛ ጴጥ. 2፡14)። ሥጋ ሌሎች ፍላጎቶችም ስላሉት «የሥጋ ምኞት»ን በዝሙት ኃጢአት አቅጣጫ ብቻ ማሰብ የለብንም። በገላትያ 5፡19-21 የተሰጠውን ዝርዝር ስታነቡ የሐሰት ሐዋርያት ወጥመዶቻቸውን የሚዘረጉበትን ብዙ ዓይነት የማታለያ ዘዴዎች ትገነዘባላችሁ።

ለምሳሌ፥ ኩራት አንዱ የሥጋ ኃጢአት ነው፤ የሐሰተኛ አስተማሪዎች ትምህርት በአድማጮች እኔነት ላይ የሚገነባ ነው። እውነተኛው የእግዚአብሔር ባሪያ በፍቅር በተሞሉ ቃላት ሰዎች በቅዱስ እግዚአብሔር ቁጣ ሥር የጠፉ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ሲያስተምር፥ የሐሰት አገልጋይ ግን ሰዎች የሕሊናቸውን ወቀሳ እንዲሰሙ አይፈልግም። ሰሚዎቹ እንዴት መልካም እንደሆኑ፥ እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወዳቸውና እንደሚፈልጋቸው እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ መግባት እንዴት

ቀላል እንደሆነ ይነግራቸዋል። እንዲያውም አሁንም በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እንዳሉና እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ሆነው መኖር መጀመር ብቻ እንደሚያስፈልጋቸው ሊነግራቸው ይችላል። በእኔነት የተጠመዱ ሰዎች ንስሐ መግባት እንደማይፈልጉ ስለሚያውቅ የሐሰት ሐዋርያው ስለ ንስሐ መናገርን አይፈልግም።

ለስኬታማነታቸው ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ፥ ከቀድሞ መንገዳቸው አሁን በቅርቡ ወደ ጌታ የመጡትን ያልበሰሉ ሰዎችን ስለ ሚያጠምዱ ነው። የሚያተኩሩት በኃጢአት ውስጥ ባሉት ላይ ሳይሆን በአዳዲስ አማኞች ላይ ነው።

አንድ መጋቢ የሆነ ወዳጄ በፊሊፒንስ ያገለግሉ የነበሩ የወንጌል አገልጋይ ለማገዝ በዩኒቨርስቲው አጠገብ በሚገኘው ሜዳ ላይ ስብሰባዎችን በመጥራትና በማስተናገድ ይተባበር ነበር። ክርስቶስን ለመቀበል ውሳኔ ያደረጉ ተማሪዎች ከአደባባዩ አጠገብ ወዳለ ሕንጻ እንዲገቡ ከተደረገ በኋላ በዚያ ልዩ ምክር ይሰጣቸዋል። በመጨረሻም የክርስትና ሕይወታቸውን እንዴት መጀመር እንደሚገባቸው የሚረዳ የክትትል ጽሑፍ ይሰጣቸው ነበር።

አዲሱ አማኝ ከበሩ ወጥቶ በመሄድ ላይ እያለ ወዲያውኑ አንድ የሐሰት ትምህርትን የሚያስፋፋ ሰው ያገኘውና የገዛ ራሱን ሃይማኖት ማስተዋወቅ ይጀምራል! የሐሰት አስተማሪዎች ማድረግ የነበረባቸው የክትትል ጽሑፍ የያዙትን ሰዎች ፈልገው ማጥመድ ብቻ ነበረ! ይህን ዓይነቱን ዘዴ በታላላቅ የወንጌል ስብሰባዎች ላይ ጭምር ብዙ ጊዜ ይጠቀሙበታል። የሐሰት አስተማሪዎች በቅርቡ ጌታን ለመቀበል ውሳኔ ባደረጉ አዳዲስ አማኞች ላይ ያነጣጥራሉ።

ክርስቲያን አገልጋዮች፥ ወንጌላውያንና መጋቢዎች አዲስ አማኞችን በእምነት ማጽናት ያለባቸው ለዚህ ነው። ለዚህ አደገኛ ዓለም እንዲጋለጡ ከማድረጋችን በፊት አዳዲስ ክርስቲያኖችን እንደሚገባ ልናስተምራቸውና በእምነት ልናጸናቸው ይገባል። ጴጥሮስ ይህንን ደብዳቤ የጻፈበት አንዱ ምክንያት አዳዲስ አማኞችን የሐሰት መምህራን ሊወስዷቸው በውጪ አድፍጠው ስለሚጠብቁ ቤተ ክርስቲያን ጥንቃቄ እንድታደርግ ነበር።

አዳዲስ አማኞችን እንዴት መቆም እንደሚገባቸው ሳናስተምራቸው «ባለመጽናታቸው» ልንፈርድባቸው አይገባም (ቁ. 14)።

የሐሰት መምህራን የሚያቀርቡት ነፃነት ሐሰተኛ ነፃነት ነው፤ ምክንያቱም በሐሰት ተስፋ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ነው። ለምን ሐሰተኛ እንደሆነ የሚያሳየን ሁለተኛ ምክንያት አለ።

## በሐሰተኛ ክርስቲያኖች የቀረበ በመሆኑ ነው
(2ኛ ጴጥ. 2፡ 19-20)

አንተ ራስህ በባርነት ሥር ሆነህ ሌላውን አርነት ልታወጣ አትችልም፤ እነዚህ የሐሰት መምህራን በኃጢአት ባርነት ቀንበር ሥር የነበሩ ናቸው። ጴጥሮስ እነዚህ ሰዎች ከዚህ ዓለም ብክለት ራሳቸውን ለጊዜው ቢለዩም፥ በቀጥታ ወደ ባርነታቸው ተመልሰው እንደሚገቡ ግልፐ አድርጎታል። እንደዳኑ ይመሰክራሉ፤ ነገር ግን ጭራሽ የተዋጁ (ነፃ የወጡ) አልነበሩም!

በቁጥር 19 ላይ ያሉት ግሦች የአሁን ጊዜ ናቸው። «ራሳቸው (የሐሰት ሐዋርያቱ) የጥፉት ባሪያዎች ሆነው፡- አርነት ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጧቸዋል (ለአዳዲስ ምእመናን)።» የእግዚአብሔር ባሪያዎች እንደሆኑ ይናገራሉ፤ ሆኖም የኃጢአት ባሪያዎች ናቸው እንጂ የእግዚአብሔር ባሪያዎች አይደሉም። የሰው ባሪያ መሆን እራሱ አንድ በቂ ችግር ነው፤ ነገር ግን በኃጢአት ባርነት ሥር መኖር አንድ ሰው ሊደርስበት ከሚችለው ክፋት ሁሉ እጅግ የከፋ ነው።

እስከአሁን ድረስ ጴጥሮስ የጻፈውን ስትመለከት የሐሰት አስተማሪዎችን ባሪያ ስላደረጓቸው የኃጢአት ዓይነቶች መረዳት ትችላለህ። በአንደኛ ደረጃ ለገንዘብ ተገዥዎች ነበሩ (ቁ. 3 ና 14)። ከመጐምጀታቸው የተነሣ የዋህ ሰዎችን ለመበዝበዝ ማንኛውንም ዓይነት የማታለያ ዘዴ እንዲጠቀሙ አስገድዷቸዋል፤ በሥጋ ምኞት ደግሞ እስራትም ውስጥ ነበሩ (ቁ. 10፥ 14)። ዓይኖቻቸው ሊያጠምዱ ባሰቧቸው ደካማ ሴቶች ላይ ነበሩ። (ጴጥሮስና ይሁዳ ስለ ሰዶምና ገሞራ በጻፉት ዓይን ስንመለከተው ምናልባት ደካማ ወንዶችንና ወጣቶችን መጨመር እንችላለን።)

በትዕቢት የተወጠሩም ነበሩ (ቁ. 10-12)። መላእክትንና እግዚአብሔርን ጨምሮ ሥልጣን ባላቸው ላይ ክፉ ሲናገሩ ምንም አይመስላቸውም! ራሳቸውን ከፍ ያደርጋሉ፤ ሌላውን ግን ይንቃሉ።

የሚያሳዝነው የዚህ ዓይነቱን ግትርነት የሚያደንቁና እነዚህን ትዕቢተኛ ሰዎች ተከትለው የሚደግፏቸው ሰዎች መኖራቸው ነው።

ጴጥሮስ በዚህ ምዕራፍ የጠቀሳቸውን ሦስት ሰዎች ሕይወት ማመሳከር በጣም ጠቃሚ ነው። እነርሱም ኖኅ፡ ሎጥ እና በለዓም ናቸው። ኖኅ በዘመኑ ከነበረው የኑፋቄ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ራሱን የለየ ነበረ። ከቤተሰቡ በስተቀር ማንም ሰው እግዚአብሔርን ባይከተልም እንኳ የእግዚአብሔርን ጽድቅ በግልጥ የሰበከና በኑዘውና በምስክርነቱ የታመነ ነበረ።

ሎጥ እውነትን አውቆ ራሱን በንጽሕና ጠብቆ ነበረ፤ ይሁን እንጂ ራሱን የለየ ሰው አልነበረም፤ በዚህም ምክንያት ቤተሰቡን አጣ። ሎጥ የሰዶምን ክፋት ጠልቶ ነበረ፤ ሆኖም በዚያ መካከል ኖረል፤ ይህንንም በማድረግ ሴቶች ልጆቹንና ሚስቱን ለረከሱ ተጽዕኖዎች አጋለጠ።

በለዓም የኃጢአትን መንገድ መከተል ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰዎች ኃጢአትን እንዲያደርጉ አበረታትቷል! የእስራኤልን ሕዝብ እንዴት ማታለል እንደሚችል ለባላቅ ነግሮታል፤ ዕቅዱም ሊሳካለት ነበር። ሎጥ ቤተሰቡን አጣ፤ በለዓም ግን ሕይወቱን አጣ።

«ከኃጢአት አታላይነት» ተጠንቀቁ (ዕብ. 3፡13)። ኃጢአት ሁልጊዜ ለአርነት ተስፋ ይሰጣል፤ ሆኖም በመጨረሻ ባርነትን ያመጣል፤ እንደዚሁ ሁሉ የሕይወት ተስፋ ይሰጣል፥ ማብቂያው ግን ሞት ይሆናል። ኃጢአት ጌታ በጸጋው ጣልቃ ገብቶ ካልታደገው በስተቀር ምንም የማምለጫ መንገድ እስከማይኖረው ድረስ አንድን ሰው ቀስ በቀስ የሚያስርበት መንገድ አለው። የታሰሩት ሰዎች ነፃ እንደሆኑ ስለሚያስቡ ኃጢአት የሚያመጣው ጠንቅ ላይሰማቸው ይችላል! በገዛ ራሳቸው ፍላጎቶችና ልማዶች ስለሚታወሩ እስረኞች መሆናቸውን የሚረዱት በጣም ዘግይተው ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ አርነት ሊያወጣን መጣ። በናዝሬት ምኩራብ ውስጥ ባደረገው የመጀመሪያው ስብከት፤ ጌታችን የነፃነትን ጥሪ መለከትና «የተወደደችውንም የጌታን ዓመት» መምጣት አሰማ (ሉቃስ 4፡16 ጀምሮ)። ክርስቶስ ነፃነትን ለመስጠት የተጠቀመበት ዘዴ ልዩ እንደሆነ ሁሉ ስለ ነፃነትም የነበረው ትርጉም ከሐሰት ሐዋርያቱ የተለየ ነበር።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አርነት ማለት «ደስ የሚልህን ነገር ማድረግ» ወይም «በፈለግኸው መንገድ መኀዝ» ማለት አይደለም። እንዲያውም እንደዚህ ዓይነቱ አመለካከት የኃጢአት ውጤት ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘው አርነት ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም የሚገኝ ደስታ ማለት ነው። ችሎታህንና ሁለንተናህን ለእግዚአብሔር ክብር ማዋል ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አርነት ያወጣን በዚህ ሕይወት እጅግ የላቅን እንድንሆንና ከዚያም በመጭው ሕይወት እንደ እርሱ እንድንሆን ነው።

የሐሰት አስተማሪዎች ተከታዮቻቸውን በስሕተት መንገድ ወደ እስራት አውርደዋቸዋል። ጌታችን ግን በእውነት መንገድ አርነት ያወጣናል። «እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» (ዮሐ. 8፡32)። ጌታችን የተናገረው ስለ እግዚአብሔር ቃል እውነትነት ነው። «በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው» በማለትም ጸልዮአል (ዮሐ. 17፡17)። በእግዚአብሔር ቃል በኩል ስለ እራሳችን፥ ስለ ዓለማችንና ስለ አምላካችን ያለውን እውነት እናገኛለን። ይህንን እውነት በቅንነት ስንቀበለው የእግዚአብሔርን መንፈስ ነፃ የማውጣት ኃይሉን እንቀምሳለን። በቅዥት ዓለም መኖር እናቆምና ወደ እውነተኛ ዓለም እንገባለን፤ በእግዚአብሔር ኃይል በኩልም ፈቃዱን ለመፈጸም፥ በጸጋ ለማደግ፥ እንዲሁም «በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ለመንገሥ» እንችላለን (ሮሜ 5፡17)።

በእግዚአብሔር እውነት የሚኖሩት ወደ ላቀ አርነት እየገቡ ይሄዳሉ፤ በውሸት የሚኖሩት ግን ወደ ከፋ ባርነት ውስጥ እየገቡ ይሄዳሉ። «ከፊተኛው ኑሮአቸው ይልቅ የኋለኛው የባሰ» ይሆንባቸዋል። (2ኛ ጴጥ. 2፡20)። ይህም በማቴዎስ 12፡43-45 ጌታችን ከተናገረው ምሳሌ ጋር ተመሳሳይ ነው። ያለ እውነተኛ ንስሐና ዳግመኛ ልደት የሚደረግ ጊዜያዊ ተሐድሶ ወደ ባሰ ኃጢአትና ፍርድ ይመራል። መታደስ የውጪውን ብቻ ሲያጸዳ፥ ዳግም ልደት ግን የውስጡን ይለውጣል።

አንድ ሰው ውጫዊ መታደስ ስላደረገ ኃጢአተኛ ዝንባሌዎቹ ወዲያውኑ ይደመሰሳሉ ማለት አይደለም። እንዲያውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያቆጠቆጡና እያደጉ ይሄዳሉ። ያልዳኑ ሰዎች እንኳ ራስን መግዛት ሊለማመዱ ይችላሉ። ቅድስና ሲባል ክፉ ነገሮችን አለማድረግ ማለት ብቻ አይደለም። እውነተኛ ቅድስና ፈተናን ከማሸነፍ በላይ ነው። እንዲያውም እግዚአብሔርን

ያለመታዘዝ ፍላጎትን እንኳ ማሸነፍ ማለት ነው። ክብደት እንድቀንስ ሐኪሜ ሲነግረኝ እንዲህ ብሎኝ ነበር «ለአንተ ጥሩ ያልሆኑትን ነገሮች መጥላት ተማር።» እውነትም ምክሩ ጥሩ ውጤት አስገኘልኝ!

የሐሰት ተስፋዎችን ከሚሰጡ የሐሰት ክርስቲያኖች «የሐሰት አርነትን» እንጂ ምንም ነገር መጠበቅ አንችልም፤ ይህ እነርሱ የሚያቀርቡት አርነት ሐሰተኛ መሆኑን የሚገልጥ ሦስተኛ ምክንያት አለ።

## ሐሰተኛ ልምድን ያካትታል (2ኛ ጴጥ. 2፡21-22)

ጴጥሮስ እነዚህን የሐሰት አስተማሪዎች «ጨካኝ አራዊቶች» (ቁ. 12) ብሎ ጠርቷቸዋል፤ ማስጠንቀቂያውንም የደመደመው በእሪያና በውሾች ከመሰላቸው በኋላ ነበር። ይህን ሲል ለእነርሱ ያለውን ንቀትና ጥላቻ ለመግለጥ ሳይሆን መሠረታዊ የሆነ መንፈሳዊ ትምህርት እያስተማረ ነበረ።

በዚህ አንቀጽ (ቁ. 17-22) ውስጥ እነርሱ እያለ የሚጠቅሰው ተከታዮቻቸውን ሳይሆን ሐሰት አስተማሪዎቹን በመግለጥ መሆኑን ልንረዳው ይገባል። እነዚህ አስተማሪዎች በእውነት ዳግመኛ የተወለዱ እንዳልሆኑ ማስታወስም አስፈላጊ ነው። ይሁዳ እነዚህኑ ሰዎች በደብዳቤው ውስጥ «ሥጋውያንም የሆኑ መንፈስም የሌላቸው» ብሏቸዋል (ቁ. 19)። የእውነተኛ አማኝ መለኪያው ውጫዊ መንፈሳዊነት ሳይሆን የእግዚአብሔርን መንፈስ ውስጣዊ ማንነታችንን ሲቆጣጠረው ነው (ሮሜ 8፡9)።

ይሁን እንጂ እነዚህ የሐሰት ሐዋርያት «ሃይማኖታዊ ልምድ» ነበራቸው! እንዲሁም ልምዳቸው ከጌታ ጋር ኅብረት እንዲያደርጉ እንደረዳቸው በድፍረት ይናገራሉ። «የጽድቅን መንገድ» ለማብራራት ይችላሉ፤ ደግሞም ትምህርቶቻቸውን ለመደገፍ የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራሉ። በእርግጥም አንድ የተወሰነ ዓይነት «ሃይማኖታዊ ለውጥ» ባያገኙ ኖሮ፥ በአጥቢያ ማኅበረ ምእመናን ኅብረት ውስጥ ለመግባት ፈጽሞ ባልተቻላቸውም ነበር። ሆኖም ግን ያገኙት መንፈሳዊ ለውጥ እንደሚሰጡት ተስፋ ሁሉ የውሸት ነበር።

ጴጥሮስ ሁለቱንም ደብዳቤዎቹን ለአንድ ዓይነት የአማኞች ስብስብ በመጻፉ፥ ሁሉም በመጀመሪያው መልእክቱ ያስፈረውን መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት በግልጥ እንደሚያውቁት ልንገምት እንችላለን። ጴጥሮስ በአዲሱ ልደት ላይ አትኩሮ ነበር (1ኛ ጴጥሮስ 1፡3፥ 22-25)። አንባቢዎቹ «ከመለኮት ባሕርዩ ተካፋዮች» እንደሆኑም አሳስቧቸዋል (2ኛ

ጴጥ. 1፡4)። በዚሁ በመጀመሪያው መልእክቱ ጴጥሮስ ምእመናንን እንደ በግ መስሎ ገልጿቸዋል (1 ጴጥሮስ 2፡25፤ 5፡1-4)። ከክሕደቱ በኋላ ጌታ የጴጥሮስን ሐዋርያነት ሲያጸናለት ተመሳሳይ ገለጻ ነበር የተጠቀመው። (ዮሐንስ 21፡15-17)።

የሐሰት መምህራኑ ዳግም ልደትን ጭራሽ እንደተለማመዱት የሚያሳይ አንዳችም ምልክት የለም፤ ዳሩ ግን የደኅንነት እውቀት ስለነበራቸው የክርስቲያኖችን ቋንቋ መጠቀም ይችሉ ነበር፤ ሆኖም በጌታ የሚገኘውን እውነተኛ ደኅንነት አላገኙም። እንዲያውም በአንድ ወቅት የእግዚአብሔርን ቃል እንኳ እስከመቀበል ደርሰው ነበር (2ኛ ጴጥሮስ 2፡21)፤ ይሁን እንጂ ውለው አድረው ችላ አሉት። በፍጹም ልባቸው ክርስቶስን በማመን በጎቹ አልሆኑም።

በጎች በመሆን ፈንታ እሪያዎችና ውሾች ነበሩ። በዚያን ጊዜ የነበሩ ውሾች ደግሞ እንደ ዛሬው በእንክብካቤ የተያዙ እንዳልነበሩ አስተውሉ! አይሁዶች አሕዛብን «ውሾች» ብለው ነበረ የሚጠሯቸው፤ ምክንያቱም ውሾች በቆሻሻ ውስጥ የሚኖሩና ጥምብ ይበሉ ስለነበረ የአክብሮትና የወዳጅነት ስያሜ አልነበረም!

እነዚህ ሰዎች ስላላቸው «ልምድ» ሊናገሩ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን ያ ልምዳቸው የውሸት ልምድ ነበር። ሰይጣን አስመሳይ ነው። ሰይጣን በሐሰተኛ አገልጋዮች የሚሰበክና (2ኛ ቆሮ. 11፡13-15) የውሸት ክርስቲያኖችን የሚያፈራ (2ኛ ቆሮ. 11፡26- «በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት») ነው። እንዲሁም የሐሰት ወንጌል እንዳለው አይተናል(ገላ. 1፡6-9)። በእንክርዳዱ ምሳሌ ውስጥ ጌታችን እውነተኛ አማኞችን በዘራበት ቦታ ሁሉ ሰይጣን የራሱን አስመሳዮች («የክፉው ልጆች») እንደሚዘራ አስተምሯል (ማቴ. 13፡24-30፥ 36-43)።

እነዚህ የሐሰት መምህራን ምን ዓይነት «ልምምድ» ነው የነበራቸው? በጴጥሮስ ግልጥ ምሳሌ ለመጠቀም እሪያው በውጭው «ታጥቦ» ነበር፤ ይሁን እንጂ ያው እሪያ ነው። ውሻው በማስታወክ የሆዱን ቆሻሻ ቢያወጣም ፤ነገር ግን ውሻነቱን አልለቀቀም። እሪያው በውጪው ደኅና መስሎ ታይቷል ውሻውም በውስጡ የተሻለ ስሜት አድሮበታል፤ ነገር ግን ማናቸውም አልተለወጡም። እያንዳንዳቸው ያንኑ የድሮ ባህርያቸውን ይዘው ነበር።

ሁለቱም እንስሳት ወደ ዱሮው ሕይወታቸው ለምን ተመለሱ ለሚለው ጥያቄ አሳማኙ መልስ የተፈጥሮ ባሕርያቸው ስለሆነ ነው የሚለው ይሆናል። እሪያ ለአጭር ጊዜ ብቻ ንጹሕ ሆኖ መቆየት ይችላል፥ ከዚያም በቅርብ ወዳለው ጭቃ መሄድ አለበት። እሪያው እሪያ እንደሚያደርገው በማድረጉ አንኮንነውም፤ ምክንያቱም የእሪያ ባሕርይ ስላለው ነው። ነገር ግን አንድ በግ ወደ ጭቃ ሲያመራ ብናይ ያሳስበናል! ምክንያቱም ባሕርዩ አይደለምና።

ወጣት እያለሁ አንድ ጎረቤታችን «ሻንቆ» የሚል ስም ያለው አንድ ከርዳዳ ጥቁር ጸጉር የነበረው ውሻ ነበራቸው። ውሾች ሊበሉ የማይገባቸውን የመብላትና ከዚያም በሰፈሩ አካባቢና በተለይም በእኛ መግቢያ ላይ የማስታወክ ልማድ ነበረው። ጉዱ ይህ ብቻ አልነበረም። ሻንቆ ወደዚያው ቦታ ይመለስና ያስታወከውን እንደገና ይበላዋል! በግልጥ ውሾች ይህንን ለዘመናት ሲያደርጉት ነበር። ሰሎሞንም በምሳሌ 26፡11 ላይ ጠቅሶታል፤ ጴጥሮስም ከዚህ ክፍል ነው የጠቀሰው።

ውሻ ሆዱን ባዶ ካደረገ በኋላ በእርግጥ ጥሩ ስሜት ሊሰማው ይችላል፤ ሆኖም አሁንም ውሻ ነው። «ትፋቱን የማስወጣቱ ልምድ» ባሕርይውን አልለወጠውም። እንዲያውም በተቃራኒው (እንደ መሰሎቹ ሁሉ) ወደ ትፋቱ ተመልሶ በመላሱ «ለውሻነት ባሕርይው» ተጨማሪ ማስረጃ ነው የሆነው። ምንም እንኳ አገላለጹ ጸያፍ ቢመስልም ጴጥሮስ በአንባቢዎቹ ላይ ሊፈጥር የፈለገው ስሜት ግን በትክክል ይህንኑ ነበር።

በአገልግሎቴ ወቅት ስለ «መንፈሳዊ ልምዶቻቸው» የነገሩኝ ሰዎች አጋጥመውኛል፤ ነገር ግን በነገሩኝ ታሪክ ውስጥ ምንም የአዲስ ባሕርይ ምልክት አላገኘሁም። አንዳንዶቹ እንደ አሳማ በውጪ የጸዱ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ እንደ ውሻ ለጊዜው በውስጣቸው ጸድተው ጥሩ ስሜት ያደረባቸው ነበሩ፤ ነገር ግን በምንም መንገድ «የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች» አልሆኑም (2ኛ ጴጥ. 1፡4)። አሁንም በቀድሞው ኃጢአተኛ ባሕርይ ውስጥ እያሉ ከችግሮቻቸውና ከኃጢአቶቻቸው ነፃ የወጡ መስሏቸዋል።

2ኛ ጴጥሮስ 2፡20 እንደሚያመለክተው እነዚህ የሐሰት ሐዋርያት «ከዓለም ርኩሰት (ብክለት) አምልጠዋል።» ብክለት በውጪ የሆነ ብልሽት ሲሆን፥ እውነተኛ አማኞች ግን «ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጠዋል (1፡4)። መበስበስ በውጪ ከሚታየው ርኩሰት ይልቅ የከፋ

ነው፤ ውስጣዊ የሆነ ብልሽት ነው። እውነተኛ አማኞች አዲስን ባሕርይ «መለኮታዊ ባሕርይ» ተቀብለዋል፤ ደግሞም አዲስና ልዩ ፍላጎቶችና ምኞቶች አሏቸው። ከእሪያዎችና ከውሾች ወደ በጎች ተለውጠዋል።

ነገር ግን ነፃ ነኝ ብሎ የሚያስብ ሰው ነፃ አለመሆኑን ሲያውቅ ሊሰማው የሚችለውን ተስፋ መቁረጥ እስቲ ገምቱት! የሐሰት አስተማሪዎች የአርነት ተስፋን ይሰጣሉ፤ ሊሰጡ የሚችሉት ግን ባርነትን ብቻ ነው። እውነተኛ አርነት መምጣት ያለበት ከውስጥ ነው፤ ዋናው ቁምነገር ከሰው የውስጥ ባሕርይ መለወጥ ላይ ነው። የአንድን ነገር እውነተኛ ባሕርይ ሊወስነው የሚችለው ተፈጥሮው ነው። እሪያና ውሻ ከእውነተኛ ባሕርያቸው ውጪ በመሆን፥ ከጭቃ ለመራቅ እና ወደ ትፋታቸው ላለመመለስ አይችሉም።

እነዚህን የሐሰት አስተማሪዎች እውነተኛ አማኞች እንደነበሩና ከክርስቶስ በመመለሳቸው ደኅንነታቸውን እንዳጡ የሚናገሩ ሰዎች አጋጥመውኛል፤ ነገር ግን የ2ኛ ጴጥሮስ መልእክት ምዕራፍ 2 እና የይሁዳን በጨረፍታ ብንመለከተው እነዚህ መምህራን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኝ እውነተኛ ደኅንነት ፈጽሞ እንዳልነበራቸው እንገነዘባለን። በእርግጥም እነዚህ ሰዎች በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር እውነተኛ መንጋ አባላት የነበሩ ቢሆኑ ኖሮ ጴጥሮስ ከእሪያና ከውሻ ጋር ፈጽሞ ባላመሳሰላቸው ነበር፤ እንዲሁም «የተረገሙ» ብሎ ባልጠራቸውም ነበር (2፡14)። ወደ ኋላ የተመለሱ እውነተኛ አማኞች ቢሆኑ ኖሮ አንባቢዎቹ እነዚህን ሰዎች እንደገና ወደ ትክክለኛው እምነት እንዲመልሱዋቸው ማበረታታቱ የጴጥሮስ ኃላፊነት በሆነም ነበር (ያዕቆብ 5፡19-20)። ጴጥሮስ ግን እንዲህ እንዲያደርጉ አላዘዛቸውም፤ በዚያ ፋንታ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሚገኙ በጣም ኃይለኛ አነጋገሮች አማካይነት የሐሰት ሐዋርያቱን ኮንኗቸዋል!

በእነዚህ መምህራን የቀረበውና ወደ ባርነት ብቻ የሚመራው «አርነት» ለምን የውሸት አርነት እንደሆነ መረዳት መልካም ነው። ትምህርታቸው አስደሳች ቢመስልም፥ ከኋላቸው ግን ምንም ዓይነት መለኮታዊ ሥልጣን በሌላቸው ባዶ ቃላት የተሞላ በሐሰት ተስፋዎች ላይ የተመሠረተ ነው። በሐሰተኛ ልምድ ከተጠመዱ ከሐሰተኛ ክርስቲያኖች የቀረበ ነው። ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ይህ የእነርሱ «አርነት» የከሳሻችን የዲያብሎስ አሠራር ውጤት ነው።

ይህን እስከተረዳን በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡10 ያለውን የጴጥሮስን ምክር ለማድነቅ እንችላለን፡- «ስለዚህ፣ ወንድሞች ሆይ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ።» ይህም በሌላ አነጋገር «ቀድሞውኑ መንፈሳዊ ኑሮአችሁ እውነተኛ ነበርን? » ማለት ነው። በአብያተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ ፈጽሞ በእውነት ዳግም ያልተወለዱ፥ ነገር ግን እንደዳኑና ወደ መንግሥተ ሰማያት እየተጓዙ እንደሆኑ የሚያምኑ ብዙ ሰዎች መኖራቸውን የማንክደው ሐቅ ነው! ምናልባትም «ልምድ» ነበራቸውና፥ «እንደ እረያው» የተሻሉ መስለው ሊታዩና «እንደ ውሻው» የተሻለ ስሜት ሊያድርባቸው ይችላል፤ ነገር ግን የ«መለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች» በመሆን የተሻሉ ሰዎች የመሆን ዕድል አላገኙም።

ምናልባት ጴጥሮስ ይህን ማለቱ የዲያብሎስ መሣሪያ የነበረውንና ፈጽሞ ዳግም ያልተወለደውን ከአሥራ ሁለቱ አንዱ የነበረውን ይሁዳን በማስታወስ ሊሆን ይችላል። ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ስለ ይሁዳ ትክክለኛውን ነገር ስላልተረዱ እስከ መጨረሻው ጊዜ ድረስ መንፈሳዊ ሰው ይመስላቸው ነበረ!

የሐሰት ሐዋርያቱ የተሳካ አገልግሎት ያላቸው መስለው ይታያሉ በመጨረሻ ግን ለውድቀት የተዘጋጁ ናቸው።

ስለዚህ ለአንተና ለእኔ አስፈላጊው ነገር ከጌታ ጋር በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ለመኖራችን እርግጠኞች መሆናችን ነው። እንዲሁም የቱንም ያህል ዝነኞች ቢሆኑ ከእነዚህ አስመሳይ አገልግሎቶች ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለን እርግጠኞች መሆናችን ወሳኝ ነው።

ክርስቶስ «እውነት» ነው (ዮሐ. 14፡6)፤ እሱንም መከተል ወደ አርነት ይመራል። የሐሰት ሐዋርያት ግን ውሸተኞችና አታላዮች ናቸውና እነሱን መከተል ወደ ባርነት ይመራል። ከሁለት አንዱን የመምረጥ እንጂ መሃል ሰፋሪ የመሆን ዕድል የለህም!

# በሚያፌዙት ላይ ማፌዝ

## 2ኛ ጴጥሮስ 3፡ 1-10

ዊል ሮጀርስ የተባለው ሰው «እያንዳንዱ ሰው ባንዳንድ ነገሮች አላዋቂ ሊሆን ይችላል» ሲል ተናግሮ ነበር።

አባባሉ ትክክለኛ ከሆነ፥ አላዋቂ የሚያደርጉን ከአንድ በላይ ምክንያቶች አሉ። አንዳንድ ሰዎች አላዋቂዎች የሆኑት የመማር ዕድል ካለማግኘት ወይም ደግሞ ምናልባት የመማር ችሎታ ከማጣት ነው፤ ሌሎች (በ2ኛ ጴጥ. 3፡5 ያለውን የጴጥሮስን ሐረግ ለመጠቀም) «ወደው አያስተውሉም።» አንድ ዝነኛ ፈላስፋ «ለዕውቀት መዳከምና ሞት ምክንያቱ አለማወቅ ሳይሆን አለማወቅን አለማወቅ ነው» ብሏል፥ ትክክልም ነው።

ጴጥሮስ በ2ኛ መጽሐፉ ምዕራፍ 2 ውስጥ ስለ ሐሰተኛ ሐዋርያት ባሕርይና ጠባይ ተናግሯል፤ አሁን ደግሞ ስለ ሐሰት ትምህርታቸው ይናገራል። ጴጥሮስ የክርስቶስን በክብር መምጣት እርግጠኝነት አስረግጧል (1፡ 16 ጀምሮ)፤ ይህም የሐሰት ሐዋርያት በጥርጣሬ የሚያዩት ብቻ ሳይሆን የሚክዱትም እውነት ነው። እንዲያውም ስለ ጌታ መመለስ፥ የዓለም ፍርድና የክብር መንግሥት መመሥረት በሚቀርቡ አሳቦች ላይ ይዘብቱ ነበር።

ለእኛ ለክርስቲያኖች ግን የእግዚአብሔርን እውነት መረዳት የቱን ያህል አስፈላጊያችን ነው! ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ መመለስና ስለ ፍርድ እርግጠኝነት ሲናገር፥ ይህን እውነት ከልባቸው ለመቀበል ፈቃደኛ በማይሆኑ ዘባቾች ተከብበናል። በዚህ አንቀጽ ጴጥሮስ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ክርስቶስ የመመለስ ተስፋ ሦስት አስፈላጊ እውነታዎችን እንዲረዱ አንባቢዎቹን ይመክራቸዋል።

### የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው
(2ኛ ጴጥሮስ 3፡ 1-4)

ንጹሕና ቀና አስተሳሰብ ቢኖርህም ቅሉ ምናልባት የማስታወስ ችሎታህ ደካማ ሊሆን ይችላል! ጴጥሮስ ይህንን ደብዳቤ የጻፈው በመጀመሪያ ደረጃ አንባቢዎቹን ለማንቃትና ለማነሣሣት ነበር (1፡ 12-15)። ለክርስቲያኖች «የእግዚአብሔርን ዕውቀት መልመድ» ቀላል ነው። እንደሚታወሰው

አውጤኪስ ያንቀላፋ የነበረው ጳውሎስ ሲሰብክ እየሰማ ነበር! (የሐዋ. 20፡7-10)። ሰማያዊ አባታችን መሥዋዕት የከፈለው የቃሉ እውነት እንዲኖረንና ያንን ለመተግበር ነፃነት እንዲኖረን ነው፤ ነገር ግን ይህንን ቸርነቱን ብዙ ጊዜ በቸልተኝነት ስለምንመለከተው ዳተኞች እንሆናለን። ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው መቀስቀስ አለባት፥ ካለበለዚያ ጠላት ተኝተን ያገኘንና መንፈሳዊ ድክመታችንን ይጠቀምበታል።

የእግዚአብሔር ቃል እውነት ስለሆነ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል፤ መልእክቱን በጥሞና መቀበል አለብን። አዳዲስ ክርስቲያኖች የሐሰተኞች መምህራን የመጀመሪያ ዒላማዎች ስለሆኑ ቃሉን በርትተው መማርና በእምነት ትምህርቶቹም ላይ ያለማወላወል መጽናት አለባቸው። ለቆዩት ክርስቲያኖችም ቢሆን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በተለይም ከክርስቶስ መመለስ ጋር ስለተያያዙት ትምህርቶች በየጊዜው ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ትንቢታዊ ትምህርቶች የሚያስለቅሱና እንቅልፍ የሚያመጡብን መሆን የለባቸውም። እንዲያውም እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት እንድንኖር ሊያነቃቁንና የጠፉትን ለማዳን እንድንነሣሣ ሊያደርጉን ይገባል (ሮሜ 13፡11-14)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጌታ ቀን የሚናገር የሐዋርያት የፈጠራ ሥራ የሆነ ትምህርት አይደለም። ይህን ትምህርት ነቢያት አስተምረውታል፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንዲሁ አስተምሮታል (2ኛ ጴጥ. 3፡2)። ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ የተደጋገፈ እንደሆነ አጠንክሮ ይናገራል። ዘባቾቹ የኢየሱስ ክርስቶስን «ኃይልና መምጣት» በመካዳቸው፥ የነቢያት መጻሕፍትን እውነትነት፥ በወንጌላት ውስጥ ያለውን የጌታችን ትምህርት፥ እንደዚሁም የሐዋሪያትን ጽሑፎች ጭምር እየካዱ ነበር! ልክ እንደ ጌታችን አንድ-ወጥ እጀ-ጠባብ ሁሉ ቅዱሳን መጻሕፍትም አንድ-ወጥ ናቸውና፥ መደበኛ መልእክታቸውን ለማፋለስ መሞከር መጻሕፍቱን መነጣጠል ማለት ይሆናል።

ከሄኖክ ዘመን ጀምሮ ፍርድ እንደሚመጣ እግዚአብሔር ሲያስጠነቅቅ ነበር (ይሁዳ 14-15)። ብዙዎቹ የዕብራውያን ነቢያት ስለ ጌታ ቀን ከማስገንዘባቸውም ሌላ ዓለም እንደሚፈረድበት አስጠንቅቀዋል (ኢሳ. 2፡10-22፤ 13፡6-16፤ ኤር. 30፡7፤ ዳን. 12፡1፤ ትንቢተ ኢዩኤል፤ አሞጽ 5፡18-20፤ ትንቢተ ሶፎንያስ፤ ዘካ. 12፡1-14፡3)። ይህ የፍርድ

ጊዜ «የያዕቆብ መከራ ዘመን» (ኤር. 30፡7) እና ታላቁ የፍዳ ዘመን በመባል ይታወቃል።

ጌታችን በደብረ ዘይት ተራራ ስብከቱ ስለዚህ የፍርድ ቀን አስተምሯል (ማቴ. 24-25)። ጳውሎስም በ1ኛ ተሰሎንቄ 5 ና 2ኛ ተሰሎንቄ 1-2 ያብራራው ሲሆን፥ ሐዋርያው ዮሐንስም ይህንን የሚያስፈራ ቀን በራእይ 6-19 ገልጾታል። ዘመነ- ፍዳ የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቦች ላይ የሚፈስበት ጊዜ ይሆናል፤ እንዲሁም ሰይጣን ለቁጣውና ለተንኮሉ የሚሯሯጥበትና የሚፈነጭበት ጊዜ ይሆናል። ይህም የሚያከትመው ኢየሱስ ክርስቶስ በክብርና በድል ሲመለስ ይሆናል።

ይህ «ታላቅ እና የሚያስፈራ የፍዳ ቀን» ከመድረሱ በፊት የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ሰማይ እንደሚወሰዱ በግሌ አምናለሁ፤ ሆኖም ይህንን በበኩሌ የቡድን መለያ ወይም የመንፈሳዊነት ደረጃ መለኪያ አድርጌ ልወስደው አልፈልግም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን የተለያዩ «ቀናት» በጥንቃቄ መለየት እንዳለብን አስባለሁ። «የጌታ ቀን» የሚለው ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመለስ የሚፈጸመው የፍርድ ቀን ነው። «የእግዚአብሔር ቀን» (2ኛ ጴጥ. 3፡12) እግዚአብሔር በክፋት ሁሉ ላይ የሚፈርድበትንና የእግዚአብሔር ሕዝብ በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር የሚኖሩበትን ቀን የሚያመለክት ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡28)። «የክርስቶስ ቀን» የተያያዘው ደግሞ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ለመንጠቅ ከሚመጣበት ጊዜ ጋር ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡7-9፤ ፊሊጵ. 1፡10፤ 2፡16)።

የትንቢት ተማሪዎች በሦስት ክፍሎች የተከፈሉ ይመስላሉ፡- አንደኛው ወገን ከጌታ ቀን በፊት ቤተ ክርስቲያን ትነጠቃለች ብለው የሚያምኑ (አብረው ወደ ላይ ይሄዳሉ 1ኛ ተሰ. 4፡13 ጀምሮ) ናቸው። ሁለተኛው ወገን ደግሞ ይህ ክሥተት በጌታ ቀን መካከል ይሆናል፤ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የመከራውን የመጀመሪያ ግማሽ ትካፈላለች ብለው የሚያምኑ ናቸው። እንደዚሁም በመከራው ዘመን ማብቂያ ላይ ጌታ ሲመለስ ቤተ ክርስቲያን ትነጠቃለች ብለው የሚያምኑ ሦስተኛ ወገኖችም አሉ። በእያንዳንዱ የአስተሳሰብ ቡድን ውስጥ መልካምና እግዚአብሔርን

የሚመስሉ ሰዎች አሉ፤ ደግሞም የአተረጓጎም ልዩነታችን ለኅብረታችንም ሆነ ለክርስቲያናዊ ፍቅራችን ዕንቅፋት መፍጠር የለበትም።

የእግዚአብሔር ቃል የሚተነብየው የጌታን ቀን መምጣት ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ያንን ቃል የሚክዱ ዘባቾች እንደሚመጡም ይተነብያል! የእነኝህ ቃሉን የሚክዱት ሰዎች በገሐድ መከሠት በራሱ የትንቢቱ ቃል እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ያረጋግጣል። ስለዚህ በእነዚህ ፌዘኞች በመካከላችን መገኘት ልንደነቅ አይገባንም (የሐዋ. 20፡28-31፤ 1ኛ ጢሞ. 4፤ 2ኛ ጢሞ. 3ን ተመልከት)።

ፌዘኛ ማለት ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባውን ነገር በቀላሉ የሚያይ ሰው ማለት ነው። በኖኅ ጊዜ የነበሩት ሰዎች ፍርድ እንደሚመጣ ሲነገራቸው ያፌዙ ነበር። የሰዶም ዜጎችም እሳትና ዲን በኃጢአት የተሞላች ከተማቸውን እንደሚያጠፉ ሲነገራቸው አፌዙ። አንተም ከአሁን በፊት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመመስከር ሞክረህ ከሆነ በሲኦል ወይም ለዚህ ዓለም ሊመጣ ባለው የፍርድ ቀን አሳብ ላይ የሚያሾፉ ሰዎች ያጋጠሙህ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

እነዚህ መናፍቃን ለምን ያፌዛሉ? የሚያፌዙበት ዋናው ምክንያት በኃጢአታቸው መቀጠልን ስለሚፈልጉ ነው። ጴጥሮስ የሐሰት መምህራን «ርኩስ ምኞትን» እንደሚከተሉና (2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 10) እንዲሁም ደካማ ሰዎችን «በሥጋ ሴሰኛ ምኞት» (2፡ 18) እንደሚማርኩ ግልጥ አድርጎታል። አንተም ብትሆን የኑሮ ዘይቤህ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን እስከሆነ አንድም የኑሮ ዘይቤህን መለወጥ ይኖርብሃል፤ አለበለዚያም የእግዚአብሔርን ቃል ለመለወጥ ትገደዳለህ ማለት ነው። መናፍቃን የኋለኛውን ይመርጣሉ፤ ስለዚህ ስለ ፍርድና ስለ ጌታ መምጣት በሚነገሩ ትምህርቶች ያፌዛሉ (ይዘብታሉ)።

መከራከሪያቸው ምንድን ነው? ዓለም ከጥንት ጀምሮ አሁን እስካለችበት ሁኔታ ነበረች የሚለው ነጥባቸው ነው። «ባለፉት የታሪክ ዘመናት ምንም ዓይነት የምድር ለውጥ አልሆነም፤ ስለዚህ ወደ ፊት ይሆናል ብሎ ለማመን ምንም ምክንያት የለም» ብለው ይከራከራሉ። ማስረጃዎችን በመመርመር፥ ምክንያቶችን በመደርደርና እንዲሁም ማጠቃለያ አሳብ በመስጠት

«ሳይንሳዊ አቀራረብ»ን ይመርጣሉ፤ ሌሎችን ማስረጃዎች ግን ላለመቀበል በፈቃዳቸው ችላ ማለታቸው የሚረብሻቸው አይመስልም።

እርግጥ ከቁስ አካላዊው ዓለም ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች የሳይንሳዊው አቀራረብ በአስደናቂ ሁኔታ ይሠራል፤ ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት ወደ ላቦራቶሪ (ቤተ ሙከራ) ወስደህ እንደሌላ መላምት ልትመረምረው አትችልም። ለነገሩ «የሳይንስ ሕጎች» ተብለው የሚጠሩት በተወሰኑ ሙከራዎችና ፈተናዎች ላይ የተመሠረቱ አጠቃላይ እውቀቶች ብቻ ናቸው። እነዚህ ሕጎች ለውጥ ሲመጣ ሊለወጡ የሚችሉ አጠቃላይ አሳቦች ናቸው። ምክንያቱም ማንም ተመራማሪ ግኝቱን ለማረጋገጥ ከቁጥር በላይ የሆኑ ሙከራዎችን ማድረግ ስለማይችል ነው። እንደዚሁም በሙከራዎቹና በገዛ ራሱ አስተሳሰብ ውስጥ የተካተቱትን ጭብጦች ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር አይችልም።

የእግዚአብሔር ቃል አሁንም «በጨለማ ስፍራ የሚያበራ መብራት» ነው (1፡19)። ልንታመንበት እንችላለን። ዘባቾች ምንም ቢሉ፥ የእግዚአብሔር ፍርድ ቀን በዓለም ላይ ይመጣል፤ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ የክብር መንግሥቱን ለመመሥረት ይመለሳል።

## የእግዚአብሔር ሥራ ቋሚ ነው (2ኛ ጴጥሮስ 3፡5-7)

ለመሆኑ ለመናፍቃን የፌዝና የሞኝነት ክርክር ጴጥሮስ እንዴት ነበር የመለሰው? «እግዚአብሔር የተረጋጋውን የፍጥረቱን ሂደት አያፋልሰውምና የክርስቶስ መምጣት የተስፋ ቃል እውነት አይደለም!» ብለው መናፍቃን ይከራከራሉ። ጴጥሮስ ያደረገው ደግሞ እግዚአብሔር ባለፉት ጊዜያት ያደረገውን በማስታወስ፥ ሥራው በዘመናት ውስጥ ቋሚና የማይለወጥ መሆኑን ማስረገጥ ነበረ፤ ለዚህም ጴጥሮስ የሐሰት መምህራን ሆን ብለው የገደፉትን በማስረጃነት አቅርቧል። እነኝህ «በምርምር ተራቅቀናል» ባዮች (ሳይንቲስቶች፥ ለዘብተኛ የሥነ - መለኮት ሊቃውንት፥ ፈላስፎች) የመረጡትን ብቻ መቀበላቸውና ከአእምሮአቸው በላይ የሆነውን ግን ችላ ማለታቸው በጣም የሚያስገርም ነው።

ጴጥሮስ ነጥቡን ለማስረገጥ በታሪክ ውስጥ ሁለት ክስተቶችን ጠቅሷል፤ ይኸውም በፍጥረት ጊዜ የነበረውን የእግዚአብሔር ሥራ (3፡5) እና በኖኅ ጊዜ የነበረውን የውኃ መጥለቅለቅ ነው (3፡6)።

እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በቃሉ ፈጠረ። «እግዚአብሔርም አለ» የሚለው ሐረግ በዘፍጥረት 1 ውስጥ ዘጠኝ ጊዜ ተጠቅሷል። «እርሱ ተናግሯልና፥ ሆኑም፤ እርሱ አዘዘ፥ ጸኑም» (መዝ. [33]:9)። ፍጥረት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን በዚያው ቃል መሠረት በአንድነት የተያያዘ ሆኗል። ኬኔት ዊስት የተባለው ሰው የ2ኛ ጴጥሮስ 3፡5 ረቂቅ ትርጉም ለማመልከት በሚከተለው መንገድ አቅርቦታል፡- «ይህንን በሚመለከት ሰማያት ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ይኖሩ እንደነበረ እና መሬትም በውኃ ላይ እንደቆመ፥ ውኃውም በእግዚአብሔር ቃል እንደተያዘ መቀበል አይፈልጉም።»

የጴጥሮስ መከራከሪያ አሳብ ግልጥ ነው። ዓለምን በቃሉ የፈጠረ ያው እግዚአብሔር፥ በራሱ ዓለም ጣልቃ ሊገባና የሚሻውን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ይችላል! የሠራውና በአንድነት የያዘው ቃሉ ነው፤ ቃሉ ደግሞ ኃያልና ብርቱ ነው።

ጴጥሮስ ያነሣው ሁለተኛው ክሥተት የኖኅን ዘመን የውኃ መጥለቅለቅ ነበር (3፡6)። በኖኅ ዘመን የደረሰው የጥፋት ውኃ የመለኮታዊ ፍርድ ምሳሌ እንደሆነ ጠቅሷል (2፡5)፤ ስለዚህ ወደ ዝርዝር ውስጥ መግባት አላስፈለገም። የውኃ መጥለቅለቁ መቅሠፍታዊ ክሥተት ነበር። በዚህ ክፍል የተጠቀመበት መጥለቅለቅ የሚለው ግሪክኛ ቃል ጥፋት ወይም መቅሠፍት ማለት ነው። ምናልባትም ከዚያ በፊት በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ውሽንፍር ወይም የምድር ጥልቆች ተከፍተው ያን ያህል ውኃ ሲያፈልቁ ለይተው አያውቁ ይሆናል፤ ነገር ግን በኖኅ ጊዜ ሁኔታዎቹ የተፈጸሙትም ይህን በሚመስል መልካቸው ነበር። የእነርሱም «ሳይንቲስቶች»፥ ዘባቾቹ እንደሚከራከሩት ሁሉ፥ «ሁሉም ነገር ከመጀመሪያው አንሥቶ እንደነበረ እየተከናወነ ነው። ሕይወት በቀደመው ሂደትዋ ናት፤ ስለዚህ ያልተለመደ ምንም ነገር ሊሆን አይችልም» ማለት ባላቃታቸውም ነበር። ያ የውኃ ጥፋት ግን በእርግጥ ደርሷል!

እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚፈጽምበት የራሱ ኃይል አለው። ከሰማይ ዝናብን ወይም ከሰማይ እሳትን መላክ ይችላል። «አምላካችን በላይ በሰማይ ነው፤ የፈቀደውን ሁሉ አደረገ» (መዝ. [115]:3)።

እግዚአብሔር በጥንቱ ዘመን የታሪክ ሂደት ውስጥ ጣልቃ መግባቱን ጴጥሮስ ካመለከተ በኋላ፥ በ2ኛ ጴጥሮስ 2፡7 ላይ ካለው አሳቡ ጋር ለማዛመድ ሁኔታዎቹን እያመቻቸ ነበር። ዓለምን የፈጠረውና ያቆየው ያው ቃል አሁንም ዓለምን በአንድነት አጽንቶ እንደያዘ ነው። በውስጡ የታመቀውንም እሳት ለዚያ ፍርድ ቀን አከማችቶታል። ከእንግዲህ ወዲህ ዓለምን በውኃ እንደማያጠፋ እግዚአብሔር ቃል ገብቷል (ዘፍ. 9፡8-17)። የሚቀጥለው ፍርድ የእሳት ፍርድ ይሆናል።

«የተጻፈን እሳት» የሚለው የኪኔት ዊስት ትርጉም በጣም ዘመናዊ ትርጉም ነው። ዘመናዊው የአውቶሚክ ሳይንስ ዓለም በተሠራችባቸው ንጥረ-ነገሮች ውስጥ ከፍተኛ የተከማቸ ኃይል መኖሩን አረጋግጧል። በጣም ግዙፍ መርከብ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል በቂ የአቶሚክ ኃይል በአንድ ብርጭቆ ውኃ ውስጥ አለ። የሰው ልጅ ይህንን ከፍተኛ ኃይል ደርሶበታል፤ ከዚያም የተነሣ ዓለም በአውቶሚክ ፈንጂ ወደምትጠፋበት ጊዜ በመቃረብ ላይ ትመስላለች። ሆኖም እንደ ጴጥሮስ አባባል ከሆነ ዓለም የምትጠፋው በአውቶሚክ ኃይልና በሰው ልጅ አማካይነት አይደለም። ጴጥሮስ በዚህ ክፍል የሚያመለክተው ያ የተወሰነው የፍርድ ቀን ሲደርስ «ቁልፉን የሚጫነው» እና የቀድሞውን ፍጥረትና ከእሱም ጋር የኃጢአተኛውን ሰው ሥራዎች ሁሉ የሚያቃጥለው እግዚአብሔር ነው። ከዚያ በኋላ የአዲስ ሰማይና ምድር ዘመን ይጀምርና እግዚአብሔር በክብር ይገዛል።

በእግዚአብሔር የመጀመሪያ ፍጥረት ውስጥ የነበረው ማንኛውም ነገር መልካም ነበር። የሰው ኃጢአት ነው መልካሙን ፍጥረት ወደ መቃተት ኑሮ የለወጠው (ሮሜ 8፡ 18-22)። እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ሰው ፍጹም መልካም በነበረው አካባቢ እንዲኖር አልፈቀደለትም፤ ከሰው በደል የተነሣ ምድርን ረገማት (ዘፍ. 3፡14-19)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው የእግዚአብሔርን ፍጥረት በመበከልና በማጥፋት ላይ ነው። ለብዙ ዘመናት ያህል ይህ ምንም ችግር የሚፈጥር አይመስልም ነበር፤ አሁን ግን አሳባችንን እየቀየርን ነን። የተፈጥሮ ሚዛን ተዛብቷል፤ ዋጋ ያላቸው ጥሬ ሀብቶች ባክነዋል፤ የኃይል ምንጭ እያሽቆለቆለ ነው፤ እንዲሁም ሥልጣኔ ቀውስ እያጋጠመው ነው። ዛሬ ታላቅ ጥፋት እያንጃበበ እንደሆነ የሚነግሩን ሰባኪዎችና ወንጌላውያን ብቻ ሳይሆኑ፥ የማኅበራዊ ኑሮ ምሁራን፥ የአካባቢ ሁኔታ ተመራማሪዎች እና የአውቶሚክ ሳይንቲስቶች ጭምር ናቸው።

ጴጥሮስ የራሱን ነጥብ አስረግጧል፡- እግዚአብሔር በታሪክ ሂደት ውስጥ ጣልቃ መግባት ይችላል። ባለፉት ጊዜያት አድርጎታል፤ አሁንም እንደገና ሊያደርገው ይችላል። በነቢያትና በሐዋርያት እንደዚሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል የተገባው የጌታ ቀን በኖኅ ዘመን እንደ ሆነው የውኃ መጥለቅለቅ እንዲሁም ሰዶምንና ገሞራን ለማጥፋት እንደ ወረደው እሳትና ዲን ዛሬም ቢሆን መምጣቱ የማይቀር ነው። ይህን በተመለከተ ዘባቾች መከራከሪያ ነጥባቸውን ቀድመው አዘጋጅተው ነበር፡- «የሚመጣ ከሆነ ለምን ዘገየ?» በማለት ይጠይቃሉ። ስለ ክርስቶስ መምጣትና የዓለም ፍርድ ለዘመናት ሲነገር ነበር፤ አሁንም ገና አልተፈጸመም። ግን ይህ ማለት እግዚአብሔር አሳቡን ለውጧል ማለት ይሆን? አይደለም! ዛሬ ዓለም በእርግጥ ለፍርድ ደርሳለች! ጴጥሮስ ሦስተኛውን ማረጋገጫ አቅርቦአል።

## የእግዚአብሔር ፈቃድ ምሕረትን የተሞላ ነው (2ኛ ጴጥሮስ 3፡8-10)

አሁንም እንደገና፥ ጴጥሮስ የዘባቾችን አለማስተዋል ያጋልጣል። ያላስተዋሉት እግዚአብሔር ባለፈው ጊዜ ያደረገውን ብቻ አልነበረም (ቁ. 5)። የእግዚአብሔርን ማንነትንም ዘንግተዋል። እግዚአብሔርን በገዛ ራሳቸው ምስል እየሠሩትና የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ የመሆን እውነታ እየካዱ ነበር። መካድ ማለት እግዚአብሔር መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ እንደሌለው አለማመን ነው። ጴጥሮስ ግን እንደሚከተለው አስረግጦ ያስተምራል፡- ሰው የማይሞት ነው፤ መጀመሪያ አለው መጨረሻ ግን የለውም። በመንግሥተ ሰማያት ወይም በገሃነም እሳት ውስጥ ለዘለአለም ይኖራል። እግዚአብሔር ግን ጅማሬ ወይም ፍጻሜ የሌለው ዘላለማዊ ነው። በዘለዓለማዊነት ይኖራል። ዘለዓለም «የተራዘመ ጊዜ» ብቻ አይደለም። ዘለዓለም ማለት ከጊዜ በላይና ከጊዜ ተለይቶ የሚኖር ማለት ነው።

ጴጥሮስ ይህንን ሲል በእርግጥም «ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን፥ እንደ ሌሊትም ንጋት ነውና» የሚለውን ከመዝ. [90]፡4 እያጠቀሰ ነበር። አይዛክ ዋትስ የተባለ ሰው «እግዚአብሔር ሆይ፥ ባለፉት ዘመናት ረድኤታችን አንተ ነህ» ለሚለው ታዋቂ መዝሙሩ መነሻ ያደረገው መዝሙር 90ን እንደሆነ ልናስታውስ ይገባል።

ሺህ ዓመት በአንተ ፊት ትናንት እንዳለፈው ምሽት ነው፤

ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት እንዳለፈው ሌሊት አጭር ነው።

በጌታ ዘንድ ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን እስከሆነ ድረስ ቃሉቹን ለመፈጸም ዘግይቷል ብለን ልንወቅሰው አንችልም። በእግዚአብሔር ዓይን ፍጥረተ-ዓለም ሁሉ የጥቂት ቀናት ዕድሜ ብቻ ነው ያለው! እንደ እኛ በጊዜ የተወሰነ አይደለም፤ በሰው መለኪያም አይለካም። በተለይም በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ሥራዎች ስታጠና ጨርሶም በችኮላ ላይ የተመሠረተ እንዳልነበር ማየት ትችላለህ፤ ሆኖም ግን እግዚአብሔር በፍጹም አይዘገይም።

ዓለምን በሙሉ በአንድ ቅጽበት ለመፍጠር ሳያቅተው እርሱ ግን በስድስት ቀናት ውስጥ መፍጠሩን መረጠ። እስራኤልን ከግብፅ በአንድ ጊዜ ሊያወጣ ይችል ነበር፥ ሆኖም ሙሴን በማሠልጠን ሰማንያ ዓመታት መቆየትን መረጠ። አዳኙን የበለጠ ቀደም ብሎ መላክ ይችል ነበር፤ ነገር ግን «የዘመኑ ፍጻሜ እስከሚደርስ» ድረስ ጠበቀ (ገላ. 4፡4)። እግዚአብሔር በጊዜ ውስጥ ቢሠራም በጊዜ የተወሰነ ነው ማለት አይደለም።

ለእግዚአብሔር፥ አንድ ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን አንድም ቀን እንደ ሺህ ዓመት ነው። ሌሎች ለመፈጸም ሺህ ዓመታት የሚወስድባቸውን እግዚአብሔር በአንድ ቀን ሊፈጽመው ይችላል! የሚሠራው ረጋ ብሎ ነው፤ መሥራት ከጀመረ ግን ነገሮችን ያከናውናል!

ዘባቾች ግን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት ወይም ምሕረት አልተረዱም። እግዚአብሔር የክርስቶስን መመለስና የጌታን ቀን መምጣት ለምን ነበር ያዘገየው? ለማድረግ ሳይችል ወይም ለማድረግ ሳይፈቅድ ቀርቶ አልነበረም። መሥራቱን ማጓተቱ ወይም ከዕቅዱ ውጪ መጓዙ አልነበረም! አንድን ነገር እግዚአብሔር መቼ ማድረግ እንዳለበት ለመወሰን የሚችል በምድር ላይ ማንም መብት ያለው ሰው የለም። እግዚአብሔር በሁሉም ነገር የበላይ ነውና መጎትጎትን ወይም ከኃጢአተኛ ሰው ምክርን አይፈልግም (ሮሜ 11፡33-36)።

እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ ስለሆነና ለጠፉት ኃጢአተኞች የመዳንን ዕድል ሊሰጣቸው በመፈለጉ የክርስቶስን መምጣትና የታላቁን ፍርድ ቀን አዘገየው። «የጌታችንም ትዕግሥት መዳናችሁ እንደሆነ ቁጠሩ» (2ኛ ጴጥሮስ 3፡15)።

የእግዚአብሔር «መዘግየት» ለዚህ ዓለም ዕቅድ እንዳለውና ዕቅዱን እያደረገ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ እግዚአብሔር ኃጢአተኞች እንዲድኑ ይፈልጋል ወይ? የሚለው ጥያቄ በማንም ሰው አእምሮ ውስጥ ሊብላላ አይገባውም። እግዚአብሔር «ማንም እንዲጠፋ አይፈቅድም» (3፡9)። 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡4 እግዚአብሔር «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ» እንደሚወድ ያረጋግጣል። እነዚህ ሁለት ጥቅሶች አሉታዊና አዎንታዊ ገጽታ ቢኖራቸውም አጣምረን ስንመለከታቸው ግን እግዚአብሔር በኃጢአተኛው ሞት እንደማይደሰት ያረጋግጡልናል (ሕዝ. 18፡23፥ 32፤ 33፡11)። ሁሉም የማይድኑ ቢሆንም ለሁሉም ምሕረቱን ያሳይል (ሮሜ 11፡32)።

እግዚአብሔር ከውኃ መጥለቅለቁ በፊት በነበሩት ዓመታት ተመሳሳይ ትዕግሥትን እንዳሳየ ማስተዋል አለብን (1ኛ ጴጥሮስ 3፡20)። የሰውን ዓመፅና ክፋት አይቷልና ወዲያውኑ ዓለምን ሊፈርድበት ይችል ነበር፤ ሆኖም ቁጣውን መለሰና በፋንታው ኖኅን «የጽድቅ ሰባኪ» አድርጎ ላከው። በሰዶምና ገሞራ ጉዳይ አብርሃም ለከተሞቹ ሲማልድ እግዚአብሔር በትዕግሥት ከመጠበቁም ሌላ፥ በሰዶም ውስጥ አሥር ጻድቃንን እንኳ ቢያገኝ ኖሮ ከመፍረድ ይቆጠብ ነበር።

እግዚአብሔር ለጠፉት ኃጢአተኞች የሚታገሥ ከሆነ፥ ጴጥሮስ «ጌታ ... ስለ እናንተ ይታገሣል» ብሎ ለምን ጻፈ? «እናንተ» የተባሉት እነማን ናቸው? እግዚአብሔር የሚታገሥ ስለ ራሱ ሕዝብ ይሆንን?

ምናልባት ጴጥሮስ «እናንተ» የሚለውን ቃል የተጠቀመበት በአጠቃላይ ሁኔታ ማለትም «የሰው ዘር» ለማለት ይሆናል። ምናልባትም ከዚህ በበለጠ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ምርጦች ወደሆኑት የመልእክቱ አንባቢዎች ሊሆንም ይችላል (1ኛ ጴጥሮስ 1፡2፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1፡10)። እግዚአብሔር ስለ ጠፉ ኃጢአተኞች ይታገሣል፤ ምክንያቱም ከእነርሱ መካከል አንዳንዶቹ አምነው የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝቦች አካል ስለሚሆኑ ነው። በዓለም ላይ ካሉት ካልዳኑት ሰዎች ውስጥ የእግዚአብሔር ምርጦች እነማን እንደሆኑ አናውቅም፤ ለማወቅም አያስፈልገንም። የእኛ ሥራ «መጠራታችንንና መመረጣችንን ማጽናት» ነው (1፡10፤ ሉቃስ 13፡23-30)።

እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች መኖራቸው መረዳታችን መልካሙን ዜና እንድናበስርና ሌሎችን ለክርስቶስ እንድንማርክ የሚያበረታታን ነው።

እግዚአብሔር በዚያን ዘመን ስለነበሩት ዘባቾች እንኳ ታግሦአል! ንስሐ መግባት ያስፈልጋቸው ነበር፤ እርሱም ሊያድናቸው ፈቃደኛ ነበር። ጴጥሮስ በሁለቱም ደብዳቤዎቹ ውስጥ ንስሐ የሚለውን ቃል የተጠቀመበት ስፍራ ይህ ብቻ ነው፤ ነገር ግን ይህ የንስሐን አስፈላጊነት አያሳንሰውም። ንስሐ ማለት «አሳብን መቀየር» ማለት ነው። «መጸጸት» ማለት ግን ብዙውን ጊዜ «በጥፋቴ ስለተጋለጥኩኝ አዝኛለሁ» እንደማለት ነው። እንደዚሁም «ማዘን» ማለት ወደ ተስፋ መቁረጥ የሚመራ ተስፋ የመቁረጥ አመለካከት ነው።

ንስሐ በፈቃደኝነት ድርጊት ላይ የተመሠረተ አሳብን የመለወጥ ድርጊት ነው። ኃጢአተኛው በቅንነት ስለ ኃጢአት ያለውን አሳቡን ከቀየረ፥ ከኃጢአት ይመለሳል። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን አሳብ በእውነት ከቀየረ፥ ወደ እሱ ይመለሳል፤ ያምነዋል፤ ስለዚህም ይድናል። «ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሐንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን» (የሐዋ. 20፡21) እግዚአብሔር ያዘጋጀው የመዳኛ መንገድ ነው።

በ2ኛ ጴጥሮስ 3፡9 ውስጥ «እንዲደርሱ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ቦታ እንዲኖራቸው» የሚለውን ትርጉም ያቀፈ ነው። በዮሐንስ 2፡6 እና 21፡25 እንደተጠቀሰው «ቦታንና ስፋትንም» ያመለክታል። የጠፋው ኃጢአተኛ ትዕቢቱን በማስወገድና የእግዚአብሔርን ቃል በትሕትና በመቀበል በልቡ ለንስሐ «ስፍራ» ያስፈልገዋል። ንስሐ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው (የሐዋ. 11፡18፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡25)፤ ያላመነው ሰው ግን ስጦታውን የሚቀበልበትን ቦታ ማዘጋጀት አለበት።

የጴጥሮስን መከራከርያ ነጥቦች ስትመረምሩ ማስረጃውን ለመቃወም የማይቻል እንደሆነ ትረዳላችሁ። ዘባቾቹ ግን በኃጢአታቸውና በፈዛቸው መቀጠል ስለፈለጉ ያቀረበውን ማስረጃ እንዳልተቀበሉ አመልክቷል። ከመጻሕፍት በመጥቀስ ባለፈው ታሪክ እግዚአብሔር ጣልቃ እንደገባ ማስረጃ አቅርቧል። ዛሬም ያንኑ ሊያደርግ ሥልጣን እንዳለው አስረግጧል። ዘባቾቹ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ በጣም ዝቅ ያለ ግንዛቤ እንዳላቸው አሳይቷል፤ ምክንያቱም ልክ ሰዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ እግዚአብሔርም በተመሳሳይ

ሁኔታ የተስፋ ቃሎችን በመጠበቅ የሚዘገይ ስለሚመስላቸው ነው። በመጨረሻም ጴጥሮስ፥ እግዚአብሔር በሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደማይኖርና የሱ «መዘግየት» ለጠፉ ኃጢአተኞች ንስሐ እንዲገቡና እንዲድኑ የበለጠ ዕድል ለመስጠት እንደሆነ አስረድቷል።

የሐሰት መከራከሪያቸውን ካጨናገፈ በኋላ ጴጥሮስ የጌታን ቀን መምጣት እርግጠኝነት በድጋሚ አረጋግጧል። መቼ ነው የሚመጣው? መቼ እንደሆነ ማንም አያውቅም፤ ምክንያቱም «ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ» ወደ ዓለም ይመጣልና። ጌታችን ይህንን ሐረግ ተጠቅሞበታል (ማቴ. 24፡43፤ ሉቃስ 12፡39)፤ እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ (1ኛ ተሰ. 5፡ ቁ2 ጀምሮ)። «ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ፥ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም» በማለት ገልጾታል (1ኛ ተሰ.5፡3)።

ይህ ቀን መቼ እንደሚሆን ባናውቅም፥ በዚያን ቀን ምን እንደሚፈጸም ግን ተነግሮናል። ኬኔት ዊስት የእነዚህን ቃላት ትክክለኛ እና ሥዕላዊ ትርጉም ይሰጠናል፡- «ሰማይና ምድር በፈጣንና ኃይለኛ ጩኸት ይቀልጣሉ፥ በውስጣቸውም ያሉ ነገሮች ሁሉ በእሳት ተቃጥለው ይጠፋሉ፥ እንዲሁም ምድር እና በውስጧ ያለው ሥራ ሁሉ ይቃጠላል» (2ኛ ጴጥ. 3፡10)

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ጴጥሮስ እዚህ ጋ የጠቀሰው የአውቶሚክ ኃይል በእግዚአብሔር ሲለቀቅ የሚሆነውን ድርጊት የሚያሳይ ነው ብለው ያምናሉ። «ታላቅ ጩኸት» የሚለውን ቃል ከከባድ የነፋስ ፉጨትና ከምድር ንቃቃት ድምፅ ጋር አመሳስለውታል። የመጀመሪያው አቶሚክ ቦምብ በኔቫዳ በረሀ ሲሞከር «የፉጨት መሳይ ድምፅ» ወይም «የንቃቃት ድምፅ» እንደተሰማ የተናገሩ ብዙዎች ናቸው። ጴጥሮስ የተጠቀመበት የግሪኩ ቃል ሕዝቡ በተለምዶ የወፎችን ክንፍ መርገብገብ ወይም የእባብን ድምፅ ለመግለጥ ይጠቀሙበት የነበረው ነው።

በቁጥር 10 ላይ ይቀልጣል የሚለው ቃል «መበታተን፥ መሟሟት» ማለት ነው፤ ይህም የአንድ ነገርን ተበታትኖ መሰባበርና ወደ መሠረታዊ ንጥረ ነገሮቹ መመለስን ያመለክታል። የአቶሚክ ኃይል ሲለቀቅ ደግሞ ፍንዳታው የሚያስከትለው ውጤት ይህን የመሰለ ነው። ጌታችን «ሰማይና ምድር ያልፋሉ» ብሏል (ማቴ. 24፡35)። ይህም ዓለም በተሠራችበት

ንጥረ ነገሮች ውስጥ የተጠራቀመው የአቶሚክ ኃይል ሲለቀቅ ሊሆን የሚችል ይመስላል፤ ነገር ግን ኬኔት ዊስት የተባለ ሰው 2ኛ ጴጥሮስ 3፡7ን እንደተረጎመው ሰማይና ምድር «በእሳት ተዳፍነዋል»። ይህንን የተዳፈነ እሳት ሊያቀጣጥለው የሚችለው ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ኃጢአተኛ ሰዎች መሬትን በማያጠፉ የአቶሚክ ጦርነት ውስጥ እንዲገቡ ይፈቅዳል ብዬ በግሌ አላምንም። ከፖለቲካ ሰዎችና ከሚያምኑ ዲፕሎማቶች ሞኝነትና አለማወቅ በላይ የሆነው እርሱ ራሱ እግዚአብሔር አዲስ ሰማይንና ምድርን ለማስገኘት «ቁልፉን ለመጫን» እና ንጥረ ነገሮቹን ለማጥፋት ሥልጣንና መብት አለው ብዬ በበኩሌ አምናለሁ። ጴጥሮስ እነዚህን ቃላት ሲጽፍ እንደ ኢሳይያስ 13፡10-11፤ 24፡19፤ 34፡4 እና 64፡1-4 የመሳሰሉትን የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች በአእምሮው ይዞ እንደሆነ ጥርጥር የለውም። የመጀመሪያው ምንባብ በተለይ ፍርድን የሚያመጣው እግዚአብሔር እንጂ ኃጢአተኛው ሰው እንዳልሆነ ያመለክታል። እግዚአብሔር «እንዲሁም እኔ ዓለምን ስለ ክፋትዋ እቀጣለሁ፥ ክፉዎችንም ስለመተላለፋቸው እቀጣለሁ» ይላል። ስለዚህ ይህን የመሰለው ከባድ ኃላፊነት ለአንድ ቅብጥብጥ ወታደራዊ መሪ ወይም ለአንድ ቁጡ ፖለቲከኛ የሚሰጥ አይመስልም።

በእርግጥ ይህ ታላቅ ፍንዳታና የሚያስከትለው ቃጠሎ እግዚአብሔር የሚኖርበትን «ሰማየ ሰማያት»ን አይነካም። እኛ ሕዋ ብለን የምናውቀውን ምድርንና በዙሪያው ያለውን የከባቢ አየር ሰማይ ያጠፋል፤ ይህም ለአዲስ ሰማይና ምድር ቦታ ያስለቅቃል (2ኛ ጴጥሮስ 3፡13፤ ራእይ 21፡1 ጀምሮ)።

የሰው ልጅ ታላላቅ ሥራዎችም ይቃጠላሉ! የሰው ልጅ የሚኮራባቸው ነገሮች በሙሉ - ታላላቅ ከተሞቹ፥ ታላላቅ ሕንጻዎቹ፥ ታላላቅ ፈጠራዎቹና ግኝቶቹ በአንድ ጊዜ ይጠፋሉ። ኃጢአተኞች በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ሲቆሙ ለታላቅነታቸው የሚያቀርቡት ማስረጃ ምንም ነገር አይኖራቸውም። ሁሉም ነገር ይጠፋል።

ይህ በእርግጥ የከበረ እውነት ነውና በግዴለሽነት መንፈስ ልናጠናው አይገባንም። በዚህ ደብዳቤ ቀሪዎቹ ቁጥሮች ውስጥ ጴጥሮስ ይህንን እውነት ከዕለት ተዕለት ኑሮዋችን ጋር ያዛምደዋል። እዚህ ላይ ቆም ብለን

እግዚአብሔር ይህን ዓለም ሲያጠፋ ስፍራዬ የት ይሆን? እኔ የምኖረው ከአውቶሚኪ አቧራ ጋር በንፍ ለመቅረት ነው? ወይስ ሥራዬ እርሱን ለዘላለም ያስከብረው ዘንድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረግሁ ነው? በማለት ራሳችንን መጠየቅ ትልቅ ማስተዋል ነው።

ስለዚህ ጊዜው ሳይዘገይ አሁኑኑ ስለምርጫህ ወስን!

# ትጉ ሁን!

## 2ኛ ጴጥሮስ 3፡ 11-18

የትንቢታዊ እውነት ዓላማ ግምታዊ አስተሳሰብ ሳይሆን ለአንድ ነገር ማነሣሣት ነው፤ ስለዚህም ጴጥሮስ ሁላችንም ልናደምጣቸው በሚገቡን ተግባራዊ ምክሮች ነው ደብዳቤውን የደመደመው። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች ወደሚብራሩባቸው የተለያዩ ጉባኤዎች ይሄዳሉ፤ የሚያገኙትንም አሳብ በማስታወሻቸው ያሰፍራሉ፤ ማስታወሻ ደብተራቸውን ሲሞሉ፥ መጽሐፍ ቅዱሳቸው ላይ ምልክት ሲያደርጉና ሰንጠረዥ ሲሥሉ ይገኛሉ። ሆኖም ግን ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር ክብር አለማኖራቸው በጣም የሚያሳዝን ነው። እንዲያውም አንዳንድ ክርስቲያኖች ከሌላ ርእስ ይልቅ ምናልባትም በበለጠ ሁኔታ በትንቢታዊ ቃሎች አተረጓጐም ላይ እርስ በርሳቸው ሲጋጩ ይታያሉ።

እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ እንደሚመጣ ያምናሉ። አንዳንድ የተወሰኑ ትንቢቶች መቼ እንደሚከሠቱ ባላቸው አመለካከት ላይ ሊለያዩ ቢችሉም፥ ቃል በገባው መሠረት እንደሚመለስ ሁሉም ያምናሉ። በተጨማሪም ክርስቲያኖች ሁሉ በሚመጣው ክብር ላይ የተመሠረተው እምነት ቤተ ክርስቲያንን ማነሣሣት እንዳለበት ይስማማሉ። አንድ መጋቢ «ስለ ጌታ ምጽአት ብዙ አጠያያቂ ባልሆኑ ነገሮች ተከራክሬያለሁ፤ አሁን ግን ዋናው የስብከቴ ዓላማ ሰዎች ለእርሱ ምጽአት እንዲዘጋጁ ማድረግ ነው» ሲል ተናግሯል። ይህም ማለት ትንቢትን ማጥናት ማቆም አለብን ወይም ሁሉም ተቃራኒ አመለካከቶች ትክክል ናቸው ማለት አይደለም፤ ይህ የማይሆን ነገር ነውና። ሆኖም ማንኛቸውንም አመለካከቶች ብንይዝ በሕይወታችን ውስጥ ግን ለውጥ ማምጣት አለባቸው።

«ትጉ!» የሚለው ቃል ጴጥሮስ በዚህ በመዝጊያ አንቀጽ ውስጥ የጻፈውን በሚገባ የሚያጠቃልል ምክር ነው። ይህንን ቃል ከዚህ በፊት በ2ኛ ጴጥሮስ 1 ላይ ተጠቅሞበታል፡- «ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ ... ጨምሩ» (ቁ. 5)፤ «መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ» (ቁ. 10)፤ «ትችሉ ዘንድ እተጋለሁ» (ቁ. 15)። የተሳካልን ክርስቲያኖች ለመሆን የምንፈልግ ከሆነ ትጉዎች ለመሆን መማር አለብን።

ጴጥሮስ ከጌታችን መመለስ ጋር በተያያዘ የአንባቢዎቹን ክርስቲያናዊ ትጋት ለማበረታታት ሦስት ምክሮችን ሰጥቷል።

## እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት ለመኖር ትጉ

## (2ኛ ጴጥሮስ 3፡ 11-14)

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ቁልፉ ቃል«መጠበቅ» ነው። ይህም «ናፍቆትንና ጉጉትን» የሚያመለክት ነው። ቃሉንም በሉቃስ 3፡ 15 «ሕዝቡም ሲጠብቁ ሳሉ» እና በ የሐዋ. 3፡5 «አንድ ነገር ከእነርሱ እንዲቀበል ሲጠብቅ» በሚሉት ላይ ታገኙታላችሁ። የጌታችንን መመለስ ስንጠብቅ የሚኖረንን ናፍቆትና ጉጉት ያመለክታል። ዓለምና ሥራዎቹ ይጠፋሉ፤ እንዲሁም እያንዳንዳቸው ንጥረ ነገሮች እንደሚበታተኑ ስለምናውቅ፥ ተስፋችንን በዚህ ዓለም ባለ ማንኛውም ነገር ላይ ሳይሆን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ብቻ እናደርጋለን።

የጌታችንን መመለሻ ቀንና ሰዓት ስለማናውቅ ሁልጊዜ ዝግጁ መሆን አለብን። «የተባረከውን ተስፋ» (ቲቶ 2፡ 13) መዘንጋት የጀመረ አማኝ ቀስ በቀስ ግዴለሽነት፥ ዓለማዊ አመለካከትና ያልታመነ ሕይወት ይኖረዋል (ሉቃስ 12፡ 35-48)። እርሱም እስካልተጠነቀቀ ድረስ እንደ ዘባቾቹ ሁሉ፥ በክርስቶስ መምጣት ተስፋ ቃል ሊቀልድ ይችላል።

ይህ የመጠባበቅ ሁኔታ በግል ሕይወታችን ወይም ጠባያችን ላይ ለውጥ ማምጣት አለበት (2ኛ ጴጥሮስ 3፡ 11)። ጠባይ የሚለው ቃል ቀጥታ ትርጉሙ «እንግዳ ነገር፥ ከዚህ ዓለም ያልሆነ፥ ያልተለመደ» እንደማለት ነው። «በዓለም ካለው ጥፋት ስላመለጥን» (1፡4)፥ በዓለም ካለው ሕዝብ በተለየ ሁኔታ መኖር አለብን። ለእነርሱ «ከሌላ ዓለም እንደመጣ ሰው» መሆን አለብን። ለምን? ምክንያቱም ይህ ዓለም ቤታችን ስላልሆነ ነው! የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ከተማ ወደሆነው የተሻለ ዓለም የምናመራ «እንግዶችና መጻተኞች» ነን (1 ጴጥ. 2፡ 11)። ክርስቲያኖች፥ በባዕድ ጠባያቸው ሳይሆን በመልካም ኑሯቸው የተለዩ መሆን አለባቸው። ልዩ ስትሆኑ ሰዎችን ትስባላችሁ፤ ባዕዳን ስትሆኑ ግን ታርቁዋቸዋላችሁ።

ጠባያችን በቅድስናና እግዚአብሔርን በመምሰል ከሌሎች መለየት አለበት። «ዳሩ ግን፡- እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ»

(1ኛ ጴጥሮስ 1፡15-16)። ቅዱስ የሚለው ቃል «መለየት፥ መገለል» ማለት ነው። እስራኤል «ቅዱስ ሕዝብ» ነበረ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከአሕዛብ መካከል አይሁድን ለይቶ አስቀምጧቸው ስለነበረ ነው። ክርስቲያኖች በዙሪያቸው ካለው እግዚአብሔርን ከማያውቅ ዓለም ተለይተው የተጠሩና ለእግዚአብሔር ብቻ ተገልለው የተቀመጡ ናቸው።

እግዚአብሔርን መምሰል የሚለው ቃል «ሃይማኖተኛ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡6-7 ውስጥ የምናገኘው «መንፈሳዊነት» የሚለው ቃል ከዚህ ቃል ጋር አንድ ዓይነት ነው፤ የዚህ ዓይነት ሰው እግዚአብሔርን ለማስደሰት የተሰጠ ሰው ሕይወት ማለት ነው። ምናልባትም ከኃጢአት በአጋጣሚ ምክንያት ለመለየት ይቻል ይሆናል። ይሁን እንጂ ይህን ማለት ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወት መምራት ማለት አይደለም። በግሪኩ ዓለም እግዚአብሔርን መምሰል ማለት «ዓለምን ፈጥረዋል የሚባሉትን ጣዖታትና ፍጥረታቸውንም በፍርሃት ዓይን ማየትና ማክበር» ማለት ነው። መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ «እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» (ዮሐ. 3፡30) ሲል ከገለጠው ዓይነት አክብሮት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነበር።

ለጌታ ዳግም መመለስ የሚኖረን ናፍቆት ግን፥ በቅድስና ሕይወት እንድንኖር ሊያነሣሣን እንደሚገባ ሌሎችም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ጭምር ያስተምሩናል (ሮሜ 13፡11-14፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡1-11፤ ፊልጵ. 3፡17-21፤ 1ኛ ተሰ. 5፡1-11፤ ቲቶ 2፡11-15፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡28-3፡3 ተመልከት)። ሆኖም ሕይወትን የሚያነሣሣው ትምህርቱን በአእምሮ ማወቅ ብቻ አይደለም፤ በልብ ውስጥ መያዝና መገለጡን መውደድ ነው እንጂ (2ኛ ጢሞ. 4፡8)።

ይህ የመጠባበቅ ሁኔታ ለውጥ ማምጣት ያለበት በጠባያችን ብቻ ሳይሆን በምስክርነታችንም ጭምር መሆን አለበት። «እየጠበቃችሁና እያስቸኮላችሁ» የሚለው ሐረግ «የእግዚአብሔርን ቀን መጠባበቅና እንዲመጣ ማስቸኮል» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ጴጥሮስ የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ ማስቸኮል እንደምንችል ያረጋግጣል።

ማስቸኮል ተብሎ የተተረጎመው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሌሎች አምስት ቦታዎች እንደተጠቀሰው «ማፋጠን» ማለት ነው። እረኞቹ

«ፈጥነው መጡ» (ሉቃስ 2፡16)፤ ኢየሱስ ለዘኬዎስ «ፈጥነህ ውረድ» አለው «ፈጥኖም ወረደ» (ሉቃስ 19፡5-6)፤ ጳውሎስ «በኢየሩሳሌም ይውል ዘንድ ይቸኩል ነበረ» (የሐዋ. 20፡16)፤ ጌታም ለጳውሎስ «ፍጠን ከኢየሩሳሌምም ቶሎ ውጣ» አለው (የሐዋ. 22፡18)። ይህንን ቃል «በናፍቆት መጠበቅ» ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ማድረግ ማለት ጴጥሮስ ቀደም ሲል የተናገረውን አሁንም በ2ኛ ጴጥሮስ 3፡12 ላይ ደግሞታል እንደማለት ነው።

በአገልግሎታችን ውስጥ ማስወገድ ያለብን ሁለት የተሳሳቱና ተቃራኒ የሆኑ አቋሞች አሉ። አንደኛው፥ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ዕቅድ ብቻ አስበን እኛ የምናደርገው ማናቸውም ነገር ምንም ለውጥ አያመጣም የሚለው ሲሆን፥ ሌላኛው አቋም ደግሞ እኛ ካላደረግነው በስተቀር እግዚአብሔር ምንም ነገር ሊያደርግ እንደማይችል ማሰብ ነው! የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ውሳኔዎች ለስንፍና ምክንያት መሆን ፈጽሞ እንደሌለባቸው ሁሉ፥ በሌላም በኩል የእኛ ዕቅዶችና ድርጊቶች የእርሱን ቦታ መውሰድ የለባቸውም።

ምናልባት ከብሉይ ኪዳን ታሪክ ሁለት ምሳሌዎችን ብንጠቅስ በእግዚአብሔር ዕቅዶችና በሰው አገልግሎት መካከል ስላለው ግንኙነት በበለጠ እንድንረዳ ሊረዱን ይችላሉ። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ አውጥቶ ርስታቸው በሆነው የከነዓን ምድር ሊያስቀምጣቸው እንደፈለገ ለሕዝቡ ነገራቸው፤ ነገር ግን ቃዴስ በርኔ ሲደርሱ ከሙሴ፥ ከኢያሱና ከካሌብ በስተቀር ሁሉም በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ ወደ ምድሪቱ ለመግባት አልፈለጉም (ዘኁ. 13-14)፤ ግን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር እንዲገቡ አስገድዷቸው ነበር? አላስገደዳቸውም። በዚያ ፈንታ ያ ዓመፀኛ ትውልድ ሞቶ እስኪያልቅ ድረስ ለሚቀጥሉት አርባ ዓመታት በምድረበዳ እንዲቅበዘበዙ አደረጋቸው። ዕቅዱን ከእነርሱ ምላሽ ጋር አስተካከለ።

ዮናስ ለነነዌ ሕዝቦች ሲሰብክ መልእክቱ ግልጽ ነበረ፡- «በአርባ ቀን ውስጥ ነነዌ ትደመሰሳለች» አለ (ዮናስ 3፡4)። ዓመፀኛይቱን ከተማ ለማጥፋት የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበረ፤ ነገር ግን ከንጉሡ ጀምሮ እስከ ተራው ሰው ድረስ ሕዝቡ ንስሐ ሲገባ እግዚአብሔር ዕቅዱን አስተካከለና ከተማይቱን ሳያጠፋት ቀረ። እግዚአብሔርም ሆነ መሠረታዊ መመሪያዎቹ አልተለወጡም፤ እነዚያን መመሪያዎች ተግባራዊ የማድረጉ ሁኔታ ግን

ተለውጧል። ሰዎች ንስሐ ሲገቡ እግዚአብሔር ለዚያ የሚገባውን ምላሽ ይሰጣል።

ታዲያ እኛ እንደ ክርስቲያንነታችን የጌታን ቀን መምጣት ማፋጠን የምንችለው እንዴት ነው? ለዚህ የምንሰጠው አንዱ መልስ ኢየሱስ እንዳስተማረን «መንግሥትህ ትምጣ» ብለን በመጸለይ ነው የሚለው ይሆናል (ማቴ. 6፡10)። ከራእይ 5፡8 እና 8፡3-4 የእግዚአብሔር ሕዝብ ጸሎት በሕዝቦች ላይ ከሚፈሰው የእግዚአብሔር ቁጣ ጋር በሆነ መንገድ የተያያዘ ይመስላል።

የዛሬው ዘመን የእግዚአብሔር ሥራ ለስሙ የሚሆንን ሕዝብ መጥራት እስከሆነ (የሐዋ. 15፡14)፥ የቤተ ክርስቲያን በቶሎ መጠናቀቅ የጌታን መመለስ ያጣድፈዋል ማለት ነው። የዚህ እውነት ይህን የሚያመለክት ጥቅስ በሐዋ. 3፡19-21 ላይ አለ። እንደዚሁም ምንም እንኳ ማቴዎስ 24፡14 በመጀመሪያ ደረጃ የሚነግረን ስለ ዘመን ፍጻ ቢሆንም መንፈሱ ግን አንድ ነው፡- ቃል የተገቡ ትንቢቶች እንዲፈጸሙ የሰው አገልግሎት ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር መተባበር አለበት።

እዚህ ላይ አእምሯችን ሙሉ በሙሉ ሊረዳቸው ወይም ሊገልጻቸው የማይችሉ ምሥጢሮች አሉ፤ መሠረታዊው ትምህርት ግን ግልጽ ነው። መጨረሻውን ያዘጋጀው ያው አንዱ እግዚአብሔር ወደ መጨረሻ የሚያደርሰውንም መፍትሔ ያዘጋጃል፤ እኛ ደግሞ የዚያ መፍትሔ አንድ ክፍል ነን። የኛ ተግባር በሰው ሠራሽ መላ-ምት መወናበድ ሳይሆን ማገልገል ነው።

በመጨረሻም ይህ የመጠባበቅ ሁኔታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስንገናኘው ለውጥ ያመጣል (2ኛ ጴጥሮስ 3፡14)። ይኸውም «በሰላም» ስለሚቀበለን «በመምጣቱ በእርሱ ፊት እንዳናፍር» በእኛ ላይ ምንም ክስ አይመሠርትብንም (1ኛ ዮሐ. 2፡28)። የክርስቶስ የፍርድ ወንበር መዘርጋቱ የሚያሳስብ ነውና (2ኛ ቆሮ. 5፡8-11) በዚያን ዕለት ስለ ሥራችን ለእርሱ መልስ እንሰጣለን (ሮሜ 14፡10-13)። በቃሉ ከሚዋጋን ይልቅ «በሰላም» ብንገናኘው ይሻላል (ራእይ 2፡16)።

መመለሱን ለመጠባበቅና ቅዱስና እግዚአብሔርን የሚመስል ሕይወት ለመኖር ትጉ ከሆንን አንፈራም ወይም አናፍርም። ያለ «እድፍና ነውር»

እንገናኘዋለን። ኢየሱስ ክርስቶስ «ነውርና እድፍ እንደሌለው በግ» ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡19)፤ እኛም በጥንቃቄ ምሳሌውን መከተል ይኖርብናል። ጴጥሮስ መናፍቃን ስለሚያመጡት ርኩሰት አንባቢዎቹን አስጠንቅቋል። «ርኩሳንና ነውረኞች ሆነው» (2ኛ ጴጥሮስ 2፡13) በማለት ገልጦአቸዋል። የተለየው ክርስቲያን በሐሰተኛ አስተማሪዎች አንደበት «እንዲነወርና እንዲነቀፍ» አይፈቅድላቸውም! ጌታውን መገናኘት የሚፈልገው ንጹሕ ልብስ ለብሶ ነው።

ይህንን ወደ ቅድስና ሕይወት የሚመራውን የጉጉት መጠባበቅ እንዴት ነው የምንኖረው? «የተስፋ ቃሉን» በልባችን በመጠበቅ ነው (3፡13)። የመምጣቱ ተስፋ በዚህ በጨለማ ዓለም የሚያበራ መብራት ነው (1፡19)፤ መገለጡንም ስለምንወድ «የንጋቱ ኮከብ» በልባችን ውስጥ እንደሚያበራ እርግጠኞች መሆን አለብን።

## የጠፉትን ወደ ጌታ ለማምጣት ትጉ
(2ኛ ጴጥሮስ 3፡15-16)

ቁጥር 15 እና ጌታ የተስፋ ቃሉን ለመፈጸም ለምን እንደዘገየ ያብራራበት ቁጥር 9 የተያያዙ ናቸው። እግዚአብሔር ከረጅም ጊዜ በፊት እንኳ ዓለምን ለመፍረድና ስፍራውንም ለማቃጠል የሚያስችሉት ብዙና በቂ ምክንያቶች ነበሩት፤ ዳሩ ግን በምሕረቱ «ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ» ስለሚወድድ እየታገሠን ነው። አሁንም ያለንበት የመዳን ቀን ነው እንጂ የፍርድ ቀን አይደለም።

ጴጥሮስ ከጳውሎስ ጽሑፎች ጠቅሷል፤ ምክንያቱም ከሌላ ከማንኛውም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊ ይልቅ በዚህ ባለንበት ዘመን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ዕቅድ በበለጠ ያብራራው ጳውሎስ በመሆኑ ነው። በተለይም በሮሜና በኤፌሶን መልእክቶቹ ጳውሎስ በእስራኤልና በቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው ግንኙነት አብራርቷል። እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ለአዳኙ መምጣት መንገድ ጠራጊ በማድረግ እንደተጠቀመበት ጠቁሟል። እስራኤል ግን የራሱን ንጉሥ አልተቀበለም፤ እንዲያውም እንዲሰቀል አደረገ። ታዲያ ይህ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ማሰናከል ችሎ ነበርን? በፍጹም! ዛሬ፥ እስራኤል ብሔራዊ ሕልውና አግኝታለች። ሆኖም እግዚአብሔር ግሩም የሆነ አዲስ ነገር እያደረገ ነው፡- አይሁድንና አሕዛብን እያዳነና በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት አንድ እያደረጋቸው ነው!

በቀደሙት ዘመናት አንድ አሕዛብ መዳን ከፈለገ እግዚአብሔርን በእስራኤል በኩል መቅረብ ነበረበት። ይህም አመለካከት በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ እንኳ የጸና ነበረ (የሐዋ. 15)። ጳውሎስ ግን አይሁድም አሕዛብም በእግዚአብሔር ፊት የተከነኑ ሆነው እንደሚቆሙና ሁለቱም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ብቻ መዳን እንዳለባቸው ግልጥ አድርጎታል። በኢየሱስ ክርስቶስ የዳኑ አይሁድና አሕዛብ የአንድ አካል ማለትም የቤተ ክርስቲያን አባላት ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ዘንድ ተደብቃ የነበረችና በኋላም በአዲስ ኪዳን ነቢያትና ሐዋርያት የተገለጠች «ምሥጢር» ናት (ኤፌሶን 3 ን ተመልከት)።

የአይሁድ ሕዝብ ለሕገ እግዚአብሔር ታላቅ ምስክር ቢሆንም፥ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ለጸጋው ምስክር ናት (ኤፌ. 1-2 ን ተመልከት)። ሕግ ለጸጋ መንገድን አዘጋጅቷል፤ ጸጋ ደግሞ የሕግን ጽድቅ እንድንፈጽም ያስችለናል (ሮሜ 8፡1-5)። ይህን ማለት ደግሞ በአሮጌው ኪዳን ሥር ጸጋ አልነበረም ወይም የአዲስ ኪዳን አማኞች ሕግ አልባ ናቸው ማለት አይደለም! ሮሜ 4 እና ዕብራውያን 11 ግልጥ እንደሚያደርጉልን በሕግ አስተዳደር ሥር የዳነ ማንም ሰው በእምነት በኩል በጸጋ የዳነ ነበረ።

ይሁን እንጂ ላልተማሩና የመንፈስ ጥንካሬ ላልነበራቸው ሰዎች የጳውሎስን ትምህርቶች ለመረዳት ይከብዳቸው ነበር። ሌላው ቀርቶ የተማሩና በእምነታቸው የዳኑ እንዲሁም መንፈሳዊ መለየት ያላቸው ሰዎች እንኳ እንደ ሮሜ 9-11 ያሉትን ታላላቅ ምንባቦች ለመረዳት ያስቸግራቸው ነበር። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የሚቃረኑ የሚመስሉ አሳቦችን ለምሳሌ (ሕግና ጸጋ፥ እስራኤልና ቤተ ክርስቲያን፥ እምነትና ሥራ) «ለማስማማት» መጻሕፍትን ያጣምሙና ያልተባለውን ነገር ለመፍጠርና ለማስተማር ይፍጨረጨራሉ፤ ይታገላሉም። «መታገል» የሚለው የግሪክ ቃል ሲተረጎም «ማሠቃየት፥ ማበላሸትና ማጣመም» መሆኑንም ይዘነጋሉ።

በጳውሎስ ጊዜ እንኳ ቃሎቹን የሚያጣምሙና አለማስተዋላቸውን ለመሸፋፈን የሚሞክሩ ነበሩ። በጸጋ እስከ ዳንን ድረስ እንደ ፈለግነው ብንኖር ለውጥ አያመጣም ብሎ ጳውሎስ እንዳስተማረ አድርገው ይከሱት ነበር። ጳውሎስ «መልካም እንዲመጣ ክፉ እናድርግ» (ሮሜ 3፡8ን ከሮሜ 6፡1 ጀምሮ ያለውን አነጻጽር) ብሎ እንዳስተማረ በማስመሰል ሐሜት ያናፍሱ

ነበር። ሌሎች ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአይሁድንና የአሕዛብን እኩልነትና (ገላ. 3፡28) በክርስቶስ ስላላቸው አርነት ስላስተማረ ጳውሎስ ሕግን እንደተቃወመ አድርገው ከሰሰውታል።

ለብዙ የመናፍቃን ቡድኖች ማቆጥቆጥ ዋናው ምክንያት ተጣምመው የቀረቡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች ናቸው። የሐሰት አስተማሪዎች ጥቅሶችን ከዐውደ ምንባባቸው አውጥተው፥ መጻሕፍትን አጣምመው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረኑ ትምህርቶችን ይፈጥራሉ። ጴጥሮስ ይህን ሲጽፍ በተለይ ለሐሰተኛ አስተማሪዎች በማለም ነው ብንልም፥ ማስጠንቀቂያው ግን ለሁላችንም ይጠቅማል፤ ስለዚህ የመጻሕፍትን ትምህርት መቀበል እንጂ በየግላችን እንዲሉ የምንፈልገውን እንዲሉ ለማድረግ መሞከር የለብንም።

እዚህ ላይ ጴጥሮስ የጳውሎስን ደብዳቤዎች እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ማለትም በመንፈስ ተመርቶ እንደተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል እንደመደበው ልናስታውስ ይገባል። የሐዋርያት ትምህርት የተስማማው ከነቢያትና ከጌታችን ትምህርት ጋር ብቻ ሳይሆን (2ኛ ጴጥሮስ 3፡2) ሐዋርያትም እርስ በርሳቸው ስምምነት ነበራቸው። አንዳንድ ዘመናዊ ምሁራን የሐዋርያት ትምህርት ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት የተለየ እንደነበረ ወይም ጴጥሮስና ጳውሎስ እርስ በርሳቸው ልዩነት እንደነበራቸው ለማሳየት ይሞክራሉ። የጴጥሮስን ሁለተኛ ደብዳቤ የተቀበሉ ሰዎች ከጳውሎስ መልእክቶችም አንዳንዶቹን አንብበው ነበር፤ ጴጥሮስ ደግሞ በሁሉቱ መካከል ስምምነት እንዳለ አረጋግጦላቸዋል።

መጻሕፍትን በጭፍን የሚያጣምሙ ሰዎች ምን ይሆናሉ? «ለራሳቸው መጥፊያ ያደርጉታል።» ጴጥሮስ የጻፈው የእግዚአብሔርን ቃል ለመተርጎም ችግር ስላለባቸው ክርስቲያኖች አልነበረም፤ ምክንያቱም ለማንም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉና በፍጹምነት መረዳት ስለሚያዳግት ነው። የጴጥሮስ ዓላማ የሐሰት ትምህርታቸውን ለማስረዳት የእግዚአብሔርን ቃል «የሚያሠቃዩትን» አወናባጅ አስተማሪዎችን ለማጋለጥ ነበር። አንድ ጊዜ አንድ ለየት ያለ «የመናፍቃን ቡድን» አባል የሆነ ሰው በዳንኤል 9፡23-27 ላይ የሚገኘውን «ሱባዔ» የሚለውን ቃል እንደፈለገ በመተርጎም የቡድኑን መሪ «አዲሱ መሢሕ» ነው በማለት «ሊያሳምን» ሲሞክር ሰማሁ። ትንቢቱን ያለምሕረት ነበር የሚያጣምመው!

ጥፋት የሚለው ቃል በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሟል (2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 1-3፤ 3፡7፥ 16)። የዚህ ውጤት የዘላለም ሞት ነውና፥ ይህን ማድረግ የዘላለምን ሕይወት አለመፈለግ ማለት ነው።

ዳሩ ግን ይህ የእኛ ዘመን የመዳን ቀን ነውና የጠፉትን ወደ ጌታ ለመመለስ የተቻለንን ለማድረግ መትጋት አለብን። ጌታ ለዚህ ክፉ ዓለም ለምን ያህል ጊዜ «እንደሚታገሥ» አናውቅም። ጸጋውን በቸልታ መመልከት የለብንም። ለዚህ ላለንበት ዘመን እግዚአብሔር ስላለው ዕቅድ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን መረዳት አለብን፤ እንዲሁም ለጠፉት ያለንን ፍቅር በማሳየት ጌታን በሚመለስበት ጊዜ ደስ የምናሰኘው ለመሆን ቆርጠን መነሣት አለብን (2ኛ ቆሮ. 5፡ 14)።

የሐሰት አስተማሪዎች እየበዙና ቤተ ክርስቲያንን በኑፋቄ ትምህርቶቻቸው እየበከሉ ናቸው። እግዚአብሔር እነዚህን የሚቃወሙ፥ እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት የሚኖሩና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ጸጋ ምስክሮች የሚሆኑ የተለዩ ወንዶችና ሴቶችን ይፈልጋል። ይህን ለማሟላት ያለን ጊዜ አጭር መሆኑን እንርሳ!

## በመንፈሳዊነት ለማደግ ትጉ (2ኛ ጴጥሮስ 3፡ 17-18)

ጴጥሮስ የሁለተኛው ደብዳቤው መደምደሚያ ወደሆነው ምዕራፍ 3 ማብቂያ ላይ ለማስረዳት የፈለገውን አሳብ ለማጠቃለል አራት ጊዜ «ወዳጆች ሆይ» በሚለው ገለጻ ተጠቅሟል።

«ወዳጆች ሆይ . . . አስቡ» (3፡ 1-2)።

«ወዳጆች ሆይ . . . አትርሱ» (3፡8)።

«ወዳጆች ሆይ . . . ትጉ» (3፡ 14)።

«ወዳጆች ሆይ . . . ተጠንቀቁ» (3፡ 17)።

«ተጠንቀቁ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ሁልጊዜ ራሳችሁን ነቅታችሁ ጠብቁ» ማለት ነው። የጴጥሮስ አንባቢዎች እውነትን ያውቁ ነበር፤ ነገር ግን እውቀት ብቻውን ራስን ለመጠበቅ በቂ እንዳልሆነ አስጠንቅቋቸዋል። ራሳቸውን መጠበቅ ነበረባቸው። ንቁ መሆን ነበረባቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ያላቸው አንዳንድ ሰዎች ከሚገባው በላይ በራሳቸው ወደ

መተማመኑ ደረጃ ስለሚደርሱ፥ «ስለዚህ እንደቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» (1ኛ ቆሮ. 10፡12) የሚለውን ማስጠንቀቂያ በቀላሉ ሲዘነጉት ይታያሉ።

ጴጥሮስ ይህን ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ምን የተለየ አደጋ ታይቶት ይሆን? በግልጥ ታይቶት የነበረው የእውነተኛዎቹ አማኞች «በረከሱ ሰዎች ስሕተት መጠመዳቸው ነው» (ቀጥታ ትርጉሙ)። ስለዚህ በእውነተኛ አማኞችና በሐሰት አስተማሪዎች መካከል ሊኖሩ የሚገባቸውን ገደቦች እንዳናፈርስ እያስጠነቀቀን ነው። በእውነትና በስሕተት መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊኖር አይችልም። እውነተኛ አማኞች በእውነት ክልል ውስጥ ሲኖሩ (2ኛ ዮሐ. 1-2) መናፍቃን ግን «በስሕተት ይኖራሉ» (2ኛ ጴጥሮስ 2፡18)።

ክፉ የሚለው ቃል (2ኛ ጴጥሮስ 3፡17) «ዓመፀኛ» ማለት ነው። በ2ኛ ጴጥሮስ 2 ላይ ስለ መናፍቃን የቀረበው የጴጥሮስ ገለጣ ክፉዎች ምን ያህል ሕግ አልባ እንደሆኑ ያሳያል። የእግዚአብሔርን ሕግ በዚህ ዓለም ላይ ለማስፈን ስለሚጥሩት ባለሥልጣናት እንኳ ክፉ ይናገራሉ! (2፡10-11)። ለተከታዮቻቸው የአርነትን ተስፋ ይሰጧቸዋል (2፡19)፤ ያ አርነት ግን ወደ ሕገ አልባነት የሚመራ ይሆናል።

እውነተኛ ክርስቲያኖች ከደኅንነት ወድቀው ሊጠፉ አይችሉም፤ ነገር ግን ራሳቸውን ለመቆጣጠር ከነበራቸው «ጽናት» ሊዘናጉ ይችላሉ። ይህ «ጽናት» ምንድን ነው? «በእርሱ ዘንድ ባለ እውነት መጽናት» ነው (1፡12)። የክርስቲያን ጽናት የሚመጣው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ካለው እምነት፥ ስለዚያ ቃል ካለው እውቀትና እንዲሁም በተግባራዊ የሕይወት (የኑሮ) ውሳኔዎች ላይ ያንን ቃል ለመጠቀም ካለው ብቃት ነው።

ወንጌልን በማስፋፋት ረገድ ከሚታዩ ታላላቅ ድክመቶች አንዱ «መንፈሳዊ ሕፃናት»ን ካገኙ (ከወለዱ) በኋላ እነርሱን መመገብና ማሳደግ፥ በእንክብካቤም ለመያዝ አለመቻል ነው። መናፍቃን ደግሞ እነኝህን ከስሕተት መንገዶች «በቅርቡ ያመለጡትን» ለጋ አማኞች አሳድደው የራሳቸው ያደርጓቸዋል (2፡18)። አዳዲስ አማኞች (መንፈሳዊ ሕፃናት) የእግዚአብሔርን ቃል መሠረታዊ ትምህርቶች መማር ያስፈልጋቸዋል፤ ካለበለዚያ «ዓመፀኞች በሆኑት ሰዎች ስሕተት አብረው ወደ መንዳት» አደጋ ውስጥ ይወድቃሉ።

እንደ አማኞች ጽናታችንን ለመጠበቅና በቀላሉ መንገዳቸውን ከሚስቱት፥እንደ «ያልጸኑ ነፍሳት» እንዳንሆን እንዴት መከላከል እንችላለን? በመንፈስ በማደግ ነው! «ባለማቋረጥ በማደግ ነው» ማለት ዕድገታችን የሚያቆምና የሚቀጥል ሳይሆን ማደግ ያለብን በማያቋርጥ ሂደት መሆን አለበት ማለት ነው።

«በጸጋ» ማደግ አለብን። ይህ ከክርስትና ባሕርይ ጋር የተያያዘ ነው። እነዚህም ጴጥሮስ በምዕራፍ 1፡5-7 እና ጳውሎስ በገላትያ 5፡22-23 የጻፋቸው ባሕርያት ናቸው። በጸጋ ድነናል (ኤፌ. 2፡8-9)፤ ጸጋ ግን እዚህ ላይ አያቆምም! በጸጋ መበርታትም አለብን (2ኛ ጢሞ. 2፡1-4)። የእግዚአብሔር ጸጋ መከራን እንድንታገሥ ያስችለናል (2ኛ ቆሮ. 12፡7-10)። መስጠት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ እንድንሰጥ (2ኛ ቆሮ. 8፡1)፥ እንዲሁም መዘመር አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ እንድንዘምር (ቆላ. 3፡16) የእርሱ ጸጋ ይረዳናል።

አምላካችን «ለትሑታን ጸጋን የሚሰጥ» (ያዕ. 4፡6) «የጸጋ ሁሉ አምላክ» (1ኛ ጴጥ. 5፡10) ነው። ቃሎቹን ስናጠና እንደ እግዚአብሔር ልጆች ለእኛ ስለ ጸጋ የተሰጡትን የተለያዩ ገለፃዎችን እንማራለን። እኛ «የእግዚአብሔር ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች ነን» (1ኛ ጴጥሮስ 4፡10)። ለእያንዳንዱ የሕይወት ገጽታ የሚስማማና ለሚገጥመን ችግር መፍትሔ የሚያስገኝ ጸጋ አለ። «ነገር ግን እኔ አሁን የሆንሁትን የሆንሁት፥ በእግዚአብሔር ጸጋ ነው» ብሎ ጳውሎስ እንደጻፈው (1ኛ ቆሮ. 15፡10 አዲስ ትርጉም)፥ የእኛም ምስክርነት እንደዚህ መሆን አለበት።

ብዙውን ጊዜ በጸጋ ማደግ ማለት በፈተናና በመከራ ውስጥ ማለፍ ማለት ነው። እኛም አለን የምንለው ኃይል እስካልተሟጠጠ ድረስ የእግዚአብሔር ጸጋ አስፈላጊነት አይታየንም። ምንም እንኳ በ«ጸጋ ትምህርት ቤት» የምንማራቸው ትምህርቶች ሁልጊዜ ውድ ቢሆኑም፥ውድ መሆን ደግሞ ይገባቸዋል። በጸጋ ማደግ ማለት የበለጠ እንደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆን ማለት ነው፤ የሚያስፈልገንን ጸጋ ሁሉ የምንቀበለው ደግሞ ከእርሱ ነው (ዮሐ. 1፡16)።

በእውቀትም ማደግ አለብን። በእውቀት አድጎ በጸጋ ግን አለማደግ እንዴት ቀላል ነው! ሁላችንም ብንሆን እንደሚገባ በሕይወታችን ውስጥ

ባይንጸባረቅም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ እናውቃለን። እውቀት ያለ ጸጋ አደገኛ መሣሪያ ነው፤ እንደዚሁም ጸጋ ያለእውቀት ጥልቀትና ውጤት የሌለው ሊሆን ይችላል። ጸጋንና እውቀትን አንድ ላይ ስናደርግ ግን የራሳችንን ሕይወት ለማነጽና ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት ግሩም መሣሪያ ይኖረናል።

በዚህም ይሁን በዚያ ማደግ እንደሚፈለግብን ማስተዋል አለብን፤ ማደግ ስንል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን በማወቅ ብቻ አይደለም (እጅግ አስፈላጊነቱ ባይካድም)። ከዚሁ ጋር «በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ማደግ አለብን። «መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ» አንድ ነገር ነው፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ አሳብ የሆነውን የእግዚአብሔርን ልጅ ማወቅ ደግሞ ሌላ ነገር ነው። በቃሉ በኩል ክርስቶስን በተሻለ ሁኔታ ስናውቀው፥ የበለጠ በጸጋ እናድጋለን፤ የበለጠ በጸጋ ስናድግ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል በተሻለ ሁኔታ እንረዳዋለን።

ስለዚህ ከዓለም የተለየው ክርስቲያን ሁልጊዜ ራሱን ነቅቶ መጠበቅ አለበት፤ አለበለዚያ ወደ ስሕተት ውስጥ ያመራል። እንደዚሁም በጸጋና በእውቀት ሁልጊዜ ማደግ አለበት። ይህ ደግሞ ትጋትን ይጠይቃል! በሥነ-ሥርዓት የታነጸ ሕይወትና ለዚሁ ጉዳይ ቅድሚያ መስጠትን ይጠይቃል። ማንም ሰው በቅጽበት መንፈሳዊ ዕድገትና ጽናትን አያገኝም፤ ራሱን ለዚሁ ጉዳይ በሰጠበት መጠን ነው የሚያድገው። «ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ፥ በይበልጥ ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል» (ዕብ. 2፡1)። ጀልባ መልሕቅ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ክርስቲያንም የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልገዋል።

የሰውነት ዕድገትና መንፈሳዊ ዕድገት በጣም ብዙ ተመሳሳይነት አላቸው። በመጀመሪያ ማደግ የምንጀምረው ከውስጥ ወደ ውጪ ነው። ጴጥሮስ ይህንን ሲገልጠው «አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት» ብሎታል (1ኛ ጴጥሮስ 2፡2)። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ለዕድገትና ለአገልግሎት ከሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ጋር ነው የተወለደው (2ኛ ጴጥሮስ 1፡3)። የሚያስፈልገውም ለማደግ የሚረዳው መንፈሳዊ ምግብና እንቅስቃሴ ብቻ ነው። ንጽሕናውንም መጠበቅ አለበት። የምናድገው በመመገብ እንጂ፥ ከምግብ በመወገድ አይደለም።

ፍቅር ባለው ቤተሰብ ውስጥ በተሻለ ሁኔታ እናድጋለን፤ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነትም እዚህ ላይ ነው። አንድ ሕፃን ለጥበቃ፥ ለሚያስፈልገው ነገርና፥ ለፍቅር ቤተሰብ ያስፈልገዋል። የአሳዳጊ ልዩ ፍቅር ሳይለገሣቸው ብቻቸውን ያደጉ ሕፃናት፥ ከሌሎቹ ቀደም ብለው አካላዊና ስሜታዊ ችግሮችን የማሳየት አዝማሚያ እንደሚኖራቸው በጥናት ተረጋግጧል። ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች እንክብካቤን የሚያገኙባትና መንፈሳዊ ምግብን የሚያገኙባት የእግዚአብሔር «ማሳደጊያ ቦታ» ናት፤ ለዕድገት የምታበረታታ በእግዚአብሔር የተመረጠች ስፍራ ናት።

ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ማደጋችን አስፈላጊ ነው። ብዙ የተለያዩ የአካል ክፍሎች ተባብረው በመሥራታቸው ነው ሰውነታችን ሚዛኑን ጠብቆ የሚያድገው። «መንፈሳዊው ሰው» ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ማደግ አለበት። ለምሳሌ፥ በጸጋም በእውቀትም ማደግ አለብን (3፡18)። በአምልኮና በአገልግሎት፥ በእምነትና በሥራ መካከል ሚዛን መጠበቅ አለብን። የእግዚአብሔር ቃል የተመጣጠነ ምግብ ነውና ሚዛናዊ ሕይወትን እንድንመራ ይረዳናል።

ነገሮችን በሚዛናዊነት እንድንጠብቅ ኃይልን የሚሰጠንና የሚያስችለን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። ጴጥሮስ በመንፈስ ከመሞላቱ በፊት በተደጋጋሚ ወዲያና ወዲህ የመዋለል አዝማሚያ ነበረው። አንድ ጊዜ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክር እናየዋለን፤ በሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ ከጌታ ጋር ለመከራከር ሲሞክር እናየዋለን! (ማቴ. 16፡13-23)። ኢየሱስ እግሩን እንዳያጥበው ተቃውሞ ነበር፤ ወዲያዉ ግን ሁለንተናውንም እንዲታጠብ ፈለገ! (ዮሐ. 13፡6-10)። ለጌታ ለመከላከል እና ከእርሱ ጋር እንኳ ለመሞት ቃል ገብቶ ነበር፤ ሆኖም በአንዲት ትንሽ የቤት ሠራተኛ ፊት ጌታን ካደ! በመንፈስ በተሞላ ጊዜ ግን በስሜቱ መወላወሉን አስወግዶ፤ ሚዛናዊ ሕይወትን መኖር ጀመረ።

የመንፈሳዊ ዕድገት ውጤት ምንድን ነው? ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን! «ለእርሱ አሁንና ለዘለዓለም ክብር ይሁን።» የእኛ ራሳችንን ከኃጢአትና ከስሕተት መጠበቅ ኢየሱስ ክርስቶስን ያስከብረዋል። በጸጋና በእውቀት ስናድግ ያን ጊዜ የበለጠ እንደ እርሱ ስለምንሆን ያ ያስከብረዋል (ሮሜ

8፡29)። ጴጥሮስ በሕይወቱና ደግሞም በሞቱም ጭምር እግዚአብሔርን አስከበረ (ዮሐ. 21፡18-19)።

ይህንን አስፈላጊ መልእክት በጽሞና ስትከታተሉ፡ በመልእክቱ አስቸኳይነት መነካታችሁ የማይቀር ነው። የሐሰት አስተማሪዎቹ ከእኛም ጋር ቢሆን አብረውን ያሉ ናቸው! በሥራ ይጣደፉሉ! ያልበሰሉ ክርስቲያኖችን እያታለሉ ናቸው! እኛ ግን የጠፉትን ለመመለስና የዳኑቱን ለማጠንከር ማንኛውንም ጥረት እያደረግን ልንጠብቅ፥ ልናድግና ጌታን ልናስከብር ይገባናል።

ትጉ! ከአደጋ የምታድኑት አገልግሎት የእናንተው ይሆናል!

# ታማኝ ቤተሰብ

## 2ኛ የዮሐንስ መልእክት

ሐሰተኞች መምህራን ወረራ ያካሄዱት በአብያተ ክርስቲያናት ላይ ብቻ ሳይሆን በክርስቲያን ቤተሰቦችም ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ሞክረዋል። ይህን የመሰለው ችግር ቲቶን በቀርጤስ ሲያጋጥመው (ቲቶ 1፡10-11)፥ እንደዚሁም ጢሞቴዎስን ደግሞ በኤፌሶን አጋጥሞታል (2ኛ ጢሞ. 3፡6)። የመንግሥትም ሆነ የቤተ ክርስቲያን መሠረቱ ቤተሰብ ነው፤ ስለዚህ ሰይጣን በእውነት ላይ በከፈተው ጦርነት ውስጥ ቤተሰብንም አንዱ ዒላማው አድርጎአል።

ይህ የዮሐንስ አጭር ደብዳቤ ለአንዲት እግዚአብሔርን ለምትፈራ እናትና ለልጆችዋ የተጻፈ ነው። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች፥ «ለተመረጠች እመቤት» የሚለው አንድን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሲጠቅስ «ለልጆችዋ» የሚለው ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኅብረት የሚያደርጉትን ምእመናንን የሚያመለክት ነው ይላሉ። እንደዚሁም «የተመረጠችው እኅት» (2ኛ ዮሐ. 13) የሚለው ክርስቲያናዊ ሰላምታ የምትልከውን ሌላዋን እኅት ቤተ ክርስቲያን የሚያመለክት ነው ይላሉ።

ዮሐንስ በዚህ ደብዳቤ የሚጽፈው ለአንድ ቡድን መሆኑ እውነት የመሆኑን ያህል (በቁጥር 6፥8፥10፥12 ላይ ያለውን ብዙ ቁጥር አስተውሉ)፥ ለአንዲት ግለሰብም እየጻፈ ለመሆኑ በዚያው መጠን እውነት ነው (ቁ. 1፥ 4-5፥ 13)። ምናልባት ለዚህ መፍትሔ የሚሆነን «ከተመረጠችው እመቤት» ቤተሰብ ጋር በመኖሪያ ቤቷ ውስጥ የክርስቲያኖች ስብሰባ ይደረግ ነበር የሚለው አስታራቂ አሳብ ይሆናል። ከዚህም የተነሣ ዮሐንስ በአእምሮው ውስጥ ቤተሰቡንም ጉባኤውንም ይዞ ነበር ለማለት ይቻላል (ሮሜ 16፡5፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡19፤ ቆላ. 4፡15፤ ፊሊሞና 2)። መልእክቱን የጻፈበትም ምክንያት እግዚአብሔርን ለምትፈራዋ ሴት ወደ ቤቷም (2ኛ ዮሐንስ 10) ሆነ ወደ ማኅበሩ ምንም ዓይነት የሐሰት ትምህርት እንዳይገባ እንድትጠነቀቅ ሊያሳስብ ፈልጎ ነበር።

ምንም እንኳ ከአሳቢነትና ከማስጠንቀቂያ ጋር የተያያዘ ቢሆንም በዚህ አጭር መልእክት ውስጥ ጎላ ብለው የሚታዩት ስሜቶች የወዳጅነትና የደስታ

ናቸው፤ ስለዚህ እናንተም ሆናችሁ እኔም ቤታችንን በእውነት ለክርስቶስ ለመጠበቅ ከፈለግን፥ ዮሐንስ ከጻፈለት ከዚህ ቤተሰብ ጋር ተመሳሳይ ባሕርያት ሊኖሩን ይገባናል ማለት ነው።

## እውነቱን ማወቅ አለብን (2ኛ ዮሐንስ 1-3)

ዮሐንስ በዚህ ሰላምታ ውስጥ እውነት የሚለውን ቃል አራት ጊዜ ተጠቅሞበታል፤ ስለዚህ የቃሉን ትርጉም መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው። በመሠረቱ እውነት ማለት ላይ ላዩን ወይም ውጪውን የሚታየን የአንድ ነገር እይታ ሳይሆን ከዚያ በተቃራኒ ውስጣዊ ይዘቱ ወይም በዙሪያችን ለምናየው ነገር ሁሉ መሠረት የሆነው ዘለቄታዊ ጠቃሚነቱ ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ «እውነት» ነው (ዮሐ. 14፡6)፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል «እውነት» ነው (ዮሐ. 17፡17)። እግዚአብሔር እውነትን በልጁ መገለጥ እና በቃሉ ውስጥ ገልጧል። እንዲያስተምረንና እውነትን እንድናውቅ እንዲያስችለን «የእውነትን መንፈስ» ሰጥቶናል (ዮሐ. 14፡16-17፤ 16፡13)።

ሆኖም ግን እውነት ከአብ የተሰጠ ተጨባጭ መገለጥ ብቻ ሳይሆን በግል ሕይወታችን ውስጥ ያለ ውስጣዊ ልምድም ጭምር ነው። እርግጥ እውነትን ማወቅ ብቻ አይበቃም! «በእውነት እንወዳለን»፤ «ለእውነት እንኖራለን»፤ «እውነት በውስጣችን ይኖራል፤ ከእኛ ጋርም ለዘላለም ይኖራል።» ይህም ሲባል ምንም እንኳ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶችን መማር፥ መላክም ቢሆንም «እውነትን ማወቅ» ከዚያ በላይ ነው ማለት ነው። የአማኙ ሕይወት እውነትን በማፍቀርና እውነትን አጉልቶ በማሳየት ፍላጎት የተገዛ ነው ማለት ነው።

ዮሐንስ ደብዳቤውን በዚህ የ«እውነት» አጭር ገለጣ ከፍቷል፤ ምክንያቱም ስሕተትን የሚያሰራጩ ሐሰተኛ አስተማሪዎች በያለበት ተሰራጭተው ስለነበሩ ነው። እርሱም አሳቾች እና «የክርስቶስ ተቃዋሚዎች» ብሎ ጠርቷቸዋል (2ኛ ዮሐንስ 7)። ዮሐንስ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሁሉም ሃይማኖታዊ ትምህርቶች እውነት አላቸው ወይም አስተማሪዎቹ ከልብ የሚናገር እስከመሰሉን አሜን ብለን መቀበል አለብን የሚል ሰው አልነበረም። ለዮሐንስ በእውነትና በስሕተት መካከል እጅግ ትልቅና ለምንጊዜም ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ በመኖሩ፥ ስሕተትን በዋዛ የሚያልፈው ጉዳይ አልነበረም።

እውነት ከእኛ ጋር ለዘለዓለም አብሮን የሚኖር ነውና ከአሁኑ ልንለማመደውና ልናፈቅረውም መጀመር ይገባናል። ማንኛውም እውነት የሚያተኩረው ለዘላለም አብረነው በምንኖረውና ዘላለማዊ በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው (ዮሐ. 14፡1-6)። በእውነት ተከብበን፥ ለእውነት ባለን እውቀት እያደግንና የእውነትን አምላክ እያገለገልን ለዘለዓለም እንደምንኖር ማሰላሰል እጅግ ጣፋጭና አስደናቂ ነው።

ለመሆኑ ይህች የተመረጠች እመቤትና ልጆችዋ ይህን እውነት እንዴት ሊያውቁና የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ቻሉ? ይህ ሊሟላላቸው የቻለው በእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት በኩል ነው (2ኛ ዮሐንስ 3)። እግዚአብሔር በምሕረትና በጸጋ ባለጠጋ ነው (ኤፌ. 2፡4፥7)። ምሕረቱንና ጸጋውን ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እኛ አፈሰሰው። የዳንነው በእግዚአብሔር ፍቅር ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ማለትም «ዋጋ በተከፈለበት ፍቅር» ነው (ኤፌ. 2፡8-9)። እግዚአብሔር ዓለሙን በሙሉ ወድዷል፤ ዓለም በሙሉ ግን አልዳነም። የተትረፈረፈ ጸጋውን የሚቀበሉ ብቻ ናቸው ከኃጢአት መዳንን የሚያገኙት።

ጸጋንና ምሕረትን ከእግዚአብሔር ስትቀበሉ፥ ሰላሙንም ትቀምሱታላችሁ። «እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ» (ሮሜ 5፡1)። እግዚአብሔር ከጠፉ ኃጢአተኞች ጋር ጦርነት አልገጠመም፤ ኃጢአተኞች ናቸው ከእግዚአብሔር ጋር ጦርነት የገጠሙት (ሮሜ 5፡10፤ 8፡7)። እግዚአብሔር ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሠራው ሥራ የተነሣ ከኃጢአተኞች ጋር ታርቋልና ከእንግዲህ ግን ኃጢአተኞች ናቸው ንስሐ በመግባትና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ያለባቸው (2ኛ ቆሮ. 5፡14-21)።

ዮሐንስ በሁለተኛው ደብዳቤው ከመጀመሪያው አንሥቶ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ማረጋገጡን ማጤን እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህንን ያደረገው «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን»ከ«እግዚአብሔር አብ» ጋር በማያያዝ ነው። እስቲ ለምሳሌ ቁጥር 3 «ከእግዚአብሔር አብና ከነቢዩ አሞጽ» ቢል ኖሮ፥ ከመቅጽበት ተነሥታችሁ «አሞጽ ከአብ ስም ጋር መያያዝ የለበትም!

አሞጽ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል እንደሆነ ያስመስላል!» ማለታችሁ የማይቀር ነው።

ዮሐንስ ግን አብንና ወልድን በአንድነት የያዘው እኩል ከመሆናቸው የተነሣ ነው። ሁለቱም በእኩል አምላክ ናቸው! ከዚያ ደግሞ አንባቢዎቹ ትኩረቱን መገንዘባቸውን ለማረጋገጥ ዮሐንስ ኢየሱስን «የአብ ልጅ» በማለትም ገልጦታል። ሁለቱን ማለያየት የማይቻል ነገር ነው። እግዚአብሔር አባት ከሆነ፥ ልጅ ሊኖረው ይገባዋል፤ ያ ልጅ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። «ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም» (1ኛ ዮሐንስ 2፡23)።

ብዙ የሐሰት አስተማሪዎች «ሁላችንም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርንና የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ሁሉ ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ ነው!» ይላሉ። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ቢልም፥ አምላክ ነኝ ማለቱ አልነበረም ሲሉም በተጨማሪ ይከራከራሉ። ኢየሱስ ግን ለአይሁድ «እኔና አብ አንድ ነን» ሲላቸው ሊወግሩት አሰቡ! ለምን? ምክንያቱም ስለተሳደበ ነው! «አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለማድረግህ ነው» አሉት (ዮሐንስ 10፡30-33)፤ ዳሩ ግን ራሱን «የእግዚአብሔር ልጅ» ብሎ ሲጠራ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል መሆኑን መናገሩ እንደሆነ ያውቁ ነበር።

የክርስትና እምነት የሚጸናውም ሆነ ወይም መሠረት የሚያጣው በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ትምህርት ላይ ነው። ሰው ብቻ ከሆነ፥ ምንም ያህል ተሰጥኦ ያለው ወይም ልዩ ሰው ቢሆን፥ ሊያድነን አይችልም። የሰውን ሥጋ ለብሶ የመጣ አምላክ ካልሆነ የክርስትና እምነት ውሸት እንጂ እውነት አይደለም ማለት ነው፤ ዮሐንስም ደብዳቤው እንዲያተኩር ያደረገው በተሳሳተ አቅጣጫ ነበር ማለት ነው።

ታላቁ የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣን የነበረው ዳንኤል ዌብስተር፥ በአንድ ወቅት ቦስተን በተባለች ከተማ ከታዋቂ ሰዎች ጋር በመሆን በመመገብ ላይ ነበር። ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ አንዳንዶቹ እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው የሚል ዝንባሌ የነበራቸው «ዩኔቴሪያን» የሚባሉት ነበሩ። «ዩኒቴሪያኖች» የሥላሴን አንድነት፥ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚክዱ ናቸው። በዚህ ግብዣ ላይ የሃይማኖት ጉዳይ በመነሣቱ፥ ዌብስተር በኢየሱስ

ክርስቶስ አምላክነት ላይ ያለውን እምነትና በመቤዠት ሥራውም እንደሚያምን በድፍረት አስረግጦ ተናገረ።

ሆኖም ከአድማጮቹ መካከል አንዱ፡- «ሚስተር ዌብስተር፥ እንዴት ክርስቶስ አምላክም ሰውም መሆን ይችላል ብለህ ታስባለህ?» በማለት ጥያቄ አቀረበለት። ዌብስተር ሲመልስለት «እንዳልከው ነገሩ በአሳብ የምደረስበት አይደለም። አስቤ ልደርስበት ከቻልኩማ እርሱም ከእኔ ምንም አይበልጥም ማለት ነው። የማምነው ግን ከእኔና ከሌሎች ፍጡራን በላይ የሆነ አዳኝ እንደሚያስፈልገኝ ነው!» አለው ይባላል።

እኛም ቤቶቻችንና አብያተ ክርስቲያኖቻችን ለክርስቶስ ታማኝ እንዲሆኑ፥ ሐሰተኛ መምህራንንም መቃወም እንድንችል አስቀድመን እውነትን ማወቅ አለብን። እውነትን እንዴት እንማራለን? የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ በማጥናትና መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምረን በመፍቀድ ነው። እንዲሁም ለእምነታቸው ታማኝ የሆኑት ሲያስተምሩ ከልብ በማዳመጥና የተማርነውን ዓይነት ሕይወት በመኖር ነው። እውነትን በአእምሯችን ብቻ መያዝ ሳይሆን፥እንዲሁም እውነትን ከልባችን ልናፈቅርና በፈቃዳችንም ልንኖረው ይገባናል። ጠቅላላ ማንነታችን ለእውነት መሰጠት አለበት።

እንግዲህ ወላጆች ለልጆቻቸው እውነትን እንዲወዱ ማስተማራቸው የቱን ያህል አስፈላጊ ነው! የሰንበት ትምህርት ቤቶችና የክርስቲያን ትምህርት ቤቶች በመቋቋማቸው እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፤ ይሁን እንጂ እውነቱን እንዲያውቁና በእውነት እንዲኖሩ በማድረግ ረገድ ትልቁ ኃላፊነት የቤተሰብ ነው።

## በእውነት መመላለስ አለብን (2ኛ ዮሐንስ 4-6)

«በእውነት መመላለስ» ማለት ለእውነት መታዘዝ፥ እያንዳንዱን የሕይወታችንን ገጽታ እውነት እንዲቆጣጠረው መፍቀድ ማለት ነው። ዮሐንስ ይህን አንቀጽ የሚጀምረውና የሚደመድመው በመታዘዝና በእውነት በመመላለስ ላይ በማተኮር ነው። እውነትን ማጥናት ወይም ደግሞ ስለ እውነት መከራከር እውነትን ተግባራዊ ከማድረግ (ከመኖር) ይልቅ በጣም ይቀላል! እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ የጋለ ስሜት ያላቸው ክርስቲያኖች ለእውነት በሚከራከሩበት መጠን ለእውነት ሲታዘዙ አይታዩም።

በቺካጎ ከተማ በመጋቢነት በማገለግልበት ወቅት አንድ እንግዳ የሆነ ወጣት፣ ወዳጆቼ የነበሩትን ብዙ ወንጌላውያን መሪዎች የሚያወግዙ ጽሑፎች በቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት ባለው የእግር መንገድ ላይ ሲያድል እመለከት ነበር። በእርግጥ ጽሑፎችን እንዳያሰራጭ ልናግደው አንችልም ነበረ፤ ስለዚህ የነበረን አማራጭ ደጋፊዎቻችን ሊሰጣቸው የሚችለውን ያህል ወረቀት እየተመላለሱ በመውሰድ እንዲያቃጥሏቸው ማድረግ ነበር።

ከዚያም ከእኛ ሰዎች አንዱ ይህን ወጣት አንድ ምሽት በድብቅ ሊከታተለው ወሰነ፤ ወጣቱንም በአቅራቢያው ወዳለ መናፈሻ ሄዶ በዛፍ ሥር ተቀምጦ ሲጋራ ሲለኩስ አየው! ሆኖም ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ወጣቱ ከቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት ቆሞ «እኔ ለእውነት የምታገል፥ በማደርገውም የማላፍርበት ነኝ!» እያለ ይጮህ ነበር። በእኔ ግምት የርሱ ብጤ አስመሳዮች በዚህ አድራጎቱ እንደሚያፍሩበት ነው። በእርሱ ግምት በአንድ በኩል እውነትን ሊያራምድ በሌላ ወገን ደግሞ ስሕተትን ማጋለጡ ነበር። ሆኖም ግን እራሱ በእውነት ውስጥ እየኖረ አልነበረም። ቆሜለታለሁ የሚለውን እውነት በአጓጉል ድርጊቱ እየካደ ነበር።

የሐዋርያው ዮሐንስ ደስታ (ቁ. 4):- የተመረጠችው እመቤት ልጆች በእውነት እየተመላለሱ በመሆናቸው ነበረ። ሆኖም ዮሐንስ ሁሉንም አያውቃቸውም ነበር፤ በመሆኑም ቀጥተኛው ትርጉም «ከልጆችሽ አንዳንዶቹ» የሚል ሊሆን ይችላል። በጉዞው ወቅት ዮሐንስ ከልጆችዋ አንዳንዶቹን አግኝቶ ከጌታ ጋር በታማኝነት ስለመመላለሳቸው ተረድቶ ነበር። «ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም» (3ኛ ዮሐንስ 4)። ዮሐንስ ሌሎቹ ልጆች የሐሰት አስተማሪዎችን ተከትለው መንገዳቸውን እንደሳቱ እየጠቆመ ነበረ ብለን ለማመን ምንም ምክንያት የለንም። «ልጆች» ሲል ዮሐንስ «የቤተ ክርስቲያን» አባላትንም በሙሉ ጨምሮ ከሆነ፥ ምናልባት አንዳንዶቹ ኅብረቱን ትተው ከሐሰተኞች ጋር ተቀላቅለው ሊሆን ይችላል።

ልጆቹ ለቃሉ መታዘዛቸው እግዚአብሔርን ያስደስተዋል። ክርስቲያን ቤተሰብ ለእውነት ሲታዘዝና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሲያደርግ አንድን የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ምን ያህል እንደሚያስደስተው ከግል ልምዴ

አውቃለሁ። የማይታዘዙና ዓመፀኞች፥ ለእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን የማይገዙ የቤተ ክርስቲያን አባሎች የመጋቢውን ልብ ክፉኛ ያቆስሉታል።

ታላቁ ሰባኪ ቻርለስ ስፐርጀን የልጅነት ጊዜውን ያሳለፈው በእግዚአብሔር አገር በስታምቦርን ከተማ ውስጥ፥ የአንድ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ከነበሩት አያቱ ጋር ነበር። ታዲያ የዚሁ ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረው ኢላይጃ ሮድስ የተባለው ሰው በየመጠጥ ቤቱ በመዞር ከልክ በላይ ቢራ በመጠጣቱና ሲጋራ በማጤሱ መጋቢው በጣም ያዝኑ ነበር።

አንድ ቀን ወጣቱ ስፐርጀን ለአያቱ:- «ሽማግሌውን ሮድስን እገድለዋለሁ! ይህን በእርግጥም አደርገዋለሁ። ከዚህ ሌላ ክፉ ነገር አላደርግም፥ እርሱን ግን መግደሌ የማይቀር ነው» በማለት ተናግሮ ነበር።

ከዚያስ ወጣቱ ስፐርጀን ምን አደረገ? ወደ መጠጥ ቤቱ በመሄድ ሮድስን እነዚህን ቃላት በመናገር ተጋፈጠው:- «ኢላይጃ፥ እዚህ ምን ታደርጋለህ? አንተ የቤተ ክርስቲያን አባል ሆነህ ሳለህ ግን እግዚአብሔርን ከማይፈሩ ጋር ተቀምጠህ በመስከርህ የመጋቢህን ልብ እያሳዘንክ ነው። ስለ አንተ እፍረት እየተሰማኝ ነው! እኔ ብሆን መጋቢዬን እንደማላሳዝነው እርግጠኛ ነኝ!»

ብዙ ሳይቆይ ኢላይጃ ሮድስ ወደ መጋቢው ቤት መጥቶ ኃጢአቱን ተናዘዘና ለድርጊቱ ይቅርታ ጠየቀ። ወጣቱ ስፐርጀን በእርግጥም ኢላይጃን ከክፋቱ መልሶታል። በዚህ መንገድ በኢላይጃ ውስጥ ያለውን ክፉ ምኞት «ገድሎታል»!

ከሐዋርያት የመከራከሪያ ነጥቦች አንዱ (ቁ. 4) እግዚአብሔር በእውነትና በፍቅር እንድንመላለስ የሰጠን ትእዛዝ ስለ መኖሩ ነው። «ትእዛዝ» የሚለው ቃል በእነዚህ ጥቂት ቁጥሮች ውስጥ አምስት ጊዜ ተጠቅሷል። የእግዚአብሔር ትእዛዛት በተወሰኑ የሕይወት ድርጊቶች «እውነት» ላይ ያተኩራሉ፤ ሆኖም ለዚህ እውነት ካልተጠነቀቅንለት ደብዛዛ እና ግብ የለሽ ሊሆን ይችላል፤ «ትእዛዛቱ» ግን ያንን እውነት ግልጽና ተጨባጭ ያደርጉታል።

ትእዛዛቱ ከእግዚአብሔር «አብ» እንደተሰጡ አስተውል። እያንዳንዱ ትእዛዝ የፍቅር መግለጫ ነው እንጂ ሕግ ብቻ አይደለም። እንደዚሁም የእግዚአብሔር ፈቃድ ማለት የእግዚአብሔር ልብ መገለጥ ማለት ነው እንጂ

(መዝ. [33]፡ 11) የአሳቡ መገለጥ ማለት ብቻ አይደለም። በዚህም ምክንያት ለቃሉ መታዘዛችን የፍቅራችን መግለጫ እንጂ የፍርሃት መግለጫ መሆን የለበትም። «ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፤ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም» (1ኛ ዮሐንስ 5፡ 3)።

ሐሰተኛ አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ከባድና አስቸጋሪ በማስመሰል ሲያቀርቡ፥ በዚህ ምትክ ለተከታዮቻቸው «እውነተኛ» አርነትን ያስገኛሉ የሚሏቸውን አማራጮች ያቀርቡላቸዋል (2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 19)። እንደ እውነቱ ግን የመጨረሻው አርነት ለእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ በመታዘዝ የሚገኘው ነው። እግዚአብሔርን የሚወድ ማንም አማኝ ትእዛዛቱን ከባድና ለመሸከምም እንደማይቻል አድርጎ አይቆጥርም።

የሐዋርያው ልመና (ቁ. 5-6) የተመረጠችው እመቤትና ቤተሰቧ እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ ነበር። ይህ ደግሞ ለእኛም አስፈላጊ ነው። «እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ» (ዮሐ. 13፡ 34)። ሆኖም ዮሐንስ ይህ አዲስ ትእዛዝ እንዳልሆነ ጽፏል (1ኛ ዮሐ. 2፡ 7-11 ተመልከት)። ይህ እርስ በርሱ የሚቃረን ነውን?

«እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው ትእዛዝ በጊዜ አንጻር ሲታይ በእርግጥ አዲስ አይደለም፤ ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን አይሁዶች እንኳ ባልንጀሮቻቸውን (ዘሌዋ. 19፡ 18፥ 34) በሀገራቸው ያሉትን ስደተኞች (ዘዳ. 10፡ 19) እንዲወዱ ታዝዘዋል። በእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድር መምጣት ግን ይህ ትእዛዝ ባገኘው ልዩ ትኩረት እና ምሳሌነት አዲስ መልክ ይዟል። ኢየሱስ ክርስቶስ ለወንድማማቾች መዋደድ አዲስ ትኩረት በመስጠት ይህንንም በገዛ ራሱ ሕይወት ምሳሌነት አሳይቷል። በልምድም አንጻር ይህን ዓይነቱ ፍቅር አዲስ ነው፤ ምክንያቱም እንድንታዘዝ የሚያስችለን በውስጣችን የሚኖር የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስላለን ነው። «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር . . . ነው» (ገላ. 5፡ 22 ከሮሜ 5፡ 5 ጋር አነጻጽር)።

ለመሆኑ ፍቅርን ማዘዝ ይቻላል? አዎን። ክርስቲያናዊ ፍቅር በትክክል ምን እንደሆነ እስከተረዳን ፍቅርን ማዘዝ ይቻላል። ብዙ ሰዎች ግን ክርስቲያናዊ ፍቅር ከሌሎች ጋር እንድንግባባና እንድንቀራረብ የሚያስችል ልዩ ዓይነት «ሃይማኖታዊ ስሜት» ነው የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ

አላቸው። በእርግጥ ስሜት የራሱ ድርሻ አለው፤ በመሠረቱ ግን ክርስቲያናዊ ፍቅር ከፈቃድ የሚመነጭ የድርጊት መግለጫ ነው። በቀላል አነጋገር፥ እግዚአብሔር እኛን በሚያይበት ሁኔታ ሌሎች ሰዎችን ማየት ማለት ነው! ይህ ብቃት እስካለን ደስ የማይሉንን ሰዎች እንኳ መውደድ እንችላለን ማለት ነው።

እርግጥ በማናቸውም ጊዜ ፍቅርን እንደፈቀድነው መቆጣጠር ያዳግተን ይሆናል። ይህም ሆኖ ግን በዝንባሌያችንና በተግባራችን ፍቅራችንን መግለጥ እንችላለን። ሰዎች ከልክ ያለፈ ክፋት ቢሠሩብንም እኛ ግን ደግ ልንሆንላቸው እንችላለን። ሰዎች ሲያሳድዱን ልንጸልይላቸውና እንዲሁም ዕድሉ ሲያጋጥመን መልካም ልናደርግላቸው እንችላለን። በስሜታችን የምንመራ ከሆነ ምናልባት የበቀል እርምጃ ለመውሰድ እንነሣሣ ይሆናል! ነገር ግን መንፈስ ፈቃዳችንን እንዲቆጣጠር ከጠየቅነው፥ ኢየሱስም ራሱ ቢሆን ያደርግ እንደነበረው እኛም በክርስቲያናዊ ፍቅር ተነሣሥተን መልካም ልናደርግላቸው እንችላለን።

ከዚህ በመቀጠልም ዮሐንስ ፍቅርና መታዘዝ አብረው መሄድ እንዳለባቸው አስረድቷል (2ኛ ዮሐንስ 6)። ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ከሰዎች ጋር ካለን ግንኙነት መለያየት አንችልም። እግዚአብሔርን እንወዳለን እያልን ወንድማችንን ግን ብንጠላ እግዚአብሔርን እንደማንወደው እያረጋገጥን ነው (1ኛ ዮሐንስ 4፡20)። ለእግዚአብሔር ከታዘዝን ፍቅሩ በእኛ ውስጥ ፍጹም ስለሚሆን ወንድማችንንም ለመውደድ ምንም ችግር አይገጥመንም (1ኛ ዮሐ. 2፡3-5)።

ይህንን አንቀጽ ልብ ብላችሁ ስትመለከቱት እርስ በርሳቸው የተያያዙ ሦስት ዐበይት አሳቦችን ታያላችሁ። እነርሱም እውነት፥ ፍቅር እና መታዘዝ ናቸው። እውነት ስንል ደኅንነትን ያገኘነው በክርስቶስና በቃሉ በማመን ነው ማለታችን ነው፤ የዚህ ደኅንነት ማስረጃ ደግሞ ፍቅርና መታዘዝ ናቸው፤ ፍቅርና መታዘዝ ደግሞ ስለ እውነት በሚኖረን የእውቀት ዕድገት መጠን ይጠነክራሉ። እውነትን በፍቅር እንናገራለን (ኤፌ. 4፡15)፤ እግዚአብሔርን ስለምንወደው ደግሞ ትእዛዛቱን እንጠብቃለን። መታዘዝ የበለጠ እውነትን እንድንማር ያስችለናል (ዮሐ. 7፡17)፤ እንዲሁም የበለጠ እውነትን በተማርን ቁጥር እውነት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የበለጠ

እንወደዋለን! በጥላቻና በጭካኔ ከመኖር ይልቅ በፍቅር፥ በእውነትና በመታዘዝ እንኖራለን።

## በእውነት ውስጥ መኖር (2ኛ ዮሐንስ 7-11)

ዮሐንስ በእውነት መኖርን ካበረታታ በኋላ ስሕተትን ወደ መቃወም አመራ። በዓለም ውስጥ አሳቾች እንዳሉ ለማስጠንቀቅ ከጴጥሮስ ጋር ድምፁን ከፍ አድርጎ እያሰማ ነበር። «አሳሳች» ወይም «አታላይ» የሚለው ቃል የሐሰት ትምህርትን ከማስተማር የበለጠ የከፋ ነው። አሳሳችነት ሐሰተኛ ትምህርትን ማስተማር ከመሆንም አልፎ ሰዎችን ወደ ተሳሳተ አኗኗር መምራትንም ያካትታል። ዮሐንስ ካሁን በፊት እውነትና ሕይወት በአንድነት እንደሚሄዱ ግልጥ አድርጓል። የምናምነው ነገር እንዴት እንደምንኖር ይወስናል። የተሳሳተ ትምህርትና የተሳሳተ አኗኗር ሁልጊዜ አብረው ይሄዳሉ።

እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች በመጀመሪያ ከየት ነበር የመጡት? «ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና»፡- ይህን ማለት የወጡት ከቤተ ክርስቲያን ነበር ማለት ነው! በአንድ ወቅት «ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ በተሰጠ ሃይማኖት» (ይሁዳ 3) ያምኑ እንደነበረ የመሰከሩ ናቸው፤ ነገር ግን ከዚያ እምነት ተመልሰው እውነትንና ቤተ ክርስቲያንን ተቃውመዋል።«ከእኛ ዘንድ ወጡ፥ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም» (1ኛ ዮሐንስ 2፡19)። «ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩስ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ» (የሐዋ. 20፡30)።

ከሐሰተኛ አስተማሪዎች የውስጥ ጥቃት፥ ቤተሰብን ወይም አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ለመከላከል ከፍተኛ መንፈሳዊ ጥንቃቄ ይጠይቃል። አንድ በጣም የተሳካለት መጋቢ «ከዚህ ሥራ ላይ ዓይኔን ለሃያ አራት ሰዓት ባነሣና መጸለዩንም ባቆም ኖሮ እኛ ከማወቃችን በፊት በሐሰተኞች ይወረር ነበር» በማለት አጫወተኝ። የራሱን ጠቃሚነት አልነበረም ያነሳው (እግዚአብሔርን የሚመስሉ መጋቢዎች ለመንፈሳዊ ቤተ ክርስቲያናት አስፈላጊ ቢሆኑም)፥ የትጋትንና የጥንቃቄን ጠቃሚነት ነበረ ለማጉላት የፈለገው።

ብዙ አሳሳቾች እንዳሉ አስተውሉ! ለምን? 2ኛ ጴጥሮስ 2፡2 መልሱን ይሰጣል፡- «ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል በእነርሱም ጠንቅ

የእውነት መንገድ ይሰደባል።» ማርክ ትዌይን የተባለ ሰው ይመስለኛል፡- «እውነት ገና ጫማዋን በማጥለቅ ላይ ሳለች ውሸት በዓለም ዙሪያ ትሮጣለች» ያለው። የወደቀው የሰው ልጅ ባሕርይ ውሸትን ማመንና የእግዚአብሔርን እውነት መቃወም ይፈልጋል። ምንም ያህል የተሳካላቸው መስለው ቢታዩም የማይጠነቀቁትንና ያልጸኑትን ሰዎች ለማታለል ሐሰተኞች የሚጠቀሙባቸውን ጠማማ ዘዴዎች ከ2ኛ ጴጥሮስ 2 ተምረናል።

እነዚህ አታላዮች «ፀረ-ክርስቶሶች» ናቸው (1ኛ ዮሐ. 2፡18-29 ተመልከት)። በግሪኩ ቃል «ፀረ» የሚለው ባዕድ መነሻ «በምትክ» እና «በመቃወም» ማለት ነው። እነዚህ አስተማሪዎች ክርስቶስን ይቃወማሉ፤ ምክንያቱም ሥጋ ለብሶ የመጣ አምላክ መሆኑን ስለሚክዱ ነው (1 ዮሐንስ 4፡1-6 ተመልከት)። ስለ ክርስቶስ ያለውን እውነት መካድ ብቻ ሳይሆን ለተከታዮቻቸው ስለ ክርስቶስ ሳይሆን «ተተኪ ክርስቶስ» ይሰጧቸዋል። ማንኛውንም አስተማሪ፥ ሰባኪ ወይም ደራሲ በመጀመሪያ መጠየቅ የሚያስፈልገው፡- «ስለ ክርስቶስ ምን ታስባለህ? ሥጋ ለብሶ የመጣ አምላክ ነውን?» በማለት መሆን አለበት። መልስ ለመስጠት ካመነታ ወይም ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ የመጣ አምላክ መሆኑን ከካደ የሐሰት አስተማሪ ለመሆኑ እርግጠኞች መሆን ትችላላችሁ።

አንድ ጊዜ በስኮትላንድ ሀገር ወንጌልን ለመስበክ እየተዘጋጀሁ እያለ አንድ ወጣት ወደ እኔ መጣ። ራሱን እንኳ ሳያስተዋውቅ «ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ስለ መወለዱ ታምናለህ?» አለኝ። እንደማምንና ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ የመጣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንደምሰብክ አጠንክሬ መለስኩለት። ደፋር የሆነውን አቀራረቡን ባልወድለትም ያለውን አቋምና «በእውነት መኖሩን» ግን ሳላደንቅ አላለፍኩም።

በእውነት መኖር ማለት ለክርስትና እምነት መሠረታዊ ትምህርቶች እውነተኛ ሆኖ መጽናት ማለት ነው። የሐሰት አስተማሪዎች ከእውነትና ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት ተለይተዋል፤ ስለዚህም አደገኞች ናቸው። ዮሐንስ በዓለም ውስጥ ካሉት አታላዮች የተነሣ ቤተ ክርስቲያንና አባሎችዋ ስለሚያጋጥሟቸው ሦስት አደጋዎች ጠቁሟል።

ከእውነት የማፈግፈግ አደጋ (ቁ. 8)፡- ይህ ቀደም ሲል የተገኘውን ስጦታ የማጣት አደጋ ነው። ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ማለት «ንቁና ጠብቁ!» ማለት

ነው። የሐሰት አስተማሪዎች የሌላችሁን ነገር ያቀረቡላችሁ ይመስላችኋል። እውነታው ግን ያላችሁን መውሰዳቸው ነው።

ሰይጣን ሌባ ነው፤ ረዳቶቹም እንዲሁ ናቸው። ዮሐንስ አንባቢዎቹ «ሙሉ ደመወዝ» እንዲቀበሉ ይፈልጋል፤ ይህም በ2ኛ ጴጥ. 1፡11 ካለው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ወደ ዘላለማዊ መንግሥት መግባት ማለት ነው። የእግዚአብሔር ባሪያዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት በታማኝነት ሲሠሩና ከዚያ ደግሞ ሥራው በሐሰት ትምህርት ሲወድም እንዴት አሳዛኝ ነው። በመሆኑም፥ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች «ምናልባት በከንቱ ለእናንተ ደከሜያለሁ ብዬ እፈራችኋለሁ» ሲል መጻፉ ከዚህ የተነሣ ነው (ገላ. 4፡11)።

ኬኔት ዊስት ቁጥር 8ን «የጨበጣችሁትን ነገሮች እንዳታጡ» በማለት ተርጉመውታል። የቤተ ክርስቲያን አባላት፥ የታመኑ መጋቢዎችና አስተማሪዎች ሥራቸውን ማክበርና መንከባከብ፥ ብሎም ለማስፋፋት ማንኛውንም ነገር ማድረግ አለባቸው። የእግዚአብሔር ባሪያዎች አንድ ቀን ስለ አገልግሎታቸው መልስ ይሰጣሉ፤ ያንንም «በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት» (ዕብ. 13፡17) መጠንቀቅ አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን ያገኘችውን እያጣች ወደኋላ ስትሄድ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ከሽልማቷ ከፊሉን ታጣለች። የእግዚአብሔርን ቃል እውነት አጥብቀን መያዝ አስፈላጊ ነው!

ወደፊት ቀድሞ የመሄድ አደጋ (ቁ. 9)፡- እዚህ ላይ ያለው አደጋ ከእግዚአብሔር ቃል ወሰን አልፎ የመሄድና በቃሉም ላይ የመጨመር ነው። መተላለፍ የሚለው ቃል «በጣም ርቆ መሄድና ቀድሞ መሮጥ፥ ከተወሰኑት ድንበሮች ማለፍ» ማለት ነው። የውሸት እድገት ነው! ሐሰተኞች መምህራን ቤተ ክርስቲያን «በማነቆ ተይዛ» ስትንፈራገጥ፥ እነርሱ «ዕድገት» እንደሚያስገኙላት ሊያሳምኑን ይሞክራሉ። «አዲስና አስደናቂ» ነገር ስላላቸው ከእነርሱ ጋር እንድንቀላቀል ይጋብዙናል። «ዕድገታቸው» ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ የመጣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚገልጸውን ትምህርት በመካድ ነው።

ከኀምሳ ዓመታት በፊት የአሜሪካ ጋዜጦች፥ ወግ አጥባቂዎችና ዘመናዊ አስተሳሰብ ያላቸው የሥነ- መለኮት ምሁራን የሚያደርጉትን ክርክር ያወጡ

ነበር። ለእምነት እውነተኞች ወገኖች በግምባር ቀደምትነት የሚገኙትን የሃይማኖት ከሐዲዎች ከመቃወማቸውም፥ የእነዚህን ክፍሎች ትምህርት ቤቶች አቋም ወደ እውነትኛ ክርስትና ለመመለስ ይጥሩ ነበር። እነዚህ «ተራማጅ» ነን ባይ ቡድኖች ራሳቸውን «ዘመናውያን» ብለው ይጥሩ እንጂ እውነታው ግን የክርስትናን ትምህርት ከመካዳቸው በስተቀር «ዘመናዊ» የሚያደርጋቸው ምንም ዓይነት አዲስ ነገር አልነበረም። እንዲያውም እነዚህ ከሕደቶች የቤተ ክርስቲያንን ያህል ዕድሜ ያላቸው ናቸው። ከመሪዎቻቸው አንዱ የሆነው ዶክተር ሃሪ ኤሜርሰን ፎዝዲክ በአንደኛው ስብከቱ ላይ «መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን የሚያምኑ ዛሬም ከእኛ ጋር አሉ፤ እነርሱ ግን ያልተማሩ ኅብረተሰብ ናቸው» ሲል ዘብቶ ነበር። ሆኖም ግን ይህ ሰው በዛሬ ጊዜ በሕይወት ቢኖር ኖሮ ይህን ዐረፍተ ነገር ደፍሮም ባልተናገረ ነበር፤ ዛሬም ታላላቅ የሰንበት ትምህርት ቤቶች፥ አብያተ ክርስቲያናት፥ ሴሚናሪዎች የሚስዮናውያን ድርጅቶች በትምህርታቸው ‹ወግ አጥባቂ› ናቸው።

አንድ ሰው በእውነተኛ ትምህርት ውስጥ ካልኖረ በስተቀር አብም ወልድም የሉትም። በአንድ ጊዜ አብን አክብሮ ወልድን መካድ (ወይም ተራ ሰው ብቻ ነው ብሎ መጥራት) የማይቻል ነው። «ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ ...። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም» (ዮሐ. 5፡23)። ክርስቶስን በመካድ የሚገኘው «ተራማጅ ሥነ- መለኮት» ሳይሆን ወደ ስሕተት የሚመራ ነው። ወደ ዘፍጥረት እንደገና ብንመለስ በዘፍጥረት 3፡1፥ «በውኑ እግዚአብሔር አዞአልን?» የሚለውን እናነባለን።

ሆኖም ዮሐንስ ይህንን ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ «ዕድገትን» እየኮነነ አልነበረም። «ጌታ ከቃሉ የሚያበራው የበለጠ ብርሃን ገና አለ።» እውነትን እንዲያስተምረንና በአዲስ መልክ ተረድተን በተግባር ላይ እንድናውለው እንዲመራን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ሰጥቶናል (ዮሐ. 16፡12-16)፤ እኛ ደግሞ ሳናቋርጥ ማደግ አለብን (2ኛ ጴጥሮስ 3፡18)።

ነገር ግን «መማራችን» ከኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት እና ሥራ መሠረታዊ ትምህርቶችም የሚያርቀን ከሆነ በአደገኛ ሁኔታ ላይ ነን።

አብሮ የመጓዝ አደጋ (ቁ. 10-11):- ዮሐንስ ለዚያ ቤተሰብ አባላት (በተጨማሪም በቤታቸው ያለችውን ቤተ ክርስቲያን) በጻፈው መልእክቱ፥ በእንግድነት ስም የሚመጡትን የሐሰት አስተማሪዎችን እንዳይቀበሉዋቸው፥ እንዳያስተናግዱቸውና ከእነርሱ ጋርም ምንም ኅብረት እንዳያደርጉ አስጠነቀቀ። ማስተናገድ በጣም አስፈላጊ የክርስትና አገልግሎት ነበር፤ ምክንያቱም መንገደኞች በተለይም ከዓለም ክፉ ተጽዕኖዎች መራቅ የሚፈልጉ ክርስቲያኖች በደኅና ሊያርፉባቸው የሚችሉባቸው ሆቴሎች በጣም ጥቂት ስለነበሩ ነው። ክርስቲያኖች ለእንግዶች ቤታቸውን ክፍት እንዲያደርጉ ተመክረው ነበር (ሮሜ 12:13፤ 1ኛ ጢሞ. 3:2፤ 5:3-10፤ ዕብ. 13:2፤ 1ኛ ጴጥሮስ 4:8-10)።

ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩ መጋቢዎችና አስተማሪዎች የሚያርፉባቸውን ቤቶች ይፈልጉ እንደነበረም እውነት ነው (3ኛ ዮሐንስ 5-8)። እነዚህን የእግዚአብሔርን ባሪያዎች በእንግድነት የሚቀበሉ አማኞች «የእውነት ደጋፊ ወገኖች» ነበሩ። የሐሰት አስተማሪዎችን የረዱ አማኞች ግን በክፉ ሥራቸው እየተካፈሉ ነበር። የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት የእውነት መመዘኛ፥ለኅብረት መሠረት፥ እንዲሁም ለእርስ በርስ ትብብር ማሠሪያ ነው።

ይህ መመሪያ በእርግጥ ዛሬም ይሠራል። ብዙ ጊዜ አታላይ ክርስቲያኖች ወደ እኛ ይመጣሉ። ካሴት ሊያጫውቱልን በመፈለግ ወይንም መጽሔቶችን ወይም መጻሕፍትን ሊሰጡን ወደ ደጃችን ይመጣሉ፤ እኛ ግን ማንነታቸውን መለየት አለብን። ከክርስቶስ እውነተኛ ትምህርት ጋር የማይስማሙ ከሆኑ እነርሱን ወደ ቤታችን አለማስገባት ብቻ ሳይሆን፥ «ደኅና ሁኑ» ወይም «እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን» ማለት እንኳ የለብንም።

ዮሐንስ ይህን በተመለከተ ለምን ያን ያህል አሳበ ግትር ሆነ? ምክንያቱም ማንኛውም የእግዚአብሔር ልጅ ይህን ጥንቃቄ የሚያደርገው:- (1) የሐሰት አስተማሪው ሐሰተኛ ትምህርቱ ተቀባይነት ያገኘ እንዳይመስለው ለማድረግ፥ (2) ኅብረት ከመፍጠርና ጓደኛ ከመሆን የተነሣ በረከስ ትምህርት ከመበከል ለመከላከልና (3) የሐሰት አስተማሪው ቀጥሎ ለአገልግሎቱ መደገፊያ እንዳያገኝ ለማድረግ ነው። ለምሳሌ እኔ አንድን ጠንቋይ ባስተናግድ፥ ሄዶ ለጎረቤቶቹ «እኔን የማታስተናግዱበት ምንም ምክንያት

የለም፤ እንዲያውም መጋቢ ዌርዝቢ እንኳ በቤቱ ጋብዞኝ ግሩም የጭውውት ጊዜ ነበረን!» ብሉ ይነግራቸዋል። የእኔ አለመጠንቀቅ ቢያንስ የአንድ ሌላ ሰውን ጥፋት ያለጥርጥር ሊያስከትል ይችላል።

ዮሐንስ ወደ ቤታችን ሊገቡ የሚገባቸው ሰዎች ዳግመኛ የተወለዱ ብቻ ናቸው አለማለቱ ግልጥ ሊሆንልን ይገባል። በጠረጴዛ ዙሪያ ያለ «የጓደኝነት የወንጌል ስርጭት» ሰዎችን ለክርስቶስ ለመማረክ ግሩም የሆነ መንገድ ነው። ክርስቲያኖች ጥሩ ጎረቤትና እንግዳ ተቀባዮች መሆን ያስፈልጋቸዋል። ሐዋርያው ግን አጥብቆ ያስጠነቀቀን ፀረ-ክርስቲያን ቡድኖችን የሚወክሉትን፥ ቤተ ክርስቲያንን የተዉና አሁንም ሌሎችን ከእውነት ለማሳሳት የሚሞክሩትን የሐሰት አስተማሪዎች እንዳንቀበል ወይም እንዳናበረታታ ነው። የሐሰተኛ መምህራን የእውነተኛ ክርስቲያኖችን ድጋፍ ለማግኘት ባገኙት ዕድል ሁሉ እንደሚጠቀሙ ከልብ ልታጤነው ይገባል።

ሐዋርያው ዮሐንስ የሐሰት ትምህርትን በተመለከተ የነበረውን አቋም የሚያሳይ አንድ አፈ ታሪክ አለ። በኤፌሶን ሲኖር ሳለ አንድ ቀን ዮሐንስ ወደ ሕዝብ መታጠቢያ ቦታ ሄዶ ኖሮ እዚያ የመናፍቃን ቡድን መሪ የነበረውን ሰረንተስን ያየዋል፤ ከዚያም ከእግዚአብሔር ዘንድ በወረደ ፍርድ ግንቦቹ እንዳይወድቁበት በመፍራቱ ዮሐንስ ከግንቦቹ በሩጫ ሸሸ ይባላል። ሰሪንተስ ኢየሱስ በሥጋ የመጣ አምላክ ሳይሆን የዮሴፍና የማሪያም የተፈጥሮ ልጅ ነው ብሎ ያስተምር ነበር።

የዮሐንስ የመዝጊያ ቃላት (2ኛ ዮሐንስ 12-13) በ3ኛ ዮሐንስ ካለው ስንብት ጋር ተመሳሳይ በመሆናቸው ማብራሪያ የሚያሻቸው አይመስለኝም። ሆኖም ግን የክርስቲያን ኅብረትን አስፈላጊነትና ይህም ለልባችን ሊያመጣ ስለሚገባው ደስታ መግለጻቸውን (1ኛ ዮሐንስ 1፡4 ተመልከቱ) ማስታወሱ ያስፈልጋል። ደብዳቤዎችን መቀበል ግሩም ነገር ነው፤ ከዚህ እጅግ አድርጎ የሚበልጠው ግን የእግዚአብሔርን ሰዎች ወደ ቤታችንና በልባችን ውስጥ መቀበልና ማስገባት ነው።

ይህ ለአንዲት ክርስቲያን እናትና ቤተሰቧ (ምናልባትም በቤታቸው ላለች ቤተ ክርስቲያን) የተጻፈ አጭር መልእክት፥ በጠራ ዕንቁ የሚመስል የተቀደሰ የደብዳቤ ልውውጥ ነው። ከሁሉም ደግሞ የደብዳቤዋ ዋና ነጥብ የሆነውን አንድ ቃል መርሳት የለብንም። ይኸውም ንቃ! የሚለውን ቃል ነው። በዓለም ውስጥ ብዙ አታላዮች አሉና ንቃ!

# እውነቱ ይህ ነው

## 3ኛ ዮሐንስ

ለእውነት መቆምና ሐሰተኛ ትምህርትን መቃወም በቤት ውስጥ ብቻ የሚወሰን አይደለም (2ኛ ዮሐንስ)፤ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ችግሩ አለ፤ 3ኛ ዮሐንስም የሚናገረው ስለዚሁ ጉዳይ ነው። (አዲስ ኪዳን በተጻፈበት በግሪክ ቋንቋ ሲታይ ይህ ከሁሉ አጭሩ መልእክት ነው።) ስለ ጥንት ክርስቲያኖች፥ ስለ ሕዝቡና ስለ ችግራቸው አጭር እይታ ይሰጠናል። ይህንን አጭር ደብዳቤ ስታነቡ «ለካስ ዘመናት ብዙም አልተለወጡም!» በማለት መገረማችሁ አይቀርም። ዛሬም ቢሆን ከቀድሞው ጋር የሚመሳሰሉ ሰዎችና ችግሮች ያጋጥሙናል!

በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ካሉት ቁልፍ ቃላት አንዱ «ምስክር» የሚለው ነው። (ቁ. 3 «ሲመሰክሩ»፥ ቁ. 6፥ ቁ. 12 «መስክረዋል፥ ይመሰክሩለታል፥ ትመሰክርለታለች»)፤ ይህ ማለት የምንናገራቸውን ቃላት ብቻ ሳይሆን የምንኖረውንም ሕይወት ማለት ነው። እያንዳንዱ ክርስቲያን ጥሩ ወይም መጥፎ ምስክር ነው፤ እኛም በየግላችን እውነትን እንዲስፋፉ እየረዳን (ቁ. 8) ወይም እያደናቀፍን ነን።

ይህ ደብዳቤ የተጻፈው ከማኅበሩ መሪዎች አንዱ ለሆነው ለጋይዮስ ነበር፤ ነገር ግን ዮሐንስ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ስለሌሎችም ሁለት ሰዎች ተናግሯል፡- ስለ ዲዮጥራጢስና ስለ ድሜጥሮስ። ሰዎች ባሉበት ቦታ ሁሉ ችግሮች አሉ፤ እንደዚሁም ችግሮችን የመፍታት ችሎታውም አብሮ ይኖራል። እያንዳንዳችን «እኔ የችግሩ ክፍል ነኝ ወይስ የመፍትሔው ክፍል?» የሚለውን ጥያቄ በታማኝነት መጋፈጥ አለብን።

በዚህ መልእክት ውስጥ ያሉትን ሦስት ሰዎች ተመልከቱና እንዴት ዓይነት ክርስቲያኖች እንደነበሩ አስተውሉ።

## ጋይዮስ አበረታቹ (3ኛ ዮሐንስ 1-8)

ሐዋርያው ዮሐንስ ይህንን ሰው በጣም ይወደው እንደ ነበር አያጠያይቅም። በሰላምታው ላይ «ለተወደደው፥ ለማፈቅረው» እንዲሁም በቁጥር 5 ላይ «ወዳጄ» ብሎ ጠርቶታል። እነዚህ አጠራሮች እኛ «ውድ አቶ ዮናስ» (ምናልባት እኛ አቶ ዮናስን በግል ላናውቀው እንችላለን) እንደምንለው ዓይነት ተራ የሆኑ የተለምዶ አጠራሮች አልነበሩም። ቁጥር 4 እንደሚያመለክተው ጋይዮስ፥ ዮሐንስ ወደ ጌታ ከመራቸው ሰዎች አንዱ ሊሆን እንደሚችል አሳብ ይሰጣል። እንደዚሁም እኛ በክርስቶስ ወደ ማመን የመራናቸው ሰዎች በተለይ ለእኛ የከበሩ ናቸው። ሆኖም የተወደደው ሐዋርያ አማኞችን ሁሉ እንደ «ልጆቹ» (1ኛ ዮሐንስ 2፡1፥ 12፥ 18) ነበር የሚመለከታቸው።

ጋይዮስ እኔ በመጋቢነት የማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን አባል ቢሆን ኖሮ እርሱን ለመውደድ ምንም ችግር አይኖርብኝም ነበር! የዚህን እጅግ በጣም ጥሩ ሰው የግል ባሕርያት ተመልከት።

መንፈሳዊ ጤንነት (ቁ. 2)፡- እዚህ ላይ ዮሐንስ ምናልባት የተወደደው ወዳጁ ሕመም እንዳደረበትና ዮሐንስም ጤናው እንዲመለስለት እየጸለየ እንደ ነበር የሚጠቁም ይመስላል። «ነፍስህ እንደሚከናወን በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህ ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ።» ነገሩ ይህ ከሆነ ሰው በመንፈስ ጤናማ ቢሆንም በሰውነት መታመም እንደሚቻል የሚያሳይ ማስረጃ ነው ማለት ነው። ሆኖም፥ እንደዚህ ዓይነት ሰላምታ በዚያን ዘመን በጣም የተለመደ በመሆኑ ብዙ የምንነጋገርበት አይደለም።

ሆኖም ጋይዮስ «መንፈሳዊ ጤንነቱ» ለሁሉም የሚታይ ሰው እንደነበር ግልጥ ነው። «የውጪው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል» (2ኛ ቆሮ. 4፡16)። የአካል ጤንነት የተመጣጠነ ምግብ፥ የእንቅስቃሴ፥ የንጽሕና፥ የተገቢ ዕረፍትና የተስተካከለ ሚዛናዊ ሕይወት ውጤት ነው። መንፈሳዊ ጤንነትም እንደዚሁ የተመሳሳይ ነገሮች ውጤት ነው። ራሳችንን በእግዚአብሔር ቃል መመገብና ያንን ምግብ እግዚአብሔርን በመምሰል ልምድ ሥራ ላይ ማዋል አለብን (1ኛ ጢሞ. 4፡6-7)። ራሳችንን በንጽሕና መጠበቅና (2ኛ ቆሮ. 7፡1) በዚህ ዓለም ያለውን ርኩሰት እና እድፍ መራቅ (2ኛ ጴጥሮስ 1፡4፤ ያዕቆብ 1፡27)

ይገባናል። እንቅስቃሴና አገልግሎት አስፈላጊ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፥ በጌታ ዓርፈን ከእሱ ጋር ባለን ኅብረት አዲስ ጉልበት ማግኘታችንም አስፈላጊ ነው (ማቴ. 11፡ 18-30)። ሚዛናዊ ሕይወት፡ - ጤናማ፥ ደስተኛና እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት ነው።

መልካም ምስክርነት (ቁ. 3-4)፡ - ጋይዮስ ለእግዚአብሔር ቃል የታዘዘና «በእውነት የተመላለሰ» (2ኛ ዮሐንስ 4 ተመልከት) ሰው መሆኑ የታወቀለት ነበር። ከወንድሞች አንዳንዶቹ ዮሐንስን በጎበኙበት ጊዜ ጋይዮስ ለመልካም ክርስቲያናዊ ሕይወት አንጸባራቂ ምሳሌ እንደ ነበር በደስታ መስክረዋል። በራሴ የመጋቢነት ልምዴ ብዙ ጊዜ ሰዎች «እገሌት የአንተ ቤተ ክርስቲያን አባል ናት?» ሲሉኝ፥ ወይም ደግሞ «ከቤተ ክርስቲያን አባላትህ አንዱን በደንብ አውቀዋለሁ!» ሲሉኝ ምን ሊነግሩኝ ይሆን እያልኩ እሸማቀቃለሁ። ዮሐንስ ግን የጋይዮስ ስም ሲነሣ ፈጽሞ አይፈራም ነበር!

ጋይዮስን እንደዚህ ላለው መልካም ምስክርነት ያበቃው ምንድን ነው? የእግዚአብሔር እውነት ነው። እውነት «በውስጡ» ነበርና ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ እንዲሄድ አስችሎታል። ጋይዮስ ቃሉን ያነብ፥ በጥሞና ያሰላስለው፥ ደስ ይሰኝበትና በዕለት ተዕለት ኑሮው ያዘወትረው ነበር (መዝ. 1፡ 1-3 ተመልከት)። ምግብን መፍጨት ለአካል እንደሆነ ሁሉ የእውነት ቃሉን ማሰላሰል ደግሞ ለነፍስ ነው። ዝም ብሎ ቃሉን መስማት ወይም ቃሉን ማንበብ ብቻ በቂ አይደለም። በውስጣችን «ልናብላላው» እና የውስጥ ሰውነታችን ክፍል ልናደርገው ይገባናል (1ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 13 ተመልከት)።

የጋይዮስ ሕይወት ሙሉ በሙሉ በእውነት የተከበበ እንደ ነበር ግልጥ ነው። እውነተኛ አኗኗር ከሕያው እውነት ይመነጫል። እውነት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ (ዮሐንስ 14፡ 6) የእግዚአብሔር እውነት በሆነው (ዮሐንስ 17፡ 17) በቃሉ ውስጥ ተገልጧል። መንፈስ ቅዱስም እውነት ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡ 7)፤ እውነትንም ያስተምረናል። የእግዚአብሔር መንፈስ በቃሉ በመጠቀም የእግዚአብሔርን ልጅ ለመግለጥና ከዚያም ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ «በእውነት እንድንሄድ» ያስችለናል።

ተግባራዊ አገልግሎት (ቁ. 4-8)፡ - ጋይዮስ ከእውነት ጋር አብሮ የሚሠራ ነበር (ቁ. 8)። ተግባራዊ በሆኑ መንገዶች ቃሉን የሚያገለግሉትን

ረድቷል። ጋይዮስ ራሱ ሰባኪ ወይም አስተማሪ እንደ ነበር የሚጠቁም ነገር የለንም፤ እንደዚያ ለሚያደርጉት ግን ልቡንና ቤቱን ከፍቶ ነበር።

በዚያን ዘመን ስለነበረው የክርስቲያን መስተንግዶ አስፈላጊነት ከዮሐንስ ሁለተኛ መልእክት ተምረናል። ዮሐንስ «የተመረጠችው እመቤት» የሐሰት አስተማሪዎችን እንዳታስተናግድ አስጠንቅቋታል (2ኛ ዮሐንስ 7-11)፤ በዚህ ደብዳቤ ግን ጋይዮስን እውነተኛ ለሆኑት የቃሉ አገልጋዮች ስላደረገላቸው መስተንግዶ አመስግኖታል። ጋይዮስ በጠቅላላው ለወንድሞች ብቻ ሳይሆን በተለይ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ኅብረት ለማድረግና ለማገልገል ለሚመጡት «እንግዶች» ማበረታቻ ነበር (ዕብ. 13፡2 ተመልከት)።

በዚህ በሚያስፈራና ዓመፅ በሞላበት ዘመን ግን እንግዶችን ወደ ቤታችን መቀበል ቀላል አይደለም። በእርግጥ በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ተጓዥ አገልጋዮች ከራሳቸው ማኅበር የትብብር ደብዳቤ ይይዙ ነበር (ሮሜ 16፡ 1)፤ ስለዚህ ልናስተናግዳቸው ስለምንፈልገው ሰዎች አንዳንድ ነገሮች ማወቃችን አስፈላጊ ነው። ከዚህም በተጨማሪ እምነትንና ፍቅርን ይጠይቃል። ባለቤቴና እኔ ቤታችንን ማካፈል ደስ የሚያሰኘንን ያህል አንዳንድ እንግዶችን ስናሰናብት ግን በቅሬታ ምትክ እፎይታ እንደሚሰማን ልንደብቃችሁ አልፈልግም፤ ሆኖም ብዙውን ጊዜ ደግሞ ሌሎቹ እንግዶቻችን ደግሞ ለቤታችን በረከት የሆኑበት ጊዜ አለ። «ሳያውቁ መላእክትን እንደተቀበሉ» ሰዎች ዓይነት ስሜት ይሰማናል።

ጋይዮስ ቤቱን ብቻ አልነበረም የከፈተው። ነገር ግን ልቡን ለፍቅር፥ እጆቹንም ለእንግዶቹ የገንዘብ እርዳታ ለመስጠት ከፍቶ ነበር። «እንደሚገባ አድርገህ በጉዞአቸው ብትረዳ» የሚለው ሐረግ «በጉዞአቸው መርዳት» ማለት ነው። ይህ ገንዘብንና ምግብን መስጠት፥ ልብሶችን ማጠብና መስፋት ሊያካትት ይችላል (1ኛ ቆሮ. 16፡6፤ ቲቶ 3፡ 13 ተመልከት)። መቼም፥ እምነታችን በሥራችን መፈተን አለበት (ያዕቆብ 2፡ 14-16)። እንዲሁም ፍቅራችን በቃል ብቻ ሳይሆን በሥራም መገለጥ አለበት (1ኛ ዮሐ. 3፡ 16-18)።

ቅዱሳንን በዚህ ዓይነቱ ተጨባጭ መንገድ ሌሎችን ለመርዳት የሚያነሣሣቸው ምክንያት ምን ይሆን? በመጀመሪያ ደረጃ አድራጎቱ እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ነው። በቁ. 6 ላይ «ለእግዚአብሔር

እንደሚገባ» የሚለው ትርጉሙ «ለእግዚአብሔር እንደሚደረግ» ማለት ነው። ሌሎችን ለማገልገል መሥዋዕትነት ከምንከፍልበት ጊዜ የበለጠ «እግዚአብሔርን የምንመስልበት» ጊዜ አይኖርም። «በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን» (ቆላ. 1፡12)። እነዚህ የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች የጌታን ስም የሚወክሉ ስለነበሩ ለእነርሱ የተደረገ ማንኛውም አገልግሎት ኢየሱስ ክርስቶስን በቀጥታ ማገልገል ነበር (ማቴ. 10፡40፤ 25፡34-40)።

ሁለተኛው ምክንያት የእግዚአብሔርን ባሪያዎች መደገፍ (መርዳት) ለጠፉት መመስከር በመሆኑ ነው (3ኛ ዮሐንስ 7)። በዚያን ዘመን አሳባቸውን እያካፈሉና ገንዘብ እየለመኑ ወዲህ ወዲያ የሚሉ ብዙ አስተማሪዎች እንደነበሩ ማስታወስ አለብን። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ባሪያዎች እርዳታ እንደሚገባቸው በግልጥ ከማስተማሩም (ሉቃስ 10፡7)፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው ግልጥ መመሪያም እርዳታው የሚዋጣው ከእግዚአብሔር ሕዝብ መሆን እንደሚገባው ነው። «ከአሕዛብ አንዳች ሳይቀበሉ» ማለት እነዚህ የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች ካልዳኑት እርዳታን አይጠይቁም ነበር ለማለት ነው። አብርሃም አብረውት የነበሩትን የሱን መመሪያ እንዲከተሉ ባያስገድዳቸውም እንኳ እርሱ ግን የዚህ ዓይነት መመሪያ ነበረው (ዘፍ. 14፡21-24)። ብዙ መጋቢዎች መባ በሚሰበሰብበት ጊዜ በጉባኤው ውስጥ ካሉት ከማያምኑት ሰዎች አንዳችም ሳንቲም እንደማይፈልጉ በግልጥ ይናገራሉ።

የእግዚአብሔር ሕዝቦች በበቂ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ባሪያዎች ሲረዱ ይህ ለጠፉት ከፍተኛ ምስክር ይሆናል። ነገር ግን አገልጋዮች፥ አብያተ ክርስቲያናትና ሌሎችም ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ካልዳኑ ሰዎችና ከተለያዩ የንግድ ድርጅቶች እየተዘዋወሩ እርዳታን ቢጠይቁ ይህ ክርስትናን ርካሽና የንግድ ሥራ አራማጅ ያስመስለዋል። ይህም ማለት ሰውየው ያልተለወጠ ቢሆንም ስጦታው ደኅንነትን እንደማይገዛለት እያወቀ በገዛ ፈቃዱ የሚሰጠውን ስጦታ የእግዚአብሔር ባሪያዎች አንቀበልም ማለት አለባቸው ማለት አይደለም። እርግጥ ያንጊዜም ቢሆን በጣም ጥንቁቅ መሆን ይኖርብናል። ለአብርሃም የሰዶም ንጉሥ በፈቃዱ ስጦታ ቢያቀርብለትም እርሱ ግን ለመቀበል አልወደደም (ዘፍ. 14፡17-24)።

የማገልገል ሦስተኛው ጥቅሙ፥ ማገልገል ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ተገዢነትን ማስመስከሪያ በመሆኑ ነው። «እኛ እንዲህ ያሉትን በእንግድነት ልንቀበል ይገባናል» (3ኛ ዮሐንስ 8)። ይህ የመስተንግዶና የእርዳታ አገልግሎት መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር ነው። ገላትያ 6፡6-10 ግልጥ እንደሚያደርገው፥ ከአንድ አገልጋይ መንፈሳዊ በረከትን የሚቀበሉ ሰዎች ከቁሳዊ በረከቶችም አብረው ሊካፈሉ እንደሚገባ ግልጥ ያደርገዋል። እንዲሁም 1ኛ ቆሮንቶስ 9፡7-11 ይህንኑ መመሪያ በተጨማሪ ያብራራዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ በመጋቢነት ባገለገልኩበት ቤተ ክርስቲያን የነበረ አንድ ዲያቆን «ለምትኖርበት ቤት ባለቤት የተመገብክበትን የቀለብ ሒሳብ ክፈል» የሚል አባባል ነበረው። የቤተ ክርስቲያን አባላት አሠራታቸውንና መባቸውን በዓለም ዙሪያ እየላኩ የራሳቸውን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ግን ችላ ማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

ዮሐንስ በቁጥር 8 ላይ አራተኛውን የአገልግሎት አስፈላጊነት ምክንያት «ከእውነት ጋር አብረን እንድንሠራ» በማለት ገልጦታል። ጋይዮስ እውነትን የተቀበለና በእውነት የሚኖር ብቻ ሳይሆን፥ እውነት እንዲስፋፋም በተጨማሪ የረዳ «አብሮ የሚሠራ» ነበረ። እርግጥ መንፈሳዊ ስጦታዎቹ ምን እንደነበሩ ወይም ጉባኤውን እንዴት እንዳገለገለ በግልጥ ባናውቅም፥ ጋይዮስ እውነትን የሚያስተምሩትንና የሚሰብኩትን በመርዳት፥ እውነትን የማስፋቱንና ለእውነት የመሟገቱን ሥራ እንዳገዘ እናውቃለን።

እኔም በተጓዥ ወንጌላዊነቴ ጊዜ በብዙ ቤቶች ውስጥ በእንግድነት እቆይ ነበር። ለሥራዬም ማበረታቻ አግኝቼአለሁ። ያስተናገዱኝ ሰዎች ልዩ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ላይሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን በቸርነት መስተንግዶአቸው ያበረከቱት አገልግሎት፥ እኔንም እንደ ስጦታዬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል አስችሎኛል። በአገልግሎቴ ውስጥ የሚገኘው ማንኛውም በረከት ለእነርሱም ጭምር የሚደርሳቸው ይሆናል(ፊልጵ. 4፡17)።

መናፍቅነትን መቃወምና የሐሰት አስተማሪዎችን አለማስተናገድ አንድ ነገር ሲሆን፥ እውነትን ለማስፋፋት ቤታችንን (እንዲሁም ቦርሳችንን) መክፈት ደግሞ ሌላ ነገር ነው። አሉታዊውም ሆነ አዎንታዊውም እርምጃ ሁለቱም ያስፈልጉናል። እንደ ጋይዮስ ያሉ በመንፈሳቸው ጤናማ የሆኑ፥ ለቃሉ ታዛዦችና እውነት እንዲስፋፋ ያላቸውን ሀብትና ንብረት የሚያካፍሉ

ብዙ ሰዎች ያስፈልጉናል። ሆኖም ግን ሁሉም ሰዎች እንደ ጋይዮስ አይደሉም! በመቀጠል ደግሞ ከጋይዮስ ሙሉ በሙሉ ልዩ ከሆኑት ክርስቲያኖች አንዱ የሆነውን ሰው ማንነት እንመለከታለን።

## አምባገነኑ ዲዮጥራጢስ (3ኛ ዮሐንስ 9-10)

እንደሚታወቀው አለቃ ለመሆንና የራሳቸውን መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚወተውቱ ብዙ አባላት ያሏቸው አብያተ ክርስቲያናት ሞልተዋል። በበኩሌም እንዳረጋገጥኩት አንዳንድ ጊዜ አምባገነናዊ ሥልጣንን የሚጨብጠውና አገልጋይ ማለት «ባሪያ» ማለት እንደሆነ የሚዘነጋው ራሱ መጋቢው መሆኑን ነው። በዚያው መጠን ደግሞ «ፈላጭ ቆራጭ ነኝ» የሚለው ወይም «የቀደምትነት መብት አለኝ» ብሎ የሚያስበው የቤተ ክርስቲያኒቱ የረዥም ጊዜ አባል ይሆናል።

የጌታችን ደቀ መዛሙርት በመንግሥተ ሰማያት ከእነርሱ መካከል የሚበልጠው ማን እንደሆነ ብዙ ጊዜ ይከራከሩ ነበር (ማቴ. 18፡1 ጀምሮ)። ኢየሱስ ግን ለአገልግሎት አርአያ ሊሆንላቸው የሚገባው ሥልጣኑን በሰዎች ላይ የሚጭነው ሮማዊ ባለሥልጣን ሳይሆን እንደ ትሑት ባሪያ ሆኖ የመጣው አዳኙ ራሱ መሆኑን አሳስቧቸዋል (ፊልጵ. 2፡1 ጀምሮ)። ከሰላሣ ዓመታት በላይ በሆነው የአገልግሎት ዘመኔ ውስጥ፥ የአገልጋይ አርአያነትን ሲለዋወጥ አይቻለሁ፤ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ከዚያ የተነሣ እየተጠቃች ነች። ዛሬ «የተሳካለት አገልጋይ» ከተገዢ ባሪያነት ይልቅ እንደ አንድ ትልቅ ባለሥልጣን ለመሆን ሲሞክር ይስተዋላል። ከፎጣ ይልቅ ሽቦየለሽ ስልክ ይይዛል፤ በልቡም የሰፈነው የጠፉት ነፍሳትና የእግዚአብሔር በጎች ፍቅር ሳይሆን የራስ ወዳድነት ስሜት ነው።

ዲዮጥራጢስ በትዕቢት የተወጠረ ነበር። የበላይነትን ለኢየሱስ ክርስቶስ ከመስጠት ይልቅ (ቆላ. 1፡18) ለራሱ አድርጎት ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለማንኛውም ነገር የመጨረሻውን ውሳኔ የሚሰጠው እርሱ ነበር፤ ውሳኔዎቹንም የሚወስነው በአንድ ነገር ላይ ብቻ በመመርኮዝ ነበር፤ ይኸውም «ይህ ነገር ለዲዮጥራጢስ ምን ጥቅም ያስገኝለታል?» ለሚለው ጥያቄ በሚያገኘው መልስ ነው። የእርሱ አስተሳሰብ «እርሱ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» (ዮሐንስ 3፡30) ከሚለው

ከመጥምቁ ዮሐንስ መንፈስ ፈጽሞ የተለየ ነበር። የግሪኩ ቃል «ራሱን ማሳደግ» የዲዮጥራጢስ ቋሚ ባሕርይ እንደ ነበር ያመለክታል።

ምን ጊዜም በቤተ ክርስቲያን አባላቶች መካከል አምባገነንነት ሲሰፍን ችግሮች መኖራቸው የማይቀር ነው፤ ምክንያቱም መንፈሳዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች የዚያን ዓይነት አመራር ለመቀበል ፈቃደኛ ስለማይሆኑ ነው። አንድ አባል የግድ የእኔ አሳብ ካልተፈጸመ ስለሚልና ከዚህም የተነሣ የአካሉ ብልቶች በራሳቸው ስጦታ መጠቀም ስለማይችሉ መንፈስ ቅዱስ ያዝናል። በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንደ ዲዮጥራጢስ ባሉ ሰዎች ግትር አገልግሎቶች የተነሣ ምን ያህል ልቦች እንደተሰበሩና ምን ያህል ቤተ ክርስቲያናት እንደጠፉ እናውቃለን። እስቲ ይህ ሰው ምን ያደርግ እንደ ነበር እንመልከት።

ሐዋርያው ዮሐንስን አይቀበልም ነበር (ቁ. 9)፡- አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ (ዲዮጥራጢስ ሽማግሌ የነበረ ሊሆን ይችላል) ከራሱ ከጌታችን ሐዋርያት ከነበሩት ከአንዱ ጋር ኅብረት አልነበረውም ብሎ ማሰብ የማይታመን ነው! ስለዚህ ዲዮጥራጢስ ከሐዋርያው ዮሐንስ ምን ያህል ሊማር በቻለ ነበር! ነገር ግን በሕይወቱ ውስጥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዋነኛውን ስፍራ የሰጠ አልነበረም፤ ስለዚህ ዲዮጥራጢስ ሽማግሌውን ሐዋርያ በዚሁ ዓይነት መንገድ አቃልሎ ቢመለከተው አያስደንቅም።

ዲዮጥራጢስ ለምን ሐዋርያው ዮሐንስን አልተቀበለም? ግልጥ የሆነው ምክንያት፡- ሐዋርያው ዮሐንስ የዚህን ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አምባገነን የመሆን ፍላጎትን በመቃወሙ መሆን አለበት። ሐዋርያው ዮሐንስ ለዲዮጥራጢስ እንደ ጦር የሚያስፈራ ነበር፤ ምክንያቱም ሐዋርያው ዮሐንስ የሐዋርያነት ሥልጣን ስለነበረው ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ በእርግጥም ስለ ዲዮጥራጢስ እውነቱን በማወቁ ጥፋቱ ይፋ እንዲወጣ ይፈልግ ነበር። የዲዮጥራጢስ ሕይወት የዲያብሎስ ዋነኛ መሣሪያዎች ከሆኑት ውስጥ በሁለቱ ማለትም በትዕቢትና ራስን በማክበር ላይ የተመሠረተ ስለነበረ በዚያች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰይጣን ሥራ ላይ ነበር። ስለዚህ ሐዋርያው ዮሐንስ በዚህ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ቢገባ ተሸናፊ የሚሆነው ራሱ ሰይጣን ይሆናል ማለት ነው።

ስለ ሐዋርያው ዮሐንስ ዋሽቶ ነበረ (ቁ. 10)፡- በእኛ ላይ በክፉ ቃል እየለፈለፈ የሚለው ሐረግ «በእኛ ላይ ሐሰተኛና ባዶ ክሶችን መሰንዘር» ማለት ነው። ዲዮጥራጢስ ስለ ዮሐንስ ይናገር የነበረው ሐሰትና ትርጉም የለሽ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን የዚያን ዓይነት ወሬ መስማት የሚወዱና የሚያምኑበትም ሰዎች ነበሩ! እርግጥ ዲዮጥራጢስ እነዚህን ክሶች በዮሐንስ ላይ የተናገረው ዮሐንስ ስለ ራሱ ለመከራከር እንዳይችል እርሱ በሌለበት በአንድ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ ነበር፤ ነገር ግን ዮሐንስ ከአምባገነኑ ዲዮጥራጢስ ጋር ፊት ለፊት የሚነጋገርበት ቀን እንደሚመጣ ያለጥርጥር ገልጦ ነበር።

ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ባሪያዎች በተለይም ሰፊ አገልግሎት ስላላቸውና በደንብ ስለሚታወቁ ባሪያዎች የሚያነቡትንና የሚሰሙትን ማንኛውንም ነገር ተሽቀዳድመው እንዳያምኑ መጠንቀቅ አለባቸው። በተለይም አንዳንድ ጋዜጦችና መጽሔቶች ዋናው ዓላማቸው እግዚአብሔር አገልግሎታቸውን የባረከላቸውን ሰዎች ስም ማብጠልጠል በመሆኑ እነኝህን የመሳሰሉትን በበኩሌ ማንበብ ትቻለሁ። አንድ ቀን ለአንድ ወዳጄ ስለ አንድ የታተመ ጽሑፍ አጫውቼው ነበር። እርሱም እንዲህ አለኝ፡- «አዎን አዘጋጁን በደንብ አውቀዋለሁ። ልክ እንደ ቀለም መምጠጫ ወረቀት ነው። የሰማውን ሁሉ አሜን ብሎ በመቀበል ማንኛውንም ነገር በማጋነን አዟዙሮ መልሶ ያወጣዋል»። እነዚህን የመሳሰሉትን የሐሰት ዜናዎች በፊልጵስዩስ 4፡8 ውስጥ በምናገኘው መመሪያ መሠረት ብናጣራቸው መልካም ነው።

የሐዋርያው የዮሐንስን ተባባሪዎች አልተቀበለም (ቁ. 10)፡- ዲዮጥራጢስ ሌሎቹን ወንድሞች እንኳ ከዮሐንስ ጋር ኅብረት ስለነበራቸው ብቻ አይቀበልም ነበረ! እርሱ ከማይፈልገው ሰው ጋር ኅብረት ስለሚያደርጉ ነበር የጠላቸው፤ ዳሩ ግን በዚህ መልኩ በሰዎች ላይ በመደዳው ጥላቻ ማሳደር ተገቢ አይደለም፤ ምክንያቱም ማንም ሰው ወንድሙ እያደረገ ስላለው ነገር ሙሉ በሙሉ ለማወቅ አስፈላጊዎቹን መረጃዎች ማግኘት ስለማይችል ነው! ለምሳሌ እኔ ከምቃወመው ሰው ጋር ኅብረት አላችሁ በማለት ከእናንተ ጋር ኅብረት ለማድረግ እንቢ ብል፥ የኅብረታችሁ ደረጃ እምን ድረስ እንደሆነ እንዴት ለማወቅ እችላለሁ? ምንስ አብራችሁ እንዳደረጋችሁ ለመከታተልና ለማረጋገጥ እችላለሁ? አንድ ሰው ጓደኞቹ ማን እንደሆኑ እና ምን

እንደሚያደርጉ ለማወቅ ፈልጎ በግሉ ክትትል ቢያደርግ እና ስለዚህ ጉዳይ የሚተባበሩት ሠራተኞችና ኮምፒዩተር ቢኖረው እንኳ አይችልም።

መጽሐፍ ቅዱስ ከሐሰተኞች ጋር ምንም ዓይነት ኅብረት ሊኖረን እንደማይገባና (ይህንን በ2ኛ ጴጥሮስ ውስጥ አጥንተነዋል) ከማያምኑ ሰዎች ጋር ከመተባበር መቆጠብ እንዳለብን (2ኛ ቆሮ. 6፡14 ጀምሮ) በግልጽ ይናገራል። እንደዚሁም የትምህርታቸው ሁኔታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚቃረነውን ሰዎችም መራቅ አለብን (ሮሜ 16፡17-19)። ይህም ሲባል ኅብረት ማድረግ ያለብን መጽሐፍ ቅዱስን እኛ በምንተረጉመው መንገድ ከሚተረጉሙት ጋር ብቻ ነው ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም መልካሞችና እግዚአብሔርን የሚመስሉ ሰዎች እንኳ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ወይም ትንቢትን በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ላይስማሙ ስለሚችሉ ነው። እውነተኞች ክርስቲያኖች በእምነት መሠረታዊ ትምህርቶች ላይ አንድነት ሲኖራቸው፥ በሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ባላቸው አተረጓጎም ግን ሙሉ በሙሉ ላይስማሙ ይችላሉ።

ስለዚህ እኔ ከማልፈልጋቸው ሰዎች ጋር ጓደኝነት ስላለው ብቻ ከወንድሜ ጋር መቆራረጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ዲዮጥራጢስ ዮሐንስን በመቃወሙ ከዮሐንስ ጋር የተባበሩትን አማኞች መቀበል አልፈለገም። እንዲያውም በዚህ ብቻ ሳይገታ ሌላም ጥፋት ፈጽሟል!

ከእርሱ ጋር ያልተስማሙትን ሰዎች ቀጥቶአቸዋል (ቁ. 10)፡- የሐዋርያው የዮሐንስን ተባባሪዎች የተቀበሉት የቤተ ክርስቲያን አባላት ከቤተ ክርስቲያን የመባረር ዕድል ገጥሟቸዋል! ይህም ራሱን የቻለ የበቀል እርምጃ ነበር። ዲዮጥራጢስ እነዚህን ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ለማባረር ሥልጣኑም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱም አልነበረውም፤ ሆኖም ግን አድርጎታል። ሰዎች የቱንም ያህል «ሃይማኖታዊ አምባገነኖች» እንኳ ቢሆኑ ተቃውሞአቸውን ከመጠን በላይ እንዳያደርጉት መጠንቀቅ አለባቸው፤ አለበለዚያ ግን በነርሱም ላይ ተመሳሳይ ተቃውሞ ሊነሣባቸው ይችላል።

አዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን ሥነ- ሥርዓትን ያስተምራል፤ ለእነዚህም መመሪያዎች መታዘዝ ያስፈልጋል፤ ዳሩ ግን የቤተ ክርስቲያን ሥነ-ሥርዓትን አንድ አምባገነን ራሱን ለመከላከል ሲል የሚጠቀምበት የጦር መሣሪያ አይደለም። ጉባኤው ቅድስናን ለማሳደግና እግዚአብሔርን ለማስከበር

የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው። ከዚህ ውጪ አንድ መጋቢ «ሥልጣኑን የሚያሳይበት» ወይም የቤተ ክርስቲያኑ ሽማግሌዎች ጉባኤ እንደ ፍርድ ሸንጎ ቅጣት የሚወስኑበት አይደለም። ይልቁኑ በዚህ ሥነ -ሥርዓት አማካይነት ጌታ የተሳሳተውን የእግዚአብሔር ልጅ ለማዳንና ለማስተካከል በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚጠቀምበት መንፈሳዊ ሥልጣን ነው።

የቤተ ክርስቲያን «አምባገነኖች» አደገኞች ሰዎች ናቸው፤ ደግነቱ ግን እነሱን ለይቶ ለማወቅ ቀላል መሆኑ ነው። ስለ ራሳቸውና «ለጌታ ስላደረጉት» ነገር ማውራት ይወዳሉ። እንደዚሁም ከእነርሱ ጋር በማይስማሙት ሰዎች ላይ የመፍረድና የመኮነን ልማድም አላቸው። በሌሎች አብያተ ክርስቲያኖች ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድና በገዛ ራሳቸው ፍላጎት ባወጧቸው ጥቃቅን መለያዎች ሳቢያ ክርስቲያኖችን በመከፋፈል የተካኑ ናቸው። ኅብረታቸውን የሚመሠርቱት ለእምነት መሠረታዊ በሆኑት ትምህርቶች ላይ ሳይሆን ለግለሰብ ባላቸው አመለካከት ነው። አሳዛኙ ነገር እነዚህ «አምባገነኖች» እግዚአብሔርን እንደሚያገለግሉና ኢየሱስ ክርስቶስን በማስከበር ላይ እንዳሉ ማመናቸው ነው።

በበኩሌ ካለኝ ረጅም የሥራ ልምድ እንደተረዳሁት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥና በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ለሚነሣው ለአብዛኛው ክርክርና መከፋፈል ዋነኞቹ መንስኤዎች ግለሰቦች መሆናቸው ነው። ዋና ባልሆኑ ትምህርቶች፥ ትርጉሞችና ተዛምዶዎች ላይ ከማተኮር ይልቅ ወደ አዲስ ኪዳን መርሆ ተመልሰን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት እና ሥራ ለኅብረታችን መፈተኛ ብናደርገው መልካም ነው፤ ነገር ግን እንደ ዲዮጥራጢስ ያሉ ከፋፋዮችና አስመሳዮች ብዙዎቹን የዋሆች፥ ያልበሰሉና ያልተማሩ አማኞችን እንዲከተሏቸው ማወናበዳቸው ምንጊዜም የማያቋርጥ ነው።

## በምሳሌነቱ የሚጠቀሰው ድሜጥሮስ
(3ኛ ዮሐንስ 11-12)

አንድ መዝገበ ቃላት «ምሳሌ» የሚለውን ቃል «ፍጹም የሆነ፥ አርአያ፥ ሊመስሉት፥ ወይም ሊከተሉት የሚገባ ሞዴል» ይለዋል። ድሜጥሮስ የዚህ ዓይነት ክርስቲያን ነበር። ዮሐንስ ዲዮጥራጢስን እንዳንመስል

አስጠንቅቋል። «በአርአያነት የምትከተሉት ሰው ካሻችሁ ድሜጥሮስን ምሳሌአችሁ አድርጉ!» ማለቱ ነበር።

ሆኖም ግን ሰብአዊ ፍጡራን የሆኑ መሪዎችን ምሳሌ ማድረግ ትክክለኛ ነገር ሊሆን ይችላልን? አዎን ይችላል! መሪዎቹ በበኩላቸው ኢየሱስ ክርስቶስን የሚመስሉ ከሆኑ ምሳሌ ልናደርጋቸው እንችላለን። «ወንድሞች ሆይ፥ እኔን የምትመስሉ ሁኑ፥ እኛም ምሳሌ እንደምንሆንላችሁ፥ እንዲሁ የሚመላለሱትን ተመልከቱ» (ፊልጵ. 3፡17)። «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» (1ኛ ቆሮ. 11፡1)። እናንተና እኔ እግዚአብሔርን ልናየው አንችልም፤ ነገር ግን በልጆቹ ሕይወት ውስጥ ሲሠራ ልናየው እንችላለን። የሌላ አማኝ እግዚአብሔርን የመሰለ ሕይወትና የተሰጠ አገልግሎት ምሳሌነት ለእኔ ሁልጊዜም ማበረታቻና ማነቃቂያዬ ነው። በመልካም ምሳሌነታችን «ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ» (ዕብ. 10፡24)።

ድሜጥሮስ ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት «መልካም ምስክርነት» ስለነበረው ምሳሌነቱን ሊከተሉት የሚገባ ሰው ነበር። አባላት በሙሉ ያውቁት፥ ይወዱትና ጽኑ በሆነው ሕይወቱና አገልግሎቱ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። «ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ» (ሉቃስ 6፡26) የተባለው አደገኛ ነገር ቢሆንም፥ በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አማኞች በሙሉ ሕይወታችሁንና ምስክርነታችሁን ከወደዱላችሁ ግሩም ነገር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የዳኑትና ያልዳኑት፥ መልካሞችና ክፉዎች በሙሉ ስለ እኛ መልካም የሚናገሩ ከሆነ፥ ለዘብተኞች ወይም ከሁሉም ተመሳስለን የምንኖር ነን ማለት ሊሆን ይችላል።

ድሜጥሮስ ግን መልካም ምስክርነት የነበረው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉት ምእመናን ጋር ብቻ ሳይሆን፥ ከቃሉም (ከእውነት) መልካም ምስክርነት ነበረው። ድሜጥሮስ እንደ ጋይዮስ ሁሉ፥ በእውነት የሄደና ለእግዚአብሔር ቃል የታዘዘ ሰው ነበር። ይህም ሲባል እነዚህ ሰዎች ፍጹማን ነበሩ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን በሕይወታቸው የጸኑና ጌታን ለማስከበር የሚጥሩ ነበሩ ማለት ነው።

ቤተ ክርስቲያንና ቃሉም፥ ለድሜጥሮስ የክርስትና ሕይወት ምስክሮች ነበሩ፤ እንደዚሁም ራሱ ሐዋርያው ዮሐንስ ምስክር ነበረ። (ይህ ማለት

ድሜጥሮስ ከዲዮጥራጢስ ጋር መጋጨቱ አይቀርም ማለት ነው!) የተወደደው ሐዋርያ ከመጀመሪያውኑ ድሜጥሮስ የእግዚአብሔር ሰው እንደነበረ አውቆ ነበር፥ ዮሐንስም ይህንን ለመመስከር አያፍርም።

ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያኗን እንደሚጎበኝና ዲዮጥራጢስን እደሚጋፈጠው አስጠንቅቆ ነበር (3ኛ ዮሐንስ 10)። ጋይዮስና ድሜጥሮስ ደግሞ «እምባገነኑን» በመቃወም ከዮሐንስ ጎን እንደሚሰለፉ አያጠራጥርም። እነርሱ እውነትን የሚደግፉና ለመንፈሳዊው ሥልጣን ራሳቸውን የሚያስገዙ ሰዎች ነበሩ። እነርሱ እውነትን የተከተሉ ናቸውና ሌሎችም አማኞች እነርሱን ቢመስሉ ምንም ጉዳት አይደርስባቸውም ነበረ።

የደብዳቤው ማጠቃለያ (ቁ. 13-14) ከ2ኛ ዮሐንስ መልእክት ማጠቃለያ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይህም ምናልባት በዮሐንስ ዘመን ደብዳቤዎችን ለመዝጋት የተለመደ መንገድ ሊሆን ይችላል። ሐዋርያው ቤተ ክርስቲያኒቷን በቅርቡ ለመጎብኘት ዕቅድ ነበረው። ይህም ለዲዮጥራጢስ ማስጠንቀቂያ፥ ለጋይዮስና ለድሜጥሮስ ግን ማበረታቻ ነበረ። የተወደደው ዮሐንስ ከማኅበሩና ከመሪዎቹ ጋር በደብዳቤ አማካይነት ከመገናኘት ይልቅ በግንባር አግኝቶ የሚያነጋግራቸው «ብዙ ጉዳዮች» ነበሩት።

«ሰላም ለአንተ ይሁን» (ቁ. 14) የሚለው የምኞት መግለጫ ለጋይዮስ እውነተኛ የሆነ የማበረታቻ ስንብት ነበር። በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ከነበረው መከፋፈልና ዲዮጥራጢስም መንፈሳዊ ባልሆነ መንገድ አባላቱን ከመጉዳቱ የተነሣ ልቡና ሕሊናው እንዳዘነ ጥርጥር የለውም። የግላስጎው ጆርጅ ሞሪስን ሲጽፉ «ሰላም የመሠረታዊ ነገሮች ባለቤት መሆን ነው» ብለዋል። አማኝ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ በቂ ሀብት ስላለው «በእግዚአብሔር ሰላም» ሊደሰት ይችላል (ፊልጵ. 4፡6-7፥ 13፥ 19)።

ከዚህ በተጨማሪም ዮሐንስ አብረውት ባሉት ክርስቲያኖችም ወደነ ጋይዮስ ሰላምታን ማስተላለፍን አልዘነጋም። «ወዳጆች ሰላምታ ልከውልሃል!» ክርስቲያን ጓደኛ ማግኘት እንዴት ያለ በረከት ነው! ጳውሎስ ወደ ሮም በቀረበ ጊዜ አንዳንድ ወዳጆቹ ሊቀበሉት በመሄዳቸው «ጳውሎስም ባያቸው ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገነ፥ ልቡም ተጽናና» (የሐዋ. ሥራ 28፡15) ተብሎ ተጽፏል፤ ስለዚህ ጳውሎስና ዮሐንስ ነፍሳትን ወደ ጌታ የሚያመጡ ብቻ ሳይሆኑ ወዳጅ የሚያፈሩም ነበሩ። ዲዮጥራጢስ በጣም

አምባገነን ከመሆኑ የተነሣ ወዳጆቹ እየሸሹት ነበር፤ ዮሐንስ ግን የክርስቶስን ፍቅር በማካፈሉ ወዳጆቹ እየበዙ ሄዱ።

«ወዳጆችን በየስማቸው ሰላም በልልኝ።» ሽማግሌው ሐዋርያ ረዥም ደብዳቤ ለመጻፍ አልፈለገም፤ ከዚህም ሌላ በቅርቡ ሊጎበኛቸው ዕቅድ ነበረው። አንዳንድ ጊዜ ጳውሎስ ደብዳቤዎቹን የሚዘጋው በግል ሰላምታዎች ነበረ (ሮሜ 16 ተመልከት)፤ ዮሐንስ ግን በዚህ ደብዳቤው ይህንን አላደረገም። ዮሐንስ ራሱ እንደሚያደርገው አድርጎ በምትኩ ጋይዮስ ለወዳጆቹ በግልና በተናጠል ሰላምታውን እንዲያደርስለት ፈልጎ ነበር። ዮሐንስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በዚያች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ ነበሩትም ግለሰቦች ግድ ይለው ነበር።

እነዚህን ሁለት ደብዳቤዎች ማወዳደርና ዮሐንስ ያቀረበውን የእውነት ሚዛን ማየት የሚማርክ ነው። 2ኛ ዮሐንስ የተጻፈው ለአንዲት እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴትና ቤተሰቦችዋ ሲሆን፥ 3ኛ ዮሐንስ ደግሞ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ደኅንነት በማስመልከት ለአንድ እግዚአብሔርን ለሚፈራ ሰው የተጻፈ ነበር። ዮሐንስ በውጪ ስላሉ የሐሰት አስተማሪዎች «የተመረጠችውን እመቤት» አስጠንቅቋታል። ጋይዮስን ግን በኅብረቱ ውስጥ ስላሉ አምባገነን መሪዎች ያስጠነቅቃል። በ2ኛ ዮሐንስ እንደ ተመለከተው የሐሰት አስተማሪዎች በፍቅር ገብተው እውነትን ያስክዳሉ፤ ዲዮጥራጢስ ግን ወንድሞቹን ለማጥቃት እንዲያመቸው ፈጽሞ ፍቅር በጎደለው መንገድ እውነትን አስተምሮአል።

«በእውነትና በፍቅር» መኖርና (2ኛ ዮሐንስ 3) «እውነትን በፍቅር መያዝ» (ኤፌ. 4፡ 15) ምንኛ አስፈላጊ ነገር ነው! ወንድሞችን እየጠሉ እውነትን እወዳለሁ ማለት የክርስትናን ሕይወት በአጠቃላይ ምን እንደሆነ አለመረዳትን በገዛ አንደበት መናዘዝ ነው።

የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርንና እውነትን ሲወዱና እርስ በርሳቸው ሲዋደዱ፥ በዚያ ማኅበር ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ኢየሱስ ክርስቶስን ለማክበር በጉባኤው መሥራት ይችላል፤ ነገር ግን መጋቢውን (እረኛውን) ጨምሮ በዚያ ጉባኤ ውስጥ ያለ ማንኛውም አባል ሲታበይና ዋና ሆኖ ለመታየት ሲሞክር መንፈስ ቅዱስ ያዝናል፤ ለመባረክም አይችልም። ቤተ ክርቲያኒቷ በውጪ ስትታይ የተሳካላት ልትመስል ትችላለች፤ በውስጧ

ግን ለጤናማ ኅብረት የሚያስፈልጋትን እውነተኛ የመንፈስ አንድነት ታጣለች።

ለእኛም የሚያስፈልጉን እንደ ጋይዮስና ዲሜጥሮስ ያሉ ብዙ ሰዎች ሲሆን፥ እንደ ዲዮጥራጢስ ያሉት ግን አያስፈልጉንም!

# - 10 -
# የክተት ጥሪ!
## ይሁዳ 1-7

የዚህ መልእክት ጸሐፊ የያዕቆብ ወንድም እስከሆነ ድረስ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከፊል ወንድም ነው ማለት ነው (ማርቆስ 6፡3 ተመልከት)። የጌታችን የሥጋ ወንድሞች በምድር እያገለገለ በነበረበት ጊዜ አላመኑበትም ነበረ (ዮሐንስ 7፡5)፤ ከትንሣኤው በኋላ ግን ያዕቆብ ተለወጠ (1ኛ ቆሮ 15፡7)፤ ይሁዳም በዚያን ጊዜ እንደዳነ ለመቀበል ብዙ ምክንያት አለን። የሐዋርያት ሥራ 1፡14 «ወንድሞቹ» መንፈስ ቅዱስን እየተጠባበቀ የሚጸልየው ቡድን አባላት እንደነበሩ ያስረዳናል፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 9፡5 «የጌታ ወንድሞች» በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን የታወቁ እንደነበሩ ይገልጻል።

ስለ ጸሐፊው ያን ያህል ከተናገርን ይበቃናል። ይሁዳ ለምን ይህን ደብዳቤ ጻፈ? የመናፍቃንን ቁጥር ማደግና መጠናከር ለአንባቢዎቹ ለማስጠንቀቅ ነበረ። ጴጥሮስ ሐሰተኛ አስተማሪዎች እንደሚነሡ ተንብዮ ነበር (2ኛ ጴጥሮስ 2፡1-3፤ 3፡3 ጀምሮ)፥ ትንቢቱም ተፈጽሞ ነበር። በግልጽ እንዲያነቃቃቸውና የጴጥሮስን ማስጠንቀቂያዎች በልባቸው እንዲይዙ ለማሳሰብ ይሁዳ የጴጥሮስን ደብዳቤ ለተቀበሉት ለእነዚያው አማኞች ነበር የጻፈው። ይህንን አስደናቂ መልእክት ግን እምብዛም የማይጠቀስ ደብዳቤ ስታጤኑ በይሁዳ መልእክትና በ2ኛ ጴጥሮስ መልእክት መካከል ብዙ ትይዩ ነገሮችን ታገኛለህ።

ይሁዳ ደብዳቤውን የጻፈላቸው ሊገሥጻቸው በማሰብ ነበር (ይሁዳ 3)። በግሪኩ ቋንቋ ይህ ቃል አንድ የጦር መሪ ለሠራዊቱ ትእዛዝ ሲሰጥ ያለውን ሁኔታ ለመግለጥ የሚያገለግል ነበር፤ ስለዚህም የዚህ ደብዳቤ መንፈስ በይበልጥ «ወታደራዊ» ነው። ይሁዳ ስለ ደኅንነት የሚገልጥ ጭምት ደብዳቤ ለመጻፍ ጀምሮ ነበር፤ መንፈስ ግን በገናውን እንዲያስቀምጥና መለከቱን እንዲነፋ መራው! የይሁዳ መልእክት የክተት ጥሪ ነው።

## ሠራዊቱ (ይሁዳ 1-2)

የሠራዊቱ አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ የሚያዛቸው ወታደሮች ደግሞ በእርሱ በማመን «የጋራ ደኅንነትን» የተቀበሉ ሕዝቦች ናቸው። ይሁዳ በቁ 3 ላይ ቅዱሳንን ሲል «የተለዩ» እንደሆኑ በመቁጠር ጠርቶአቸዋል። (አንዳንድ ጽሑፎች «በእግዚአብሔር አብ የተወደዱ» ይላሉ)። ምናልባት ቅዱሳን፥ የተቀደሱና የተወደዱ የሚሉት ሦስቱ ቃላት መጠቀስ የ1ኛ ጴጥሮስ 1፡2ን መንፈስ በማስተጋባት በደኅንነታችን ውስጥ የአንዱ እግዚአብሔርን ወይም የአብ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ተሳታፊነት ለማሳየት ሊሆን ይችላል።

በእርግጥ ደኅንነት የሚጀምረው በእግዚአብሔር ልብ እንጂ በሰው ፈቃድ አይደለም (ሮሜ 9፡16)። ሉዓላዊ የሆነው የእግዚአብሔር የመምረጥ ጸጋ ምሥጢራት በዚህ ሕይወት ሊገቡን የማይችሉና ወደ ክብሩ መንግሥት እስክንገባ ድረስ በፍጹም የማንረዳቸው ናቸው፤ ከዚህ የተነሣ ለክርክርና ለክፍፍል አመቺ ሁኔታን እንዳንፈጥር ማስተዋል ይገባናል። «ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው» (ዘዳግም 29፡29)።

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13-14 የመረጠን አምላክ በመንፈስ እንደ ለየንና ከዚያ በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ እንድናምን በወንጌል እንደጠራን ግልጥ ያደርገዋል። መጨረሻውን (መዳናችንን) የሚወስነው አምላክ ወደ መጨረሻ የሚያደርሰንንም መንገድ (ወደ ክርስቶስ የሚጠራንን ሰው) የሚወስነው እርሱ ነው። የእግዚአብሔር ምርጫና የእግዚአብሔር ጥሪ አብረው የሚሄዱ ናቸው። ከመለወጣችን በፊት የእግዚአብሔር መንፈስ እንዴት በሕይወታችን ውስጥ ይሠራ እንደነበር ባይገባንም፥ ነገር ግን በዚሁ ሁኔታ ለኢየሱስ ክርስቶስ «ሊለየን» ይሠራ ነበር።

የእግዚአብሔር ቅዱሳን የተለዩ ብቻ ሳይሆኑ የተጠበቁም ናቸው፤ ይህም ማለት «በጥንቃቄ የተያዙና የተጠበቁ» ነበሩ ማለት ነው። አማኝ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ የተጠበቀ ነው። ይኸው ቃል በይሁዳ 6 ና 13 ላይ «ጠብቆአቸዋል»፤ ከዚህም በተጨማሪ በቁጥር 21 «ራሳችሁን ጠብቁ» ተብሎ ተጠቅሷል። እግዚአብሔር የወደቁትን መላእክትና (መናፍቃን) ለፍርድ ቀን ሊያቆያቸው ጠበቃቸው፤ የራሱን ልጆች ግን ለክብር

እየጠበቃቸው ነው። በዕለት ከዕለት እርምጃችን ሊጠብቀንና ከመሰናከል ሊታደገን ይችላል።

የእግዚአብሔር ወታደሮች የተለዩና የተጠበቁ ስለሆኑ የእግዚአብሔርን ምርጥ በረከቶች ተቀባዮች ናቸው:- እነዚህም ምሕረት፥ ሰላምና ፍቅር ናቸው። እንደ ሐዋርያው ጴጥሮስ ይሁዳም እነዚህ ልዩ የሆኑ በረከቶች ደብዳቤውን በጻፈላቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ እንዲበዙላቸው ይፈልጋል (1ኛ ጴጥሮስ 1:2፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1:2)። እግዚአብሔር በምሕረቱ እንደ ሥራችን መጠን ሊቀጣን አይፈልግም። በዚያ ፈንታ የእኛን ቅጣት ለገዛ ልጁ በመስቀል ላይ ሰጠው። «በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል . . . እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ» (ኢሳ. 53:4-5)።

ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሠራው ሥራ የተነሣ አማኞች ባገኙት ሰላም ይደሰታሉ። ያልዳነው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ጦርነት ገጥሟልና እግዚአብሔርን ሊያስደስተው አይችልም (ሮሜ 8:7-8)፤ ነገር ግን አዳኙን ሲያምን ጦርነቱ ያበቃና የእግዚአብሔርን ሰላም ይቀበላል (ሮሜ 5:1)።

እንደዚሁም የእግዚአብሔርን ፍቅር ይለማመዳል (ሮሜ 5:5)። መስቀሉ የእግዚአብሔር የፍቅር መግለጫ ነው (ሮሜ 5:8)። ሆኖም ግን መንፈሱ ወደ አማኙ ልብ ውስጥ እስከሚገባ ድረስ ፍቅሩን መለማመድ አይቻልም። አማኙ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገ ሲሄድ ወደ ጠለቀ የፍቅር ግንኙነት ውስጥ ይገባል (ዮሐንስ 14:21-24)።

በእውነት ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው የሚያውቁ ልዩ የሆነ ማዕረግ አላቸው። ለእግዚአብሔር ተለይተው ከእግዚአብሔር ጋር ፍቅር ይኖራቸው ዘንድ በእግዚአብሔር የተጠሩ ናቸው። ከአብ ጋር ያላቸው ኅብረት ከቀን ወደ ቀን ሊለዋወጥ ቢችልም፥ እንደ ልጅነታቸው ያላቸው ግንኙነት ግን ሊለወጥ አይችልም። «በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠበቁ» ናቸው። ይሁዳ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ስለ ኃጢአትና ፍርድ ብዙ ስለሚጽፍ ገና ከመጀመሪያው አማኞች በእግዚአብሔር ልብና ዕቅድ ውስጥ ስላላቸው ልዩ ቦታ ለማብራራት ልዩ ጥንቃቄ አድርጎአል። ሐሰተኛ መምህራን ኃጢአትን ያደርጋሉ፤ ይወድቃሉ፤ ከዚያም ተፈርዶባቸው ይሠቃያሉ፤ እውነተኛ አማኞች ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ለዘለዓለም ተጠብቀው ይኖራሉ።

ሐሰተኛ መምህር ደኅንነቱን ያጣል፤ እውነተኛ አማኝ እንዳልሆነ ተደጋግሞ ሊገለጥ ይገባል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው እውነትን እንደ ተቀበለና የክርስቶስን አዳኝነት እንዳመነ ሲያስመስል የኖረና፥ ከዚያም «ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ከተሰጠው ሃይማኖት» (ይሁዳ 3) የተመለሰ ሰው ነው። ጴጥሮስ ከጻፈው ጋር ይሁዳ አልተቃረነም፥ ጴጥሮስም ሐሰተኛ መምህራን የእግዚአብሔር በጎች ሳይሆኑ እሪያዎችና ውሾች እንደሆኑ በግልጥ አስቀምጧል (2ኛ ጴጥሮስ 2፡21-22)። እሪያው በውጪ፥ ውሻው ደግሞ በውስጥ ንጹሕ ነበሩ፤ ነገር ግን አንዳቸውም የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች መለያ የሆነው ያ አዲሱ ባሕርይ አልተሰጣቸውም (2ኛ ጴጥሮስ 1፡3-4)።

በዚህ ክፍል ደግሞ ይሁዳ የሚጽፍለት «መንፈሳዊ ሠራዊት» ተጠቅሶአል። አንተም በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንህ የዚህ ሠራዊት አባል ነህ። እግዚአብሔር የሠራዊቱ አባል ለመሆን በፈቃደኝነት የሚመዘገቡትን እየፈለገ አይደለም ያለው፤ አንተን አስቀድሞ መዝግቦሃል! ስለዚህ ጥያቄው «ወታደር ልሁን ወይ?» የሚል ሳይሆን በዚያ ፈንታ «ታማኝ ወታደር ነኝ ወይ?» የሚለው ነው።

ይስሐቅ ዋትስ የተባለ ሰው አንድ ጊዜ በ1ኛ ቆሮንቶስ 16፡13 ላይ አንድ ስብከት ሰበከ። መልእክቱም «ንቁ፥ በሃይማኖት ቁሙ፥ ጐልምሱ፥ ጠንክሩ» የሚል ሲሆን፥ ይህን ስብከቱን ባሳተመበት ጊዜ አንድ ግጥም ጨምሮበት ነበር። ዛሬ እኛ ይህንን ግጥም እንደ አንድ መንፈሳዊ መዝሙር እንዘምረዋለን።

እኔስ ነኝ ወይ - የእግዚአብሔርን በግ ተከታይ

ለመስቀሉ የታመንኩኝ - ቆራጥ አርበኛ ተጋዳይ?

በጌታ ስም - የምኮራ

ልሠዋለት - የማልፈራ?

ወይንስ ስወሰድ - ከሰማይ

ሙካሽ ይነጠፍ - ይድላኝ ባይ?

ሌሎች ሲዋጉ - በደም ዋኝተው

አክሊል ሊጭኑ - ድል አድርገው?

ጠላታችን (ይሁዳ 3-4)

ይሁዳ ስለ «የጋራ ደኅንነት» የጻፈውን አበረታች መልእክት አስቀድመን አስተውለናል። ይሁዳ የሚለው ስም «ምስጋና» ማለት ነው፤ እርሱም እግዚአብሔርን ለማመስገንና እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በሚሰጠው ደኅንነት ለመደሰት የተጋ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ ግን አሳቡን እንዲለውጥና በዚህ ዓለም ካሉት የክፋት ኃይላት ጋር ስላለው ውጊያ እንዲጽፍ መራው። ለምን? ምክንያቱም የርሱ መልእክት ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ስለነበረ ነው።

በበኩሌ ስለ ይሁዳ ኅዘኔታ እንደሚሰማኝ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። ከራሴ አገልግሎት እንደተገነዘብኩት በሐሰተኞች ላይ ጦርነት ከማወጅ ይልቅ ቅዱሳንን ባበረታታ የበለጠ እመርጣለሁ፤ ነገር ግን ጠላት በሜዳ እያለ ጠባቂው ማንቀላፋት የለበትም። የክርስትና ሕይወት የጨዋታ ሜዳ ሳይሆን የውጊያ ሜዳ ነው።

## ይሁዳ ጠላትን ለይቶ ለማወቅ ጊዜ አላባከነም።

እግዚአብሔርን የማይመስሉ ነበሩ። ይህ ከይሁዳ ምርጥ ቃላት አንዱ ነው። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር እንደሆኑ ቢናገሩም እውነቱ ሲታይ ግን በአስተሳሰባቸውና በአኗኗራቸው እግዚአብሔርን የማይመስሉ ነበሩ። «የአምልኮት መልክ» ሊኖራቸው ይችላል፤ በእውነተኛው ክርስቲያን ውስጥ የሚኖረው እግዚአብሔርን የመምሰል ኃይል ግን አልነበራቸውም (2ኛ ጢሞ. 3፡5)።

አታላዮች ነበሩ፡- «ሾልከው የገቡ» ነበሩ። የግሪኩ ቃል «በስውር መሹለክለክ፥ በሽፋን ሥር ሆኖ መስረቅ» የሚል መልእክት አለው። አንዳንድ ጊዜ የሰይጣን ስውር መልእክተኞች «በስውር የሚገቡት» በውስጥ ባሉት ሰዎች ሽፋንነት ነው (ገላ. 2፡4)። ሰዎቹ ግን የገቡት ያለሽፋን በራሳቸው ስም ነው። ጴጥሮስ እነዚህ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገቡ እንደነበረ አስጠንቅቋል (2 ጴጥሮስ 2፡1)። በይሁዳ መልእክት ጊዜ ግን በእርግጥም ገብተው ነበር።

ሐሰተኞች ወንድሞች እውነተኛ ወደሆኑ የቅዱሳን ማኅበሮች እንዴት ሊገቡ ቻሉ? የቻሉት በጥበቃ በታቸው ላይ የነበሩ ወታደሮች

በማንቀላፋታቸው ነው! በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የነበሩት መንፈሳዊ መሪዎች ተዝናንተው እና ግድየለሽ ሆነው ነበር። ይህም የእነርሱ ግዴለሽነት ይሁዳን ለምን የማንቃቂያ መለከት መንፋት እንዳስፈለገው ያስረዳል። ጌታችንና ሐዋርያቱ በሙሉ የሐሰት አስተማሪዎች እንደሚነሡ አስጠንቅቀው ነበር። ሆኖም አብያተ ክርስቲያናት ማስጠንቀቂያዎቹን በልባቸው አላኖሯቸውም። የሚያሳዝነው ዛሬም አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ማስጠንቀቂያዎቹን መቀበል አለመፈለጋቸው ነው።

ለእግዚአብሔር ጸጋ ጠላቶች ነበሩ፡- እነኚህ ሐሰተኞች ለምን ወደ ቤተ ክርስቲያናት ገቡ? ትምህርቱን ለመለወጥና «የአምላካችንን ጸጋ ወደ ሴሰኝነት ለመለወጥ» ሙከራ ለማድረግ ነበር (ይሁዳ 4)። ሴሰኝነት የሚለው ቃል «ልቅ፥ ግብረገብነት የሌለው፥ ጨዋ ያልሆነ» ማለት ነው። ሴሰኛ የሆነ ሰው የሚያስበው ፍትወታዊ ምኞቱን ለማርካት ብቻ ነው፤ እርሱም የሚነካው ሁሉ በኃጢአት የተበከለ ነው። ሴሰኝነት ከሰው ክፉ ልብ የሚወጣ (ማር. 7፡21-22) ከሥጋ ሥራዎች አንዱ ነው (ገላ. 5፡19)።

ጴጥሮስ፥ እነዚህ መናፍቃን «በጸጋ ድናችኋል፤ እንደፈለጋችሁት ለመኖር ነፃነት አላችሁ!» ብለው እንደሚከራከሩ አስቀድሞ አስጠንቅቋል። ለሕዝቡ የአርነትን ተስፋ ቢሰጡም፥ የተስፋ ቃላቸው ግን ወደ አስከፊ ዓይነት እስራት የሚመራ አርነት ነበር (2ኛ ጴጥሮስ 2፡13-14፥ 19)። ጴጥሮስም ይሁዳም የጻፉላቸው አንባቢዎች ጳውሎስ የጻፈውን ያውቁ ነበር (2ኛ ጴጥሮስ 3፡15-16)፤ ስለዚህ በሮሜ 6 እና በ 1ኛ ቆሮንቶስ 5-6 መሠረት መታጠቅ ነበረባቸው።

በዘመናችን እንዳሉት ሐሰተኛ መምህራን ሁሉ እነዚህም መናፍቃን የሐሰት ትምህርቶቻቸውን ለማስፋፋትና ምላሽ ለመስጠት በእግዚአብሔር ቃል ይጠቀማሉ። በቅዱስ መጻሕፍት እውቀታቸው ሥር ያልሰደዱትን ለጋና ያልበሰሉ ክርስቲያኖች ይማርካሉ። እያንዳንዱ የመስቀሉ ወታደር የመንፈሳዊ ጦር ዕቃዎችን እንዴት መጠቀም እንዳለበት እንዲያውቅ፥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በሚሰጠው «መሠረታዊ ሥልጠና» ውስጥ መካፈል አለበት (2ኛ ቆሮ. 10፡4-5)።

የእግዚአብሔርን እውነት ክደው ነበር፡- «የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው» ነበር (2ኛ ጴጥሮስ 2፡1)። ይሁዳ «ንጉሣችንንና ጌታችንንም፥ ብቻውን

ያለውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን» ብሎ ሲጽፍ፥ ስለ ሁለት የተለያዩ ስብእናዎች አልነበረም የሚጽፈው፤ ምክንያቱም የግሪኩ ሰዋሰው እነዚህ ሁለት ስሞች አንድን አካል እንደሚጠቅሱ ስለሚያሳይ ነው። በሌላ አነጋገር ይሁዳ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት አበክሮ እያስረገጠ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው።

መናፍቃን ግን ይህንን ይክዳሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ጥሩ ሰውና ታላቅ አስተማሪ እንደ ነበር እንጂ የሰው ሥጋ ለብሶ የመጣ ዘላለማዊ አምላክ እንደሆነ አያምኑም። ለማንኛውም ሃይማኖታዊ አስተማሪ የመጀመሪያው መፈተኛ እንዳየነው «ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ታስባለህ? በሥጋ የመጣ አምላክ ነው?» የሚለው ጥያቄ ነው። ይህንን ዋና ትምህርት የሚክድ ማንኛውም ሰው ምንም ያህል በሌሎች ጉዳዮች ላይ ትክክል ቢሆን እርሱ የሐሰት አስተማሪ ነው። የክርስቶስን አምላክነት ከካደ በየትኛውም ትምህርቱ ውስጥ ቢሆን ሁልጊዜ የሚጎድለው አንድ ነገር ይኖራል።

ለፍርድ የተገለሉ ናቸው፡- ይሁዳ እነዚህ ሰዎች መናፍቃን እንዲሆኑ አስቀድሞ ስለመወሰኑ ወይንም ለኃጢአታቸው እግዚአብሔርን ተጠያቂ በማድረግ አልጻፈም። ወደው ከእውነት በፈቃዳቸው ስለተመለሱ መናፍቃን ሆኑ፤ ነገር ግን እንደዚህ ያሉ ሰዎች እንደሚፈረድባቸውና እንደሚኮነኑ እግዚአብሔር ወስኖ ነበር። የብሉይ ኪዳን ነቢያት በዘመናቸው የነበሩትን የሐሰት ነቢያት አውግዘዋል፤ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስም፥ ሐዋርያቱም በእነርሱ ላይ ፈርደዋል።

እግዚአብሔር ለምን በእነዚህ ሰዎች ላይ ይፈርዳል? በመጀመሪያ ልጁን ክደዋል! ለኩነኔያቸው ያ በቂ ምክንያት ነው! ከዚያም በላይ የእግዚአብሔር ጸጋ ኃጢአትን እንዲያደርጉ እንደፈቀደላቸው በማስተማር የእግዚአብሔርን ሕዝብ አርክሰው ነበር። በተጨማሪም የክርስቶስን የመምጣት ትምህርት ነቅፈዋል (2 ጴጥሮስ 3)። «የመምጣቱ የተስፋ ቃል ወዴት ነው?» ይላሉ። በክርስቶስ የመምጣት ተስፋና እግዚአብሔርን በማይፈሩት ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ያፌዛሉ።

በእርግጥ እነዚህን ነገሮች ሁሉ በሃይማኖት ስም ነበር የሚያደርጉት፤ ይህም ኃጢአታቸውን የበለጠ አጉልቶታል። የዋህ ሰዎችን በማታለል ገንዘባቸውን ለመውሰድና የወሰዱትንም ገንዘብ እግዚአብሔርን መፍራት

በሌለበት አኗኗር ለማጥፋት ወደኋላ አይሉም ነበር። ኢየሱስ እነዚህን አታላዮች የበግ ለምድ ከለበሱ ተኩላዎች ጋር አመሳስሏቸዋል (ማቴ. 7፡15)።

ታዲያ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ የውስጥ ጠላት ምን ምላሽ ነው መስጠት ያለባት? ለእምነት ብርታት በመጋደል ነው!

«እምነት» የሚለው ቃል ከእግዚአብሔር በሐዋርያት በኩል ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን የመሠረታዊ ሃይማኖት ትምህርት የሚያቅፍ ነው። መሠረተ እምነት የሚለው ቃል በእነዚህ መልእክቶች ውስጥ ብቻ ቢያንስ አሥራ ስድስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስንና ቲቶን ምእመናኑ «ትክክለኛ ትምህርት» ማለትም «ጤናማ ትምህርት» መከታተላቸውን እንዲያረጋግጡ ሲመክራቸው፥ ይህም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ጤንነት የሚያሳድግ ትምህርት መሆኑን በግልጥ አስረድቷቸዋል። ግለሰብ መምህራንና ሰባኪዎች በተወሰኑ የሥነ- መለኮት ትምህርት ነጥቦች ላይ ላይስማሙ ቢችሉም ሁሉም እውነተኛ ክርስቲያኖች ግን የሚቀበሉት አንድ መሠረታዊ የሆነ የእውነት ትምህርት አለ።

ይህም የእውነት ትምህርት ለቅዱሳን ተሰጥቷል (ይሁዳ 3)። ቃሉ «በአደራነት» የተላለፈላቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህንንም አደራ ማሟላት ለቤተ ክርስቲያን በጋራ የተሰጣት ኃላፊነት ሲሆን እያንዳንዱም ሊያሟላው የሚገባ ግዴታ ነው። «ነገር ግን ወንጌልን አደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን፥ እንዲሁ እንናገራለን» (1ኛ ተሰ. 2፡4)። እግዚአብሔር እውነትን ለጳውሎስ አደራ ሰጠ (1ኛ ጢሞ. 1፡11)፤ እርሱ ደግሞ እንደ ጢሞቴዎስ ላሉት ለሌሎች አካፈለው (1ኛ ጢሞ. 6፡20)። ጢሞቴዎስ ቃሉን ለሌሎች ለታመኑ ሰዎች አደራ እንዲሰጥ ተመክሯል (2ኛ ጢሞ. 2፡2)። በዘመናት መካከል ይህንን የከበረ ሀብት ጠብቀው ለሌሎች ያስተላለፉ ታማኝ አማኞች ባይኖሩ ኖሮ ዛሬ እናንተና እኔ ቃሉ አይኖረንም ነበር።

ቤተ ክርስቲያን እውነቱን ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ካላስተላለፈች ትጠፋለች። ስለዚህ የእኛም ትውልድ እውነትን በመጠበቅ ለልጆቻችን ማስተላለፍ ካቃተው፥ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ እዚያ ላይ ያበቃል ማለት ነው! የእግዚአብሔርን እውነት ስንረዳ፥ እኛም ይህንን እውነት እንድናገኝ

የተሠቃዩትንና የሞቱትን ቅዱሳንና ሰማዕታት ስናስታውስ፥ በእግዚአብሔር ሠራዊት ውስጥ መደበኛ ቦታችንን ለመያዝና እስከ ሞት ድረስ የታመንን ለመሆን መንፈሳችን ይነሣሣል።

«ለሃይማኖት እንድትጋደሉ» ማለት ምን ማለት ነው? የግሪኩ ቃል የሞት የሽረት ትግልን የሚያሳይ ነው። «መጋደል» በግሪክ ጨዋታዎች ለመወዳደርና ለማሸነፍ ተፎካካሪው ጅማቶቹንና ጡንቻዎቹን ለማሳዘዝ የሚያሳልፈውን ድካምና ልምምድ የሚያመለክት ነው። የጌታን ጦርነቶች ለመዋጋት በተሽከርካሪ ወንበር ላይ እየተንፈላሰሱ፥ ወይም በለስላሳ አልጋ ላይ እየተዝናኑ መዋጋት ፈጽሞ አይቻልም! ወታደሩም፥ ሯጩም በፍጹም ቆራጥነት መታገልና ማናቸውንም ያላቸውን ሁሉ ነገር መሥዋዕት ለማድረግ ቆርጠው መነሣት አለባቸው። ከዚህም በተጨማሪ አማኞች ጠላትን ለማጥቃትና ለማሸነፍ በአንድነት የሚሠሩበት የቡድን ሥራም መኖር አለበት።

አንዳንድ ጊዜ ልበ ቅን የሆኑ ሰዎች «ለእምነታችን ጥብቅና መቆም መልካም ነገር ነው፤ እምነትን ማክረር ግን ጥሩ አይደለም» ሲሉ ትሰማላችሁ። አንዳንድ የእግዚአብሔር ወታደሮች ለጥልና ለመከፋፈል መንሥኤዎች መሆናቸው እውነት ቢሆንም፥ ሌሎቹ ደግሞ እውነትን ለመከላከል ታላቅ መሥዋዕትነት መክፈላቸው የማይካድ ነው። እንደ ክርስቲያን ወታደሮች እርስ በርሳችን መጣላት ወይም ችግርን መፍጠር የለብንም፤ ነገር ግን የክርስቶስ ሰንደቅ ዓላማ በጠላት ሊማረክ በአደጋ ላይ በወደቀበት ጊዜ፥ እጃችንን አጣጥፈን ልንመለከት ወይም በአጉል ምኞት ድል እናገኛለን ብለን ተስፋ ማድረግ አይገባንም።

አንድ ጊዜ ቻርለስ ስፐርጀን እንዲህ አለ:- «አዳዲሶቹ አመለካከቶች በተሻለ ሽፋን የቀረቡ የድሮ እውነቶች አይደሉም፤ ልንርቃቸው የሚገቡ አስጊ ስሕተቶች ናቸው።» ሐሰተኛ ትምህርት ሊታወቅ፥ምልክት ሊደረግበትና ሊወገድ የሚገባው መርዝ ነው። ስፐርጀን እንዲህም ብሏል:- «ምንም ያህል አምሮ ቢቀርብልኝም ሐሰተኛ ትምህርትን መቀበል አልችልም፤ በምርጥ ዕቃ ስለቀረበ ብቻ የተመረዘ ሥጋ መብላት አለብኝን?»

ሁልጊዜ እውነትን በፍቅር መናገር አለብን፤ የምንጠቀምባቸውም የጦር ዕቃዎች መንፈሳዊ መሆን አለባቸው። አቋማችን በተመሳሳይ ጊዜ

አንዳንዶችን ቢያስቀይምና ሌሎችን ደግሞ ቢያሳዝንም «ለእምነት» ያለንን አቋም ለመያዝ መድፈር አለብን። የምንዋጋው የግል ጠላቶችን ሳይሆን የጌታን ጠላቶች ነው። ነቀፋው እየተሰነዘረ ያለው በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ማንነት ላይ ነው። «መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል» (1ኛ ጢሞ. 6፡ 12)።

## ድሉ (ይሁዳ 5-7)

እንደ ሐዋርያው ጴጥሮስ ይሁዳም ከብሉይ ኪዳን ታሪክ ሥልጣኑን በተቃወሙትና ከእውነት ዞር ባሉት ላይ እግዚአብሔር ያገኘውን ድል የሚገልጹ ሦስት ምሳሌዎችን ሰጥቷል። ጴጥሮስ የወደቁትን መላእክት፥ ኖኅንና ሎጥን ጠቅሶ (2 ጴጥሮስ 2፡ 4-9)፥ ታሪካዊ ቅደም ተከተላቸውን በመከተል ጽፏል። እንደዚሁም ጻድቁን እግዚአብሔር እንደሚታደግና እግዚአብሔርን የማይፈሩትን እንደሚፈርድባቸው አጠንክሮ ተናግሯል። ይሁዳ ግን ኖኅንና የውኃ መጥለቅለቁን አልጠቀሰም፤ በዚያ ፈንታ ግን በእስራኤል ሕዝብ እንደ ምሳሌ ተጠቅሟል።

ይሁዳ ለማሳየት የሚፈልገው ነጥብ እግዚአብሔር መናፍቃንን እንደሚፈርድባቸው ነው። ስለዚህ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልከው የገቡት የሐሰት አስተማሪዎችም አንድ ቀን ይፈረድባቸዋል። የተሳካ የሚመስለው ነገራቸው ሁሉ አይቆይም፤ የመጨረሻው ድል የእግዚአብሔር ይሆናል።

እስራኤል (ቁ. 5)፡- ጳውሎስና (1ኛ ቆሮንቶስ 10) የዕብራውያን ጸሐፊውም (ምዕራፍ 3-4) አስፈላጊ መንፈሳዊ እውነቶችን ለመግለጽ በእስራኤላውያን ገጠመኞች ተጠቅመዋል። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ኃይል ከግብፅ ወጥተው ወደ ተስፋይቱ ምድር ድንበር ደርሰው ነበር፤ ነገር ግን ሕዝቡ ፈርተው ለመግባትና ምድሪቱን ለመውረስ እምነት አልነበራቸውም (ዘኁ. 13-14 ተመልከት)። ሙሴ፥ ኢያሱና ካሌብ በእምነት እግዚአብሔርን እንዲታዘዙ ሕዝቡን ሊያበረታቱ ሞከሩ፤ ሕዝቡ ግን ሊቀበሉዋቸው አልፈለጉም። እንዲያውም የነገዶቹን አለቆች ሊያስተባብሩና የባርነት ቦታ ወደ ሆነው ወደ ግብፅ ለመመለስ ፈለጉ!

ይህ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቃል ላይ ማመፅ ነበር፤ እግዚአብሔር ደግሞ ዓመፅን አይታገሥም። ከዚህም የተነሣ ሃያ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ሁሉ

በሚቀጥሉት አርባ ዓመታት ውስጥ ባለው ጊዜ እንዲሞቱ ሆነ። አለማመናቸው ወደ ጥፋት መራቸው።

እዚህ ላይ ይሁዳ በአንድ ታሪካዊ ክሥተት እንደ ምሳሌ እየተጠቀመ መሆኑን አስቡ። እኛም እያንዳንዱን ዝርዝር ማጥናትና ማየት አያስፈልገንም። ሕዝቡ ሁሉ ከግብፅ ወጥቶ ነበር፤ ይህን ማለት ግን እያንዳንዱ ሰው በጌታ በኩል ባለ እምነት በግሉ ድኗል ማለት አይደለም። የመልእክቱ ፍሬ አሳብ ልዩ በረከቶች ኃላፊነትን እንደሚያስከትሉ ነው፤ እግዚአብሔርም የሕዝቡን ኃጢአት በቀላሉ ማለፍ አይችልም። ከይሁዳ መልእክት የምንረዳው ከአንባቢዎቹ አንዳቸውም የሐሰት አስተማሪዎችን ለመከተል ቢደፍሩ፥ እነሱም የእግዚአብሔርን ቅጣት ይቀበላሉ። «ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» (1ኛ ቆሮንቶስ 10፡12)።

የወደቁት መላእክት (ቁ. 6)፡- ይህንን ገለጣ በ2ኛ ጴጥሮስ 2፡4 ላይ አጥንተነዋል፤ ይሁዳ ግን የመላእክትን መውደቅ ከሰዶምና ገሞራ ጥፋት ጋር በማያያዝ አዲስ አመለካከት የሚያክልበት (ይሁዳ 7 «እንዲሁም እንደ እነርሱ») ይመስላል። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ይሁዳ ያስተምር የነበረው መላእክት በእግዚአብሔር ላይ ስለማመፃቸው ብቻ ሳይሆን፥ በእነዚህ በወደቁ መላእክት የምድርን መወረር ጭምር ነው ብለው ያምናሉ። ዘፍጥረት 6፡1-4ን በመጥቀስ «የእግዚአብሔር ልጆች» የተባሉት የሰውን አካል ለብሰው፥ ከሰው ሴቶች ልጆች ጋር በመኖር በምድር ላይ የትላልቅ ፍጡራን ዘርን የወለዱ የወደቁ መላእክት ነበሩ ብለው ይናገራሉ። እግዚአብሔርም ወደ ምድር የጥፋት ውኃን የላከበት አንዱ ምክንያት ይህ ነበር ይላሉ።

ይህ አመለካከት የሚማርክና በአንዳንዶች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም፥ በበኩሌ ግን ለመቀበል እንደምቸገር መናገር አለብኝ። «የእግዚአብሔር ልጆች» የሚለው ለመላእክት የተሰጠ ስያሜ መሆኑ እውነት ነው (ኢዮብ 1፡6፤ 2፡1፤ 38፡7)፤ ነገር ግን ሁልጊዜ ላልወደቁት መላክእት የተሰጠ ስያሜ ነው። ለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ በሙሴ በኩል በጻፈበት ወቅት ዓመፀኞቹን መላእክት «የእግዚአብሔር ልጆች» ብሎ የጠራቸው ይመስላችኋል? እኔ በበኩሌ ግን አይመስለኝም።

ሁለተኛው ችግሬ፡- የመላእክት መናፍስት መሆንና አካል የሌላቸው መሆናቸው ነው። በብሉይ ኪዳን ዘገባ ውስጥ በሰው መልክ ስለተገለጡ መላእክት እናነባለን፤ ይህ ግን በሥጋ መገለጥ አልነበረም። አንድ መንፈሳዊ አካል ጊዜያዊ የሆነ አካል ለብሶ ሊገለጥ ቢችልም፥ እንዴት ከሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊኖረው ይችላል? መላእክት ጾታ እንደሌላቸው ጌታችን አስተምሯል (ማቴ. 22፡30)።

ሦስተኛ፡- እግዚአብሔር የውኃ መጥለቅለቅ የላከው ሰው ካደረገው ክፋት የተነሣ እንጂ መላእክት ካደረጉት ነገር የተነሣ አይመስልም። «መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም . . . እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ . . . አየ። እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ» (ዘፍ. 6፡3፥ 5-6)። ይህ «የወደቁ መላእክት» ለውኃው ጥፋት መንስኤ ናቸው የሚለው አመለካከት ትክክል ከሆነ፥ እግዚአብሔር መላእክትን ስለፈጠረ መጸጸት ነበረበት!

አራተኛ፡- በቁጥር 7 ላይ ያሉት «እንዲሁም» እና «እንደነርሱም» የሚሉት ሐረጎች መላእክቱ ሰዶማውያን ያደረጉትን አድርገዋል ማለት ነው ተብሎ መተርጎም የለበትም። በቁጥሩ ላይ ያሉትን ሰዋሰዋዊ ግንኙነቶች ተመልከቱና መልእክቱን ታገኙታላችሁ «እንዲሁም ሰዶምና ገሞራ . . . እንደ እነርሱ . . . ምሳሌ ሆነዋል»። መላእክቱ የእግዚአብሔር ፍርድ ምሳሌ የሆኑትን ያህል ሰዶምና ገሞራም በተመሳሳይ ሁኔታ ለፍርዱ ማስረጃዎች ናቸው።

ዘፍጥረት 6፡4 የወደቁት መላእክት ከሴቶች ጋር ተጋብተው የታላላቅ ፍጥረታትን ዘር እንደወለዱ ቢያስረዳም፥ በዚህ አመለካከት ላይ ጠንካራ ተቃውሞ ማቅረብ እንደሚቻል ለመግለጽ እወዳለሁ። «በነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ ደግሞ ከዚያ በኋላ. . .» ይህ ሁለተኛ የወደቁ መላእክት ወረራ ተደርጓል ማለት ሊሆን ሲችል፥ ዳሩ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህን የሚደግፍ ዘገባ አናገኝም።

በመጨረሻ ጴጥሮስና ይሁዳ ሁለቱም እነዚህ ዓመፀኞች መላእክት ከጨለማ በታች ታስረው ለፍርድ እንደተጠበቁ በግልጥ ይናገራሉ። አለበለዚያ ግን በእግዚአብሔር ከመያዛቸውና ከመታሰራቸው በፊት ምድርን ወርረው ነበር ማለት ነው። እግዚአብሔር ሴቶቹን ወደ ኃጢአት

እስኪያስገቡና ለታላቁ የውኃ መጥለቅለቅ ምክንያት እስኪሆኑ ድረስ በነፃ ለመመላለስ ለምን ፈቀደላቸው? ብለን እንገረማለን። ምንም እንኳ ለዚህ የሚሆን ማብራሪያ እኔ በማከብራቸው ምሁራን የቀረበ ቢሆንም በበኩሌ ግን ለመቀበል ያዳግተኛል። እንደኔ የዘፍጥረት ምዕራፍ 6 ቀላሉ ማብራሪያ እግዚአብሔርን የሚፈራው የሴት ዘር ማለትም «የእግዚአብሔር ልጆች» እግዚአብሔርን ከማይፈራው ከቃየን ዘር ጋር መደባለቅ ጀመሩ፤ ይህም የልዩነት ግድግዳዎችን ሰብሮ የማወላወልና ቀስ በቀስም በኃጢአት የመዝቀጥን ውጤት አስከተለ የሚል መሆን አለበት። ነገር ግን የትኛውንም ዓይነት አተረጓጐም ብንቀበል፥ መዘንጋት የሌለብን ዋናው ትምህርት ግን መላእክቱ አምጸዋል፤ በአመጻቸውም ተቀጥተዋል የሚለውን ነው።

ሰዶምና ገሞራ (ቁ. 7):- ጴጥሮስና ይሁዳ ሁለቱም እግዚአብሔር በእርግጥ ኃጢአትን እንደሚቀጣና ሰዶምና ገሞራንም እግዚአብሔርን የማይፈሩትን ለማስጠንቀቅ ምሳሌ እንዳደረጋቸው ይናገራሉ (2ኛ ጴጥሮስ 2፡6 ተመልከት)። አገላለጻቸቸውን ስታገናኛቸው የሰዶምና የገሞራ (እንዲሁም የተካተቱት ሌሎቹ ከተሞች) ዜጎች:- እግዚአብሔርን የማይፈሩ፥ ክፉዎች፥ ሕግ የሌላቸው፥ ከጽድቅ ውጪ የሆኑ፥ እና ለዝሙት የተሰጡ እንደነበሩ ትረዳለህ። ተፈጥሮአዊ ያልሆኑ የዝሙት ኃጢአቶችን የሚያደርጉት አልፎ አልፎ አልነበረም፤ ከመጠን በላይ ተዘፍቀውባቸው፥ እራሳቸውንም ለምኞታቸው ተገዢ አድርገው ነበር። የግሪኩ ግሥ የባሰ የሚል ነው፥ «ከመጠን ያለፈ ኢ-ግብረገባዊ ልምድ ውስጥ መግባት»። ይህ የሕይወት ዘይቤአቸው ነበር፤እንዲሁም የሞት!

እንግዳ ሥጋ ማለት «የተለየ ሥጋ» ማለት ነው። ሕይወታቸው ሁልጊዜ ተፈጥሮአዊ ወዳልሆኑ ድርጊቶች በማዘንበል ወደታች የሚያሽቆለቁል ነው (ሮሜ 1፡24-27 ተመልከት)። ዘፍጥረት 6ን በ«ወደቁት መላእክት» አተረጓጐም የሚረዱት ሰዎች «ሌላ ሥጋ» የሚለው መላክእትን በሰው አምሳል ለማሳየት እንደሆነ ያቀርቡታል፤ ነገር ግን መላእክት ሰዶምና ገሞራን የወረሩት መቼ ነበር? ደግሞ የወደቁ መላእክት ናቸው ካልን፥ በአሁኑ ጊዜ እኛን ሊፈትኑ ወይም ሊያታልሉ የሚችሉ የወደቁ መላእክት ስለሌሉ የእነርሱን ኃጢአትና የሰዶማውያን ኃጢአት ከዛሬው ሁኔታ ጋር ልናዛምደው እንዴት እንችላለን? በእርግጥ በሎጥ ደጅ የነበሩት ሰዎች እንግዶቹ ከሆኑት መላእክት ጋር በግብረ ሰዶም ሊገናኙ ፈልገው ነበር፤ ነገር ግን ሰዶማውያን

እነዚያ ሰዎች መላእክት እንደነበሩ አያውቁም ነበር። ሌላው አማራጭ ሰዶማውያን ጥፋተኛ የሆኑት እርስ በርሳቸው በሚያደርጉት ተፈጥሮአዊ ባልሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን ከእንስሳትም ጋር ያደርጉት ስለነበር ነው፤ ይህም ማለት «ሌላ ሥጋ» ማለት ይሆናል። ግብረ ሰዶምም ሆነ ከእንስሳት ጋር የሚደረግ ግንኙነት በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠሉ ናቸው (ዘሌ. 18፡22-25)።

እነዚህ ከተሞች ዛሬ እግዚአብሔርን ለማይፈሩ ሰዎች እንደ ምሳሌና ማስጠንቀቂያ በመሆን ቀርበዋል። ቀርበዋል ማለት «ማጋለጥ» ማለት ነው (ሰዎች ሁሉ አይተው እንዲዘባበቱበት በአደባባይ እንደተጣለ ሬሳ ማለት ነው።) ነገር ግን እነኛ ሰፋፊ ከተሞች ዛሬ ለሕዝብ የሚታዩ አይደሉም። በጠቅላላው ሰዶምና ገሞራ በሙት ባሕር ደቡባዊ መጨረሻ ሥር እንደተቀበሩ በምድር ቁፋሮ ተመራማሪዎች ስምምነት ቃል አማካይነት ተረጋግጦአል። እንዴት ታዲያ ምሳሌ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ? እነዚህ ሊያገለግሉን የሚችሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጠው በምሳሌነታቸው ብቻ ነው። ማንም ሰው ቢሆን ዘፍጥረት 18-19ን በሚያነብበት ጊዜ እግዚአብሔር ለኃጢአት ያለውን ጥላቻና በተመሳሳይ ሁኔታ ፍርድን ለማስተላለፍ ያለውን ትዕግሥትና ፈቃደኝነት በግልጥ መገንዘቡ አይቀርም። ይህም የክርስቶስን የመመለስ የተስፋ ቃል በተመለከተ እግዚአብሔር የዘገየ ስለመምሰሉ ጴጥሮስ ከሰጠው ማብራሪያ ጋር የተያያዘ ነው (2ኛ ጴጥሮስ 3፡8 ጀምሮ)።

የእስራኤል ኃጢአት ለአለማመን ማመፅ ነበር (ዕብ. 3፡12)። የመላእክት ኃጢአት ደግሞ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ማመፅ ነበር፤ እንዲሁም የሰዶምና የገሞራ ኃጢአት ተፈጥሮአዊ ባልሆነ ፍትወት እግዚአብሔርን ማሳዘን ነበር። አለማመን፥ በሥልጣን ላይ ማመጽና ፍትወት የሐሰተኛ መምህራን ኃጢአት ባሕርያት ናቸው። ማጠቃለያው ግልጽ ነው፡- ሐሰተኞች መምህራን ይፈረድባቸዋል። እስከዚያ ድረስ ግን የእግዚአብሔር እውነተኛ አገልጋዮች ብዙዎቹ በሥራ ላይ መቆየት አለባቸው። እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ከፍ ያለውን ስፍራ ይዘው ሕዝቡን ወደተሳሳተ አቅጣጫ እንዳይመሩ መከታተል ይኖርባቸዋል። «ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ» (1ኛ ጢሞ. 4፡16)።

ጠላትን ለመቃወምና የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕናና አንድነት ለመጠበቅ በተግባር ልናደርግ የምንችለው ምንድን ነው? በመጀመሪያ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅና ልንከላከልለት ድፍረቱ ሊኖረን ይገባናል። እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተቋም መሆን አለበት፤ እንዲሁም እያንዳንዱ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ መሆን አለበት። መድረኩ አዎንታዊ እውነትን ማወጅና እንዲሁም ስሕተትን ማውገዝ ይገባዋል።

ሁለተኛ፡- «መጠበቅና መጸለይ» አለብን። ጠላታችን ያለው በመካከላችን ነውና ጨርሶ ለመተኛት መከጀል የለብንም! በአጥቢያ ማኅበረ ምእመናን ያሉ መንፈሳዊ መሪዎች ለጥምቀትና ለቤተ ክርስቲያን አባልነት እጩዎችን ሲያነጋግሩ ንቁ መሆን ያስፈልጋቸዋል። ኮሚቴዎች የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎችን፥ የወጣት ኃላፊዎችን፥ ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ሲመድቡ የክርስቶስን ልብ መፈለግ ያስፈልጋቸዋል። ጉባኤዎች ሽማግሌዎችን ሲመርጡ የመለየት ስጦታን መለማመድ አለባቸው።

ሦስተኛ፡- ጉባኤዎችና አባላት ገንዘባቸውን ለነማን እንደሚሰጡ መጠንቀቅ አለባቸው። «ከሐዲውን ታግዛለህን? ወይስ እግዚአብሔርን የሚጠሉትን ትወድዳለህን?» (2ኛ ዜና 19፡2)።

በመጨረሻ፡- ክርስቶስንና የቃሉን መሠረታዊ ትምህርቶች ከሚክዱት፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የመለየት አቋም ለመያዝ ድፍረቱ ሊኖረን ይገባል (ሮሜ 16፡17-20፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡15 ጀምሮ፤ 2ኛ ዮሐንስ ቁ.6-11)። ይህ ጥቃቅን በሆኑ የትምህርት ልዩነቶች የተነሣ ከአማኝ ወገኖቻችን መለየት አለብን፤ ወይም «በተዛምዶ ሰዎችን መወንጀል» መለማመድ አለብን ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር እውነተኛ ሠራዊት የሆን ለእውነት በሚደረገው ውጊያ ላይ በአንድነት መሰለፍ ያስፈልገዋል።

አንተስ ለክተቱ ጥሪ ተዘጋጅተህ ይሆን?

# መናፍቃንን እወቃቸው!

## ይሁዳ 8-16

ይሁዳ አንባቢዎቹን ጴጥሮስ የጻፈውን እንዲያስተውሉ በማሳሰብ ብቻ አላበቃም። የሐሰት አስተማሪዎች እንዴት ያሉ እንደ ነበሩና በቤተ ክርስቲያን ላይ ምን እንደሚያደርጉ በመግለጥ የገዛ ራሱን የማስጠንቀቂያ ቃላት ለመጨመር ፈልጎ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ የጴጥሮስን ቃላት በማጠናከርና በተመሳሳይ ጊዜ መረጃን በመጨመር ይሁዳ የመናፍቃንን ባሕርያት እንዲገልጥ መራው። ይሁዳ ቁ. 8-16 እና 2ኛ ጴጥሮስ 2 ተመሳሳይነትና ተጓዳኝነት ያላቸው ናቸው።

ግን ለምን ይህ አላስፈላጊ የሚመስል ድግግሞሽ ተደረገ? ሐዋርያው ጳውሎስ መልሱን ሰጥቷል:- «ስለ አንድ ነገር መልሼ ልጽፍላችሁ እኔን አይታክተኝም ለእናንተ ግን ደኅና ነው» (ፊልጵ. 3፡1)። ወላጆች ለልጆቻቸው ማስጠንቀቂያዎችንና መመሪያዎችን በመደጋገም ይሰጣሉ፤ ስለዚህም አንዳንድ ጊዜ ልጆቹ «አውቃለሁ! ብዙ ጊዜ ነግረኸኛል!» ብለው ይመልሳሉ፤ ነገር ግን አስተዋይ ወላጆች አንዳንድ ነገሮችን ለልጆቻቸው ደኅንነትና ጥበቃ ሲባል በተደጋጋሚ መነገር እንዳለባቸው ያውቃሉ። ልጆቹ ሊያዳምጧቸው ቢፈልጉም ባይፈልጉም ይነግሩዋቸዋል!

ይሁዳ በእነዚህ ቁጥሮች ስለ መናፍቃን የጻፈው ነገር ሁሉ በሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ሊጠቃለል ይችላል።

### መለኮታዊ ሥልጣንን ይጋፋሉ (ይሁዳ 8-11)

ሥልጣን ሁሉ፥ የቤተሰብ ወይም የቤተ ክርስቲያን ወይም የመንግሥት ሥልጣን ቢሆንም፥ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዙፋን ነው። ሥልጣን ያላቸው ሰዎች በመጀመሪያ ከሥልጣን ሥር ሆነው ተጠሪነታቸው ለእግዚአብሔር መሆን አለበት። የሐሰት አስተማሪዎች ግን መለኮታዊ ሥልጣንን በመጋፋት የራሳቸውን ሥልጣን ይመሠርታሉ።

የዓመፃቸው መነሾ «ሕልመኞች» (ቁ. 8) በሚለው ቃል ውስጥ ይገኛል። እነዚህ ሰዎች እውን ባልሆነና በተሳሳተ የሕልም ዓለም ውስጥ ይኖራሉ። «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ» (ዘፍ. 3፡5) የሚለውን የሰይጣንን

የማታለያ ቃል ያምናሉ። ከእግዚአብሔር እውነት ተመልሰው እኔነታቸውን ከፍ በሚያደርግ፥ ዓመፀኝነታቸውን በሚያደፋፍር፥ የሐሰት ትምህርት አእምሯቸውን ያደልባሉ። ቁጥር 10 ሐሰተኞች መምህራን ምን እንደሚናገሩ የማያውቁ አላዋቂ ሰዎች እንደሆኑ ያስረዳናል። ጴጥሮስ እነዚህን ሰዎች «ጨካኝ አውሬዎች» (2 ጴጥሮስ 2፡12፥22) ብሎ የሰጠውን ገለጻ ይሁዳም አስተጋብቶታል። እንስሳት የሚኖሩት በተፈጥሮአዊ ደመ-ነፍሳቸው ነው! ሐሰተኞችም መምህራን እንደዚህ ናቸው። ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ሲያምፁ ወደ እንስሳነት ደረጃ ይዘቅጣሉ።

የዓመፃቸውን መንገድ ይሁዳ በግልጥ ዘርዝሮታል። ከዓመፃቸውና ከእምቢታቸው የተነሣ እንስሳዊ ምኞታቸውን ለማርካት እየኖሩ «ሥጋቸውን ያረክሳሉ።» አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ሥልጣን ሲነቅፍ ለእግዚአብሔር ሕግጋት ላለመታዘዝና እንደፈለገው ለመኖር ነፃነት ይሰማዋል። የሚረሳው ቁም ነገር ግን ለእነኝህ ሕጎች አለመገዛት፥ ውሎ ቢያድርም ሸሽተው ወደማያመልጡት ቅጣት ማድረሱን ነው።

ከዚህ በተጨማሪም መናፍቃን በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን ዓመፀኝነት ለመግለጥ በምላሳቸው ይጠቀማሉ። «ምላሳችንን እናበረታለን፤ ከንፈራችን የእኛ ነው፥ ጌታችን ማን ነው?» (መዝሙር [12]፡4)። በቁጥር 8 ና 10 ላይ ያለው «ይሳደባሉ» የሚለው ሐረግ «ክፉ መናገር» ማለት ነው። መሳደብ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ብቻ ሳይሆን ከዚህ በተጨማሪም ሌሎችን ከአንደበት የሚወጡ ጸያፍ ቃላትን ይይዛል። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል በማቃለል ሲመለከት ወይም ሲቀልድበት ወይም ሆን ብሎ እግዚአብሔር እንዲፈርድበት ሲገዳደር፥ እግዚአብሔርን ተሳደበ ማለት ነው። «አፋቸውን በሰማይ አኖሩ፥ አንደበታቸውም በምድር ውስጥ ተመላለሰ። ...እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል? በልዑልስ ዘንድ በውኑ እውቀት አለ? ይላሉ» (መዝሙር [73]፡9፥ 11)።

የዓመፃቸው ውጤት የሚታየው በገዛ ራሳቸው ጥፋት ነው። ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል (ይሁዳ 10) እና ራሳቸውን ያረክሳሉ (ቁ. 8)። እንዲሁም ራሳቸውን ያጠፋሉ፤ ሆኖም ራሳቸውን እያሳደጉ እንደሆኑ ያስባሉ! «በክፉ ሥራ ላይ ፈጥኖ ፍርድ አይፈረድምና ስለዚህ በሰው ልጆች

ውስጥ ልባቸው ክፉን ለመሥራት ጠነከረ» (መክብብ 8፡11)። የዓመፅ መንገድ ሌላ ሳይሆን የጥፋት መንገድ ነው።

የኩራት ንግግር አደገኛ ነገር ነው፤ እግዚአብሔር የመሠረተውን ሥልጣን መንቀፍም እንዲሁ ነው። የመላእክት አለቃ ሚካኤል እንኳ (ዳን. 10፡13) ሰይጣንን ለመገሠጽ አልደፈረም፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ሥልጣን አከበረ። ሚካኤል የሚለው ቃል «እንደ እግዚአብሔር ያለ ማነው?» ማለት ነው። ሰይጣን በዓመፅ ጊዜ በምጸት አነጋገር «በልዑል እመስላለሁ» (ኢሳ. 14፡14) ብሏል፤ ለሰዎች የሚያቀርበው ማታለያው ደግሞ «እንደ አማልክት ትሆናላችሁ» (ዘፍጥረት 3፡5) የሚል ነው።

በሙሴ አካል ላይ በሰይጣንና በሚካኤል መካከል ስለተነሣ ግጭት ምንም መረጃ የለንም። ሙሴ ሲሞት እግዚአብሔር ቀበረው፤ መቃብሩም የት እንደሚገኝ ማንም ሰው አያውቅም (ዘዳግም 34፡5-6)። የአይሁድ ሕዝብ የመቃብሩን ቦታ ቢያውቁት ኖሮ ግን በላዩ ላይ የመስገጃ ስፍራ በመሥራት እንደ ጣዖት ቤት ባመለኩትም ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ያንን እውቀት ለራሱ ብቻ አስቀረው። መጽሐፉ «ማንም ሰው» ቦታውን እንዳላወቀ ይነግረናል። ስለዚህ ምናልባት ሰይጣን ቦታውን አውቆ የሙሴን አካል ለራሱ ሊያደርግ ሞክሮ ይሆናል። በሞት ግዛት ውስጥ ሰይጣን የተወሰነ የሥልጣን ክልል ስላለው ምናልባትም ጣልቃ ለመግባት መብት እንዳለው ተሰምቶት ሊሆን ይችላል (ዕብ. 2፡14-15)።

ዋናው ነጥብ ሚካኤል ሰይጣንን በመገሠጽ ምትክ ለጌታ አሳልፎ መስጠቱ ነው። ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሰይጣንን በቀጥታ መግጠምና ከእርሱ ጋር መከራከር አደገኛ ነገር ነው፤ ምክንያቱም እርሱ ከእኛ በጣም ስለሚበረታ ነው። ሊቀ መለእክቱ እንኳ ከዲያብሎስ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ጥንቃቄ ካደረገ፥ እኛ ደግሞ የቱንስ ያህል የበለጠ ጥንቁቆች መሆን ይኖርብን! ከክርስቶስ ድል ጋር የምንካፈል መሆናችን እውነት ቢሆንም ከመጠን በላይ ደፋር ልንሆን ደግሞ አይገባም። ሰይጣን አደገኛ ጠላት ነው፤ ስንቃወመውም ራሳችንን መቆጣጠርና ጠንቃቃ መሆን አለብን (1ኛ ጴጥሮስ 5፡8-9)።

«እግዚአብሔር ይገሥጽህ» የሚለው ቃል በዘካሪያስ 3፡1-5 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ነቢዩ ሊቀ ካህኑን እድፋም ልብስ ለብሶ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ቆሞ በራእይ ያይ ነበር። ይህም ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የእስራኤል

ሕዝብ የነበረበትን የኃጢአት ርኩሰት የሚያሳይ ነበር። ሰይጣን ከአንድ ነገር በስተቀር ሕዝቡን የሚከስበት ሙሉ መብት ነበረው (ራዕይ 12፡9-11 ተመልከት)። ይኸውም ለእግዚአብሔር የተመረጡ የቃል ኪዳን ሕዝቡ መሆናቸውና የእግዚአብሔርም ይህንን ቃሉን አለማጠፍ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ይቅር ብሎ ንጹሕ ልብስም አልብሶ፥ እርሱ በሚፈቅድላቸው መንገድ እንዲጓዙ አስጠንቀቃቸው። ይህ የ1ኛ ዮሐንስ 1፡5-2፡2 የብሉይ ኪዳን መግለጫ ነው።

የሐሰት አስተማሪዎች ኩነኔ (ፍርድ) በይሁዳ 11 «ወዮላቸው» ተብሎ ተጠቅሷል። «ወዮ ለእነርሱ።» ይሁዳ የኃጢአታቸውን ክብደት ለማሳየት፥ በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ ዓምፀው በዚያ ምክንያት ስለተቀጡት ሦስት ሰዎች የሚናገሩ ሦስት ምሳሌዎችን ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ጠቅሷል።

ቃየል በእግዚአብሔር የማዳን መንገድ ላይ ዓመፀ (ዘፍ. 4፤ 1ኛ ዮሐንስ 3፡11-12)። አዳምንና ሔዋንን የታረዱ እንስሳትን ቁርበት በማልበስ (ዘፍ. 3፡21) እግዚአብሔር የይቅርታ ብቸኛ መንገድ በደም መፍሰስ እንደሆነ ግልጥ አድርጓል። ይህ የእምነት መንገድ ነው እንጂ የመልካም ሥራ መንገድ አይደለም (ኤፌሶን 2፡8-10)። ቃየል ግን ይህንን በመለኮታዊ አሠራር ሥልጣን የተሰጠውን መንገድ ትቶ የገዛ ራሱን የልፋት ፍሬ የሆነውን ወደ መሠዊያው ይዞ መጣ። እግዚአብሔር ቃየልን ስላልተቀበለ መሥዋዕቱንም አልተቀበለም፡- ልቡ በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ አልነበረም። የአቤል መሥዋዕት የቀረበው በእምነት ነበር፤ እግዚአብሔርም የተቀበለው ለዚያ ነበር (ዕብ. 11፡4)።

«የቃየን መንገድ» እምነት የሌለው ሃይማኖት መንገድ ነው፤ ይኸውም በግለሰቡ መልካም ሥራ ላይ ከተመሠረተ ጽድቅ ጋር የሚመሳሰል ነው፤ «የቃየን መንገድ» የትዕቢት መንገድ ነው፥ ሰው በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ጽድቅ በራሱ የጽድቅ ሥራዎች ለመተካት ሲሞክር ነው የምናየው (ሮሜ 10፡1-4፤ ፊልጵ. 3፡3-12)። ቃየል ኮብላይ ሆነ፥ ከተማን በመገንባትና ሥልጣኔን በማስፋፋት ችግረኛነቱን ለማሸነፍ ሞከረ (ዘፍ. 4፡9 ጀምሮ)። በመጨረሻም ከእግዚአብሔር በቀር ሰው ሊያገኝ የሚመኘውን ማንኛውንም ነገር አገኘ።

«የበለዓምን መንገድ» ከዚህ በፊት አጥንተነዋል (2ኛ ጴጥሮስ 2፡15-16 ተመልከት)። «የበለዓም መንገድ» ግላዊ ተሰጥኦንና አገልግሎትን ገንዘብ ለማግኛ ሲባል ብቻ መሸጥ ነው። ቁሳዊውን ለማግኛ በመንፈሳዊው መጠቀም ማለት ነው (1ኛ ተሰ. 2፡5-6፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡3-21 ተመልከት)። ሐሰተኞች አስተማሪዎች ቁሳቁስ ለመሰብሰብ ስግብግቦች ነበሩና እንደ በለዓም ለገንዘብ ሲሉ ማንኛውንም ነገር ያደርጋሉ። «የበለዓም ስሕተት» በዚህ ዓይነቱ ዓመፅ ቢካፈሉም ያለፍርድ ማምለጥ ይቻላል ብሎ ማሰብ ነው። በለዓም እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር፤ ነገር ግን ስጦታዎቹን ለመሸጥና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት ፈለገ። እግዚአብሔር የበለዓምን እርግማኖች ወደ በረከቶች ለወጣቸው (ዘዳ. 23፡4-5)።

ስለ በለዓም ስንነጋገር እግረ መንገዳችንንም «ስለ በለዓም ትምህርት» ያጤንነው ነገር ሊኖር ይችላል (ራዕ. 2፡14)። የበለዓም ትምህርት በሥልጣንህ የፈለግኸውን አድርግ የሚል ነበር። ለንጉሥ ባላቅ የእስራኤልን ሕዝብ ለማጥፋት ፈጣኑ መንገድ ሕዝቡ በዙሪያቸው ካሉት አረመኔ መንግሥታት ጋር ራሳቸውን እንዲያረክሱ ማግባባት እንደሆነ ነገረው። መከራከሪያው «እናንተ የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝቦች ናችሁ» የሚል ነበር። «ከጎረቤቶቻችሁ ጋር ጥቂት ጓደኝነት ምንም አይጎዳችሁም!» ይህም «የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት መለወጥ» ነው (ይሁዳ 4)። እግዚአብሔርም እስራኤልንና በለዓምን ሁለቱንም ቀጣ።

የቆሬ ታሪክ የሚገኘው በዘኍልቁ 16 ነው፤ ይህም ታሪክ ሥልጣንን በመቃወም በሚነሣ ዓመፅ ላይ ያተኩራል። ቆሬና ተከታዮቹ የሙሴን አመራር ከመሳደባቸው ስለ ዓመፃቸው እግዚአብሔር እንደመሰለው ይፈርድባቸው ዘንድ ተገዳደሩት። በሙሴ ላይ ክፉ መናገር ማለት ሥልጣኑን ለሙሴ በሰጠው በእግዚአብሔር ላይ መናገር ነበር። ዛሬም ቢሆን በመንፈሳዊና በመንግሥታዊ መሪዎች ላይ በግዴለሽነት መናገር በጣም ቀላል ስለሆነ፥ በቆሬ ላይ የደረሰው ቅጣት ለእኛ ማስጠንቀቂያ ነው (ቲቶ 3፡1-2 ተመልከት)። እግዚአብሔር ቆሬንና ተከታዮቹን ቀጥቶ የባሪያውን የሙሴን ሥልጣን በግልጥ አጸና።

ቃየል እግዚአብሔር እንዳዘዘ የደም መሥዋዕት አላቀርብም በማለቱ በእግዚአብሔር የማዳን ሥልጣን ላይ ዓመፀ። በለዓም ስጦታዎቹን በገንዘብ ከመሸጡም እስራኤል ከሌሎች ሕዝቦች ጋር እንዲቀላቀሉ በመምራቱ በእግዚአብሔር የመለየት ሥልጣን ላይ ዓመፀ። ቆሬ ሙሴ በእግዚአብሔር የተቀባ ባሪያ እንደሆነ በመካድና ሥልጣኑን ያለአግባብ ለመንጠቅ በመሞከር በእግዚአብሔር የአገልግሎት ሥልጣን ላይ ዓመፀ።

ይሁዳ በዚህ ቁጥር ላይ የተጠቀመባቸውን ግሦች ማስተዋል ጠቃሚ ነው። ሐሰተኛ አስተማሪዎች በቃየል መንገድ «ሄደዋል»፤ ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው «ሰጥተዋል»፤ እንዲሁም በቆሬም ዓመፅ «ጠፍተዋል»። ሥልጣንን የመግፋት አሳዛኝ ገጽታ ይህን ይመስላል።

## እያወቁ በግብዝነት ይሠራሉ (ይሁዳ 12-13፥ 16)

ቁጥር 12 ና 13 የሐሰት አስተማሪዎችን ስድስት ዓይነተኛ ባሕርያት ከመግለጣቸውም ለምን ለቤተ ክርስቲያን አደገኞች እንደሆኑም ያብራሩልናል።

«ነውረኛ ዕንቅፋቶች»፡- ጴጥሮስ ነውረኞችና ርኩሳን ብሎ ጠርቷቸዋል (2ኛ ጴጥሮስ 2፡13)። እነዚህ ሰዎች በአጥቢያ ጉባኤዎች በነበሩት ክርስቲያኖች «የፍቅር ግብዣዎች» መካከል ገብተው ነበር፤ ያደረጉት ግን እነዚያን ግብዣዎች ማርከስ ነበር። ይሁዳ ኢየሱስ ባከበረው በመጨረሻው ፋሲካ ላይ እንደ አደረገው ሁሉ እነዚህም የሐሰት አስተማሪዎች ለፍቅር ግብዣው ቅድስናን በመጨመር ፈንታ ክብሩን ቀንሰውበታል። በጣም የሚያሳዝነው ነገር የማኅበሩ አባላት የእነዚህን ሰዎች እውነተኛ ባሕርይ አለመረዳታቸው ነው። ሰዎቹ መንፈሳውያን እንደሆኑ አስበው ነበር!

«ዕንቅፋት» ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል «የተሰወሩ ቋጥኞች» ማለትም ሊሆን ይችላል። የተሰወሩትን ቋጥኞች ያላስተዋለ መርከበኛ ሳይታወቀው መርከቡን በማጋጨት ሊያሰጥም ይችላል። ስለዚህ ጸጥ ያሉና የረጉ ውኆች በሚያጋጥሙት ጊዜ ሁሉ የመርከቡ ነጂ ንቁና ጥንቁቅ መሆን አለበት። መንፈሳዊ መሪዎች ሁልጊዜ በተጠንቀቅ መቆም አለባቸው።

ራስ ወዳድ እረኞች፡- «እረኝነት» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «መመገብ» ማለት ነው። ለመንጋቸው እረኛ በመሆንና ለሕዝቡ ፍላጎት

በመጠንቀቅ ፈንታ እነዚህ መናፍቃን ግን የሚጠነቀቁት ለራሳቸው ብቻ ነው። ምናልባትም ይሁዳ ይህንን በሚጽፍበት ጊዜ ሕዝቡን በመጨቆናቸውና ለራሳቸው ብቻ በማሰባቸው ነቢዩ ኢሳይያስ 56፡ 10-12 እና ሕዝቅኤል 34 የወቀሷቸው ፖለቲካዊና መንፈሳዊ መሪዎች ታውሰውት ሊሆን ይችላል።

በእግዚአብሔር መንጋ ላይ እረኛ መሆን ከባድ ነገር ነው። ምሳሌያችን መሆን ያለበት ለበጎቹ ነፍሱን የሰጠው መልካም እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የሐሰት አስተማሪዎች የሚፈልጉትን ለማግኘት በሰዎች ቢጠቀሙና ወደ ርኩሰት ቢመሯቸውም አንዳንዶች ግን ይህን ተግባራቸውን ይወዱላቸዋል! ጳውሎስ 2ኛ ቆሮንቶስ 11፡20ን ሲጽፍ በዚህ ነገር ተደንቋል - «ማንም ባሪያዎች ቢያደርጋችሁ፥ ማንም ቢበላችሁ፥ ማንም ቢቀማችሁ፥ ማንም ቢኮራባችሁ፥ ማንም ፊታችሁን በጥፊ ቢመታችሁ ትታገሣላችሁና።»

እነዚህ ራስ ወዳድ እረኞች ይህንን ሁሉ የሚያደርጉት «ያለ ፍርሃት» ነው። ከመጠን በላይ በራሳቸው የሚተማመኑ ናቸው። በእውነተኛ እረኛና በምያተኛ መካከል ያለው ልዩነት ግን የሚከተለውን ይመስላል፡- ቅጥረኛው እረኛ ለራሱ ብቻ ሲጠነቀቅ እውነተኛው እረኛ ግን ለመንጋው ይጠነቀቃል። «ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው! እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን?» (ሕዝቅኤል 34፡2)፤ ነገር ግን እነዚህ ሐሰተኞች ፍርዳቸው እየቀረበ ስለሆነ መፍራት በተገባቸውም ነበር!

ባዶ ደመናዎች፡- ዝናብ እንደሚኖር ተስፋ የሚሰጡ ደመናዎች፥ ታይተው አንዳችም ጠብታ ሳይዘንብ ቢቀር ለሰብሎቹ ውኃ ለሚፈልገው ገበሬ የልብ ኀዘን ናቸው። የሐሰት አስተማሪዎች መንፈሳዊ እርዳታ መስጠት የሚችሉ ሰዎች ከመምሰላቸውም ስለችሎታቸውም ይመካሉ፤ ነገር ግን ፍሬቢሶች ናቸው። «ስለ ስጦታው በሐሰት የሚመካ ሰው ዝናብ እንደማይከተለው ደመና ነፋስም ነው» (ምሳ. 25፡14)። የአርነትን ተስፋ ይሰጣሉ፥ መስጠት የሚችሉት ግን እስራትን ብቻ ነው (2ኛ ጴጥሮስ 2፡19)።

የእግዚአብሔር ቃል አንዳንድ ጊዜ ከዝናብና ከካፊያ ጋር ይመሳሰላል። «ትምህርቴ እንደ ዝናብ ትፈስሳለች፥ ነገሬ እንደ ጠል (ካፊያ) ትንጠባጠባለች» (ዘዳግም 32፡2)። ኢሳይያስ 55፡10 የእግዚአብሔርን ቃል መሬትን ፍሬ እንድታፈራ ከሚያደርጉት ከዝናብና ከበረዶ ጋር

ያመሳክረዋል። በሰማይ ላይ እንዳሉት ደመናዎች የሐሰት አስተማሪዎቹ የተከበሩና የሚስቡ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ዝናብን መስጠት ካልቻሉ ግን የማይጠቅሙ ናቸው።

የሞቱ ዛፎች:- በዚህ ርእስ ሥር የምናገኘው መልእክት ገበሬ ፍሬ የሚጠብቅበትን የመፀው ወራት የተመለከተ ነው። ገበሬው ዛፎቹ እንደሚያፈሩለት ቢጓጓም፥ ዛፎቹ ፍሬ አልባ ነበሩ፤ «በፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ» (ማቴ. 7፡16)። ቃልን የሚያስተምሩና የሚሰብኩት ሰዎች ሌሎችን የመመገብ ኃላፊነት አለባቸው፤ የሐሰት አስተማሪዎች ግን የሚሰጡት ምንም ነገር የላቸውም። ፍሬ አልባዎች ብቻ ሳይሆኑ ሥር አልባም ናቸው። «ከነሥራቸው የተነቀሉ» የተባሉትና «ሁለት ጊዜ የሞቱ» ናቸው የተባሉት ለዚህ ነው። ይህ በመዝሙር 1፡3 ላይ ካለው እግዚአብሔርን ከሚፈራው ሰው ጋር እንዴት ያለ ተቃራኒ ነው!

ከእውነተኛ ደኅንነት ማረጋገጫዎች አንዱ የመንፈስ ፍሬ ማፍራት ነው። ባልለሰለሰ ዓፈር፥ ጥልቀት በሌለው ዓፈርና በሥራሥር በተያዘ ዓፈር ላይ የወደቀው ዘር ፍሬ አላፈራም፤ ነገር ግን «በመልካም መሬት» ላይ የወደቀው ዘር ፍሬ አፍርቷል (ማቴ. 13፡1-9፥ 18-23)። የሐሰት አስተማሪዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንም ያህል ቢጠቅሱ፥ ዘሩ በእነርሱ በራሳቸው ሕይወትም ውስጥ ሆነ ወይም በአገልግሎታቸው በኩል ፍሬ አያፈራም። ለምን? ምክንያቱም መንፈሳዊ ሥር ስለሌላቸው ነው። መንፈሳዊ ሕይወት ይጎድላቸዋል።

በአንድ ፍሬ ውስጥ ለብዙ ፍሬዎች የሚያበቃ ዘር አለ (ዘፍ. 1፡11-12)። የአንድ ሰው አገልግሎት በእውነትም ከእግዚአብሔር ለመሆኑ አንዱ ማረጋገጫ የፍሬው መብዛት ነው። ሰው ሠራሽ «ፍሬዎች» መካንና የሞቱ ናቸው፤ እውነተኛ ፍሬ ግን ማደጉንና ዘሩን ማራባቱን ይቀጥላል።

ጨካኝ የባሕር ማዕበል:- እኔ በግሌ በውቅያኖስ ውስጥም ሆነ ወይም ላይ መሆንን አልወድም፤ ማለትም፥ ጥሩ ዋናተኛ አይደለሁም። ሆኖም ከውቅያኖስ አጠገብ መቀመጥና ታላቅነቱንና ኃይሉን ማሰላሰል እወዳለሁ። ነገር ግን በማዕበል ጊዜ በውቅያኖሱ ውስጥ ወይም ላይ ላዩን መሆንን ፈጽሞ አልፈልግም! ብዙ መርከበኞች እንደሚናገሩት በእነዚያ ማዕበሎች ውስጥ ትልቅ ኃይል አለ። ይሁዳም መናፍቃንን ከ«ጨካኝ የባሕር ማዕበል» ጋር

ያመሳስላቸዋል። ይህም ከኃይላቸው የተነሣ ሳይሆን ከትዕቢታቸውና ከኩራት ንግግራቸው የተነሣ ነው። «አፋቸው ከመጠን ይልቅ ታላቅ ቃል ይናገራል» (ቁ. 16)፤ እንደ ባሕሩ ሞገድ ብዙ ድምፅ ያሰማሉ፤ ግን ምንድነው የሚያፈሩት? ለመሆኑ ከማዕበል በኋላ ባለው ማግሥት ወደ ባሕር ዳርቻ ብቅ ብላችሁ በዚያ የተከማቸውን የሚያስጠላ ቆሻሻ አይታችሁ ታውቁ ይሆን?

ይሁዳ በአሳቡ ምናልባት ኢሳይያስ 57፡20ን አስታውሶ ይሆናል፡- «ክፉዎች ግን እንደሚንቀሳቀስ ባሕር ናቸው፤ ጸጥ ይል ዘንድ አይችልምና፥ ውኆቹም ጭቃና ጉድፍ ያወጣሉና።» የመናፍቃን «ከመጠን የላቀ ታላቅ ቃል» ውጤት ዓረፋና እጣቢ ብቻ ነው! እውነተኛ የቃሉ አስተማሪዎች በጥልቅ ተመራምረው የከበረን መዝገብ ያስገኛሉ፤ የሐሰት አስተማሪዎች ግን የሚያፈሩት ቆሻሻና ጥራጊ ብቻ ነው። እናም ጉራ በሚነዙበት ነገር ሊያፍሩ ይገባቸዋል (ፊልጵስዩስ 3፡ 19 ተመልከት)።

የሚንከራተቱ ከዋክብት፡- ይሁዳ ይናገር የነበረው ቋሚ ቦታ ስላላቸው ከዋክብት፥ ዓለማት ወይም ፈለኮች አልነበረም፤ ምክንያቱም እነሱ የተወሰኑ ቦታዎችና ምሕዋሮች ስላሏቸው ነው። እርሱ ግን ይናገር የነበረው በአንድ ጊዜ ታይተው ዳግመኛ ላለመታየት ወደ ጨለማ ገብተው ስለሚጠፉት ተወርዋሪ ከዋክብት ነበር። ጌታችን በከዋክብት ተመስሏል (ራዕይ 2፡28፤ 22፡16)፤ ክርስቲያኖችም በዚህ ጨለማ ዓለም እንደ ከዋክብት የሚያበሩ ናቸው (ፊልጵ. 2፡15)። በቦታቸው ቋሚ የሆኑ ከዋክብት ተጓዦችን በጨለማ ውስጥ ለመምራት አስተማማኝ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወዲህ ወዲያ የሚሉ ከዋክብት ግን ሊመሩት የሚችሉት ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ብቻ ነው።

በግሌ ማድረግ ከምወዳቸው ነገሮች አንዱ የስብከት መጻሕፍትን መሰብሰብ ነው፤ ታዲያ በታወቁ ሰባኪያን የተሰበኩትን ብቻ ሳይሆን በአንድ ወቅት ስማቸው ዝነኛ በነበሩና በተረሱ ሰዎች የተሰበኩትንም ነው። «የመድረክ መብራት» የነበሩ ብዙዎች የወደቀ ኮከብ እንደሆኑ አስተውያለሁ! ታሪኮችንና የሕይወት ታሪኮችን ማንበብና «ኃይለኞች እንደወደቁ» ማየት የሚረብሽ ነው። በአብዛኛው ለቃሉ እውነተኞች የነበሩት በጨለማ እንደሚያበሩ መብራቶች ዛሬም እያገለገሉ ሲሆን፥ የሐሰት ትምህርት ሰባኪያን ግን ተረስተው ወድቀዋል።

እግዚአብሔር ለዓመፀኞቹ መላእክት የጨለማ ሰንሰለት አዘጋጅቶላቸዋል (ይሁዳ 6)። እንዲሁም ለሐሰተኞች መምህራን የዘላለማዊ ድቅድቅ ጨለማ ጠብቆላቸዋል። ስለዚህ የሚወድቅ ኮከብ እንዳትከተሉ ተጠንቀቁ! ወደ ዘላለም ጨለማ ይመራችኋል!

እነዚህን ስድስት የሐሰት አስተማሪዎችን ገላጭ ባሕርያት ደጋግማችሁ በምታጤኑበት ጊዜ የቱን ያህል አደገኞች እንደሆኑና ቤተ ክርስቲያንም ያለ ምንም ይሉኝታ ልታገልላቸው እንደሚገባ ለመረዳት ትችላላችሁ። ቁጥር 16 ገለጣውን ከጨረሰ በኋላ፥ በመቀጠል እነኝህ ሰዎች ለምን አደገኞች እንደሆኑ አጉልቶ ያሳያል። እነርሱም በሌሎች ትከሻ ራሳቸውን ለማስደሰት ሌት ተቀን የሚጥሩ ናቸው። ይህም የጴጥሮስን አነጋገር ያስታውሰናል (2ኛ ጴጥሮስ 2፡14)፤ « መመኘትን የለመደ ልብ አላቸው» ወይም ፊሊጵስ የሚባለው የእንግሊዘኛ ትርጉም እንደሚለው፡- «የሚፈልጉትን የሚያገኙበት ዘዴያቸው በረዥም ጊዜ ልምድ የካበተ ነው።» ሊረዱችሁ እንደመጡ ያስመስላሉ፤ ነገር ግን የራሳቸውን ምኞት ማሟላት ብቻ ነው የሚፈልጉት።

አቀራረባቸው እንዴት ነው? እነርሱ በራሳቸው ሕይወት በማማረርና በማጉረምረም ለሌሎች ሕይወት መማረር ምክንያት ይሆናሉ፤ በዚህም ሰዎች በኑሮአቸው እንዳይረኩ ተስፋ ያስቆርጣሉ። ምንም እንኳ እያንዳንዳችን እግዚአብሔር በፈቀደልን መጠን ኑሮአችንን ለማሻሻል የምንችለውን ሁሉ ማድረግ ቢገባንም፥ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን ማዘጋጀት እንዳናንቋሽሽ ወይም ዕቅዶችን እንዳናደናቅፍ መጠንቀቅ አለብን። የእስራኤል ሕዝብ ከማጉረምረሙ የተነሣ ተቀጥቷል (1ኛ ቆሮ. 10፡1-10)፤ ክርስቲያኖችም እንዳያጉረመርሙ ታዝዘዋል (ፊሊጵስዩስ 2፡14-16)። አንድ ሐሰተኛ አስተማሪ አንድን ሰው ስለ መጋቢው ወይንም ስለ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲያጉረመርም ወይም ቅሬታ እንዲያድርበት ለማድረግ ከቻለ፥ በመቀጠል ወደ ሐሰት ትምህርት ሊመራው ይችላል።

እንዲሁም የሐሰት አስተማሪዎች የማያውቁትን ሰዎች ለመማረክ «ከንቱ በሆኑ ታላላቅ ቃላት» ይጠቀማሉ። ጴጥሮስ ንግግራቸውን «ከንቱና ከመጠን ይልቅ ታላቅ ቃል» የሆነውን ብቻ ነው ብሎታል (2ኛ ጴጥሮስ 2፡18)። በአነጋገራቸው ሰዎችን ይማርካሉ፤ የሚናገሩት ግን «ባዶ ወሬ» ብቻ ነው።

አድማጮቻቸውን በመቆጣጠር በሙገሳ ቃላት በመደለል ይጠቀማሉ። ለእነርሱ የሚጠቅም ከሆነ ለሌሎች «የተጋነነ ክብር» ከመስጠት ወደኋላ አይሉም።

ይህን ሁሉ እያወቀ ማንም ሰው እነዚህን መናፍቃን መከተሉ ያስገርመናል፤ የሚደንቀው ደግሞ አሁንም ቢሆን ብዙዎች እየተታለሉባቸው መሆኑ ነው! ወደ ተሻለ ደረጃ እንደማያደርሰው ቢረዳም፥ በወደቀው የሰው ልጅ ባሕርይ ውስጥ ግን በውሸት የመታለልና የመከተል ዝንባሌ ጎልቶ ይታያል። ይሁንና የመናፍቃን ፍርዳቸው እየቀረበ በመሆኑ በማታለል የሚያገኙት ስኬታማነት ጊዜያዊ ነው።

## የሚገባቸውን ቅጣት ይቀበላሉ (ይሁዳ 14-15)

ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሄኖክ የምናውቀው ነገር ሁሉ የሚገኘው በዘፍጥረት 5፡18-24፥ በዕብራውያን 11፡5 እና በይሁዳ መልእክት ውስጥ ባሉት በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ብቻ ነው። ቃየልም የዚህ ዓይነት ስም ያለው ልጅ ስለነበረው (ዘፍጥረት 4፡17)፥ የቃየልን ልጅ ሄኖክ እግዚአብሔርን ከሚፈራው ሄኖክ ለመለየት ሲባል «ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ» ተብሎ ተጠርቷል። ከኃጢአቱ መብዛት የተነሣ በፍጥነት እየተበከለና እየጠፋ ባለ ኅብረተሰብ ውስጥ ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ ሕይወቱን በንጽሕና ጠበቀ። እንደ ነቢይም በማገልገል ስለሚመጣው ፍርድ አስታወቀ።

የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይህ ጥቅስ «መጽሐፈ ሄኖክ» ከሚባል ከሰማንያ አንዱ መጽሐፍ እንደተጠቀሰ (አፓክሪፋል መጽሐፍ) ይነግሩናል። ይሁዳ ከዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ መጽሐፍ በመጥቀሱ «መጽሐፈ ሄኖክን» በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፈና አስተማማኝ መጽሐፍ አያደርገውም። ይህ ከሆነማ፤ ጳውሎስም ከግሪክ ባለቅኔዎች ጠቅሶ ጽፎ ነበር፤ ዳሩ ግን ይህን መጥቀሱ የግሪክ ባለቅኔዎች የጻፉትን ሁሉ «የእግዚአብሔርን ማረጋገጫ ማኅተም» እንዳገኘ ሊያስቆጥረው አይገባም። የእግዚአብሔር መንፈስ ግን ይሁዳን ይህንን ጥቅስ እንዲጠቀምበትና በመንፈስ ምሪት የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዲያደርገው መራው።

ሄኖክ ይህንን መልእክት በመጀመሪያ ሲሰጥ፥ እየመጣ ስላለው የጥፋት ውኃ መናገሩ ሊሆን ይችላል። ሄኖክ እግዚአብሔር በማይፈራበት ዘመን እንደኖረ እርግጥ ነው። በዚያም ወቅት ኃጢአተኞች ለጊዜውም ቢሆን በከፉ

ሥራቸው አልተፈረደባቸውም ነበር። ሄኖክ ግን ፍርድ እየመጣ እንደሆነና እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሰዎች ቅጣት እንደሚቀበሉ ግልፕ አድርጓል።

ሆኖም ይህ ትንቢት ተፈጻሚነት የሚኖረው በዚች ዓለም የመጨረሻ ቀናት ሲሆን ይህም ጴጥሮስ በ2ኛ መጽሐፉ ምዕ. 3 ላይ የጻፈው ፍርድ ነው። የሐሰት አስተማሪዎች ግን በዚህ ትንቢት ላይ ከማሾፋቸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጽሞ እንደማይመለስና እግዚአብሔርም ፍርድን እንደማያመጣ ይከራከሩ ነበር። ነገር ግን ጌታችንም ሐዋርያቱም እንደዚሁም ነቢያት በመጨረሻው ዘመን ዘባቾችና አሿፊዎች እንደሚመጡ ስለተናገሩ የእነዚህ ሰዎች ሁኔታ፥ በራሱ ለቃሉ እውነተኛነት ተጨማሪ ማስረጃ ነበር (2ኛ ጴጥሮስ 3፡1-4)። ሄኖክ ትንቢቱን የተናገረው ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ነበር! እንግዲህ እግዚአብሔር ዓመፀኞችን ምን ያህል እንደሚታገሣቸው አስተውሉ!

ስለሚመጣው ፍርድ የሄኖክ ትንቢት ምን ይላል? በዚያን ዕለት ለእያንዳንዱ ሰው እንደየሥራው ፍርድ የሚሰጠው ሲሆን፥ ፍርዱም በእግዚአብሔር የሚተላለፍ ነውና በዓለም ላይ ሊፈርድ ይመጣል። ራብ ወይም የጥፋት ውኃ አይልክም፤ ወይም ደግሞ ይህን ተግባር እንዲፈጽመው ለአንድ መልአክ ውክልናውን አይሰጥም። እርሱ ራሱ ይመጣል። ይህ የነገሩን ከባድነት እንዲሁም መጨረሻነት ያሳያል። «ፈራጅ በደጅ ቆሞአል» (ያዕቆብ 5፡9)።

እግዚአብሔር ግላዊ ፍርድ የሚሰጥ ቢሆንም ብቻውን ግን አይፈርድም፤ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ከእርሱ ጋር ይሆናሉ። በይሁዳ 14 ላይ ያለው ቅዱሳን የሚለው ቃል «ፍጹምነትን» ስለሚያመለክት መላእክትንም ሊጨምር ይችላል (ዘዳግም 33፡2፤ ማቴ. 25፡31)። ከዚህም በተጨማሪ ከራእይ 19፡14፤ ከቆላስይስ 3፡4 እንዲሁም ከ1ኛ ተሰሎንቄ 3፡13 እንደምንረዳው፥ ጌታ ጠላቶቹን ለማሸነፍና የጽድቅ መንግሥቱን ለመመሥረት ወደ ምድር ሲመለስ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሚያጅቡት እናውቃለን (1ኛ ቆሮ. 6፡2-3 አነጻጽር)። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለዘመንና ዘመናት በኃጢአተኞች ሰዎች እጅ ተሰቃይተዋል፤ አንድ ቀን ግን ሁኔታዎቹ ይለወጣሉ።

ዓለም አቀፍ ፍርድ ይሆናል። የሚፈርደው «በሁሉም ላይ» ነውና ከዚያ ፍርድ ማንም አያመልጥም። የጥፋቱ ውኃ ከመርከቡ ውጭ የነበሩትን ሁሉ እንዳጠፋ፥ እንዲሁም እሳቱና ዲኑ ከሎጥና ከሚስቱ፥ ከሁለቱ ሴቶች ልጆቹም በቀር ሰዶምንና ገሞራን በሙሉ እንዳጠፋ፥ የመጨረሻውም ፍርድ ኃጢአተኞችን በሙሉ ያጠቃልላል። ለማንም ግልጥ እንደሚሆነው በዚሁ ቁጥር ውስጥ ብቻ «ኃጢአተኞች» የሚለው ቃል አራት ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅሷል! ያም ቀን «እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች የሚጠፉበት የፍርድ ቀን» ይሆናል (2ኛ ጴጥሮስ 3፡7)።

ፍርዱም አድሏዊነት የሌለበት ፍጹም ፍትሐዊ ነው። እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታቸው ይወቅሳቸዋል፤ ጥፋተኞች እንደሆኑም ያስታውቃቸዋል። ከዚያም ተገቢውን ፍርዳቸውን በመስጠት ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ያደርጋል። ይህም ዳኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐንስ 5፡22)፤ ነገር ግን ፍርዱን የሚተች ሸንጎ አይኖርም። በኃጢአተኛው ላይ ፍርድ ይተላለፋል እንጂ ሙግት አይኖርም፤ እንደበት ሁሉ ይዘጋልና (ሮሜ 3፡ 19) አቤቱታም ማቅረብ አይቻልም። የፍርዱ ሥርዓት ፍትሐዊ ከመሆኑም፥ ዳኛውም ጻድቁ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ሂደቱ በሙሉ በጽድቅ ይሆናል።

ጌታ የእያንዳንዳቸው «የበደል ሥራ» የተመዘገበበት መዝገብ ይኖረዋል። እንደዚሁም እነዚህን የከፋት ሥራዎች ሲፈጽሙ የነበራቸው የውስጥ ምኞት እና የተሰወረው ፍላጎታቸው ሁሉ የሰፈረበት የኃጢአት መዝገብ በዚያን ቀን ይፋ ይሆናል! በጌታም ላይ የተናገሩት «የድፍረት ቃል» ሁሉ (ይሁዳ 15) ያስታውሳል። «ድፍረት» የሚለው ቃል «ስድ፥ ኃይለኛ፥ ግትር፥ የባለገ» የሚለውን አሳብ ይይዛል። በመሠረቱ እነዚህ ሰዎች «የሚያንጎራጉሩ» እና «የሚያጉረመርሙ» (ቁ. 16)፥ እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ የድፍረት ቃል የተናገሩ ናቸው። ሥልጣን ያላቸውን ሲሳደቡ» አይፈሩም (2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 10)፤ በፍርድ ጊዜ ግን ንግግራቸው በእነርሱ ላይ ይመሰክራል። «ከንቱ የሆነ ታላቅ ቃል» ተናግረዋልና (2ኛ ጴጥሮስ 2፡ 18፤ ይሁዳ 16) በፍርድ ጊዜ እነዚያ ታላላቅ ቃላታቸው ታላቅ ቁጣን ያደርሱባቸዋል።

የእግዚአብሔር ልጆች፡- «አቤቱ ኃጢአተኞች እስከመቼ ይጓደዳሉ? ይከራከራሉ፤ ዓመፃንም ይናገራሉ፥ ዓመፃንም የሚያደርጉ ሁሉ ይናገራሉ» (መዝ. [94]፡ 3-4) ብለው የሚጠይቁበት ጊዜ ይመጣል። ለዚህም መልሱ

በመዝሙር[50]፡ 3 ላይ ተሰጥቷል፡- «አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም፤ እሳት በፊቱ ይቃጠላል፥ በዙሪያውም ብዙ ዐውሎ አለ።»

እነዚህን ቃላት ማዳመጥ የተለመደ ነው። ይህንንም አስመልክቶ ጄምስ ራስል ሎዌል የተባለው ገጣሚ አንድ ግጥም ገጥሞአል። የግጥሙም አሳብ ባጭሩ የሰው ታሪክ በመላ በጨለማ ሥርዓትና በእግዚአብሔር የጽድቅ ሥርዓት መሀከል የሚታገል ይመስላል። ምንም እንኳ እውነትና ውሸት ለጊዜው በጦርነት ላይ ቢሆኑም፥ በመጨረሻ ግን እውነት በአሸናፊነት እንደሚወጣ የተረጋገጠ ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን እግዚአብሔር በስውር እየተመለከተና የራሱ የሆኑትን ሁሉ እየጠበቃቸው መሆኑን ግጥሙ ያብራራል።

«ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን» (2ኛ ጴጥሮስ 3፡ 13)።

«ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና»

# መሰናከል የለብህም

(ይሁዳ 17-25)

ታላቁ የቻይና ግምብ ቢያንስ ሦስት ጊዜ በጠላት እንደተደፈረና በእያንዳንዱም ጊዜ ጠባቂዎቹ በጉቦ እንደተታለሉ ከአንድ ጽሑፍ ላይ አንብቤያለሁ።

ጠንካራ መከላከያን የሚወስነው የጠንካራ ሰዎች መኖር ነው። ይህ ደግሞ በመንፈሳዊ ውጊያም ሆነ ወታደራዊ ሰልፍ ላይ የሚሠራ ነው። ቤተ ክርስቲያን ሐሰተኞች አስተማሪዎችን ለመቃወምና ለማሸነፍ ካስፈለጋት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለን ሁላችንም ጠንካሮችና «የዲያብሎስን ሽንገላ ለመቃወም» የምንችል (ኤፌ. 6፡ 11) መሆን አለብን። ሁልጊዜ የመሰናከል አደጋ አለ (ይሁዳ 24)፤ መሰናከል ደግሞ ለመውደቅ የመጀመሪያው እርምጃ ነው።

በዚህ የመዝጊያ አንቀጽ ይሁዳ የተወደዱ አንባቢዎቹ ጸንተው ለመቆምና መናፍቃንን ለመቃወም እንዲችሉ አራት መመሪያዎችን ሰጥቷቸዋል።

## የእግዚአብሔርን ቃል አስታውሱ (ይሁዳ 17-19)

ሰይጣን ከመጀመሪያው አንሥቶ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ተቃወመ ነበር። በመሆኑም ሔዋንን በገነት አግኝቶ ወደ አለመታዘዝ የመራት «በውኑ እግዚአብሔር ... እንዳትበሉ አዝዞአልን?» (ዘፍ. 3፡1) የሚለውን የማግባቢያ ጥያቄ በቅድሚያ በማቅረብ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል መጠራጠር ከጀመርን ለሌሎች የሰይጣን ጥቃቶች የተጋለጥን እንሆናለን። ከዲያብሎስ ማታለያዎች ሊጠብቀን የሚችለው የቃሉ እውነት ብቻ ነው። «ወደ ሕግና ወደ ምስክር ሂዱ! እንዲህም ያለውን ቃል ባይናገሩ ንጋት አይበራላቸውም» (ኢሳ. 8፡20)።

ቃሉን ማን እንደተናገረ አስቡ (ቁ. 17)፡- ጌታችን ብዙ ደቀ መዛሙርት ቢኖሩትም፥ ሐዋርያት እንዲሆኑ የመረጣቸው ጥቂቶችን ብቻ ነው። ሐዋርያ ማለት «አንድን ዓላማ ለማሳካት የተላከ መልእክተኛ» ማለት ነው። ለዚህ ተልእኮ ብቁ ለመሆን አንድ አማኝ የትንሳኤው ምስክር መሆን ነበረበት (1ኛ ቆሮ. 9፡1፤ የሐዋ. 1፡21-22)። ሐዋርያት በአገልግሎቱ ጊዜ ከጌታ ጋር

ኖረዋል፤ ከእርሱ ተምረዋል። በተጨማሪም ከእርሱ የተቀበሉትን የደኅንነትን የምሥራች ዜና ለዓለም ሁሉ እንዲያደርሱ የተላኩ ነበሩ።

እውነተኛ ነገር ባለበት ቦታ ሁሉ በዚያው መጠን አስመሳዮች ብቅ ብቅ ይላሉ። ይህ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የታየ ነገር ነው። የሐሰት ሐዋርያትና አስተማሪዎች መታየት በመጀመራቸው ቤተ ክርስቲያንን ከሐሰት ትንቢቶችና ከተጭበረበሩ መልእክቶች ለመከላከል አንድ ዘዴ መፍጠር አስፈላጊ ሆነ። ክርስቶስ «ሃይማኖትን» (ይሁዳ 3) በአደራ የሰጠው ለሐዋርያቱ ስለነበር፥ በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ተቀዳሚው የመፈተኛ ጥያቄ «ይህ ሐዋርያት ያስተማሩት ትምህርት ነውን?» የሚለው ነበር። ቤተ ክርስቲያን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ስታሰባስብ የነበራት ዋናው መመዘኛ እያንዳንዱ መጽሐፍ በሐዋርያ ወይም ከሐዋርያ ጋር በጣም ቅርበት በነበረ ሰው የመጻፉ ጉዳይ ነበር፤ ስለዚህ ሐዋርያዊ ትምህርት ጥንትም የእውነት መፈተኛ እንደነበር ሁሉ ዛሬም ነው።

ከይሁዳ በፊት የተጻፉ የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ስላልነበሩ እርሱም ለመጀመሪያ ጊዜ በሐዋርያት ‹የተነገሩትን› ቃላት ጠቅሷል። ከዚያም በሚቀጥሉት ዓመታት በመንፈስ ምሪት ሌሎች መልእክቶች በጳውሎስ፥ በጴጥሮስና በዮሐንስ ተጽፈው ነበር። እነዚህ መልእክቶች በአዲስ ኪዳናችን ውስጥ ሰፍረዋል። እንዲሁም ከስብከቶቻቸው አንዳንዶቹ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛሉ። ስለዚህ ብሉይንና አዲስ ኪዳንን ያካተተ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ስላለን ከእንግዲህ ወዲህ በአፈ ታሪክ ላይ አንደገፍም።

ምንጊዜም አንድ ሰው «አዲስ መገለጥ» ሊያቀርብላችሁ ሲሞክር፥ በቅድሚያ ሐዋርያት በጻፉትና ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረው ፈትኑት። «መገለጡ» ውሸት ከሆነ ቶሎ ትደርሱበታላችሁ።

ሐዋርያት የተናገሩትን አስቡ (ቁ. 18)፡- በመጨረሻ ቀናት የእግዚአብሔርን ቃል የሚክዱ ዘባቾች እንደሚመጡ ተንብየዋል። ይሁዳ ጴጥሮስ የጻፈውን አስተጋብቷል (2ኛ ጴጥሮስ 3፡3 ጀምሮ)። እንደዚሁም ጳውሎስና ዮሐንስም ስለ ሐሰተኞች ለአንባቢዎቻቸው አስጠንቅቀዋል (1ኛ ጢሞ. 4፤ 2ኛ ጢሞ. 3፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡18 ጀምሮ፤ 4፡1-6)። አንድ ማስጠንቀቂያ ብዙ ጊዜ ሲሰጥ አክብደን እንድናየው ያደርገናል።

«እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ» የሚለው ሐረግ በ2ኛ ጴጥሮስ 3፡3ና በይሁዳ 16 እና 18 ላይ ይገኛል፤ ደግሞም ሐሰተኞች ለምን የእግዚአብሔርን እውነት እንደሚክዱ ያስረዳል። እንዴት መኖር እንደሚገባቸው እግዚአብሔር እንዲነግራቸው አይፈልጉም። የገዛ ራሳቸውን ኃጢአተኛ ፍላጎቶች ለማርካት ይፈልጋሉ፤ የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ራስ ወዳድነት የሞላበትን አኗኗራቸውን ይነቅፋል። አንድ ሰው «መጽሐፍ ቅዱስን የመረዳት ችግር አለብኝ» ሲል፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ነገር ከድርጊቱ ጋር ስለሚጋጭ ምናልባት የትክክለኛ አኗኗር ችግር አለብኝ ማለቱ ሊሆን ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረንን እውነታ ለማወቅ ብቸኛው አስተማማኙ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን መታዘዝ ነው (ዮሐንስ 7፡17)።

ሰይጣን የራሱን ውሸቶች ለማሳመን ከመቻሉ በፊት የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ማስካድ አለበት። ተከራክሮ ማሸነፍ ካልቻለ ያልተሸነፈ በመምሰል ስቆ ያልፋል፥ ብዙውንም ጊዜ ደግሞ አብሮት የሚስቅ ሰው ያገኛል።

ለምን እንደተናገሩት አስቡ (ቁ. 19)፡- የሐሰት አስተማሪዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመከፋፈልና ሰዎችን ከእውነተኛ ኅብረት ወደ ሐሰተኛ ኅብረት ለመምራት ይፈልጋሉ። «ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንደተነሡ እኔ አውቃለሁ» (የሐዋ. 20፡30)። ብዙውንም ጊዜ ማጥመጃቸው «ቤተ ክርስቲያናችሁ የሌላት ጥልቅ የሆነ የቃሉ እውቀት እኛ አለን፤ እናንተ ካላችሁ የተሻለ ትንቢቶችን ወይም የክርስትና ሕይወትን የመረዳት ብቃት አለን» የሚል ነው። ከሐዋርያትም ይልቅ «የበለጠ ጥራት ያለው» ሃይማኖት እንዳላቸው ይሰብካሉ። የሐሰት አስተማሪዎች «ሥጋዊያን የሆኑ መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው በመሆኑ» የሚያደርጉት ቤተ ክርስቲያንን መከፋፈል ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንን እስከማታለልም ይደርሳሉ። ሥጋውያን የሚለው ቃል የ«መንፈሳውያን» ተቃራኒ ነው። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 2፡14-16 ውስጥ «ፍጥረታዊ» ተብሎ የተተረጐመውን የተጠቀመበት በዚህ መንፈሱ ነው። (የግሪኩ ቃል ሱኪኮስ ማለትም «ነፍሳዊ» የሚል ነው።) የሐሰት አስተማሪዎች የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሌላቸው፥ በምትኩ

በተፈጥሮአቸው ማለትም «በነፍስ ኃይላቸው» ብቻ ነው መሥራት የሚችሉት።

ዛሬ ባለው አገልግሎት ውስጥ ካሉት አሳዛኝ ነገሮች አንዱ፥ አንዳንድ የእግዚአብሔር ሰዎች በ«ነፍስ አገልግሎት» እና በእውነተኛ የመንፈስ አገልግሎት መካከል መለየት አለመቻላቸው ነው። በዚህ ዘመን ብዙ «ሃይማኖታዊ አመለካከቶች» ከመኖራቸው የተነሣ ቅዱሳን ግራ ተጋብተዋል፤ አልፎ አልፎም ይታለላሉ። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ «የሐሰት እሳት» እንደነበር ሁሉ (ዘሌዋውያን 10)፥ ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «የሐሰት እሳት» አለ፤ ስለዚህ ጥንቃቄ የተሞላበት የመለየት ልምድ እንዲኖረን ያስፈልጋል።

በ«ነፍሳዊ» ና በ«መንፈሳዊ» አገልግሎት መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት መለየት እንችላለን? ነፍስንና መንፈስን መለየት በሚችለው በእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም ነው (ዕብ. 4፡12)። እንዲሁም በውስጣችን ያለውን የእግዚአብሔርን መንፈስ ምስክርነት በማድመጥ ነው (ሮሜ 8፡16)። «ነፍሳዊ» አገልግሎት ሰውን ያጎላል፤ «መንፈስ» ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ያከብራል። መንፈስ ቅዱስ በቃሉ በኩል ሲያገለግል መታነጽ አለ፤ ነገር ግን ነፍስ አገልግሎትን «አስመስላ ስትፈጥር» የሚኖረው መዝናናት ወይም ግፋ ቢል አእምሮአዊ እውቀት ብቻ ይሆናል። ለመንፈሳዊ ዕድገታችንና በበለጠም ኢየሱስ ክርስቶስን እንመስል ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያስፈልጋል።

## የክርስትና ሕይወታችሁን ገንቡ (ይሁዳ 20-21)

የክርስትና ሕይወት ፈጽሞ በአንድ ስፍራ ብቻ ቆሞ መቅረት የለበትም፤ እንደዚያ ከሆነ ወደኋላ ይሄዳል። ለራሱ የተተወ ቤት ይፈርሳል። የሐሰት አስተማሪዎች በመለያየት ሥራ ላይ ናቸው፤ ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን በመገንባት ላይ መጠመድ አለበት፤ በመጀመሪያ የራሱን መንፈሳዊ ሕይወት ከዚያ ደግሞ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑን መገንባት ይኖርበታል።

ለክርስትና ሕይወታችን መሠረቱ «ከሁሉ ይልቅ የተቀደሰ ሃይማኖታችን» ነው (ቁ. 20)፤ «ይህም ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ከተሰጠ ሃይማኖት» (ቁ. 3) ጋር አንድ ነው። በእርግጥ ለዕድገታችን መሠረቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለን እምነት እንደሆነ የታወቀ ነው፤ ሆኖም ግን ያ እምነት

እንኳን እግዚአብሔር በቃሉ በገለጠልን እውነት ላይ የተመሠረተ ነው። እኛ ለእግዚአብሔር እውነት የምንሰጠው ምላሽ መተማመኛችን በእግዚአብሔር ላይ በተገለጠ እውነት የተመረኮዘ ይሆናል።

የእግዚአብሔር ቃል ለመንፈሳዊ ዕድገት መሠረት ነው። እስከ አሁን ባለኝ ልምድ መጽሐፍ ቅዱስን ዘንግቶ ጠንካራና ፍሬያማ የሆነ ክርስቲያን አላጋጠመኝም። በየቀኑ የእግዚአብሔርን አሳብ በመሻት ቃሉን በጥሞና ማሰላሰል አለብን። እንዲሁም የሚያስተምረውን በተሻለ እንድንረዳ ምን ጊዜም ቃሉን በሥነ -ሥርዓት ማጥናት ይገባናል። ትልቅ ስጦታ የነበረውና ዋች ማን ኒ የተባለው ቻይናዊ ሰባኪ በየወሩ አንድ ጊዜ አዲስ ኪዳንን በሙሉ ያነብ ነበር። መጻሕፍቶቹን ስታነቡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ባሉት አስደናቂ መረጃዎች ማስተዋል ስለምታገኙ ይህ ግልጥ ይሆንላችኋል። የቻይና ቤተ ክርስቲያን አባላት «መጽሐፍ ቅዱስ ሳይነበብ ቁርስ አይበላም!» የሚል አባባል ነበራቸው። ይህንን አባባል ብንከተለው ኖሮ ምን ያህሉ ክርስቲያኖች በተራቡ ነበር?

የክርስትና ሕይወትን ለመገንባት ኃይል የምናገኘው ከጸሎት ነው። «በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ» የተባልነው ለዚህ ነው (ቁ. 20)። በመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ውስጥ የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት አብረው ይሄዳሉ። መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብና በማጥናት ብቻ የምናተኩር ከሆነ ብርሃንን ብናገኝም ኃይል ግን አይኖረንም፤ እንደዚሁም በጸሎት ላይ አተኩረን መጽሐፍ ቅዱስን ከተውን እውቀት የሌለበት ቅንዓት ብቻ ይኖረናል። በእምነት ለማደግ ቃሉን እናነባለን (ሮሜ 10፡17)። ከዚያም ያንን እምነት የሚያስፈልገንንና ቃሉ እንዲኖረን የሚነግረንን ከእግዚአብሔር ለመጠየቅ እንጠቀምበታለን።

የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት አብረው የሚሄዱ ናቸው (የሐዋ. 6፡4)። ወንጌላዊው ቢሊ ሰንደይ ጌታን ለተቀበሉት ሰዎች የክርስትና ሕይወታቸው የተሳካላቸው እንዲሆኑ ሦስት መመሪያዎች ይሰጥ ነበር። የመጀመሪያው፥ ክርስቲያኖች በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና እግዚአብሔር እንዲናገራቸው መጠየቅ ነበረባቸው። ሁለተኛው፥ መጸለይ ነበረባቸው፤ በሌላ አነጋገር ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነበረባቸው። እንዲሁም

ሦስተኛው፥ መመስከርና ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር መናገር ነበረባቸው። እነዚህን መመሪያዎች ማሻሻል እጅግ የሚከብድ ይሆናል።

«በመንፈስ ቅዱስ መጸለይ» ምን ማለት ነው? (በቁጥር 19 ላይ «መንፈስም የሌላቸው» ተብሎ ከተጠቀሰው ጋር የሚቃረን መሆኑን አስታውሱ።) እንደ መንፈስ ቅዱስ አመራር መጸለይ ማለት ነው። «ጸሎት የሰውን ፈቃድ በሰማያት ተፈጻሚነት እንዲያገኝ መለመን ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር ተፈጻሚ እንዲሆን መለመን ነው» የሚል አንድ መልካም አባባል አለ። ይህ ከ1ኛ ዮሐንስ 5፡ 14-15 ጋር ይስማማል።

እንደ ክርስቲያኖች በግላችን ልንጸልይ እንችላለን (ማቴ. 6፡6)፤ ይህ ማለት ግን ለብቻችን እንጸልያለን ማለት አይደለም። የእግዚአብሔርን አሳብ ስለሚያውቅና ሊመራን ስለሚችል የእግዚአብሔር መንፈስ ስንጸልይ ከእኛ ጋር ይሆናል (ሮሜ 8፡26-28)። ከቃሉ ጥበብንና እውቀትን ሊሰጠን ይችላል (ኤፌ. 1፡ 15 ጀምሮ)። በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ባለን መብት ወደ አብ እንድንቀርብ ሊረዳንም ይችላል (ኤፌ. 2፡ 18)። እግዚአብሔርን «በመንፈስ» እናመልከዋለን (ፊልጵስዩስ 3፡ 3)። መንፈስ ቅዱስ «የሞገስና የልመና መንፈስ» ስለሆነ (ዘካ. 12፡ 10) እንድንጸልይ ይቀሰቅሰናል። አማኝ ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ሲሆን፥ መንፈስ ቅዱስ በጸሎት ሕይወቱ ያግዘዋል፤ እግዚአብሔርም ጸሎትን ይመልሳል።

በክርስትና ሕይወት ውስጥ ያለ «የመገንባት ሂደት» የእግዚአብሔርን ቃል፥ የእግዚአብሔርን መንፈስና ጸሎትን ያካትታል። ዳሩ ግን እነዚህ ነገሮች አስፈላጊ የመሆናቸውን ያህል ልማዳዊም ሊሆኑ ይችላሉ፤ ስለዚህም ነው ይሁዳ፡- በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ መኖር (ቁ. 21) የሚለውን ሌላ ተፈላጊ ነጥብ ያከለበት። እርሱም የመከራቸው «ደኅንነታችሁን ጠብቁ!» በማለት አይደለም፤ ምክንያቱም «በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠበቁ እንደሆኑ» ከዚህ በፊት አረጋግጦላቸዋል (ቁ. 1)። «በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ» ነው ያላቸው። በዮሐንስ 15፡9 ላይ እንደምናገኘው፥ ጌታችን «በፍቅሬ ኑሩ» ሲል ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል።

እግዚአብሔርን መውደድ ማለት በልዩ ዓይነት ስሜት ከመደሰት በጣም የሚበልጥ ነገር ነው። በእርግጥ በጸጋ ስናድግ ከአብ ጋር ጥልቅ የሆነ ኅብረትን እንለማመዳለን (ዮሐንስ 14፡21-24)። እንዲሁም ከአጠገባችን እንደሚገኝ

ይሰማናል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ከባልና ሚስት ጋር ያነጻጽረዋል (ኤፌ. 5፡22 ጀምሮ)። ደስተኞች ባልና ሚስት ዓመታት ሲያልፍ ፍቅራቸው እንደሚጨምር ልታዩ ትችላላችሁ።

ነገር ግን የተሳካ ትዳር ወይም የተሳካ የክርስትና ሕይወትን ለማግኘት ከኃይለኛ የመፈለግ ስሜት የበለጠም ነገር ያስፈልጋል። መታዘዝና የእርስ በርስ መተሳሰብም ያስፈልጋል። «ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሞአል» (1ኛ ዮሐንስ 2፡5)። «ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ» (ዮሐንስ 15፡10)። ቃሉን ስናዳምጥ፥ ስንታዘዘውና ለእርሱ ደስ የሚያሰኘውን በማድረግ እኛም ስንደሰት ያን ጊዜ ለእግዚአብሔር ባለን ፍቅር እናድጋለን። ራሳችንን በእግዚአብሔር ፍቅር የምንጠብቀው እንደዚያ ነው።

የእግዚአብሔር ፍቅር ቅዱስ ፍቅር ነው፤ የላይ የላይ የሆነ ስሜት አይደለም። «እግዚአብሔርን የምትወዱ፥ ክፋትን ጥሉ» (መዝ. [97]፡10)። እግዚአብሔርን መውደድ እርሱ የሚወደውን መውደድና የሚጠላውን መጥላት ነው! ያዘዛቸውን ነገሮች በማድረግ እናስደስተዋለን። በቤተሰቡ ውስጥ ከአባቱ ጋር በጣም የጠለቀ ኅብረት የሚመሠርተው ያ ልጅ ለእግዚአብሔር የተሰጠና የተለየ ክርስቲያን ነው (2ኛ ቆሮ. 6፡14-18)።

የክርስትና ሕይወታችንን በእምነት፥ በፍቅር መሠረት ላይ እንገነባለን፤ ነገር ግን «ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ» እንደተባለው በተስፋ ልንኖር ያስፈልገናል። የአማኝ ዓይኖች ወደ ሰማይ ማየት አለባቸው። «የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን» (ቲቶ 2፡13) እና «የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኮላችሁ» (2ኛ ጴጥ. 3፡12) በሚለው መሠረት ወደ ሰማይ ማቅናት አለበት።

«እየጠበቃችሁ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል (ይሁዳ 21) «በቁም ነገር መጠባበቅ» ማለት ነው። በጌታችን የመመለስ የተስፋ ቃል የተመሠረተ የአኗኗር ሁኔታን ይገልጻል። ሐሰተኞች መምህራን የሚጠባበቁት ፍርድ ብቻ ነው፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ ግን ምሕረቱን ይጠባበቃሉ። የእግዚአብሔር የምሕረት ስጦታ የሆነው የእኛ ከኃጢአት መዳን ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን

የቤተ ክርስቲያኑ ከዚህ ከክፉ ዓለም መዳንም ነው። በምሕረቱ ለእኛ መጥቶ ወደ ራሱ ይወስደናል።

የጌታን መምጣት መጠባበቅ ለክርስትና ኑሮ ትልቅ ማበረታቻ እንደሆነ ከዚህ በፊት አስተውለናል። ንጹሕ እንድንሆንና (1ኛ ዮሐንስ 3:3) የሥጋንና የዓለምን ነገሮች እንድናርቅ (ፊልጵ. 3:17-21) ያደርገናል። በክርስቶስ ያለን ተስፋ በሕይወት ማዕበል ውስጥ እንደሚያቆመን መልሕቅና (ዕብ. 6:19) በሕይወት ውጊያ ውስጥ እንደሚከላከልልን የራስ ቁር (1ኛ ተሰሎንቄ 5:8) ነው።

ሦስቱ «የክርስትና ጸጋዎች» ማለትም እምነት፥ ተስፋና ፍቅር በመንፈሳዊ እርምጃችን እንድናድግ ያስችሉናል። ሕይወታችንንም በማይዝግና በማይበሰብስ ጠንካራ መሠረት ላይ ለመገንባት ያስችለናል። ተራ የከንፈር ምስክርነት ብቻ ብቁ አያደርገንም። «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» (ማቴ. 7:21)። የሁለቱ ግንበኞች ምሳሌ (ማቴ. 7:24-27) የእግዚአብሔርን ፈቃድ መታዘዝ ማለት ሊደረመስ በማይችል መሠረት ላይ መገንባት ማለት እንደሆነ ግልጽ ያደረገዋል።

## መንፈሳዊ መለየትን ተለማመዱ (ይሁዳ 22-23)

በመናፍቃን እየተወሰዱ ስላሉት ሰዎች በማደግ ላይ ያለው ክርስቲያን ሊኖረው የሚገባው አመለካከት ምን መሆን አለበት? ይሁዳ አንባቢዎቹ መለየትን እንዲለማመዱና በዚያ መለየት መሠረት እንዲራመዱ አዟቸዋል። መንፈሳዊ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሦስት የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን ገልጿል።

«አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ፥

አንዳዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ፥

አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ ቢሆን በፍርሃት ማሩ።»

ተጠራጣሪዎች (ቁ. 22):- እነዚህ የሚያወላውሉ ሰዎች ናቸው። ምናልባት ጴጥሮስ «ያልጸኑ ነፍሳት» በማለት የጠቀሳቸው ይሆናሉ (2ኛ ጴጥሮስ 2:14)። እነዚህ ሰዎች ተለውጠዋል፤ ነገር ግን በእምነታቸው ሥር

አልሰደዱም። የእኛ ኃላፊነት ለእነርሱ ምሕረት ማድረግ ወይም ከሐሰተኞች ተጽዕኖ እንድንታደጋቸው ለእነርሱ ርኅራኄ ማድረግ ነው። የዚህ ዓይነት አገልግሎት ትልቅ ፍቅርንና ትዕግሥትን ይጠይቃል። እንዲሁም ያልበሰሉ አማኞች ከፉን ከደጉ ለይተው የሚያውቁ እንደሚመስላቸው እንደ ትንንሽ ልጆች እንደሆኑ መርሳት የለብንም። የሚሉትን «አይሆንም» ካላችኋቸው ያምጹና የበለጠ ግትሮች ይሆናሉ!

እነርሱን ከሐሰት አስተማሪዎች ለመመለስ ጥሩ ከሆኑት መንገዶች አንዱ በክርስቶስ ያላቸውን ተስፋ ማጉላትና የርሱን ፍቅር ተግባራዊ በሆኑ መንገዶች ማካፈል ነው። ለሐሰተኛ ትምህርቶች ፍላጎት እንዲያጡ፥ ደኅንነታቸው ምን ያህል ታላቅ ነገር እንደሆነ ቃሉም የተወደደ ስለመሆኑ አስረዷቸው። የሐሰት ትምህርቶች ስሕተት እንደሆኑ ማስረገጥ ብቻ በቂ አይደለም፤ ወጣቱን እርግጠኛ አማኝ የሚያደርገው የሞቀ ፍቅር በመካከላችን መኖር አለበት። «ለአንተ ግድ ይለናል» ማለት አለብን።

የሐሰት አስተማሪዎች በተለይ ጥሩ ስሜት በሌላቸው የቤተ ክርስቲያን አባላት ላይ እንደሚያደቡ የአደባባይ ምሥጢር ነው (ቁጥር 16ን «የሚያንጎራጉሩ» እና «የሚያጉረመርሙ» የሚለውን አስታውስ)። መጋቢውና ምእመኑ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች ልዩ ፍቅር ማሳየትና ለቤተ ክርስቲያኒቱ የበሰሉ አባላትም በተገቢው መንገድ ማገልገላቸው አስፈላጊ ነገር ነው። ይህ ካልሆነ ግን ከእንክብካቤ ጉድለት የተነሣ አንድ ሰው መንገዱን ሊስት ይችላል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በእምነታቸው እንዲያጸናቸው በተሰሎንቄ ወደሚገኙት ወጣት አማኞች ላከው (1ኛ ተሰ. 2)። እያንዳንዱ ለጋ ክርስቲያን እንዴት መቆምና መራመድ እንዳለበት የሚያስተምረው ከርሱ የበለጠና የበሰለ አማኝ ያስፈልገዋል።

ለመቃጠል የተዘጋጁት (ቁ. 23)፡- እነዚህ ኅብረቱን የተዉና አሁን የሐሰተኞች መምህራን ተከታዮች የሆኑ ሰዎች ናቸው፤ ስለዚህ ከእሳቱ ተነጥቀው መውጣት ያስፈልጋቸዋል! መላእክት ሎጥን እጁን ይዘው ከሰዶም ጎትተው አወጡት (ዘፍ. 19፡16)። እኛም የማያውቁትንና ያልጸኑትን አማኞች ከሐሰት አስተማሪዎች እጅ ለማዳን እንደዚያ ማድረግ አለብን።

ይህ አሳብ ምናልባትም ከዘካርያስ 3፡2 እና እንዲሁም ከአሞጽ 4፡11 ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። በዘካርያስ ውስጥ «ትንታግ» የተባለው

ከባቢሎን ምርኮ ተመልሶ በምድሩ የሰፈረው የእስራኤል ሕዝብ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከእሳት እንደወጣ ትንታግ ነበር የሚያየው። በአሞጽ 4 ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር ሕዝቡ ማስጠንቀቂያዎቹንና ፍርዱን ስላላደመጡ እየወቀሳቸው ነበር፤ ራብ፥ የጫጪ ሰብል፥ ድርቅ፥ ቸነፈር፥ ጦርነትና ሰዶምንና ገሞራን እንደ ገለበጧቸው ያሉ (ፍርዶች) ቅጣቶች እንኳ ከመንገዳቸው አልመለሳቸውም። ከእሳት ውስጥ እንደ ተነጠቀ ትንታግ ቢቆጠሩም ቅሉ፥ የእግዚአብሔርን ምሕረት ሲያደንቁ አንመለከታቸውም።

አደገኞቹ (ቁ. 23):- በፍርኃት የሚለው ቃል «በጥንቃቄ» ማለት ነው። የተሳሳቱትን ለመርዳት ስንሞክር እኛ ራሳችን እንዳንጠመድ መጠንቀቅ አለብን! ብዙዎች ሌላውን ለማዳን ሲሞክሩ ራሳቸው በዚያው ስሕተት ወድቀዋል። ያልጸና አማኝ በሐሰት ትምህርት ከተጠመደ፥ እኛንም ለማርከስ ሰይጣን በእርሱ ሊጠቀም ስለሚችል ልንረዳው በምንሞክርበት ወቅት በጣም መጠንቀቅ አለብን። እርሱን ለማዳን ስንሞክር ራሳችን ልንበከል ወይም ልንቃጠል እንችላለን!

ይሁዳ የሰጠው መመሪያ ጠንካራ አማኞች ከሰይጣን ተጽዕኖ በላይ እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን መቁጠር እንደሌለባቸው የሚያሳስብ ነበር። ጌታን እያገለገልንና ከልጆቹ አንዱን ለማዳን እየፈለግን ባለንበት ወቅት እንኳ ልንረዳቸው በምንፈልጋቸው ሰዎች አማካይነት ልንረክስ እንችላለን። የብሉይ ኪዳን አይሁዶች ከርኩሰት በጣም መጠንቀቅ ነበረባቸው። ይህም ሌላው ቀርቶ ልብሳቸውን እንኳ የተመለከተ ነበር (ዘሌ. 13፡47 ጀምሮ፤ 14፡47፤ 15፡17)። «ንጹሕ» ሰው «ያልነጻውን» ልብስ ከነካ ይረክስ ነበር።

እኛ በእርግጥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መውደድ አለብን፤ ነገር ግን ኃጢአትን መጥላትም አለብን። ኃጢአት ባለበት ሁሉ ሰይጣን ዕድል ስለሚያገኝ ሥራውን ሊቀጥል ይችላል። ርኩሰት በፍጥነትና በስውር ይስፋፋል፤ ስለዚህ ጭራሹኑ መወገድ አለበት። የአይሁድ ካህን አንድ ልብስ በለምጽ እንደተበከለ ከተጠራጠረ ልብሱን ያቃጥላል።

ሁሉም ክርስቲያን ከሐሰት አስተማሪዎች ወይም በትምህርታቸው ካጠመዷቸው ተከታዮቻቸው ጋር ለመጋጠም ዝግጁ ላይሆን ይችላል። ይህን ለማድረግ ቃሉን በጥልቀት መረዳትን፥ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድን፥

የሰይጣንን ስልቶች ማወቅና እንዲሁም የእግዚአብሔርን መንፈስ ሙላትን ይጠይቃል። እንዲሁም መናፍስትን መለየትን ይጠይቃል። አዳዲስ ክርስቲያኖችን ከእሳት ነጥቆ ከማውጣት ይልቅ እነርሱን መምራትና ከሐሰት አስተማሪዎች ማራቅ በጣም ይቀላል።

## ራሳችሁን ለኢየሱስ ክርስቶስ ስጡ (ይሁዳ 24-25)

ይህ በደንብ የታወቀ ቡራኬ አማኙ ሊቀበለው የሚገባውን ብዙ የመንፈሳዊ እውነት ይዟል፤ በመንፈሳዊ እግራችን ጸንተን ቆመን ለመጠበቅ፥ በቀጥታ ለመራመድና ላለመሰናከል ከፈለግን ሙሉ በሙሉ ራሳችንን ለአዳኙ ማስገዛት አለብን፤ እርሱ ብቻ ነው ሊጠብቀን የሚችለው። ነገር ግን እኛም በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችንን መጠበቅ አለብን (ቁ. 21)። እኛ ፈቃደኞች ከሆንን እርሱ ሊጠብቀን ይችላል።

ይሁዳ የሚገልጸው አማኝ ኃጢአት ለመሥራትና ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመሰረዝ ስለመቻሉ አልነበረም። ከዚህ በፊት በቁጥር 1 ላይ በግልጥ እንደሰፈረው እውነተኞች አማኞች «የተጠበቁ» እንደሆኑና ሊጠፉ እንደማይችሉ አይተናል። ይሁዳ የሚገልጸው አማኙ በየቀኑ ከጌታ ጋር ስላለው እርምጃና ወደተሳሳተ አቅጣጫ የመሄድንና የመሰናከልን አደጋ በተመለከተ ነበር። እግዚአብሔርን ያልታዘዝንበት አጋጣሚ ቢኖር ኃጢአታችንን ተናዝዘን ይቅርታውን መቀበል እንችላለን (1ኛ ዮሐ. 1፡9)። ባለመታዘዝ ከጸናን ግን በፍቅር ይቀጣናል (ዕብ. 12፡5-11)። የራሱ ከሆኑት አንድ እንኳ እንዲጠፋ ፈጽሞ አይፈቅድም።

ሕዝቡ ሁሉ አንድ ቀን ክብሩን እንደሚያዩና እንደሚካፈሉ እግዚአብሔር አብ ከወልድ ጋር ቃልኪዳን ገብቷል (ዮሐንስ 17፡22-24 ተመልከት)። ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራይቱ ቤተ ክርስቲያንን ከአብ ዙፋን ፊት ማቅረብ ልዩ ደስታ ይሰጠዋል! ይህን «ደስታ» መጠበቁ ነው በመስቀል ላይ መከራን እንዲታገሥ የረዳው (ዕብ. 12፡2)። የደኅንነት ዓላማ ኃጢአተኞችን ከሲኦል መታደግ ብቻ አይደለም፤ ምንም እንኳ ይህም ግሩምና አስደናቂ ነገር ቢሆንም ዋናው ዓላማ እግዚአብሔር ለዘለዓለም እንዲከበር ነው (ኤፌ. 1፡6፥ 12፥ 14)።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነውሮችና ነቀፋዎች አሉ። በዚያን ቀን ግን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ያለ ነቀፋ ይሆናሉ። ሰይጣን የሚከስበት ምንም ነገር

አያገኝም። ሙሽራይቱ ለእግዚአብሔር ክብር የክርስቶስን ጽድቅ ትለብሳለች።

ይህንን የሚያውቅ አማኝ ለክርስቶስ ለመኖርና ለቃሉ ለመታዘዝ ጠንካራ ፍላጎት አለው። ሙሽራይቱን ወደ ሰማይ ሲወስድ የሚኖረውን ደስታ ለመካፈል የምንመኝ ሁላችንም ዛሬ እርሱን ለማስደሰት እንፈልጋለን! የ1ኛ ዮሐንስ 3፡3 ዋነኛ መልእክትም ይኸው ነው፡- «በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደሆነ ራሱን ያነጻል» (ኤፌሶን 5፡27፤ ፊሊጵ. 2፡15 ከሚለው ጋር አነጻጽር)።

በዚህ ትንሽ ደብዳቤ ውስጥ ይሁዳ ጌታችንን «መድኃኒታችን» ብሎ የጠራበት ቦታ ቁጥር 25 ብቻ ነው። ጴጥሮስ በዚህ ስያሜ አምስት ጊዜ ተጠቅሟል። ይሁዳ ግን ደብዳቤውን የከፈተው ብዙዎች አንባቢዎቹ በኢየሱስ ክርስቶስ ካላቸው እምነት የተነሣ ስለሚካፈሉት «የጋራ ደኅንነት» በማስታወስ ነበር (ቁ. 3)። ኢየሱስ ክርስቶስ «አዳኛችንን» ወይም «አዳኙ» እንደሆነ መናገር በቂ አይደለም፤ «አዳኙን» አዳኜ ማለት አለብን።

ደግሞም እርሱ አዳኛችን ብቻ ሳይሆን «ብቻውን ጥበበኛ አምላካችን» ነው። ሕይወታችሁን ለእግዚአብሔር ክብር እንድትኖሩ የሚያስፈልጋችሁን ጥበብ ሊሰጣችሁ ይችላል፤ ሐሰተኛ አስተማሪዎች በእውቀታቸው ተኩራርተዋል፤ ነገር ግን መንፈሳዊ ጥበብ ጎድሏቸዋል። እግዚአብሔር በየዋህነት ሊታዘዙት ፈቃደኞች ከሆኑ ለሚጠይቁት ጥበብን ይሰጣል (ያዕቆብ 1፡5)። ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የእግዚአብሔርን ጥበብ ለማግኘት ከሻቱ በሐሰተኞች አስተማሪዎች ወጥመድ አይሰናከሉም፤ በዚያ ምትክ ጌታን ለማስደሰት ይመላለሳሉ (ቆላስ. 1፡9-10)።

ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ መሄድ ያለብን ለምንድን ነው? ክርስቶስ ክብርን እንዲቀበል ነው።

«ክብር»፡- የእግዚአብሔር አምላክነቱና በአምላክነቱም ያደረገው ሁሉ ጠቅላላ ድምር ነው። የእርሱ ሁለመናው የከበረ ነው! የሰው ክብር እንደታጨደ ሳር ይጠፋል፤ የእግዚአብሔር ክብር ግን ለዘላለም ይጸናል።

«ግርማ»፡- ማለት «ታላቅነት፥ አስደናቂነት» ማለት ነው። እግዚአብሔር ብቻ ነው ትልቅ። እግዚአብሔርን ስናመሰግን ከሁሉም

የሚበልጠውን እጅግ አስደናቂ አምላክ እናመሰግናለን። እርሱ ንጉሥ ብቻ አይደለም፤ የነገሥታት ንጉሥ ነው! ጌታ ብቻ አይደለም፤ የጌቶች ጌታ ነው!

«ግዛት»፡- ከእግዚአብሔር ወሰን የሌለው ኃይልና በሁሉ ላይ ካለው ገዢነት ጋር የተያያዘ ነው። የግሪኩ ቃል «ብርታት፥ ኃያልነት» ማለት ነው። በተጨማሪም ሁሉን ነገር ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠርን አሳብ ይይዛል።

«ሥልጣን»፡- ማለት «የበላይ ገዢነትን» ማለትም በኃይል የመጠቀም መብትን የሚያመለክት ነው። በጨለማው ኃይላት ላይ ያለውን ሥልጣን ሁሉ ጨምሮ ማንኛውም ሥልጣን (ኤፌ. 1፡19-23) የኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማቴ. 28፡18)። ለእርሱ ስንገዛ ሥልጣኑን እንካፈላለን፤ ፈቃዱንም እንፈጽማለን።

ይህ እንዴት ያለ ዕፁብ ድንቅ የሆነ የውዳሴ ቃል ነው! ይሁዳ ይህንን ደብዳቤ ሲጽፍ በአሳቡ ውስጥ የነበረውን ዓላማ ካወቅን፥ የውዳሴው ቃል የበለጠ ክብደት እንዳለው እንረዳለን። ይሁዳ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅነት ለአንባቢዎቹ እያሳሰባቸው ነበር። ያንን ከተቀበሉ በሐሰት አስተማሪዎች ወደ ስሕተት ፈጽሞ አይመሩም። በፍቅር የተነደፈላትን ልጃገረድ የማግባት ዕድል ያገኘው ወጣት ዳግመኛ ከቀደሞዎቹ ከንፈር ወዳጆቹ ጋር ለመዳራት እንደማይሻ ሁሉ፥ እንደዚሁም በአዳኙ ክብር ተጠምዶ «በእግዚአብሔር ፍቅር» (ይሁዳ 21) የተጠበቀው አማኝም ወደ ሰይጣን ጎራ ለመመለስ ጨርሶ አይፈልግም።

መሰናከል የለባችሁም!

እናንተም ቃሉን ካስታወሳችሁ፥ የክርስትና ሕይወታችሁን በእምነት፥ በተስፋና በፍቅር ከገነባችሁ፥ መንፈሳዊ መለየትን ከተለማመዳችሁና ራሳችሁን ለክርስቶስ ካስገዛችሁ እርሱ ከመሰናከል ይጠብቃችኋል።

ንቁ!

ጠላት በጣም ብልጥ ነው፤ አደጋዎቹም እጅግ የከፉ ናቸው።

ሆኖም ግን ብቻውን ጥበበኛ የሆነው አዳኛችሁ ከክፋት ከልሎ አንድ ቀን በደስታ ወደ ክብሩ ያገባችኋልና ነቅታችሁ ጠብቁ! ነቅተህ ጠብቅ!